ዐውደ ፡ ቀለም ፤ የጽሑፍ ፡ ማምረቻ

ክለሳ ፡ 1.3 ፤ ለዊንዶውዝ

AwdeQelem text processor • AwdeQelem traitement de texte

Version 1.3 for Windows • Version 1.3 pour Windows

• ፊደል ፡ መጠንቀቂያ ፡ (ዐማርኛ ፣ ግእዝ ፣ እንግሊዝኛ ፣ ፈረንሳይኛ ፣ ሶማልኛ)
• መዝገበ ፡ ቃላት ፡ (ዐማርኛ ፣ ግእዝ ፣ እንግሊዝኛ ፣ ፈረንሳይኛ ፣ ሶማልኛ) ፡ ከቃል ፡ ማተርጐሚያ ፡ ጋራ
• ጸሐፊ ፡ መመለሻ ፡ (ከምዕራባዊ ፡ ጸሐፊ ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ ጸሐፊ ፤ ላሜሪካዊ-እንግሊዝኛና ፡ ለሶማልኛ)

ያለው ፡ የመዠመሪያ ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ ነጻ ፡ የጽሑፍ ፡ ማምረቻ ፡ መግበር ፡ ለዊንዶውዝ ፡ ምግባር ።

First free Ethiopian text processing tool with: • Premier outil de traitement de texte éthiopien gratuit avec:

Spell-checker • *Correcteur orthographique*
(Amharic, G'z, English, French, Somali) • (amharique, g'z, anglais, français, somali)

Dictionary with simultaneous translation of word • *Dictionnaire avec traduction simultanée de mot*
(Amharic, G'z, English, French, Somali) • (amharique, g'z, anglais, français, somali)

Transcriber • *Transcripteur*
(American English, Somali) • (anglais américain, somali)

for the Windows operating system • pour le système d'exploitation Windows

ዐጭር ፡ መመሪያ

(ያማርኛ ፡ ጽሑፍ ፡ ካጭር ፡ የእንግሊዝኛና ፡ የፈረንሳይኛ ፡ ትርጒም ፡ ጋራ)

concise guide • guide concis

(Amharic text with abridged English and French translations • Texte amharique avec des traductions française et anglaise abrégées)

ወሌ ፡ ነጋ • Welé Negga

awde-qelem.net gzamargna.net

3ኛ ፡ ዝግጅት ፤ 1ኛ ፡ ዕትም • 3rd edition, 1st print • 3ème édition ፤ 1ère impression

ዐውደ ፡ ቀለም • AwdeQelem ©ወሌ ፡ ነጋ ፤ መስከረም ፡ 2008 ፡ – ፡ የካቲት ፡ 2014 ፡ ዓ.ም. • Welé Negga, Sept. 2015 – Feb. 2022 A.D.

ለድል ፡ በዓል ፡ ፹ኛ ፡ ዓመት ፡ መታሰቢያ ፡
(1933-34 ፡ ዓ.ም.-2013-14 ፡ ዓ.ም.) ።

ዐውደ ፡ ቀለም ÷ የጽሑፍ ፡ ማምረቻ

ክለሳ ፡ 1.3 ÷ ለዊንዶውዝ ፡ ምግባር ።

AwdeQelem, text processor • AwdeQelem, traitement de texte

Version 1.3 for Windows operating system • Version 1.3 pour le système d'exploitation Windows

ማውጫ • Contents • Table des matières

ማውጫ • Contents • Table des matières 5

ማሳሰቢያ • Foreword • Avertissements 6

ምስጋና • Acknowledgement • Remerciements 8

መቅድም • Preface • Préface 11

መግቢያ • Introduction 21

1 ጠቅላላ ፡ መግለጫ • general presentation • présentation générale 25

2 ማሟሻ • getting started • mise en marche 27

2.1 ክለሳዎች • versions • versions 27

2.1.1 ክለሳ ፡ 1.3 ፡ ምን ፡ ዐዲስ ፡ ይዞ ፡ መጣ? • what is new in v.1.3? • quoi de neuf dans v.1.3? 27

2.2 ዕቃሜ • system requirements • besoins en ressources 28

2.3 ተከላ • installation 30

2.4 አገልግሎት • usage • utilisation 32

2.4.1 የነባር ፡ ሰነድ ፡ ከፈታ • opening of an existing file • ouverture d'un fichier existant 35

2.4.2 የቃል ፡ መረጣና ፡ ግኝታ • word selection and finding • sélection et recherche de mot 37

2.4.3 የቃል ፡ አጻጻፍ ፡ ጥሪትና ፡ ዕርማት • spell-checking and correction of word • vérification et correction de mot 43

2.4.4 የመዘርዘርና ፡ የማሞካሸት ፡ ዐቅም ፡ በዐውደ ፡ ቀለም • derivational / inflectional and homonymic capabilities of AwdeQelem • aptitudes dérivationnelles / flexionnelles et homonymiques de AwdeQelem 49

2.4.5 በዐውደ ፡ ቀለም ፡ የታገዘ ፡ የጽሑፍ ፡ ዝግጅት • AwdeQelem assisted text edition • édition de texte assisté par AwdeQelem 50

2.4.6 ያሜሪካዊ ፡ እንግሊዝኛ ፡ ጽሑፍና ፡ የሶማልኛ ፡ ጽሑፍ ፡ ምለሳ ፡ ከምዕራባዊ ፡ ጸሕፈ ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ ጸሕፈ • Transcription of American English text and Somali text from Western Script to Ethiopian Script • Transcription de textes en anglais américain et en somali, de l'écriture occidentale vers l'écriture éthiopienne 74

2.4.7 የቃላት ፡ መተረሪያና ፡ የጽሑፍ ፡ መሰደሪያ • WordList Maker and Text Sorter • "Établisseur" de liste de mots et trieur de texte 82

2.5 ተደጋጋሚ ፡ ጥያቄዎች • frequently asked questions • questions fréquemment posées 87

2.6 ወደ ፡ ፊት • perspectives 88

3 ስለግእዝ-ዐማርኛ ፡ ቃላት ፡ አጻጻፍ ፣ አገባብና ፡ ትርጕም ፡ መጠንቀቅ
Notes on G'z-Amharic spelling, grammar and semantic checking • brèves observations sur la correction orthographique, grammaticale et sémantique g'z-amharique 91

መደምደሚያ • conclusion 103

መጠቈሚያ • Index 105

ማሳሰቢያ • Foreword • Avertissements

የዐውደ፡ቀለም፡መመሪያ፡በሦስት፡ቋንቋዎች፡ተደርሷል፡[ዐማርኛ • English • Français]።

በፊደሉም ፣ በቃሉም ፣ በሐሳቡም፡የተቻለውን፡ያኽል፡ከስሕተት፡የነጻ፡እንዲኾን፡ጥንቃቄው፡ኹሉ፡ቢደረግም ፥ ፈጽሞ፡ማጥራት፡አይቻልምና ፥ አንባብያን፡አስተያየት፡እንዲያደርጉልኝ፡አስቀድሜ፡እለምናለኹ።

ዐልፎ፡ዐልፎ፡ለጥቂቶቻችን፡ሊብራሩልን፡የሚያሹ፡ቃላት፡ወይም፡ሐሳቦች፡ሲገጥሙ ፥ እገጹ፡እግርጌ፡ላይ፡በኅዳግ፡ማስታወሻ፡ተብራርተዋል። ለብዙዎቻችኹ፡ትርፍ፡መኾኑ፡ይሰማኛል ፤ ኾኖም ፥ ኹላችንም፡በእኩል፡መረዳት፡ጉዳዩን፡እንድናነበው፡ተብሎ፡ነውና ፥ ዳግመኛ፡ትዕግሥታችኹን፡እጠይቃለኹ። በቅጂ፡ቅጂነት፡በኅዳግ፡ማስታወሻ፡የተመለከቱትን፡ሐሳቦች፡ኹሉ ፥ ከምንጫቸው፡የምንቀዳበትን፡ዐቅም፡ዐውደ፡ቀለም፡ራሱ፡ከንግዲህ፡ለማንኛችንም፡ሰጥቶናልና ፥ የዚህ፡መመሪያ፡ቀጣይ፡ክለሳዎች፡ይህኑ፡በማገናዘብ፡አብዛኛውን፡የኅዳግ፡ማስታወሻ፡ቀስ፡በቀስ፡ይሠርዙታል።

እጽሑፉ፡ውስጥ፡የሚገኙ፡ስሕተቶችና፡እንከኖች፡ኹሉ፡በታዩ፡ወይም፡በተጠቈሙ፡ቊጥር፡ይታረማሉ።

ውርድ ፡—

ይህ፡"ዐውደ፡ቀለም፡የጽሑፍ፡ማምረቻ"፡የተሠኘ፡መሳሊያ ፥ ለነጻ፡አገልግሎት፡ሲቀርብ ፥ ባሠራሩም፡ኾነ፡በብቃቱ፡ምንም፡ዐይነት፡ዋስትናን፡አይሰጥም። ለብጀታውም፡የሚከተሉት፡ንምራውያን፡ዐቅሞች ፥ በተመለከተባቸው፡ያገልግሎት፡ፈቃድ፡መሠረት ፥ ውለዋል ፡—

- ነጻው፡የአምስተርዳም፡ምድራስ፡SWI-Prolog፡መቀመሪያ ፤
- ነጻው፡የፕሪንስተን፡ምድራስ፡WordNet፡እንግሊዝኛ-እንግሊዝኛ፡ንምራዊ፡መዝገበ፡ቃላት ፤
- ነጻው፡MyThes፡የፈረንሳይኛ-ፈረንሳይኛ፡ግስ ፤
- ነጻው፡WOLF፡የፈረንሳይኛ፡WordNet፡ግስ ፤
- ነጻው፡የካርነጊይ፡ሜለን፡ምድራስ፡CMUDict፡የአሜሪካዊ፡እንግሊዝኛ፡ላሕይ፡ንምራዊ፡ምእላድ።

እባክዎ፡www.awde-qelem.net ንና፡www.gzamargna.net ን፡ይጐብኙ!

The AwdeQelem User's Manual is written in three languages [ዐማርኛ • English • Français]. The spelling, wording and meaning of the text have all been checked for mistakes; it is, however, likely that there still remain some. I ask the reader's leniency, considering the absence of an editorial team.

Any error or inconsistency will be removed as soon as it is noticed or notified.

DISCLAIMER:

The software AwdeQelem is provided as-is, with no explicit or implied warranties in respect of its properties, including, but not limited to, correctness and/or fitness for purpose.

The following digital resources have been integrated to AwdeQelem, while respecting their license requirements:

- Amsterdam University's free-ware SWI-Prolog programming system;

Le manuel utilisateur de AwdeQelem est rédigé en trois langues: [ዐማርኛ • English • Français]. L'orthographie, l'énoncé ainsi que le sens du texte ont tous été vérifiés. Il est, cependant, plus que probable qu'il reste encore à faire à cet égard; je prie le lecteur de faire preuve d'indulgence, vue l'absence d'une équipe éditoriale.

Toute erreur ou inconsistance sera corrigée dès qu'elle est remarquée ou signalée.

DÉCHARGE DE RESPONSABILITÉ:

Le logiciel AwdeQelem est offert tel quel, sans aucune garantie explicite ou implicite, quant à ses propriétés de justesse ou d'aptitude entre autres.

Les ressources numériques suivantes ont été intégrées dans le logiciel AwdeQelem, tout en respectant les exigences de leurs licences respectives:

- le système de programmation gratuit SWI-

• Princeton University's free-ware English-English digital dictionary WordNet release 2.1;

• MyThes free-ware French-French glossary;

• WOLF free-ware WordNet-French glossary;

• Carnegie Mellon University's free-ware CMUDict American English Pronunciation Database.

Please visit:

Prolog de l'université d'Amsterdam;

• le dictionnaire gratuit anglais-anglais WordNet version 2.1 de l'université de Princeton;

• le glossaire gratuit français-français MyThes;

• le glossaire WordNet-français gratuit WOLF;

• la base de données des prononciations de l'anglais américain gratuit CMUDict de l'université Carnégie Mellon.

Veuillez visitez:

awde-qelem.net & gzamargna.net

ዐውደ ፡ ቀለም ፡ መሳሊያንም ፡ ኾነ ፡ መመሪያውን ፥ እንዳለም ፡ ኾነ ፡ ለዋውጦ ፡ መሸጥ ፡ ፈጽሞ ፡ ክልክል ፡ ነው ።

It is strictly forbidden to sell the AwdeQelem software
or its documentation, with or without modification.

Il est formellement interdit de vendre le logiciel AwdeQelem ainsi que sa documentation, avec ou sans modification.

© በጽሑፉም ፡ ኾነ ፡ በመሳሊያው ፡ ረገድ ፡ ያለው ፡ መብት ፡ ኹሉ ፡ ለደራሲው ፡ በሕግ ፡ የተጠበቀለት ፡ ነው ።
All rights reserved • Tous droits réservés.

ምስጋና • Acknowledgements • Remerciements

የምዕራብ ፡ ሥልጣኔ ፡ ዐይነተኛዎች ፡ ውጤቶች ፡ የኾኑት ፡ ዘመናውያኑ ፡ ጥበብና ፡ ኪነት ፥ ከጥንታውያኑ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሥልጣኔና ፡ ዕውቀት ፡ ጋራ ፡ በገቢር ፡ ሲሳተፉ ፥ ለሰው ፡ ልጅ ፡ የላቀ ፡ ጥቅምን ፡ እንደሚያስገኙ ፡ አያጠራጥርም ።

ኢ.ምንት ፡ በኾነ ፡ ደረጃና ፡ ዐቅም ፡ ከመከናወኑ ፡ በቀር ፥ ዘመናዊውን ፡ የስሌትኛ ፡ ኪነትና ፡ ጥንታዊውን ፡ ኢ.ትዮጵያዊ ፡ የቀለም ፡ ዕውቀት ፡ በማዋሐድ ፡ የተበጀው ፡ "ዐውደ ፡ ቀለም ፥ የጽሑፍ ፡ ማምረቻ" ፥ እንሆ ፥ በመሣሪያነቱ ፡ ዐዲስ ፡ የሥነ ፡ ጽሑፍ ፡ ዐቅምን ፡ አስገኝቶልን ፥ ይህን ፡ እውነት ፡ በአማን ፡ መስክሯል ።

ይህን ፡ ደኀኛ ፡ ክንዋኔ ፡ ያስቻለ ፦ ከማጯለም ፡ ይልቅ ፡ ማብራት ፤ ከመንፈግ ፡ ይልቅ ፡ መስጠት ፤ ከመቅበር ፡ ይልቅ ፡ ማውጣት ፤ ከመጐዳት ፡ ይልቅ ፡ መጥቀም ፤ ከማደኸየት ፡ ይልቅ ፡ ማበልጸግ ፤ ከመናናቅ ፡ ይልቅ ፡ መከባበር ፤

የሚለው ፡ ደኀኛ ፡ የሥልጣኔ ፡ ጠባይ ፡ ነውና ፥ በርሱ ፡ ተመርተው ፡ ዕውቀትን ፡ ከነማከናወኛ ፡ ንምራዊ ፡ ዐቅሙ ፡ ለሰው ፡ ልጅ ፡ በማዳረስ ፡ ዘወትር ፡ የሚጥሩትን ፡ ግለኞችና ፡ ተቋማት ፣ ማኅበራትና ፡ መንግሥታት ፡ ዅሉ ፡ ከልብ ፡ አመሰግናለኹ ። በተለይ ፥ ደግሞ ፦

- የኢ.ትዮጵያዊ ፡ ቀለም ፡ ወይም ፡ ሥነ ፡ ጽሑፍ ፡ እናት ፡ የኾነችዪቱን ፡ የኢ.ትዮጵያ ፡ ኦርቶዶክስ ፡ ተዋሕዶ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፤
- የቀለምን (1) ፡ ምንነት ፡ አጥርተው ፡ ያሳወቁኝን ፥ የወጠንኩትን ፡ ሥራ ፡ ምትና ፡ ግቱን ፣ መነሻና ፡ መድረሻውን ፡ በሐሳብ ፡ የነደፉልኝንና ፥ መሠረታዊ ፡ የወጣኒ ፡ ዕውቀትን ፡ ጐልመው ፡ የሰጡኝን ፡ ሊ.. ፡ ዤኔራል ፡ ነጋ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ ፤
- የሥራውን ፡ ታናሽነት ፡ ሳይንቁ ፥ ስውርና ፡ ገሀድ ፡ ዕንቅፋቶች ፡ መኖራቸውንም ፡ በማስተዋል ፥ በማናቸውም ፡ ነገር ፡ እንዳልቸገር ፥ መካርና ፡ ታዳጊ ፣ ደራሽና ፡ ዳራጊ ፡ ኾነው ፡ የተከባከቡኝን ፡ ቤተሰቦቼ ፤
- በቀጥታም ፡ ኾነ ፡ በተዘዋዋሪ ፥ ዕውቀታቸውን ፡ አውርሰውን ፡ ያለፉትን ፣ ያሉትንም ፡ የኢ.ትዮጵያ ፡ ሊ.ቃውንት ፤
- የፈረንሳይን ፡ ዘመናዊ ፡ ትምህርት ፡ ካንደኛ ፡ ደረጃ ፡ እስከ ፡ ምድራስ ፡ ("ዩኒቨርስቲ") ፡ ድኅረ ፡ ምረቃ ፡ ጥርየትኛን ፡ ያስተማረኝንና ፡ ከምዕራባዊው ፡ ባህል ፡ ያስተዋወቀኝን ፡ የፍረንሳይ ፡ ሥርዐተ ፡ ትምህርት ፤
- የስሌትኛን ፡ ትምህርት ፡ በምድራስ ፡ ደረጃ ፡ አስተምሮ ፡ ለምረቃ ፡ ያበቃኝን ፡ የብሪታንያ ፡ ሥርዐተ ፡ ትምህርት ፤
- ዐውደ ፡ ቀለም ፡ መግበርን ፡ ለማብጀት ፡ (ያውም ፡ ባማርኛ ፡ ቅመራ!) ፡ ያገለገሉኝን ፡ SWI-Prolog ና ፡ XPCE ፡ የተባሉትን ፡ የድንቅ ፡ ድንቅ ፡ መቀመሪያዎች ፥ በኢ.ንተርኔት ፡ አማካይነት ፥ ለማንኛውም ፡ አስሊ. ፡ አገልግሎት ፡ በነጻ ፡ የናኙትን ፡ የአምስተርዳም ፡ ምድራስ ፡ (Amsterdam University) ፡ ተመራማሪዎች ፡ ያን ፡ ቪ.ለሜከርን ፡ (Jan Wielemaker) ፣ አንዦ ፡ አንዠቪ.ርደንን ፡ (Anjo Anjewierden) ፡ እና ፡ የ SWI-Prolog ፡ የብጅት ፡ ቡድንን ፤
- የዓለምን ፡ ሕዝቦች ፡ በማስማማትና ፡ በማገናኘት ፡ እጅጉን ፡ የሚያገለግለንን ፡ የእንግሊ.ዝኛ ፡ ቋንቋን ፡ ቃላት ፡ በሞላ ፡ ከነፍቻቸው ፡ በ WordNet ፡ ንምራዊ ፡ መዝገበ ፡ ቃላት ፡ አጠናቅረው ፡ በታላቅ ፡ ቸርነት ፡ ለዓለሙ ፡ ዅሉ ፡ በነጻ ፡ የናኙትን ፡ የፕሪንስተን ፡ ምድራስ ፡ (Princeton University Cognitive Science Lab) ፡ ተመራማሪዎች ፤
- ከእንግሊ.ዝኛ ፡ ቋንቋ ፡ ጋራ ፡ ተመሳሳይ ፡ አገልግሎት ፡ የሚሰጠውን ፡ የፈረንሳይኛ ፡ ቋንቋ ፡ ግስ ፡ አጠናቅረው ፡ ለማንኛችንም ፡ በነጻ ፡ ያበረከቱልንን ፡ ኬቪ.ን ፡ ሄንድሪክስ ፣ ፍሬዴሪክ ፡ ላቤ ፡ እና ፡ ሎራን ፡ ጎዳር ፡ (Kevin Hendricks ፣ Frederic Labbé ፣ Laurent Godard) ፤
- ከእንግሊ.ዝኛ ፡ WordNet ፡ ግስ ፡ ጋራ ፡ ከሞላ ፡ ጐደል ፡ የሚነጻጸረውን ፡ WOLF ፡ የፈረንሳይኛ ፡ WordNet ፡ ግስ ፡ አጠናቅሮ ፡ ለማንኛችንም ፡ በነጻ ፡ ያበረከተልንን ፡ በኗ ፡ ሳጎ ፡ (Benoît Sagot) ፤
- የእንግሊ.ዝኛን ፡ ጽሑፍ ፡ ከምዕራባዊ ፡ ጻሕፍ ፡ ወደ ፡ ኢ.ትዮጵያዊ ፡ ጻሕፍ ፡ ለመመለስ ፡ ያገለገለኝን ፡ CMUDict ፡ የአሜሪካዊ ፡ እንግሊ.ዝኛ ፡ ላሕይ ፡ መዝገብን ፡ አብጅተው ፡ ለነጻ ፡ አገልግሎት ፡ ያበረከቱትን ፡ የካርነጊይ ፡ ሜለን ፡ ምድራስ ፡ (Carnegie Mellon University) ፤
- እንዲሁም ፥ በልዩ ፡ ልዩ ፡ መንገድ ፡ የረዱኝን ፡ ዅሉ ፤

እግዚ.አብሔር ፡ ይስጥልኝ ፡ እያልኹ ፥ ጥልቅ ፡ ምስጋናዬን ፡ በትሕትና ፡ አቀርብላቸዋለኹ ።

መሣሪያ ፡ ለደግም ፡ ለክፉም ፡ ይውላልና ፤ ከክፉው ፡ ይልቅ ፡ ደጉ ፡ እያመዘነ ፥ የሰው ፡ ልጅ ፡ ዅሉ ፡ እንዲጠቀም ፡ የእግዚ.አብሔር ፡ ረድኤት ፡ አይለየን ፤ አሜን ።

አነሣሥቶ ፡ ላስዠመረኝ ፥ አስዠምሮ ፡ ላስፈጸመኝ ፡ ለልዑል ፡ እግዚ.አብሔር ፡ ክብር ፡ ምስጋና ፡ ይግባ ፥ ለዘለዓለሙ ፤

አሜን ፨

ወሴ ፡ ነጋ ።

1 "ቀለም" ፡ ብዙ ፡ ትርጕም ፡ አለው ፤ (1) ፡ ቀሠም ፡ ወይም ፡ ቀጪን ፡ መቃ ፤ (2) ፡ ቀለም ፡ በያይነቱ ፥ አረንጓዴ ፣ ብጫ ፣ ቀይ ፣ ... ፤ (3) ፡ ሥነ ፡ ጽሑፍ ፥ "የቀለም ፡ ትምህርት" ፡ እንዲሉ ። እዚ.ህ ፡ ላይ ፡ 3 ኛውን ፡ ትርጕም ፥ ሥነ ፡ ጽሑፍን ፡ ለማለት ፡ ውሏል ።

There is no possible doubt that from the dialogue between any two Civilisations — in this instance, Western and Ethiopian Civilisations — will come out a greater good.

At an infinitely modest level, this same truth has been verified through the development of the application AwdeQelem: the result of the fusion of Western science, technology, languages and script with their Ethiopian counterparts.

This has been made possible thanks to the free dissemination of knowledge and its means of digital implementation, by the tireless efforts of individuals, associations, institutions, and States driven by the enduring principles of all civilisations: *enlightenment, openness, goodwill, solidarity, and mutual respect*. As one of their beneficiaries, I express to all of them my deepest gratitude.

In particular, I would like to thank:

- the Ethiopian Orthodox Tewahdo Church, mother of Ethiopian literature;
- the late Lt. Gen. Negga Hayle Sllasé (Negga Haile Sellassie) who first made me aware of the profound significance of literature, sketched the broad dimensions of the present work, and passed on to me the basic literary skills required;
- my close relatives, who, conscious more than anyone, of the many obstacles to overcome, even for such a humble enterprise, unfailingly lent me their generous support and precious advice;
- the generations of Ethiopian scholars who bequeathed us their knowledge through diverse means;
- the French education system which from primary school to post-graduate studies in Economics, completed my education, and introduced me to Western culture in general;
- the British university system for providing me with a sound graduate level education in Informatics;
- Jan Wielemaker, Anjo Anjewierden and the SWI-Prolog and XPCE development team from Amsterdam University for making freely available the superb SWI-Prolog programming system which I have used for the implementation of AwdeQelem, moreover

Il ne fait aucun doute que du dialogue entre deux civilisations — en l'occurrence les civilisations occidentale et éthiopienne — émergera un bien supérieur.

À un niveau infiniment modeste, cette même vérité a été vérifiée par le développement de l'application AwdeQelem: le résultat de la fusion de la science, la technologie, les langues et l'écriture occidentales et de leurs équivalentes éthiopiennes.

Ceci est rendu possible par la dissémination gratuite de la connaissance et des moyens de son implémentation numérique, grâce à l'effort incessant d'individus, associations, institutions et États guidés par les principes perpétuels de civilisation: *la lumière, l''ouverture, la bonne volonté, la solidarité, et le respect mutuel*. Étant moi-même un des bénéficiaires, je leur exprime ici ma profonde gratitude.

En particulier, je voudrai remercier:

- l'église orthodoxe tewahdo éthiopienne, mère de la littérature éthiopienne;
- feu le Lt. Gén. Negga Hayle Sllasé (Negga Haile Sellassie), qui le premier m'a fait prendre conscience de l'importance de la littérature; a dessiné les grandes lignes du présent travail; m'a transmis les compétences de base requises;
- mes proches, qui, conscients mieux que quiconque des nombreux obstacles à surmonter, même pour une entreprise aussi humble, m'ont immanquablement apporté leur soutien généreux et prodigué leurs précieux conseils;
- les générations de savants éthiopiens qui nous ont légués leurs connaissances par divers moyens;
- le système éducatif français, pour avoir complété mon éducation depuis la primaire jusqu'aux études supérieures de troisième cycle en sciences économiques, et pour m'avoir introduit à la culture occidentale en général;
- le système universitaire britannique qui m'a donné une formation solide de premier cycle en informatique;
- Jan Wielemaker, Anjo Anjewierden et l'équipe de développement de SWI-Prolog et XPCE de l'université d'Amsterdam pour avoir dispensé gratuitement le superbe système de programmation qu'est SWI-Prolog, et que j'ai utilisé pour l'implémentation de AwdeQelem, qui

coded in Amharic!

• The Princeton University Cognitive Science Lab for making freely available that most important resource, WordNet, the full English language digital dictionary; a truly great act of generosity; the WordNet dictionary is integrated into AwdeQelem;

• Kevin Hendricks, Frederic Labbé and Laurent Godard who, in the absence of a free-ware "WordNet-français", availed all of us of an extensive glossary of the French language; this too is integrated into AwdeQelem;

• Benoît Sagot who has partly filled in the gap resulting from the absence of a free-ware "WordNet-français", by offering us instead WOLF (WordNet Libre Français) which is also integrated into AwdeQelem;

• Carnegie Mellon University for blessing the whole world with a very useful American English pronunciation database, CMUDict, which is extensively used in the transliteration module of AwdeQelem;

• all those who supported me in different ways.

With the advent of new capabilities, may the good always triumph over evil.

plus est, codé en amharique!

• le laboratoire de science cognitive de l'université Princeton qui a aussi gratuitement mis à la disposition de tous cette importante ressource que constitue WordNet, le dictionnaire numérique de la langue anglaise; un acte d'une très grande générosité; le glossaire WordNet est intégré dans AwdeQelem;

• Kevin Hendricks, Frederic Labbé et Laurent Godard qui, en l'absence d'un "WordNet-français" gratuit, nous ont doté d'un considérable glossaire français-français; celui-ci aussi est intégré dans AwdeQelem;

• Benoît Sagot, qui a en partie comblé le vide créée par l'absence d'un "WordNet-français" gratuit, en nous offrant à la place WOLF (WordNet Libre Français) qui est maintenant intégré dans AwdeQelem;

• l'université Carnégie Mellon qui a gratifié le monde entier d'une très utile base de données des prononciations de l'anglais américain, CMUDict, largement utilisé par le module de transcription de AwdeQelem;

• tous ceux qui m'ont aidé de diverses manières.

Avec l'avènement de nouvelles capacités, puisse le bien triompher toujours sur le mal.

Welé Negga

መቅድም • Preface • Préface

ነፍሳቸውን ፡ ይማርና ፥ ከጄኔራል ፡ ነጋ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ ፡ ጋራ ፡ ከሥራ ፡ መሳተፍ ፡ በውነት ፡ ከታላቅ ፡ ዕድል ፡ ይቈጠራል ። ከሕይወቴ ፡ አብዛኛውን ፡ ዘመን ፡ ዕድሉን ፡ በማግኘቴ ፥ እግዚአብሔርን ፡ ዘወትር ፡ አመሰግናለኹ ። ይህን ፡ ሳላስታውስ ፡ ባልፍ ፥ አንባብያንን ፡ እንደ ፡ በደልኳቸው ፥ ትልቅ ፡ ግንዛቤን ፡ እንደ ፡ ነፈግኋቸው ፡ ሊቈጠርብኝ ፡ ይገ̇ባ̇ልና ፥ ባጪሩም ፡ ቢኾን ፥ ምስክርነቴን ፡ በጽሑፍ ፡ ላስፍር ፤ ይፈቀድልኝ ።

ሕይወታቸውና ፡ ሥራቸው ፡ እንደሚገልጸው ፥ ገድላቸውና ፡ መሥዋዕትነታቸው ፡ እንደሚመሰክረውም ፥ ጄኔራል ፡ ነጋ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ ፡ በ 20 ኛው ፡ ምእትያ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ካፈራቻቸው ፡ ምርጥ ፡ ልጆቿ ፡ አንዱ ፡ ናቸው ። ታሪካቸው ፡ ገና ፡ አልተጻፈም ፡ (ለነገሩ ፥ የማኘኛውስ ፡ ታላቅ ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ ታሪክ ፡ ተጽፏል?) ፤ ሥራቸውም ፡ አፍርቶ ፡ ገና ፡ አላበቃም ።

ዐውደ ፡ ቀለም ፡ የጽሑፍ ፡ ማምረቻ ፥ ከሥራ ፡ ዘመናቸው ፡ የመጨረሻው ፡ ምዕራፍ ፥ አንዱ ፡ የድካማቸው ፡ ፍሬ ፡ ነው ።

ከወጣትነታቸው ፡ ዘመን ፡ አንሥቶ ፡ እስከሕይወታቸው ፡ ፍጻሜ ፡ ድረስ ፥ እብሪታንያ ፡ በስደት ፡ በኖሩበት ፡ ዘመንም ፡ እንኳ ፡ (ከ 1967 ፡ ዓ.ም. ፡ እስከ ፡ 1999 ፡ ዓ.ም.) ፥ ከሀገራዊ (2) ፡ የግዛት ፡ ጕዳይ ፡ ጋራ ፥ የቀለምን ፡ ወይም ፡ የሥነ ፡ ጽሑፍን ፡ ጕዳይ ፡ ሥራዬ ፡ ብለው ፡ ሲደክሙለት ፡ ኖረዋል ። በተፈጥሮ ፡ ካላቸው ፡ የቋንቋ ፣ የሥነ ፡ ጽሑፍ ፣ የመመራመር ፡ ፍቅር ፡ ጋራ ፥ ቀለም ፡ ለሀገራዊ ፡ ህልውና ፡ ያ̇ለውን ፡ ፋይዳ ፡ ክፍ ፡ አድርገው ፡ ይገምቱ ፡ ስለ ፡ ነበር ፥ በቤተሰብ ፡ ደረጃም ፡ ኾነ ፡ በማኅበራዊ ፥ ተገቢ ፡ በመሰላቸው ፡ አጋጣሚ ፡ ኹሉ ፡ ሥነ ፡ ጽሑፍን ፡ ከማበረታታት ፣ ከማረማመድና ፡ ከማስፋፋት ፡ ጽኑ ፡ ፍላጎት ፡ ጋራ ፥ በተግባር ፡ የተመሰከረ ፡ ውለታን ፡ ለሀገር ፡ ውለዋል ። ይህኑ ፡ ቁም ፡ ነገራቸውን ፡ ካስተዋሉ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ታላላቅ ፡ ሊቃውንት ፡ መኻከል ፥ እንደ ፡ አለቃ ፡ ደስታ ፡ ተክለ ፡ ወልድ ፡ ያ̇ሉ ፡ ወዳጆችን ፡ አፍርተዋል ። አለቃ ፡ ደስታ ፡ ተክለ ፡ ወልድ ፥ በተለይ ፡ በዝነኛው ፡ ያማርኛ ፡ መዝገበ ፡ ቃላታቸው (3) ፥ እንዲሁም ፡ የቀደሙ ፡ ሀገራውያን ፡ ሊቃውንት ፥ እንደ ፡ መምህር ፡ ክፍለ ፡ ጊዮርጊስ ፣ አለቃ ፡ ኪዳነ ፡ ወልድ ፡ ክፍሌ (4) ፥ ከነርሱም ፡ በኋላ ፥ እንደ ፡ መልአከ ፡ ብርሃን ፡ አድማሱ ፡ ጀንበሬ ፣ ከሣቴ ፡ ብርሃን ፡ ተሰማ ፡ ሀብተ ፡ ሚካኤል ፡ ግጽው ፡ ያ̇ሉ ፥ ሌሎችም ፥ መጻሕፍት ፡ ባለማሳተማቸው ፡ ትውልድ ፡ የረሳቸው ፡ ታላላቅ ፡ ሊቃውንት ፥ ከነገሥታት ፣ ካገር ፡ አዋዮች ፡ ያላነሰ ፡ ለሀገር ፡ ህልውና ፡ መ̇ጠበቅ ፣ ለሀገር ፡ እግዚእናና ፡ ነጻነት ፡ መከበር ፡ የማይተካ ፡ ውለታን ፡ ውለዋል ። ውለታቸውም ፡ ሊረ̇ሳ̇ ፡ አይገባም ፤ በእየጊዜው ፡ መታሰቢያው ፡ እየተዘከረና ፡ እየተከበረ ፥ በአርኣያነቱ ፡ ትውልዶችን ፡ እያነጸ ፡ ሊቀጥልና ፡ ሊለመልም ፡ ይገ̇ባ̇ል ።

መምህር ፡ ክፍለ ፡ ጊዮርጊስ ፡ (1917 ፡ ዓ.ም.–1881 ፡ ዓ.ም.) ፡ የተባሉት ፡ "አራት ፡ ዐይና" ፡ ሊቅ ፥ ደቀ ፡ መዝሙራቸው ፡ አለቃ ፡ ኪዳነ ፡ ወልድ ፡ ክፍሌ ፡ የጨረሱላቸውን ፡ የግእዝ ፡ መዝገበ ፡ ቃላት ፡ ለማዘጋጀት ፡ የተነሡበት ፡ አንዱ ፡ ምክንያት ፥ የፈረንጅ ፡ ሊቃውንት ፡ በሚያስደንቅ ፡ ብልኀነትና ፡ ታታሪነት ፡ የኢትዮጵያን ፡ ቋንቋዎች ፡ እዚያው ፡ አውሮፓ ፡ ኾነው ፡ ተምረው ፤ ወደ ፡ ኢትዮጵያም ፡ እየዘለቁ ፡ ዕውቀታቸውን ፡ አዳብረው ፥ በዚህችው ፡ ዕውቀታቸው ፡ የግእዝም ፡ ያማርኛም ፡ መዛግብተ ፡ ቃላትን ፡ አሳትመው ፡ ስላዩ ፥ ከመንፈሳዊ ፡ ቅንአትም ፡ በላይ ፥ እመዛግብተ ፡ ቃላቱ ፡ ውስጥ ፡ ብዙ ፡ ስሕተትና ፡ ግድፈት ፡ መኖሩን ፡

---

2 ሀገር ፥ በግእዝ ፥ ከተማ ፣ መዲና ፣ የታጠረ ፣ የተቀጠረ ፡ ማለት ፡ ኾኖ ፥ የመንግሥት ፡ ሥልጣን ፡ መቀመጫን ፡ ጨምሮ ፥ ሕግና ፡ ሥርዐት ፡ የሰፈነበትን ፡ አካባቢ ፡ ኹሉ ፥ ገጠርንም ፡ ያጠቃልላል ፤ ወይም ፥ በሌላ ፡ አነጋገር ፥ ሀገር ፡ የሕዝብና ፡ የብሔር ፡ (የምድር) ፡ ውሕደት ፡ ነው ። በመሠረቱ ፥ በፈረንጅኛ ፡ "city" ፡ ከሚባለው ፡ ጋራ ፡ ይስማማል ። "ሀገራዊ"ም ፥ በስምነትም ፡ በቅጽልነትም ፡ ከ"citizen" ፡ ጋራ ፡ ይስማማል ። "nation" ፡ የሚለው ፡ ቃል ፡ ደግሞ ፥ ላቲን ፡ "nasci" ፡ ("ተወለደ") ፡ ካለው ፡ የወጣ ፡ ሳቢ ፡ ዘር ፡ እንደ ፡ መኾኑ ፡ መጠን ፥ "ውልደት" ፡ በትኽክል ፡ ይተረጕመዋል ፤ "national" ፡ ደግሞ ፡ "ውልደታዊ" ፣ "የውልደት" ፣ "ተወላጅ" ፣ ወይም ፡ "ወለደኛ" ፡ ሊባል ፡ ይችላል ። ኾኖም ፥ በጊዜ ፡ ብዛት ፡ "national" ፡ የ"ሀገራዊ"ን ፡ ትርጕም ፡ ይዞ ፥ ከተወላጅነትም ፡ ይልቅ ፡ ሀገራዊነትን ፡ (citizenship • citoyenneté)ን ፡ አመልክቶ ፡ ይገኛል ። በኛም ፡ ከ"ሀገራዊ" ፡ ይልቅ ፡ "ዜጋ" ፡ የሚለው ፡ ተለምዷል ፤ ኾኖም ፡ "ዜጋ" ፡ ግእዝ ፡ "ዜገ=ተገዛ ፣ ተዋረደ" ፡ ካለው ፡ የወጣ ፡ በመኾኑ ፡ "subject"ን ፡ እንጂ ፡ "citizen"ን ፡ አይፈታም ። ስለዚህ ፥ ከ"ዜጋ" ፡ ይልቅ ፡ "ሀገራዊ" ፡ ወይም ፡ "አገራዊ" ፡ ወይም ፡ ደግሞ ፡ "አገሬ" ፡ ማለቱ ፡ ይመረጣል ። "nation"ን ፡ በስሕተት ፡ "ብሔር" ፡ ብለው ፡ የሚተረጕሙም ፡ አሉ ። "ብሔር" ፡ ግን ፡ ግእዝ ፡ "ብሒ̇ር/ብሒሮት ፤ መስፋት ፣ መዘርጋት ፣ መንጣለል" ፡ ካለው ፡ አንቀጽ ፡ የተገኘ ፡ የቦታና ፡ የጊዜ ፡ ስፋትን ፡ የሚያመለክት ፡ ስም ፡ ስለ ፡ ኾነ ፥ "nation"ን ፡ ፈጽሞ ፡ አይፈታም ። የ"ብሔር" ፡ ፈረንጅኛ ፡ ትርጕም ፥ ሲጠብ ፡ "territory • territoire" ፥ ሲሰፋ ፡ ደግሞ ፡ "universe • univers" ፡ ማለት ፡ እንጂ ፥ ከውልደት ፡ ጋራ ፡ የሚያገናኘው ፡ ነገር ፡ የለም ። ለማጠቃለል ፥ ለ"citizen" ፡ "ሀገራዊ" ፥ ለ"nation" ፡ ደግሞ ፡ "ውልደት" ፡ የሚለውን ፡ ትርጓሜ ፡ ይዘናል ።

3 **ደስታ ፡ ተክለ ፡ ወልድ** ፡ (አለቃ) ፤ ዐዲስ ፡ ያማርኛ ፡ መዝገበ ፡ ቃላት ። አርቲስቲክ ፡ ማተሚያ ፡ ቤት ፤ ዐዲስ ፡ አበባ ፥ 1962 ፡ ዓ.ም. ። 1284 ፡ ገጽ ። http://www.gzamargna.net/html/amargnaMezgebeQalat.html

4 **ኪዳነ ፡ ወልድ ፡ ክፍሌ** ፡ (አለቃ) ፤ መጽሐፈ ፡ ሰዋስው ፡ ወግስ ፡ ወመዝገበ ፡ ቃላት ፡ ሐዲስ ። አርቲስቲክ ፡ ማተሚያ ፡ ቤት ፤ ዐዲስ ፡ አበባ ፥ 1948 ፡ ዓ.ም. ። 908 ፡ ገጽ ። http://www.gzamargna.net/html/gzMezgebeQalat.html

ተገንዝበው ፣ "መንቀፍ ፡ በሥራ ፡ ነው" ፡ በማለት ፡ ግዴታቸውን ፡ ለመወጣት ፡ ነበር ። ይህም ፡ የግእዝ ፡ መዝገበ ፡ ቃላታቸው ፣ ባለቃ ፡ ኪዳነ ፡ ወልድ ፡ ክፍሌ ፡ ብሩህ ፡ አእምሮና ፡ ሰፊ ፡ ዕውቀት ፡ ተከናውኖ ፣ ባለቃ ፡ ደስታ ፡ ተክለ ፡ ወልድ ፡ ብርታትና ፡ ትጋት ፡ ተዘጋጅቶ ፣ በአርቲስቲክ ፡ ማተሚያ ፡ ቤት ፡ ባለቤት ፡ በኢትዮጵያዊው ፡ አርመን ፡ ኤልያስ ፡ ጄርሃያን ፡ ልጨኝነት ፡ ለኅትመት ፡ በቅቶ ፣ እንሆ ፡ ዛሬ ፡ ለግእዝና ፡ ዐማርኛ ፡ ቋንቋዎቻችን ፡ "ዳግማዊ ፡ ሐመረ ፡ ኖኅ"ን ፡ ኾኖላቸው ፣ ለሀገራዊ ፡ ቀለም ፡ መስፋፋት ፡ የማይናወጽ ፡ መሠረትን ፡ ለመጣል ፡ አስችሏል ።

እንግዲህ ፣ ከኢትዮጵያ ፡ ሊቃውንት ፡ ቀጥሎ ፣ የውጭ ፡ ሊቃውንትና ፡ ተቋማትም ፡ ውለታ ፡ ሊታሰብ ፡ ይገባል ።

በዚህ ፡ ረገድ ፣ በ 1920 ዎቹ ፡ እተፈሪ ፡ መኰንን ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ባማርኛና ፡ በፈረንሳይኛ ፡ ይሰጥ ፡ የነበረው ፡ ዘመናዊ ፡ ትምህርት ፣ የመዠመሪያዎቹን ፡ የኹለተኛ ፡ ደረጃ ፡ ተማሪዎች ፡ ሲያፈራ ፣ ተማሪዎቹ ፡ የ"ኡኒቬርሲቴ • université" ፡ መግቢያ ፡ የ"ባካሎሬያ" ፡ ፈተናቸውን ፡ እንዲፈተኑ ፡ የኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ የትምህርት ፡ ምጋቤ ፡ ("ሚኒስቴር") ፡ የፈረንሳይን ፡ መንግሥት ፡ ትብብር ፡ ጠየቀ ። ዘመኑ ፡ የቅኚ ፡ ግዛት ፡ መስፋፊያ ፡ ነበርና ፣ ምንም ፡ የፈረንሳይ ፡ መንግሥት ፡ በጎ ፡ ፈቃድ ፡ ቢታይ ፣ በተለይ ፡ የብሪታንያና ፡ የኢጣሊያ ፡ ሌጋስዮኖች ፡ "አይደረግም!" ፡ ብለው ፡ በመቃወም ፡ የፈረንሳይን ፡ መንግሥት ፡ ቢወተውቱ ፣ የኢትዮጵያ ፡ እውነተኛ ፡ ወዳጅ ፡ የኾኑ ፡ መስየ ፡ ዣን̄ ፡ ጋሪኮኢክስ ፡ (Monsieur Jean Garicoïx) ፡ የተባሉት ፡ የተፈሪ ፡ መኰንን ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ፈረንሳዊ ፡ ሥራ ፡ አስኪያጅ ፣ ብቻቸውን ፣ የፈረንሳይን ፡ መንግሥት ፡ ዕጥፉን ፡ ወትውተውና ፡ አሳምነው ፣ ለመዠመሪያ ፡ ጊዜ ፡ የ"ባካሎሬያ" ፡ ፈተና ፡ በ 1926 ፡ ዓ.ም. ፡ ተካኼደ ። በዚህም ፡ ፈተና ፣ የጄኔራል ፡ ነጋ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ ፡ ታላቅ ፡ ወንድም ፣ አሰፋ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ ([5]) ፡ የ"ባካሎሬያ ፡ ሲያን̄ቲፊክ" ፡ ፈተናቸውን ፡ አንደኛ ፡ በመውጣት ፡ በ"ኤክሴላን̄" ፡ ማዕርግ ፡ ዐልፈው ፣ ይህን ፡ ታሪካዊ ፡ ክብር ፡ አግኝተዋል ። ጄኔራል ፡ ነጋ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴም ፡ ከታላቅ ፡ ወንድማቸው ፡ ከለማ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ ([6]) ፡ ጋራ ፣ በዚሁ ፡ በ"ባካሎሬያ ፡ ሲያን̄ቲፊክ" ፡ ዘርፍ ፣ ፈተናቸውን ፡ በ"ትሬ ፡ ቢየን̄" ፡ ማዕርግ ፡ ዐልፈው ፡ ተመርቀዋል ። ከርሳቸው ፡ ጋራ ፡ የተመረቁት ፡ ወጣት ፡ ተማሪዎችም ፣ ብዙዎቹ ፡ ዐብረዋቸው ፡ እገነት ፡ ሆሎታ ፡ ጦር ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ገብተው ፡ ዳግመኛ ፡ በመኰንንነት ፡ ተመርቀው ፣ ታሪክ ፡ የመዘገበላቸውን ፡ ታላቅ ፡ መሥዋዕትነት ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ዐርበኞችና ፣ ቀጥሎም ፡ በርዳታ ፡ ከመጣው ፡ ከብሪታንያ ፡ ጦር ፡ ጋራ ፡ ፈጽመው ፣ ፋሺስት ፡ ኢጣልያን ፡ ድል ፡ አድርገዋል ። ከድልም ፡ በኋላ ፣ የብሪታንያ ፡ ጦር ፣ ያልተጠበቀ ፤ ኢትዮጵያን ፡ ቅኝ ፡ ግዛት ፡ የማድረግ ፡ ስውር ፡ ዕቅዱን ፡ ይፋ ፡ ባወጣ ፡ ጊዜ ፣ እፊቱ ፡ ተጋርጠው ፡ የመለሱት ፡ እነዚሁ ፡ መኰንኖችና ፡ ዐርበኞች ፡ ናቸው ። ታዲያ ፣ ዣን̄ ፡ ጋሪኮኢክስ ፡ ለብሔራዊት ፡ ርትዕ ፡ መከበር ፡ ሲል ፡ የዋለልን ፡ ይህ ፡ ታላቅ ፡ ውለታ ፡ እንዴት ፡ ይረሳ?

የቅኝ ፡ ግዛት ፡ አደጋ ፡ ዐልፎ ፣ ዛሬ ፡ በተሐድሶ ፡ ቅኝ ፡ ግዛት ፡ አደጋ ፡ ተተክቷል ፤ ያእምሮ ፡ ቅኝ ፡ ግዛት ፡ አንዱ ፡ አስከፊው ፡ መልኩ ፡ ነው ። ጦርነቱ ፡ ከአፍኣ ፡ ይልቅ ፡ ወደ ፡ ውስጥ ፣ ከባዕድ ፡ ይልቅ ፡ ወደ ፡ ወገን ፣ ከሥጋ ፡ ይልቅ ፡ ወደ ፡ ነፍስ ፡ ተሸጋግሯል ። መከላከያው ፡ መንፈሳዊ ፡ ትጥቅ ፡ እንደ ፡ መኾኑ ፡ መጠን ፣ ከሃይማኖት ፡ ጋራ ፡ ቀለም ፡ ወይም ፡ ሥነ ፡ ጽሑፍ ፡ ዐይነተኛው ፡ ብርሃናዊ ፡ ኀይል ፡ ነውና ፤ ፈጥነን ፡ ልንጨብጠው ፡ ይገባል ።

ነገሩን ፡ በጥልቅ ፡ የተረዱት ፡ ጄኔራል ፡ ነጋ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ ፣ ከ 1960 ዎቹ ፡ አጋማሽ ፡ እስከ ፡ 1990 ዎቹ ፡ ዓ.ም. ፡ መፈጸሚያ ፡ እብሪታንያ ፡ በኖሩበትም ፡ የስደት ፡ ዘመን ፣ ብዙ ፡ ሰው ፡ ተስፋ ፡ በቈረጠበት ፣ ርሳቸው ፡ ገና ፡ ታላላቅ ፡ የሥራ ፡ ዕቅዶችን ፡ ነድፈው ፣ ለሥራው ፡ የሚተባበራቸው ፡ ሰው ፡ ቢያጡም ፣ "ረዳት ፡ እስኪገኝ" ፡ ብለው ፡ ሳያቅማሙና ፡ ሥራን ፡ ሳይወዝፉ ፣ እግዚአብሔር ፡ በሰጣቸው ፡ ጊዜና ፡ ዐቅም ፡ ዘወትር ፡ ይደክሙ ፡ ነበር ። ከዕቅዶቻቸው ፡ አንዱን ፣ በየካቲት ፡ ወር ፡ 1988 ፡ ዓ.ም. ፡ ተወጥኖ ፡ "የኢትዮጵያ ፡ ዐውደ ፡ ቀለም" ፡ በተሠኘ ፡ የማኅበር ፡ ስም ፡ እውን ፡ ኾኖ ፡ ለማየት ፡ በቅተዋል ።

---

5 **አሰፋ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ** ፡ (1907–1927 ፡ ዓ.ም.) ፣ ትምህርታቸውን ፡ ባስደናቂ ፡ ፍጥነትና ፡ ውጤት ፡ እንደ ፡ ጨረሱ ፣ በሐረርጌ ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ የትምህርት ፡ ቤቶች ፡ ዋና ፡ አስተዳዳሪ ፡ ተብለው ፡ ከመሾማቸው ፡ በፊት ፣ ለጥቂት ፡ ጊዜ ፡ በንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ በልዩ ፡ ጸሓፊነት ፡ አገልግለው ፡ ጥቂት ፡ የውጭ ፡ መጻሕፍትንም ፡ ለንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ተርጕመዋል ። እንዲሁም ፣ "የጥንት ፡ አባቶቻችን ፡ ዕውቀቶች • Les connaissances de nos pères anciens" ፡ የተሠኘ ፡ ድርሰትን ፡ ደርሰው ፡ ነበር ፤ ባለመታደል ፣ የእጅ ፡ ጽሑፉ ፡ በኢጣሊያ ፡ ወረራ ፡ ዘመን ፡ ጠፍቷል ። ብዙ ፡ ተስፋ ፡ ተጥሎባቸው ፡ የነበሩት ፡ ጐልማሳ ፣ በ 1927 ፡ ዓ.ም. ፡ ገና ፡ የ 20 ፡ ዓመት ፡ ወጣት ፡ ኾነው ፣ ድንገት ፡ በጠና ፡ ታመው ፡ ሕይወታቸው ፡ ዐልፏል ።

6 **ለማ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ** ፡ (1909–1988 ፡ ዓ.ም.) ፣ ከድል ፡ በኋላ ፣ የምህንድስና ፡ ትምህርታቸውን ፡ በቤልጀክ ፡ "ኡኒቬርሲቴ ፡ ደ ፡ ናሙር" ፡ አጠናቀው ፣ የመዠመሪያው ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ የ"ጄት ፡ ኤንጅን" ፡ መሀንድስ ፡ በመኾን ፣ በዚሁ ፡ ሚያቸው ፡ በኢትዮጵያ ፡ አየር ፡ ኀይል ፡ ውስጥ ፡ አገራቸውን ፡ እስካ 1960 ዎቹ ፡ አገልግለዋል ።

ማኅበሩ ፥ ምንም ፡ የከበረ ፡ ዐላማ ፡ ቢኖረው ፥ የማይተኛለት ፡ ፀርም ፡ አለበትና ፥ አደጋው ፡ የታያቸው ፡ አንዳንድ ፡ የሚቀርቧቸው ፡ ወገኖቻቸው ፦ ይቅርብዎ ፤ ተንኰለኞች ፡ ከዋናው ፡ ሥራዎ ፡ ሊያዘናጉዎና ፥ የቀረችዎን ፡ ዕድሜ ፡ ሊያባክኑብዎ ፡ ይኾናል ፥ እያሉ ፡ ቢያሳስቧቸውም ፤ ርሳቸው ፥ በተፈጥሯቸው ፡ ተስፋ ፡ መቍረጥን ፡ የማያውቁ ፣ ሰውን ፡ አማኝ ፡ ስለ ፡ ኾኑ ፥ ሥጋቱ ፡ ሥጋት ፣ አደጋውም ፡ አደጋ ፡ አልመሰላቸው ። በመታደል ፥ በዚህ ፡ ዕቅዳቸው ፡ ዐብሬያቸው ፡ ሠርቻለኹ ፤ ኹኔታውንም ፡ በቅርብ ፡ ተከታትያለኹ ። ማኅበሩ ፡ በወር ፡ አንዴ ፡ እየተሰበሰበ ፥ ካሥር ፣ ካሥራ ፡ ዐምስት ፡ የማይበልጡ ፡ ቋሚ ፡ ተሳታፊዎችን ፡ ይዞ ፥ በእውነቱ ፡ በሚያስመሰግን ፡ ትጋት ፡ እየሠራ ፥ የህልውናው ፡ ዋነኛ ፡ መሠረት ፡ የኾነውን ፡ መሠረታዊ ፡ ደንቡን ፡ አርቅቆ ፡ እንደ ፡ ጨረሰ ፥ እማጽደቁ ፡ ላይ ፡ ነገሩ ፡ ኹሉ ፡ መጓተት ፡ ዠመረ ። መቼም ፥ "ክፉን ፡ ሳያልፉ ፡ ደግ ፡ አይገኝም"ና ፥ የገነገነ ፡ ብንገነግንም ፥ ዤኔራል ፡ ነጋ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ ፥ ፍንክች ፡ ሳይሉ ፥ የማጽደቁን ፡ ቀሪ ፡ ረድፍ ፡ በትዕግሥት ፡ አስፈጽመው ፥ መስከረም ፡ 24 ፡ ቀን ፡ 1990 ፡ ዓ.ም. ፡ ማኅበሩ ፡ መሠረታዊ ፡ ደንቡን ፡ አጽድቆ ፥ ሕጋዊ ፡ ሰውነቱን ፡ በገቢር ፡ አገኘ ። በሥራው ፡ ቅደም ፡ ተከተል ፡ መሠረት ፥ የደንቡን ፡ መጽደቅ ፡ ተከትሎ ፡ በኅዳር–ታኅሣሥ ፡ 1991 ፡ ዓ.ም. ፡ ሰፊ ፡ ጉባኤን ፡ ለመጥራት ፡ ዝግጅቱ ፡ ተጠናቆ ፥ የጥሪው ፡ በራሪ ፡ ወረቀት ፡ በሚሰናዳበት ፡ ወቅት ፥ የተፈራው ፡ ደረሰና ፥ የሥራው ፡ ግሥጋሤ ፡ ተሰናክሎ ፡ ክፉኛ ፡ ተገታ ። ረዥም ፡ መንገድ ፡ በእግር ፣ በባቡር ፡ እየተጓዙ ፡ ለሦስት ፡ አራት ፡ ዓመት ፡ የደከሙለት ፡ ሥራ ፡ ለጊዜው ፡ ፍሬቢስ ፡ መስሎ ፡ ጥቂት ፡ ቢታዘንም ፤ ዋናው ፡ ቁም ፡ ነገር ፡ የደንቡ ፡ መረቀቅና ፡ መጽደቅ ፡ ስለ ፡ ነበር ፥ የማኅበሩን ፡ ዐላማ ፡ ወደን ፡ እስከዚህ ፡ ጸንተን ፡ የቈየነው ፡ አባላት ፥ "ጊዜም ፡ አልባከነ ፤ ጉልበትም ፡ አልጣመነ ፤ ሥራም ፡ አልመከነ" ፡ ብለን ፡ ዕንቅፋቱን ፡ ዐልፈን ፥ ሥራችንን ፡ ባዲስ ፡ ስልት ፡ ቀጠልን ። ጉባኤ ፡ እየጠሩ ፡ ዐመድ ፡ ዐፋሽ ፡ ከመኾን ፡ ይልቅ ፥ በዘመኑ ፡ ኪነት ([7]) ፥ በማስሊያ ([8]) ፡ እና ፡ በኢንተርኔት ፡ የተሻለ ፡ ውጤት ፡ እንደሚገኝ ፡ በማመን ፥ የሥራ ፡ ስልታችንን ፡ ዐደስን ። በወቅቱ ፡ የስሌትኛ ([9]) ፡ ትምህርቴን ፡ አጠናቅቄ ፡ ነበርና ፥ ከምረቃዬ ፡ በኋላ ፥ ሥራዬ ፡ ብዬ ፡ "ዋዜማ ፡ ሥርዐት" ፡ የተሠኘውን ፡ ነጻ ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ የማስሊያ ፡ መጻፊያ ፡ ሥርዐት ፡ አከናውኜ ፥ በነሐሴ ፡ ወር ፡ 1992 ፡ ዓ.ም. ፡ በኢንተርኔት ፡ ይፋ ፡ አወጣኹት ። ተለምነው ፡ ከሚመጡ ፡ ጥቂት ፡ ጉባኤተኞች ፡ ይልቅ ፥ ስፍር ፡ ቍጥር ፡ የሌላቸውን ፡ ብርቱ ፡ ሠራተኞች ፡ ለዚሁ ፡ ለቀለም ፡ ዐላማ ፡ በመላ ፡ ዓለም ፡ አገኘንበት ። ዐይነተኛው ፡ የቀለም ፡ ሥራ ፡ የሚመጥነውን ፡ መሣሪያ ፥ በኢንተርኔት ፡ አማካይነት ፥ ታጠቀ ፤ ወሰን ፡ አልባ ፡ ብሔሩን ፡ አለበሰ ፤ ኹለንተናዊ ፡ ምላቱን ፡ አገኘ ። ጊዜና ፡ ቦታ ፡ ሳይለያያቸው ፥ ሥራና ፡ ሠሪ ፣ መምህርና ፡ ተማሪ ፡ ተገነኛኙበት ።

በዚሁ ፡ ሥራ ፡ ተጠምጄ ፡ ስሠራ ፡ ቈይቼ ፥ ዤኔራል ፡ ነጋ ፡ ኀይል ፡ ሥላሴ ፡ ከክብርት ፡ ባልተቤታቸው ፡ ከወይዘሮ ፡ ከፈይ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ ፡ ጋራ ፥ ሚያዝያ ፡ 7 ፡ ቀን ፡ 1999 ፡ ዓ.ም. ፡ ወደ ፡ ውድ ፡ አገራቸው ፡ ኢትዮጵያ ፡ ሲመለሱ ፥ እኔ ፥ እዚሁ ፡ እብሪታንያ ፡ ቈየኹ ።

የያዝኩትን ፡ ሥራ ፡ በማሳለጥ ፥ ከ"ዋዜማ ፡ ሥርዐት" ፡ ጐን ፥ ጠቃሚና ፡ መሠረታዊ ፡ የኾነውን ፡ "ግእዝ–ዐማርኛ" ([10]) ፡ የተባለውን ፡ ለግእዝና ፡ ላማርኛ ፡ የመሠረተ ፡ ትምህርት ፣ የመዛግብተ ፡ ቃላትና ፡ የመጻሕፍት ፡ ንምራዊ ([11]) ፡ መድበል ፡ አሰናድቼ ፥ ይፋ ፡ ከማውጣቴ ፡ ጥቂት ፡ ቀናት ፡ በፊት ፥ ዐዲስ ፡ አበባ ፡ ስልክ ፡ ደውዬ ፡ የምሥራቹን ፡ ለዤኔራል ፡ ነጋ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴና ፡ ለወይዘሮ ፡ ከፈይ ፡ አበሠርኳቸው ። ዤኔራል ፡ ነጋ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴም ፦ እጅግ ፡ በጣም ፡ ደስ ፡ አለኝ ፤ እግዚአብሔር ፡ ይስጥኽ ፡ ብለው ፡ መረቁኝ ።

ኾኖም ፥ መርበቢያውን ([12]) ፡ አጠናቅቄ ፥ የማስታወቂያ ፡ በራሪ ፡ ወረቀቱን ፡ ዐይነተኛ ፡ ረቂቅ ፡ ለኅትመት ፡ ባስረከብኹ ፡ በኹለተኛው ፡ ቀን ፥ ዤኔራል ፡ ነጋ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ ፥ ሐምሌ ፡ 16 ፡ ቀን ፡ 2000 ፡ ዓ.ም. ፡ ማረፋቸውን ፡ በታላቅ ፡ ድንጋጤና ፡ ሐዘን ፡ ተረዳኹ ።

ቅን ፡ ሥራቸው ፡ ግን ፥ እንሆ ፥ ሕያው ፡ ኾኖ ፥ ዛሬ ፥ "ዐውደ ፡ ቀለም ፥ የጽሑፍ ፡ ማምረቻ" ፡ በተሠኘ ፡ መግበር ፡ ፍሬውን ፡ አቅርቧል ።

እግዚአብሔር ፡ ይመስገን!

---

7 **ኪነት** ፤ የኪንነት ፡ ኹኔታ ፥ ጠቅላላው ፡ የኪን ፡ ውጤት ፤ ኪንኛ ፥ ነገረ ፡ ኪን ፥ የኪን ፡ ጥናት ። (technology • technologie)

8 **ማስሊያ** ፤ የስሌት ፡ መሣሪያ ። (computer • ordinateur)

9 **ስሌትኛ** ፤ ነገረ ፡ ስሌት ፥ የስሌት ፡ ጥበብ ። (informatics • informatique)

10 http://www.gzamargna.net

11 **ንምራዊ** ፤ የንምር ። (digital • numérique)

12 **መርበቢያ** ፤ የመረብ ፡ መገኛ ፡ (website • site "web") ።



"A foundry was erected, and the «Great Sebastopol», which was destined to be the crushing blow for him, and the means of our salvation, was begun."
Henry Blanc, London, 1868 A.D.

ከጥንት ፣ ከመሠረት ፡ሲወርድ ፡ ሲዋረድ ፡ በመጣው ፡ የኢትዮጵያ ፡ የግዛት ፡ ሥርዐት ፥ "ሕዝብ ፡ አንጋሽ ፤ መስፍን ፡ ነጋሽ ፤ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ቀዳሽ" ፡ በሚል ፡ መሪ ፡ ቃል ፥ ከባለቃል ፡ ኪዳኑ ፡ የአጋቦስ ፡ ወሰሎሞናዊ ፡ ዘርዐ ፡ ነገሥት ፡ በወንድ ፡ በኩል ፡ የሚወለደው ፡ መስፍን ፥ ዐልጋ ፡ ወራሽ ፡ በመኾን ፥ የንጉሥ ፡ ነገሥትነትን ፡ ሥልጣን ፡ ከሕዝብ ፡ እየተሠየመ ፥ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ እየተቀባ ፥ በሞት ፡ ወይም ፡ በሌላ ፡ ምክንያት ፡ ዘመነ ፡ መንግሥቱ ፡ ያከተመውን ፡ የቀደመ ፡ ንጉሥ ፡ ነገሥት ፡ ይተካ ፡ ነበር ። ዐልፎ ፡ ዐልፎ ፥ ወይ ፡ ከዘርዐ ፡ ነገሥቱ ፡ ከሚወለዱት ፡ አንዱ ፡ የይገባኛል ፡ ጥያቄን ፡ በባላንጣነት ፡ ያነሣል ፤ ወይም ፡ የማይወለደው ፡ ሌላ ፡ ልበ ፡ ትልቅ ፡ ያምፃል ፤ ወይም ፡ ደግሞ ፡ ጠቅላላው ፡ ኹኔታ ፡ አስገድዶ ፥ የንጉሥ ፡ ነገሥትነቱን ፡ ሥልጣን ፡ አላግባብ ፡ በጕልበት ፡ እየተቀናቀኑ ፥ የፊተኛው ፡ በ"ዐምባ ፡ ገነንነት" ፣ የኋለኛው ፡ በ"ዐፄ ፡ በጕልበቱነት" ፡ እሥልጣኑ ፡ ሰገነት ፡ ላይ ፡ እየወጡ ፥ በፈላጭ ፡ ቈራጭነት ፡ በመንግሥታዊው ፡ ኀይል ፡ የወነበዱበት ፡ የታሪክ ፡ ወቅት ፡ መፈራረቁም ፡ አልቀረ ። ባግባቡ ፡ ባልተሠየመ ፡ ያገዢ ፡ ላይ ፡ ሕዝቡ ፡— ማን ፡ ሠየመኽና? ፡ ማን ፡ ነኝስ ፡ ብለኽ ፡ ነው? ፡ እያለ ፡ ተራውን ፡ አልገዛም ፡ ብሎ ፡ በያግጣጫው ፡ ማመፁ ፡ ስለማይቀር ፥ ዐምባ ፡ ገነኑም ፡ ኾነ ፡ ዐፄ ፡ በጕልበቱው ፥ እሕዝብ ፡ ዘንድ ፡ ተቀባይነትን ፡ እንደማያገኙ ፡ ስለሚያውቁ ፥ በኀይል ፡ ደፍጥጦና ፡ በጭካኔ ፡ አስሰቅጥጦ ፡ ለመግዛት ፡ ይገደዳሉ ።

ይህን ፡ በመሰለ ፡ የታሪክ ፡ ኺደት ፡ ከተጓዙቱ ፡ ውስጥ ፡ አንዱ ፡ ዐፄ ፡ በጕልበቱ ፡ "አባ ፡ ታጠቅ" ፡ ቴዎድሮስ ፡ ነበሩ ። በዘመነ ፡ መሳፍንት ፡ ተከፋፍላ ፡ የተዳከመችውን ፡ ኢትዮጵያ ፡ ዳግመኛ ፡ "አንድ ፡ አደርጋለኹ" ፡ ብለው ፡ ከመነሣታቸው ፡ ጋራ ፥ ዘመናዊውንም ፡ ጥበብ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ለማሥረጽ ፡ የፈረንጅ ፡ መሀንድሶችንና ፡ ብረተኞችን ፡ እያስመጡ ፥ ብዙ ፡ መጣራቸው ፡ ይተረካል ። ከጥረታቸው ፡ አንዱ ፡ ተምሳሊታማ ፡ ውጤት ፡ "ሴባስቶፖል" ፡ የተባለው ፡ መድፍ ፡ ነው ፡ (የታወቀው ፡ "ሴባስቶፖል" ፡ ይኹን ፡ እንጂ ፥ ሌሎችም ፡ ተሠርተው ፡ ነበር) ። «መድፍ ፡ ሥሩልኝ» ፡ ብለው ፡ ያዘዟቸው ፡ የፈረንጅ ፡ መሀንድሶች ፥ አመጣጣቸው ፡ ምናልባት ፡ አገርን ፡ ለቅኝ ፡ ግዛትነት ፡ ለመቃኘት ፡ ቢኾን ፡ እንጂ ፥ አንዲት ፡ አፍሪቃዊት ፡ አገርን ፡ የምዕራባዊ ፡ ጥበብ ፡ ባለቤት ፡ ለማድረግ ፡ አልነበረምና ፥ ለንጉሡ ፡ መታዘዝ ፡ ግዴታቸው ፡ ቢኾንም ፥ ቀላሉን ፡ ሥራ ፥ ዙሪያ ፡ ጥምጥም ፡ አድርገው ፡ አክብደው ፥ በተንኰል ፡ አመከኑት ።

በመቶ ፣ በኹለት ፡ መቶ ፡ ኪሎ ፡ ብረት ፡ ተሠርቶ ፡ የሚፈለገውን ፡ አገልግሎት ፡ ሊሰጥ ፡ የሚችለውን ፡

መድፍ ፥ ሠላሳ ፣ አርባ ፡ ዕጥፍ ፡ አክብደውት ፥ ለርሱ ፡ የሚበቃውን ፡ ብረታብረት ፡ ለማግኘት ፡ ያለ ፡ የሌለ ፡ ማረሻና ፡ ዶማ ፣ ሰይፍና ፡ ጐራዴ ፣ ካራና ፡ ዱቢት ፣ ነፍጥና ፡ ሽጉጥ ፣ ንዋየ ፡ ቅድሳት ፡ ሳይቀር ፡ ተሰበሰበ ። ይሄን ፡ ኹሉ ፡ ብረት ፡ ለማቅለጥ ፡ ከሰል ፡ እንዲከማች ፥ እልፍ ፡ አእላፍ ፡ ዛፍ ፡ ተቈረጠ ፤ አገር ፡ መሬት ፡ ጫካ ፡ ተመነጠረ ። መድፉም ፡ በውድ ፡ ተሠርቶ ፡ ሲያበቃ ፥ እንዴት ፡ ተደርጎ ፡ እመቅደላ ፡ ዐምባ ፡ ላይ ፡ ይውጣ ፦ የፈረደበት ፡ ባላገር ፡ በትእዛዝ ፡ ወጥቶ ፥ ይህን ፡ ስምንት ፡ ቶን ፡ መድፍ ፡ በገመድ ፡ እየጐተተ ፥ ጥቂቱም ፡ ገደል ፡ እየገባ ፡ እያለቀ ፥ መጨረሻውን ፡ አፋፍ ፡ ደረሰ ። ግዙፉ ፡ መድፍ ፡ የሚጐርሠውን ፡ አንድ ፡ የመድፍ ፡ ጥይት ፡ ለመሥራት ፡ ደግሞ ፥ ላሥር ፡ ሺ ፡ የነፍጥ ፡ ጥይት ፡ የሚበቃ ፡ ባሩድ ፡ ባከነ ። መጨረሻውን ፥ ኹሉም ፡ ነገር ፡ ተሰናድቶ ፥ በቍርጡ ፡ ቀን ፥ ባጠቃቸው ፡ በእንግሊዝ ፡ ሰራዊት ፡ ላይ ፡ ተተኰሶ ፥ «ድራሻቸውን ፡ ያጠፋዋል» ፡ ተብሎ ፡ ባላዋቂ ፡ የዋህ ፡ አእምሮ ፡ ሲጠበቅ ፥ የመዠመሪያውን ፡ ጥይት ፡ እንደ ፡ ተኰሰ ፥ "ሴባስቶፖል" ፡ ለኹለት ፡ ተሠንጥቆ ፡ ወልቆ ፡ ቀረ ፤ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስም ፡ ከወደቀበት ፡ ቦታ ፡ ያነቃነቀው ፡ አልተገኘ ። ከዚያ ፡ በኋላ ፡ የደረሰውን ፡ ኹሉም ፡ ያውቀዋል ፡ ... ። ምንም ፡ የተነሡለት ፡ ሀገራዊ ፡ ዐላማ ፡ የሚመሰገን ፡ ቢኾን ፥ ሥልጣንን ፡ ከሕዝብ ፡ ያልተሠየሙት ፡ ዐፄ ፡ በጒልበቱ ፡ ቴዎድሮስ ፥ በመጨረሻ ፥ ሕዝቡም ፡ ሰራዊቱም ፡ ከድቷቸው ፥ ብቻቸውን ፡ እመቅደላ ፡ ዐምባ ፡ ላይ ፦ *ለባዕድ ፡ እጄን ፡ ከምሰጥ ፡ ሞቴን ፡ እመርጣለኹ* ፡ ብለው ፥ የመጨረሻዋን ፡ ጥይት ፡ በገዛ ፡ እጃቸው ፡ ጠጥተው ፡ ሞቱ ። በቀቢጸ ፡ ተስፋ ፡ ራስን ፡ ማጥፋት ፡ በባህላችን ፡ ምንም ፡ የተነወረ ፣ በሃይማኖቶችም ፡ የተከለከለ ፡ ቢኾን ፥ የኢትዮጵያዊነትን ፡ ክብር ፡ በእምቢተኛነት ፡ በማስጠበቃቸው ፥ ለዘለዓለሙ ፡ ሲታሰቡ ፡ ይኖራሉ ።

ያንኑ ፡ ያኽል ፡ ግን ፥ የሥልጣንን ፡ ተገቢነት ፡ በሚሸርና ፡ መንግሥትን ፡ በሚያዳክም ፡ መንገድ ፡ በጒልበት ፡ እሥልጣኑ ፡ ሰገነት ፡ ላይ ፡ የመውጣት ፡ የዐመፃ ፡ አስተሳሰብ ፡ ከዚያ ፡ ወዲህ ፡ እንደ ፡ ተገቢ ፡ አደራረግ ፡ እንዲቈጠርና ፥ ወጣቱ ፡ ትውልድ ፡ በአርኣያነቱ ፡ እንዲከተለው ፥ በከፍተኛ ፡ የትምህርት ፡ ማእከሎች ፡ ኹሉ ፡ ሥራዬ ፡ ብለው ፡ የሚሰብኩትና ፡ የሚያለምዱት ፥ በተለይ ፡ ባዕዳን ፡ መምህራን ፡ እስከ ፡ ዘመናችን ፡ ሲጥሩ ፡ ኖረዋል ። አንዳንድ ፡ የእኛው ፡ ደራስያንም ፡ እጅግ ፡ በተጋነነ ፥ አንዳንዴም ፡ ፍርደ ፡ ገምድል ፡ በሚያሠኝ ፡ አገላለጽ ፡ ሲተርኩልን ፡ ኖረዋል ። መጨረሻውን ፥ እንዲህ ፡ በንትልዮሽ ፡ (በ"ኒኺሊዝም") ፡ አጥፊ ፡ ባህል ፡ የተኰተኰተው ፡ ዐዲስ ፡ ወጣት ፡ ትውልድ ፥ *"ይህን ፡ ያረጀ ፡ ሥርዐት ፡ ገርስሰን ፡ ጥለን ፥ ባዲስ ፡ ሥርዐት ፡ እንተካዋለን"* ፡ በሚል ፡ ጊድር ፡ ብቻ ፡ ሲነሣሣ ፥ መገርሰሱን ፡ ዐሰበ ፡ እንጂ ፥ የሚተካበት ፡ ዐዲስ ፡ ሥርዐት ፡ ባሕርይ ፡ ምን ፡ እንደሚኾን ፥ በመጨረሻስ ፡ ማንን ፡ እንደሚጠቅም ፡ መርምሮ ፡ የሚያውቅበትን ፡ በቂ ፡ ተሞክሮ ፡ ዐብሮ ፡ አላገኘም ፡ ነበርና ፥ ሳያውቀው ፡ ያጥፊዎችና ፡ የነጣቂዎች ፡ መሣሪያ ፡ ኾኖ ፥ ሀገራዊ ፡ ሥርዐቱን ፡ አጠፋ ፥ ሀገሩን ፡ ተነጠቀ ፥ ለሞት ፣ ለስደት ፣ ለጭቈና ፣ ለብዝበዛ ፡ ተዳረገ ።

ኢ.ሕ.አ.ዴ.ግ. ፡ ዐዲስ ፡ አበባ ፡ በገባ ፡ ሰሞንም ፥ ራሳቸውን ፡ "የኢትዮጵያ ፡ ወዳጆች" ፡ ያሠኙ ፡ ጥቂት ፡ ባዕዳን ፥ ያለፈው ፡ አልበቃ ፡ ብሏቸው ፥ ዳግመኛ ፡ ሲያጮሉን ፥ ተሽቀዳድመው ፡ የ"ሴባስቶፖል" ፡ መድፍን ፡ ሐውልት ፥ በየዋሃን ፡ ያገር ፡ ልጆች ፡ ጻማ ፡ ገንዘብ ፥ እመኻል ፡ ዐዲስ ፡ አበባ ፡ ላይ ፡ አስተከሉ ። ኾኖም ፥ በማፌዝ ፡ የተከሉት ፡ ይህ ፡ ሐውልት ፥ ምስክርነቱ ፡ አይታበልምና ፥ በነርሱም ፡ ላይ ፡ እንሆ ፡ ሲመሰክርባቸው ፡ ይኖራል ።

የሥልጣንን ፡ ተገቢነት ፡ በማረጋገጥ ፡ መንግሥቷን ፡ እያጸናችና ፡ ለማንም ፡ የባዕድ ፡ ኀይል ፡ ሳትገዛ ፡ የኖረች ፡ ኢትዮጵያ ፥ ይህን ፡ የሥልጣን ፡ ተገቢነት ፡ ስታጣ ፡ ምንኛ ፡ እንደምትዳከምና ፡ እንደምትጋለጥ ፡ ለማወቅ ፡ ከቴዎድሮስ ፡ ወዲህ ፡ ያለውን ፡ ታሪካችንን ፡ መመርመር ፡ ይበቃል ። ይህን ፡ በሚገባ ፡ ያጤኑት ፡ የውጭ ፡ ኀይሎች ፡ ግን ፥ ዐልፎ ፡ ተርፎ ፥ የጥቃት ፡ ስልታቸው ፡ አድርገውታል ። መንግሥትን ፡ የሥልጣን ፡ ተገቢነትን ፡ በመንሣት ፡ ማድከምና ፡ ግዛቱን ፡ መቀራመት ፡ ዛሬ ፡ በመላው ፡ ዓለም ፥ በተለይ ፡ ደግሞ ፡ በ"ሢሶው ፡ ዓለም" ፡ የዓለማችን ፡ "ኀያላን" ፡ በሰፊው ፡ የሚከተሉት ፡ ዐይነተኛ ፡ ስልት ፡ ኾኗል ። ኹለት ፡ አሠቃቂዎች ፡ የዓለም ፡ ጦርነቶችን ፡ በታላቅ ፡ መሥዋዕትነት ፡ ያሳለፉ ፡ መንግሥታትና ፡ ኀይሎች ፥ ይማራሉ ፡ ብለን ፡ በጠበቅን ፡ ነበር ፤ ዳሩ ፡ ግን ፥ ያንኑ ፡ ጥፋት ፡ አላንዳች ፡ ሥጋት ፡ ዛሬም ፡ እንዳዲስ ፡ ሲደግሙት ፡ እናያለን ። ውጤቱ ፥ ዛሬም ፡ እንደ ፡ ቀድሞው ፥ መላ ፡ ዓለምን ፡ ለዕልቂት ፡ የሚዳርግ ፡ የሰላም ፡ መደፍረስ ፡ መኾኑን ፡ ኹላችንም ፡ በያለንበት ፡ በትካዜ ፡ ታዝበን ፡ ደምድመናል ።

በተለይ ፡ ሀገራችንን ፡ በተመለከተ ፥ በባህላችን ፡ "ቴዎድሮስን ፡ ይዘዝብኽ" ፡ የሚል ፡ አባባል ፡ አለና ፥ የታዘዘብንም ፡ ፍርጃ ፡ ኖሮ ፡ ይኾናል ። ቢኖርም ፡ ቅሉ ፥ መቼም ፡ ቢኾን ፥ የፈረሰን ፡ ሥርዐት ፡ በተገቢ ፡ ሥርዐት ፡ መልሶ ፡ መሥራት ፥ የታጣን ፡ ሥልጣን ፡ በተገቢ ፡ ሥልጣን ፡ መልሶ ፡ መሠየም ፡ ማማረጫ ፡

የማይገኙላቸው ፡ አንድያ ፡ መፍትሔዎች ፡ ናቸውና ፥ ለዚህም ፡ ለዚያም ፡ ሥራ ፥ እንደ ፡ ሕዝብ ፥ ቀንተን ፡ መገኘት ፡ ይኖርብናል ። በንጉሠ ፡ ነገሥታዊም ፡ ኾነ ፡ በሕዝባዊ ፡ መንግሥት ፣ በዋሕድነትም ፡ ኾነ ፡ በደባልነት ፣ ወይም ፡ በሌላ ፡ በሚስማማን ፡ ዐዲስ ፡ ሥርዐት ፡ የምናድርበትን ፡ ሕገ ፡ መንግሥታችንን ፡ በነጻነት ፡ መክረን ፣ ዘክረን ፥ ወደን ፣ ፈቅደን ፡ የመወሰንና ፥ በእግዚእናችን ፡ የማጽደቅ ፡ ሀገራዊ ፡ መብታችንን ፡ ለማንም ፡ ለምንም ፣ በማንም ፡ በምንም ፡ የማንለውጠው ፡ ሕይወታችን ፡ ነውና ፥ ዛሬ ፡ ሕይወታችንን ፡ የምንሰጥለት ፡ ዐላማችን ፡ ኾኗል ። ዛሬ ፥ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ እፊቱ ፡ የተደቀኑበት ፡ የሞት ፡ ሽረት ፡ ግዴታዎቹ ፡ እግዚእናውን ፡ መልሶ ፡ የማስከበርና ፡ የሚያድርበትን ፡ ሕገ ፡ መንግሥቱን ፡ የመሥራት ፡ ዐይነተኛዎቹ ፡ ግዴታዎቹ ፡ ናቸው ። እነዚህን ፡ ግዴታዎቹን ፡ አስቀድሞ ፡ ሳይወጣ ፥ ሌላ ፡ የልማትም ፡ ኾነ ፡ የምቾት ፡ ምኞቶቹን ፡ የሚያሟላበትን ፡ ሥርዐትም ፣ ችሎታም ፣ ነጻነትም ፡ አያገኝም ። የነጠቁትን ፡ ሀገሩን ፡ መልሶ ፡ እጁ ፡ ያግባ!

"ተመኘና ፡ ተሞኘ ፡ ብዙ ፡ ሩቅ ፡ አይደሉም"ና ፥ ለሥርዐት ፡ ያልተገባ ፣ የሕዝብን ፡ ውዴታ ፡ ያላገኘ ፣ ዐቅምን ፡ ያላገናዘበ ፡ ምኞት ፥ ብቻውን ፥ ፍሬቢስ ፡ መኾኑን ፡ ይህ ፡ የሴባስቶፖል ፡ ታሪክ ፡ በማስረጃነት ፡ ያስተምራል ። ዛሬስ ፥ ምን ፡ ያኽል ፡ ተምረንበታል ፧

የዛሬዩቱ ፡ ኢትዮጵያ ፡ በ«እድገትና ፡ "ትራንስፎርሜሽን" ፡ ዕቅድ» ፡ በተታጋችበት ፥ ከዚያም ፡ በ"ብልጽግና ፡ ጎስፐል" ፡ በተጭበረበረችበት ፡ ኹኔታ ፡ "ዳግም ፡ ሴባስቶፖል"ን ፡ እንዳታመርት ፡ ያሠጋል ። በተፈጥሮ ፡ የበለጸገች ፡ ሀገራችን ፡ ኢትዮጵያ ፥ "አብዮቱ" ፡ ከፈነዳ ፡ ሰባተኛ ፡ ሱባዔውን ፡ ብንደፍንም ፥ አኹንም ፡ በሰው ፡ ሠራሽ ፡ ችግር ፡ ምክንያት ፥ ከችግረኞች ፡ አገሮች ፡ ተርታ ፡ ገና ፡ አልወጣችም ። ርግጥ ፡ ነው ፥ ከጥቂት ፡ ዓመት ፡ ወዲህ ፥ "ይህን ፡ ያኽል ፡ መንገድ ፡ ተሠራ ፤ ... ፡ የግብርና ፡ ምርት ፡ ይህን ፡ ያኽል ፡ አደገ ፤ ... ፡ ይህን ፡ ያኽል ፡ ሕዝብ ፡ የጤና ፡ አገልግሎት ፡ አገኘ ፤ ... ፡ የአንከርት ፡ ስልክ ፡ አገልግሎት ፡ ለይህን ፡ ያኽል ፡ ሚልዮን ፡ ሰው ፡ ተዳረሰ ፡ ... ፤ ወዘተ." ፡ የሚል ፡ ዜና ፡ እኛም ፡ ኾላችን ፡ ከ"ኢትዮጵያ ፡ ብሮድካስቲንግ ፡ ኮርፖሬሽን" ([13]) ፡ ዝግጅቶች ፡ አግኝተናል ። ከኹሉም ፡ ከኹሉም ፡ የሕዝቡን ፡ ታታሪነት ፡ አይተን ፡ አድንቀንበታል ። በውጤት ፡ ረገድ ፡ ግን ፥ እንኳን ፡ ከቀረው ፡ ዓለም ፥ ከዚያው ፡ ካፍሪቃችን ፡ አገሮችም ፡ እንኳ ፡ "ቅኝ ፡ ገዦችን ፡ ድል ፡ ያደረገች ፡ አገር" ፡ በሚለው ፡ ባባቶቻችን ፡ ትውፊት ፡ እንኩራ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ እንጂ ፥ በሌሎች ፡ መሳፍርት ፡ ኹሉ ፥ "ልማታችንን" ፡ ስናስተያየው ፥ መግሪብና ፡ ደቡብ ፡ አፍሪቃ ፣ ግብጽና ፡ ናይጄሪያ ፡ ጥለውን ፡ ኼደዋል ። ዛሬ ፡ ደግሞ ፥ "በመደመር ፡ ፍልስፍና" ፡ መነጽር ፡ ሲታይ ፥ ልማቱ ፡ ፍጹም ፡ ሙስናና ፡ ሌብነት ፥ "ዴሞክራሲውም" ፡ ፍጹም ፡ ውንብድናና ፡ ቁማር ፡ ኾኖ ፡ ተገኝቷል ።

እንኳን ፡ የቢልዮን ፡ ዶላር ፡ "ርዳታ" ፡ እየተገኘ ፥ በራሳችንም ፡ ዐቅም ፡ በተሻለ ፡ ፍጥነትና ፡ በደኅነኛ ፡ አረማመድ ፡ ጥሩ ፡ ደረጃ ፡ ላይ ፡ መድረስ ፡ በተቻለ ፡ ነበር ። በየት ፡ ታዲያ ፥ ገንዘቡ ፡ ኹሉ ፡ በሙስና ፡ ቀልጦ ፡ ቀረ ። ርዳታውስ ፡ ምኑን ፡ ያኽል ፡ ርዳታ ፡ ነው ፧ ምኑን ፡ ያኽል ፡ ለጥቅማችን ፡ ይውላል ፧ ምኑን ፡ ያኽልስ ፡ ለባዕዳን ፡ መንግሥታት ፡ "ፎሬይን ፡ ፖሊሲ" ፡ ማስፈጸሚያና ፡ ለውክልና ፡ አገዛዝ ፡ ይውላል ፧ ምን ፡ ያኽል ፣ ምንስ ፡ ይዞ ፡ ተመልሶ ፡ ይወጣል ፧ "ርዳታ" ፡ ከመለመንስ ፥ ምን ፡ አለ ፡ በእየዕለቱ ፡ በጥያራ ፡ ወደ ፡ ለንደን ፡ አሸጋግረን ፡ የምንኰኳውን ፡ ወርቅ ፡ እዚሁ ፡ እማእከላዊ ፡ "ባንክ" ፡ አካብተን ፡ ይዘን ፥ የሚፈለገውን ፡ ያኽል ፡ የውጭ ፡ ምንዛሪ ፡ ብንዋጅበት ፧ የግል ፡ ባንኮቻችን ፡ ገንዘብን ፡ የመፍጠር ፡ ዐቅምስ ፡ በክብት ፡

---

13 በነገራችን ፡ ላይ ፥ የብሪታንያው ፡ "ብሪቲሽ ፡ ብሮድካስቲንግ ፡ ኮርፖሬሽን ፡ (B.B.C.)" ፡ ወኪሎች ፥ በከፊል ፡ ትውልደ ፡ ኢትዮጵያዊት ፡ በኾነችዋ ፡ ተወዳጅ ፡ ዜነኚት ፡ ዘይናብ ፡ በዳዊ ፡ ፊታውራሪትነት ፥ ለ"ኢትዮጵያ ፡ ቴሌቪዥን ፡ (ኢ.ቴ.ቪ.)" ፡ "የሚያ ፡ ድጋፍ"ን ፡ ለመስጠት ፡ ዐዲስ ፡ አበባ ፡ ከከራረሙ ፡ በኋላ ፥ "ኢ.ቴ.ቪ."ን ፡ በአርኣያቸው ፡ የሰመዩት ፡ ይመስል ፥ "የኢትዮጵያ ፡ ብሮድካስቲንግ ፡ ኮርፖሬሽን ፡ (E.B.C.)" ፡ መባሉን ፡ ሰማን ። እውን ፡ ያማርኛ ፡ ቃል ፡ ጠፍቶ ፡ ነውን ፧ ብዙ ፡ መራቀቅ ፡ ሳያስፈልገው ፥ "የኢትዮጵያ ፡ ለፈፋ ፡ አካል" ፡ (ኢ.ለ.አ) ፡ ሊባል ፡ በተቻለ ፡ ነበር ። ይህ ፡ አልበቃ ፡ ብሎ ፥ ፊደል ፡ በመጠኑም ፡ ቢኾን ፡ ይጠነቀቅበት ፡ የነበረው ፡ ድርጅት ፥ ከዚያ ፡ ጊዜ ፡ አንሥቶ ፡ ነገር ፡ ዓለሙን ፡ ፈጽሞ ፡ የተወው ፡ መስሏል ። "ሕዝብ" ፡ "ህዝብ/ኀዝብ" ፡ ተብሎ ፥ "ዓመት" ፡ "አመት" ፡ (በአልፍ ፡ አ ፡ ሲጻፍ ፡ "አመት" ፡ አገልጋይ ፡ ማለት ፡ ነው) ፡ ተብሎ ፡ መጻፍ ፡ ዠምሯል ፤ ...የ"ክልል" ፡ ዝግጅቶችም ፡ በቁቤና ፡ ባማርኛ ፡ ይጻፉ ፡ የነበር ፥ ከዚያ ፡ ወዲህ ፡ በቁቤና ፡ በእንግሊዝኛ ፡ ብቻ ፡ ኾኗል ። ... ፡ ይህ ፡ ነውን ፡ የሞያ ፡ ድጋፍ ፧ ... ፡ አንድ ፡ ፊቱን ፡ "አላዋቂ ፡ ቤት ፡ እንግዳ ፡ ናኘበት" ፡ እንዳንል ፡ ድርጅቱ ፡ የተማሩ ፡ ሰዎች ፡ አሉት ፤ ታዲያ ፡ ምን ፡ ይኾን ፡ ችግሩ ፧ የ"E.B.C." ፡ (ኢ.ለ.አ.) ፡ ሲደንቀን ፥ "ኢሳት"ን ፡ ጨምሮ ፥ "ነጻ ፡ የማወራኛ ፡ ድርጅት ፡ ነን" ፡ የሚሉ ፡ ሌሎች ፡ የማወራኛ ፡ ድርጅቶችም ፡ በዚሁ ፡ መሥመር ፡ ተሰልፈዋል ። ላማርኛ ፡ ምንም ፡ ዐይነት ፡ የፊደልም ፡ ኾነ ፡ የቃላት ፣ የትርጕምም ፡ ኾነ ፡ ያነባበብ ፡ ተገቢ ፡ ጥንቃቄ ፡ ሳያደርጉ ፥ በዘፈቀደ ፡ የሚለፍፉበት ፡ ኹኔታ ፡ ሲታይና ፡ ሲሰማ ፥ እውነትም ፡ ባማርኛ ፡ ላይ ፡ ተዘምቶበታል ፡ ያሠኛል ፡ እንጂ ፥ ማንም ፡ ቢኾን ፡ በገዛ ፡ ሀገሩ ፡ ላይ ፣ በገዛ ፡ ሀገራዊ ፡ ቋንቋው ፡ ላይ ፡ ይህን ፡ ያኽል ፡ አለመቈርቈር ፡ አያሳይም ፡ ነበር ። በጎ ፡ ፈቃድም ፡ ችሎታም ፡ ያላቸው ፡ ዜነኞች ፡ ("ጋዜጠኞች") ፡ በነዚህ ፡ ድርጅቶች ፡ ውስጥ ፡ መኖራቸው ፡ አይዘነጋም ፤ በመዠመሪያ ፡ ደረጃ ፡ ተጠያቂዎቹ ፡ አዘጋጆቹን ፡ የሚመለምሉና ፡ የሚሾሙ ፥ እንዲሁም ፡ አዘጋጆቹ ፡ ራሳቸው ፡ ናቸው ። ምክንያቱም ፥ ባለማወቅ ፡ ነው ፡ እንዳይባል ፥ ተደጋግሞ ፡ መልክትም ፣ አስተያየትም ፣ ነቀፋም ፡ በርከት ፡ ካሉ ፡ አድማጮችና ፡ ተመልካቾች ፡ ተልከዋል ፤ "ዐውቆ ፡ የተኛ ፥ ቢጠሩት ፡ አይሰማም"ና ፥ ማደናቈሩ ፡ ቀጥሏል ። ሌላ ፡ መፍትሔ ፡ የለም ፤ ኢትዮጵያውያን ፡ ተበራተን ፥ ከባዕዳን ፡ ድጐማም ፡ ኾነ ፡ ቍጥጥር ፡ የነጻ ፥ ለፍጹም ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ ዐላማ ፡ የሚሠራ ፡ ሀገራዊ ፡ ማወራኛን ፡ መደርጀት ፡ አለብን ፤ መፍትሔው ፡ ይህው ፡ ነው ።

ወርቃችን ፡ መያዣነት ፡ ምን ፡ አለ ፡ እንደእንግሊዝ ፡ ባንኮች ፡ ዐቅም ፡ ቢዳብርልን ፣ ቢበለጽግልን ፧ ዛሬኮ ፡ የእንግሊዝ ፡ ማእከላዊ ፡ ባንክ ፡ ("ባንክ ፡ ኦፍ ፡ ኢንግለንድ") ፡ አንድ ፡ ወቄት ፡ ወርቅን ፡ አካብቶ ፡ የዋጋውን ፡ 1000 ፡ ዕጥፍ ፡ ፓውንድ ፡ በንግድ ፡ ባንኮቹ ፡ አማካይነት ፡ እምኀበ ፡ አልቦ ፡ ይፈጥራል ። በወርቃችን ፥ 1000 ፡ ዕጥፍ ፡ ቀርቶ ፥ 100 ፡ ዕጥፍ ፡ ብር ፡ ፈጥረንበት ፡ ቢኾን ፡ ኖሮ ፥ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ኹለት ፡ ሦስት ፡ ያባይ ፡ ግድቦችን ፡ በሠራን ፡ ነበር ።

ሰው ፡ ሠራሽ ፡ ችግራችንን ፡ የመፍታት ፡ በጎ ፡ ምኞታችን ፡ እንዲፈጸም ፦ *ከምኞት ፡ ጋራ ፡ ተፈላጊዎቹን ፡ የእግዚእና ([14]) ፡ እና ፡ የርትዕ ፡ መከበርን ፣ የሥርዐትና ፡ የሥልጣን ፡ መኀባትን ፣ የዕውቀትና ፡ የዝግጅት ፡ መሟላትን ፥ ሀገሪቱ ፡ አስቀድማ ፡ እበቂ ፡ ደረጃ ፡ ላይ ፡ አድርሳቸዋለችን ፧ የሚሉ ፡ መሠረታውያን ፡* ጥያቄዎች ፡ እንሆ ፡ ቀርበውልናልና ፥ ኢትዮጵያውያን ፡ አስቀድመን ፡ ልንመልሳቸው ፡ ይገባል ።

እድገት ፡ በ"ኤሌትሪክ" ፡ ኀይል ፡ የማመንጨት ፡ ዐቅም ፡ ቢለካ ፥ በጣልያን ፡ መሀንድሶች ፡ ዐቅድ ፡ ተሠርቶ ፡ ከማያልቀው ፡ ከ"ሕዳሴ" ፡ ግድብ ፡ ይልቅ ፥ የ"ንዩክሊየር" ፡ ኀይል ፡ ማመንጫን ፡ ቻይና ፡ ወይም ፡ መስኮብ ፡ ባጪር ፡ ጊዜና ፡ በግማሽ ፡ ዋጋ ፡ ባነጹልን ፡ ነበር ፤ ከእድገትም ፡ እድገት ፥ ኢትዮጵያ ፡ "ያፍሪቃ ፡ ቻይና" ፡ የምትባልበትን ፡ የምንሃብ ([15]) ፡ መዋቅር ፡ ባበጁልን ፡ ነበር ። ኾኖም ፥ ይህ ፡ ኹሉ ፡ ሀገራዊ ፡ እግዚእናችንን ፡ አያስከብርልንም ፤ የመንግሥትን ፡ ኀይል ፡ በሥልጣን ፡ ተገቢነት ፡ አያከብርልንም ፣ አያጸናልንም ፤ ነጻነታችንን ፡ አያስጠብቅልንም ፤ በግዛትም ፡ ኾነ ፡ በጥርየት ፣ በባህልም ፡ ኾነ ፡ በማኅበራዊ ፣ በቀለምም ፡ ኾነ ፡ በተሰሚነት ፥ ካገር ፡ ጭራነት ፡ አውጥቶ ፡ ያገር ፡ አውራ ፡ አያደርገንም ። እንዲያውም ፥ ሀገራዊ ፡ እግዚእናችንን ፡ ያላስከበርንበት ፡ ይህ ፡ ኹኔታ ፡ ቢቀጥል ፥ የባሰውን ፥ እማንወጣበት ፡ ዐዘቅት ፡ ቀርቅሮ ፥ በ"ቴክኖሎጂ" ፡ ፍንጅ ፡ "ጠርንፎ" ፥ የህልውናችንን ፡ ባለቤትነት ፡ ለመቼውም ፡ አሳጥቶ ፡ ሊያስቀረን ፡ ይችላል ።

እንደ ፡ ቻይና ፡ ያሉ ፡ የውጭ ፡ መንግሥታት ፥ እንዲህ ፡ ለኢትዮጵያ ፡ የተረፉላት ፡ — ፡ ለዚሁም ፡ እናመሰግናቸዋለን ፡ — ፡ አስቀድመው ፡ እግዚእናቸውን ፡ አስከብረው ፥ አንድነታቸውን ፡ ራሳቸው ፡ በሠሩት ፡ ሕገ ፡ መንግሥታቸው ፡ ባንድ ፡ ሕዝብነት ፡ ከውነው ፥ በሀገራዊ ፡ ቋንቋቸው ፡ ዕውቀታቸውን ፣ ምርምራቸውን ፣ ምርታቸውን ፡ አዘምነው ፥ ራሳቸውን ፡ ችለው ፥ ከራሳቸውም ፡ ዐልፈው ፡ ለቀረው ፡ ዓለም ፡ ተርፈው ፡ ነው ።

በተቃራኒው ፥ ኢትዮጵያ ፡ ዛሬ ፥ ባልሠራችው ፡ "ሕገ ፡ መንግሥት" ፡ ተጠፍራ ፡ ትገኛለች ። ያሜሪካ ፡ መንግሥት ፥ ቀደም ፡ ሲል ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ሰጥቶ ፡ የነበረውን ፡ ዕርቅን ፡ የማውረድ ፡ የሽምግልና ፡ ቃሉን ፥ "ፐርል ፡ ሀርበር"ን ፡ በሚያስንቅ ፡ ፍጹም ፡ ክዳት ፥ በግንቦት ፡ ወር ፡ 1983 ፡ ዓ.ም. ፡ በዓለም ፡ ፊት ፡ አፍርሶ ፥ ወዲያው ፥ ዕርቅ ፡ ሳይወርድ ፥ መመሪያ ፡ አስይዞ ፡ በላካቸው ፡ መልክተኞቹ ፥ አላግባብ ፡ በተቋቋመ ፡ የሕገ ፡ መንግሥት ፡ አርቃቂ ፡ ጉባኤ ፥ ይህን ፡ ባዕድ-ሠራሽ ፡ የአፓርትሀይድ ፡ "ሕገ ፡ መንግሥት" ፡ ከተተፋበት ፡ ከደቡብ ፡ አፍሪቃ ፡ አምጥቶ ፡ በእጀ ፡ መናኛ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ላይ ፡ ጭኖባታል ። በዚህ ፡ ባዕድ-ሠራሽ ፡ "ሕገ ፡ መንግሥት" ፡ የባዕዳን ፡ "ጥቅም" ፡ ሲረማመድ ፥ የባለቤቱ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ እግዚእና ፡ ይረመረምበታል ፤ በገዛ ፡ ሀገሩ ፡ በአሕዛብነት ([16]) ፡ እንጂ ፡ ባንድ ፡ ሕዝብነት ፡ "የለኽም!" ፡ ተብሎበታል ፤ ከርስቱ ፡ ተነቅሎበት ፥ ዛሬ ፡ ርስቱ ፡ በእጅ ፡ አዙር ፡ ለ"ሄጅ ፡ ፉንዶች" ፡ ይቸበቸብበታል ፤ ርሱም ፡ ለእስርና ፡ ለችጋር ፥ ለስደትና ፡ ለዕልቂት ፡ ይዳረግበታል ። የግፍ ፡ ግፍ ፥ አኹን ፡ ደግሞ ፥ በ"ዘር ፡ ማጽዳት" ፡ ዘመቻ ፡ ንጹሓን ፣ የዋሃን ፡ ሀገራውያን ፡ በእየዕለቱ ፡ ከእየ"ክልሉ" ፡ ይባረራሉ ፥ የዘገዩትም ፡ ጭዳ ፡ ይባላሉ ። በዚህ ፡ ግፍ ፡ የፈሰሰው ፡ ደም ፣ የጠፋው ፡ ሕይወት ፡ ለፍርድ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ አቤት ፡ ይላሉ ። የየዋሃን ፡ ተበቃይ ፡ ይበቀላል ።

ሀገራዊ ፡ እግዚእናችን ፡ ሲገሰስ ፥ ሀገራችንን ፡ ሲነጥቁን ፥ ዝም ፡ ብለን ፡ አንመለከትም! ፡ ሕይወታችንና ፡ ሥራችን ፡ ኹሉ ፡ የተገሰሰውን ፡ እግዚእናችን ፡ ለማስከበር ፣ የተነጠቅነውን ፡ ሀገራችን ፡ ለማስመለስ ፡ ያለቡ ፡ ሊኾኑ ፡ ይገባል ። በሀገር ፡ ይሉኝታ ፡ የለምና ፥ እኔም ፡ እንደ ፡ አንድ ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ ሀገራዊ ፥ እንሆ ፥ የዐውደ ፡ ቀለምን ፡ መመሪያ ፡ ሳዘጋጅ ፥ በዚሁ ፡ መንፈስ ፡ ስለምጽፍ ፥ በጉዳዩ ፡ እንደ ፡ እኔው ፡ የምትንገበገቡ ፡ ሀገራውያን ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ትረዱልኛላችኹ ፡ ብዬ ፡ አምናለኹ ።

ከ 2010 ፡ ዓ.ም. ፡ አጋማሽ ፡ ወዲህ ፡ የለውጥ ፡ ንቅናቄ ፡ በሀገሪቱ ፡ ቢታይም ፥ ለውጡ ፡ ገና ፡ እውን ፡

---

14 **እግዚእና** ፤ ገዢነት ፣ ባላገርነት ፣ ባለቤትነት ፡ (sovereignty • souveraineté) ። ("እግዚእና" ፡ ሲባል ፡ የሚገባውን ፡ "ሉዐላዊነት" ፡ ሲሉ ፡ ይሰማል ፤ ስሕተት ፡ ነው ። ሉዐላዊነት ፡ በላይነትን ፡ እንጂ ፡ ገዢነትን ፡ አይገልጽም ። የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ የሚፈልገው ፡ ገዢነቱን ፡ ማስከበርና ፡ ሕገ ፡ መንግሥቱን ፡ መሥራት ፡ እንጂ ፥ ከሌሎች ፡ መንግሥታት ፡ ወይም ፡ ከሌሎች ፡ ሕዝቦች ፡ በላይ ፡ ኾኖ ፡ መታየትን ፡ አይደለምና ፥ ያልጠየቀውን ፡ አንዋሸለት ።)

15 **ምንሃብ** ፤ መሥሪያ ፡ ከወር ፥ "ፋብሪቃ" ። (industry • industrie)

16 **አሕዛብ** ፤ (ግ.) ፡ ሕዝቦች ፤ አንድነት ፡ የሌላቸው ፡ ሕዝቦች ።

አልኾነም ። በሙስና ፡ የተደወየው ፡ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ፡ ይዘት ፥ ወይ ፡ በዘዴ ፡ የመወገድን ፡ ደጎኛ ፡ ፍጻሜ ፥ አለዚያም ፡ በራሱ ፡ የመደርመስን ፡ ክፉ ፡ ፍጻሜ ፡ የሚጠባበቅ ፡ ይመስላል ። ርግጥ ፡ ነው ፥ እሥልጣኑ ፡ ሰገነት ፡ ላይ ፡ የተተኩት ፡ ሰዎች ፥ እያደር ፡ ለመፍረስ ፡ የተቃረበውን ፡ ሥርዐታቸውን ፡ "እያደሱ" ፡ ለመቀጠል ፡ የሚፈልጉትን ፡ ያኽል ፥ "ተፎካካሪ" ፡ ያሏቸውን ፡ የስያሳ ፡ ድርጅቶችንም ፡ ከኺደቱ ፡ ባጫፋሪነት ፡ አሳትፈዋል ። ስለሕዝብ ፡ እግዚእና ፡ መከበርም ፡ ኾነ ፣ ዐዲስ ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ስለ ፡ መሠራት ፥ አላግባብ ፡ ከወጡበት ፡ የሥልጣን ፡ ሰገነት ፡ ስለ ፡ መውረዳቸውም ፡ ኾነ ፣ ስለ ፡ ሽግግር ፡ መንግሥት ፡ መመሥረት ፡ የቀረበላቸውን ፡ ጥያቄ ፡ ኹሉ ፡ እንደማይቀበሉ ፡ በይፋ ፡ ተናግረዋል ። በዚህ ፡ ኹኔታ ፡ የለውጥ ፡ ነገር ፡ አክትሞ ፥ ቀሪው ፡ ሥራ ፡ ባለቤቱ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብና ፡ ርሱ ፡ ብቻ ፡ የሚያገምረውና ፡ የሚፈጸም ፡ ኾኗል ።

የምንኖርባት ፡ ዓለም ፡ ስግብግብነት ፡ የሰፈነባት ፥ ፈሪሀ ፡ እግዚአብሔር ፡ የጠፋባት ፥ ምሕረት ፡ የሌላት ፡ የነጣቂዎች ፡ ዓለም ፡ ነችና ፥ ኢትዮጵያ ፡ ፈጥና ፡ በኹለት ፡ እግሯ ፡ ቆማ ፡ ራሷን ፡ ካልቻለችና ፡ እግዚእናዋን ፡ ካላስከበረች ፡ በቀር ፥ እንኳን ፡ ለሌላ ፡ ልትተርፍና ፥ ለራሷም ፡ አትበቃ ፤ ያጠቃላይ ፡ ምልክዮሽ ፡ (የ"ግሎባል ፡ ኢምፔሪያሊዝም") ፡ ነጣቂዎች ፡ ሊያጠፏት ፡ ተነሥተዋል ።

ዕውቀትና ፡ ኪነት ፥ እንደ ፡ ሐሳብነታቸው ፣ እንደ ፡ ኀሊነታቸው ([17]) ፥ "ዜግነት" ፡ የላቸውም ፤ የሰው ፡ ልጅ ፡ ኹሉ ፡ የጋራ ፡ ዕሴቶች ፣ የጋራ ፡ ክብረቶች ፣ የጋራ ፡ ሀብቶች ፡ ናቸው ። እያንዳንዱ ፡ ሀገርና ፡ ሕዝብ ፡ ደግሞ ፡ እነዚህን ፡ ዕውቀቶችና ፡ የኪነት ፡ አዋዋላቸውን ፡ የራሱ ፡ አድርጎ ፡ የሚገነዘብባቸውንና ፡ የሚጠቀምባቸውን ፥ ከጨለማ ፡ ወደ ፡ ብርሃን ፣ ከተመሪነት ፡ ወደ ፡ መሪነት ፣ ከድኽነት ፡ ወደ ፡ ብልጽግና ፣ ከጠፍነት ፡ ወደ ፡ ለምነት ፣ ከኋላ ፡ ቀርነት ፡ ወደ ፡ ግንባር ፡ ቀደምነት ፡ የሚሸጋገርባቸውን ፡ መዋቅሮች ፡ ኹሉ ፡ አስቀድሞ ፡ ሊያዋቅር ፡ ይገባል ። ከሀገራዊ ፡ የሥልጣን ፡ መዋቅር ፡ ጋራ ፥ ዋነኛው ፡ መዋቅር ፡ ሀገራዊ ፡ ልሳን ፡ በመኾኑ ፥ የኹለቱን ፡ መቅናት ፡ ከሥራ ፡ ኹሉ ፡ ልናስቀድም ፡ ይገባል ።

የኢትዮጵያ ፡ ሀገራዊ ፡ ልሳን ፥ ዐማርኛ ፥ በግእዝ ፡ መሠረትነት ፥ እነዚህን ፡ ብሔራውያን ([18]) ፡ የጥበብና ፡ የኪነት ፡ ዕውቀቶች ፡ በተሟላ ፡ ለማስገንዘብና ፡ ለማራቀቅ ፡ ከበቂ ፡ በላይ ፡ መኾኑ ፡ እየታወቀ ፥ ይህን ፡ ችሎታውን ፡ ኢትዮጵያና ፡ ሕዝቧ ፡ ሊጠቀሙበት ፡ ሲገባ ፥ ቦታውን ፡ ለእንግሊዝኛ ፡ መልቀቃችን ፡ ምን ፡ ይባላል ፧ አዎን ፥ 37 ፡ "ዩኒቨርስቲዎች" ፡ ተከፈቱ ፤ ዕሠዬው! ፡ ታዲያ ፥ ያ ፡ ኹሉ ፡ ተማሪና ፡ ተመራማሪ ፡ የራሱን ፡ ዕንቍ ፡ ግእዝ–ዐማርኛን ፡ እየጣለ ፡ በባዕድ ፡ ዕንቍ ፡ እንግሊዝኛ ፡ ቢጽፍ ፡ ቢፈለስፍ ፥ ቢቈጥር ፡ ቢቀምር ፡ ጥቅሙ ፡ ምኑ ፡ ላይ ፡ ነው ፧ የቀረውስ ፡ ዓለም ፡ ቢኾን ፥ ከኢትዮጵያዊ ፡ ጥበብ ፣ አስተሳሰብ ፣ ቋንቋ ፣ ባህል ፣ ፈጠራ ፣ ምርምር ፣ መፍትሔ ፣ ጸጋ ፡ ኹሉ ፡ ሊያገኘው ፡ የሚገባውን ፡ ጥቅም ፡ ለምን ፡ ይነፈግ ፧

ይህን ፡ የመሰለው ፡ ጥፋት ፡ ካልተወገደ ፥ ለዘለቄታው ፡ እንኳን ፡ "ትራንስፎርሜሽን" ፡ "ፎርሜሽን"ም ፡ እንኳ ፡ አይገኝ ፤ አገርን ፡ ለተሐድሶ ፡ ቅኝ ፡ ግዛትነት ፣ ትውልድንም ፡ ለአእምሮ ፡ ቅኝ ፡ ግዛትነት ፡ ከመዳረግ ፡ በቀር ፥ ሌላ ፡ አንዳች ፡ ርባና ፡ አይኖርም ።

እንደምታዩት ፥ ጉዳዩ ፡ ክፉ ፡ መዘዝ ፡ አለው ፤ ስለ ፡ ህልውናችን ፡ ነውና ፥ ሳያጠፋን ፡ ቀድመን ፡ ልንገታውና ፡ ፈጥነን ፡ ልናስወግደው ፡ ይገባል ።

ባ 19 ኛው ፡ ምእትያ ፡ የነበሩት ፡ ራስ ፡ መንገሻ ፡ ዮሐንስ ፥ እጅግ ፡ ዝምተኛ ፡ ሰው ፡ ነበሩ ፡ ይባላል ። ከዕለታት ፡ አንድ ፡ ቀን ፥ የቅርብ ፡ ዘመድ ፡ ሞቶባቸው ፡ ቀብረው ፡ ሐዘን ፡ እንደ ፡ ተቀመጡ ፥ የተለመደው ፡ ዝምታቸው ፡ የሰለቻቸው ፡ አንድ ፡ ባለሟላቸው ፡ ጠጋ ፡ ይሉና ፦ *ጌታዬ ፥ እኚህን ፡ ሰው ፡ የቀበርናቸው ፡ እኮ ፡ ዝም ፡ ስላሉ ፡ ነው!* ፡ ዐሏቸው ፡ ይባላል ። አኹንም ፥ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ዝምታን ፡ በመተው ፥ በቅርቡ ፡ ያሳየውንም ፡ መነሣሣት ፡ በማጐልበት ፥ የተደቀነበትን ፡ አጠቃላይ ፡ ጥቃት ፡ ሊቋቋምና ፡ በድል ፡ አድራጊነት ፡ ሊወጣ ፡ ይችላል ። አስቀድሞ ፡ ግን ፡ የዐላማ ፡ አንድነትን ፡ ማግኘት ፡ ይኖርበታል ።

"የኢትዮጵያ ፡ ባለቤት ፡ ማን ፡ ነው ፧ " ፡ ለሚለው ፡ ጥያቄ ፡ የምንመልሰው ፡ መልስ ፡ ይህን ፡ የዐላማ ፡ አንድነት ፡ ይሰጠናል ። "የኢትዮጵያ ፡ ባለቤት ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ እና ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ብቻ ፡ ነው" ።

በቅርብ ፡ ዘመን ፡ የተፈራረቁብን ፡ አገዛዞች ፡ የነጠቁንን ፡ የባለቤትነት ፡ መብታችንን ፡ (ሀገራዊ ፡ እግዚእናችንን) ፡

17 <u>ኀሊ</u> ፤ የሐሳብ ፡ ነቅዕ ፣ የሐሳብ ፡ ምንጭ ፥ ሐሳብ ። (idea • idée)
18 <u>ብሔራዊ</u> ፤ የፍጥረት ፡ ኹሉ ፣ የመላ ፡ ዓለም ፡ (universal • universel)

በአንድነት ፡ እናስመልስ ፤ በሥልጡንሕዝብና ([19]) ፡ (በ"ዴሞክራሲ") ፡ ርትዕ ፡ ዐዲሱን ፡ ሕገ ፡ መንግሥታችንን ፡ መሥርተን ፡ የርትዕ ፡ መንግሥታችንን ፡ እናቁምበት ።

በመላ ፡ ኢትዮጵያ ፡ በተለይ ፡ ባዲስ ፡ አበባ ፡ ዙሪያ ፣ በሐረርጌ ፣ በዐሩሲ ፣ በወለጋ ፣ በጐንደር ፣ በወሎ ፣ በገምቤላ ፣ በጋሞጎፋ ፣ በሌላውም ፡ ክፍለ ፡ ሀገር ፡ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ፡ ይዘት ፡ የፈጸማቸውን ፡ አረመኔያውያን ፡ የሙብት ፡ ጥሰቶችና ፡ ዐይን ፡ ያወጡ ፡ ሌብነቶች ፡ በታላቅ ፡ ሐዘንና ፡ ኀፍረት ፡ ሰምተናል ፤ በጥብቅ ፡ እናወግዛቸዋለን ። ያንኑ ፡ ያኽል ፡ ደግሞ ፥ የተበደሉት ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ሀገራውያን ፡ መኾናቸው ፡ እየታወቀ ፡ "የእገሌ ፡ ነገድ" ፣ "የእገሌ ፡ ዘር" ፡ እያሉ ፡ ለመከፋፈያ ፡ ምክንያት ፡ የሚያውሏቸውንም ፡ መሠሪዎች ፡ እኩል ፡ እናወግዛቸዋለን ።

አኹንም ፥ ችግሮቻችንን ፡ ልንፈታ ፡ የምንችለው ፡ በጠቅላላው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ሕጋዊ ፡ ፈቃድና ፡ ሥልጣን ፡ ስለ ፡ ኾነ ፥ ይህ ፡ የጠቅላላው ፡ ኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ሕጋዊ ፡ ፈቃድና ፡ ሥልጣን ፡ የሚገኝበትን ፡ ሕዝባዊ ፡ አንድነታዊ ፡ አካላችንን ፡ መከወን ፡ ከምንም ፡ አስቀድመን ፡ ልንሠራው ፡ የሚገባ ፡ ሥራችን ፡ ኾኗል ። እኔም ፡ አባል ፡ የኾንኩለት ፡ "የኢትዮጵያውያን ፡ ሀገራዊ ፡ ሥልጡንሕዝባዊ ፡ አንድነት" ፡ (ኢ.ሀ.ሥ.አ.) ፥ ከተቋቋመበት ፡ ከ 1967 ፡ ዓ.ም. ፡ አንሥቶ ፥ ይህኑ ፡ የኢትዮጵያን ፡ ሕዝብ ፡ አንድነታዊ ፡ አካል ፥ በሥልጡንሕዝብና ፡ ርትዕ ፡ አስተባብሮ ፡ ለመከወን ፡ ይታገላል ([20]) ።

ሌሎች ፥ በመሰላቸው ፡ አስተያየት ፥ በ"ፓርቲ" ፣ በ"ቡድን" ፣ በ"ሲቪክ ፡ ማኅበራት" ፣ ወዘተ. ፡ ተደራጅቶ ፡ መታገልን ፡ መርጠዋል ። ኾኖም ፥ በርትዕ ፡ ከመተባበር ፡ ይልቅ ፥ ባስተያየት ፡ ተለያይቶ ፥ በ"ደጋፊ"ና ፡ በ"ተቃዋሚ" ፡ ተከፋፍሎ ፡ መደነቋቈርና ፡ መናቈር ፥ ሥቃያችንን ፡ ከማርዘም ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ አያመጣልንም ። ይልቅስ ፥ ከእየራሳችን ፡ አስተያየት ፡ በፊት ፡ የሥልጡንሕዝብናን ፡ ርትዕ ፡ እናክብር ። ማንኛችንም ፡ ለባዕዳን ፡ የመከፋፈያ ፡ ወሬ ፡ ዦሮን ፡ ሳንሰጥ ፥ በኢትዮጵያዊነት ፡ አንድ ፡ ኾነን ፥ ለዚህ ፡ ለተቀደሰ ፡ ሀገራዊ ፡ ዐላማ ፡ መሳካት ፥ በቀና ፡ መንፈስ ፡ እዚያው ፡ ሀገራችን ፡ ላይ ፡ ልንሰባሰብና ፡ ልንመክር ፣ ልንሠራ ፡ ይገባል ። ለታሪካዊ ፡ ውድቀታችን ፡ የእየራሳችንን ፡ ኀላፊነት ፡ አንረሳም ፥ አናሳንስምም ። አኹን ፡ ደግሞ ፥ ሀገራችንን ፡ የምንክሳትና ፡ የምንታደጋት ፡ ለሥልጡንሕዝብና ፡ ዐላማዋ ፡ ስንሠራና ፡ ስንሠዋ ፡ ብቻ ፡ ነው ።

ቀደም ፡ ብሎ ፡ እንደ ፡ ገለጽኩት ፥ ከጥቂት ፡ ዓመታት ፡ ወዲህ ፡ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ፡ ይዘት ፥ ራሱን ፡ ለማዳን ፡ ሲል ፡ የለውጥን ፡ ኺደት ፡ ለመደገፍ ፡ ተገዶ ፥ የአመራር ፡ አባላቱን ፡ በከፊል ፡ በመለዋወጥና ፡ ጥቂቶቹን ፡ ደግሞ ፡ ሽልቅቆ ፡ በመጣል ፥ እስረኞችን ፡ በከፊል ፡ በመፍታትና ፡ "ተወዳዳሪዎች/አሯሯጮች" ፡ ያላቸውን ፡ የስያሳ ፡ ቡድኖች ፥ በሰላማዊ ፡ መንገድ ፡ በሀገር ፡ ውስጥ ፡ "በነጻነት" ፡ እንዲንቀሳቀሱ ፡ "ፈቅጃለኹ" ፡ ብሎ ፡ ነበር ። ኾኖም ፥ ጒዳዩ ፡ በኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ፡ ይዘት ፡ በጎ ፡ ፈቃድ ፡ አይወሰንም ። ጒዳዩ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ እግዚእና ፡ መከበር ፣ የዐዲስ ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ መሠራትና ፡ የሥልጡንሕዝባዊ ፡ መንግሥት ፡ መቋቋም ፡ ስለ ፡ ኾነ ፥ ከዐላማችን ፡ ገና ፡ ሩቅ ፡ ነን ። ሳንዘናጋ ፡ ሀገራዊ ፡ ትግላችንን ፡ አዋሕደንና ፡ አደራጅተን ፡ ማጧጧፍ ፡ ይጠበቅብናል ።

በማንም ፡ ላይ ፡ የማትደርስ ፡ ሥልጡን ፡ ሀገር ፡ ኢትዮጵያን ፡ ለማጥፋት ፡ ሌት ፡ ተቀን ፡ የሚዳክሩትን ፡ ጥቂት ፡ ምዕራባውያን ፡ ኀይሎች ፡ ግን ፥ አኹንም ፦ *ይቅርባችኹ !* ፡ እንላለን ። ሕግን ፡ እየጣሱ ፡ "ሕግ ፡ ይከበር!" ፡ ማለት ፡ ሰላምን ፡ አያመጣም ፤ ጊዜው ፡ ሳያልፍባቸው ፥ ከጥፋት ፡ እንዲመለሱ ፡ እንመክራለን ። በምዕራቡ ፡ ዓለም ፡ ድምፁን ፡ ማሰማት ፡ የዠመረው ፡ የጦርነት ፡ ዐውሎ ፡ ነፋስ ፡ ለዓለሙ ፡ ኹሉ ፡ የሚተርፍ ፡ የዕልቂት ፡ ወጀብ ፡ እንዳይኾን ፥ ለፍትሕ ፡ እና ፡ ለርትዕ ፡ ከመቆም ፡ ሌላ ፡ ማማረጫ ፡ አይኖረንም ።

በሀገራዊ ፡ ልሳናችን ፡ በግእዝ–ዐማርኛ ፡ ጒዳናነት ፥ ወዳለምነው ፡ ሀገራዊ ፡ የሥልጡንሕዝብና ፡ ዐላማችን ፡ ለመድረስ ፥ ዘመናችን ፡ የጠየቀውን ፡ የቀለም ፡ ዑደት ፡ ወይም ፡ ነኰርኳር ፡ አበርትቶ ፡ ለመቀጠልና ፡ እፍጻሜው ፡ ለማድረስ ፥ ይህ ፡ የዐውደ ፡ ቀለም ፡ መግበር ፡ የድርሻውን ፥ በተወሰነ ፡ ደረጃና ፡ ለተወሰነ ፡ ርቀት ፥ እንደ ፡ መንኰራኵር ፡ እንዲያገለግለን ፡ ከልብ ፡ እመኛለኹ ።

ወሌ ፡ ነጋ ።

ለንደን ፥ መስከረም ፡ 2008 ፡ ዓ.ም. ፡ – ፡ የካቲት ፡ 2014 ፡ ዓ.ም. ።

---

19 <u>ሥልጡንሕዝብና</u> ፤ ሥልጡንሕዝብነት ፡ ወይም ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሥልጣኔ ፤ እያንዳንዱ ፡ ሰው ፡ የብጤውን ፡ መብትና ፡ ነጻነት ፡ በማክበር ፡ ውዴታ ፥ የራሱን ፡ መብትና ፡ ነጻነት ፡ በብጤው ፡ አስከብሮ ፡ የሚኖርበት ፡ ሥልጡን ፡ የውዴታና ፡ የርትዕ ፡ ሥርዐት ፡ ወይም ፡ ዐዳር ፡ (democracy • démocratie) ።

20 ዝርዝር ፡ መረጃው ፡ ከኢ.ሀ.ሥ.አ. ፡ መርበቢያ ፡ ይገኛል ፦ www.slttunhzb.net

መግቢያ • Introduction

ዐማርኛ ([21]) ፥ የኢትዮጵያ ([22]) ፡ ሀገራውያን ፡ የጋራ ፡ ቋንቋ ፡ የኾነው ፡ ከሦስት ፡ ሺሕ ፡ ዘመን ፡ በፊት ፥ በቀዳማዊ ፡ ምኒልክ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ መኾኑ ፡ ይተረካል ። ቀጥሎ ፥ ባ 11 ኛው ፡ ምእትያ ፥ ከዮዲት ፡ ምዝበራ ፡ በኋላ ፥ መንግሥት ፡ ከአኵስም ፡ ፈልሶ ፡ ወደ ፡ ላስታ ፡ ሲዛወር ፥ የነገድ ፡ ቋንቋዎችን ፡ ኹሉ ፡ በሀገራዊነት ፡ በማዋሐዱ ፥ በተናጋሪ ፡ ብዛት ፡ አቻ ፡ የሌለው ፡ ዐማርኛ ፥ በግእዝ ፡ ምትክ ፡ የኢትዮጵያ ፡ መንግሥታዊም ፡ ሀገራዊም ፡ አንድያ ፡ ልሳን ፡ ኾኖ ፡ እስከ ፡ ዘመናችን ፡ ለአንድ ፡ ሺሕ ፡ ዓመት ፡ ዘለቀ ።

በ 2007 ፡ ዓ.ም. ፥ ዐማርኛ ፥ በሀገሪቱ ፡ ከ 100 ፡ ሚልዮን ([23]) ፡ ያላነሰ ፡ ተናጋሪ ፥ በቀረው ፡ ዓለም ፡ ደግሞ ፡ ከ 3 ፡ ሚልዮን ፡ ያላነሰ ፡ ተናጋሪ ፡ አፍርቷል ፤ ከዓለም ፡ አንጋፋ ፡ 15 ፡ ቋንቋዎች ፡ ተርታም ፡ ይቈጠራል ።

ዐውደ ፡ ቀለም ፡ የጽሑፍ ፡ ማምረቻ ፥ በጠቅላላ ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ቋንቋዎች ፥ በተለይ ፡ ደግሞ ፡ ላማርኛ ፡ አገልግሎት ፡ እንዲውል ፡ ተብሎ ፥ በሚስማማ ፡ ዐይነት ፡ ተሰናድቷል ። ዘመኑ ፥ አህጉራዊ ([24]) ፡ ተሳትፎም ፡ የዳበረበት ፡ ስለ ፡ ኾነ ፥ እንደ ፡ እንግሊዝኛና ፡ ፈረንሳይኛ ፡ ያሉ ፡ አህጉራውያን ፡ ቋንቋዎችም ፡ ተሟልተው ፡ ከመግበሩ ፡ ተዋሕደዋል ፤ ወደ ፡ ፊት ፥ ዐቅም ፡ በፈቀደ ፡ መጠን ፥ ሌሎች ፡ ቋንቋዎችም ፡ ይታከሉለታል ።

ወረድ ፡ ብለን ፡ እንደምናየው ፥ ግእዝና ፡ ዐማርኛ ፥ እንደ ፡ ሌሎቹ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ቋንቋዎችና ፥ በጠቅላላው ፡ እንደ ፡ ሴማውያን ፡ ቋንቋዎች ፥ እጅግ ፡ የዳበሩ ፡ የመርባት ፣ የመዘርዘርና ፡ የመዋሐድ ፡ ጠባዮች ፡ ስላሏቸው ፥ የሚመጥናቸውን ፡ የማስሊያ ፡ መግበር ፡ ማብጀት ፡ ብርቱ ፡ ሥራን ፡ ይጠይቃል ። ባንጻሩ ፥ ከአህጉራውያን ፡ ቋንቋዎች ፡ መኻከል ፡ የሚቈጠሩት ፡ እንግሊዝኛና ፡ ፈረንሳይኛ ፥ ብዙም ፡ የመርባት ፡ ጠባይ ፡ የላቸውምና ፥ አያስቸግሩም ፤ እንደፊደል ፡ መጠንቀቂያ ፡ ያሉ ፡ መግበሮች ፡ በቀላሉ ፡ ተበጅተውላቸዋል ። ምንም ፡ ሳያጋንኑ ፥ ያማርኛው ፡ ፊደል ፡ መጠንቀቂያ ፡ መግበር ፥ 100 ፡ ጊዜ ፡ የባሰ ፡ አስቸጋሪ ፡ ነው ፡ ማለት ፡ ይቻላል ።

---

21 **ዐማርኛ** ፡ የ"ዐማራ ፡ ቋንቋ" ፡ ማለት ፡ ነው ። ዐማራ ፡ ወይም ፡ ዐምሐራ ፥ ቃል ፡ በቃል ፥ "ነጻ ፡ ሕዝብ" ፡ ("ዐም"=ሕዝብ ፥ "ሐራ"=ነጻ) ፣ ሀገራዊ ፡ (citizen • citoyen) ፡ ማለት ፡ እንጂ ፥ ዘር ፡ አይደለም ። ከመላ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ነገዶች ፡ ቢወለዱም ፥ በሀገራዊነት ፡ ባንድ ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ ሕዝብነት ፡ ተዋሕደው ፡ የኢትዮጵያን ፡ መንግሥት ፡ ዐቅፈው ፥ ሲሾሙትና ፡ ሲሽሩት ፡ የኖሩት ፥ መላ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ማለት ፡ ነው ። በዘር ፡ ሳይኾን ፥ በሀገራዊነት ፡ (በ"ሲቲዘንሺፕ") ፡ ከተሠሩት ፡ የዓለም ፡ ሕዝቦች ፥ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ቀዳሚ ፡ መኾኑ ፡ በዚህ ፡ ይታወቃል ።

22 "**ኢትዮጵያ**" ፡ የሚለውን ፡ ቃል ፡ የዕብራይጥ ፡ መጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ "ኵሽ" ፡ ይለዋል ፤ ምድሩም ፥ ከምሥራቅ ፡ እስከ ፡ ምዕራብ ፥ ከሂንዱ-ኵሽ ፡ እስከ ፡ ካናሪያ ፡ ደሴቶች ፤ ከሰሜን ፡ እስከ ፡ ደቡብ ፥ ከግሪክ ፡ አገር ፡ እስከ ፡ ደቡብ ፡ አፍሪቃ ፡ ይዘረጋል ። "ኢትዮጵያ"ና ፡ "ኵሽ" ፡ አምሳያዎች ፡ ናቸው ፤ ከኵሽ ፡ ልጆች ፡ አንደኛው ፡ "ኢትዮጲስ" ፡ ወይም ፡ "ጦብያ" ፣ ሌላው ፡ "አቢስ" ፡ ይባሉ ፡ እንደ ፡ ነበር ፡ በታሪክ ፡ ይነገራል ። "ኢትዮጲስ" ፡ "ኢትዮጵያ"ን ፡ ሰጠን ፥ "አቢስ" ፡ ደግሞ ፡ "አበሻ"ን ፡ ሰጠን ። ስለዚህ ፥ ሕዝቡ ፡ "ኢትዮጵያዊ"ም ፣ "ኵሻዊ"ም ፣ "አበሻ"ም ፡ ቢባል ፡ ትርጕሙ ፡ አንድ ፡ ነው ። ["ሐበሻ" ፡ ደግሞ ፡ ከደቡብ ፡ ዐረብ ፡ የፈለሱ ፡ የነገደ ፡ ሐበሻት ፡ ስም ፡ ነው ፤ እነሱም ፡ ጥንቱኑ ፡ ተዋሕደው ፡ በሀገራዊነት ፡ ዐማራን ፡ (ኢትዮጵያዊን) ፡ ኾነዋል ።]

የጥንታዊቷ ፡ ዋና ፡ ከተማ ፡ የአኵስምም ፡ ትርጕም ፡ "የኵሻውያን ፡ መዲና" ፡ ማለት ፡ ነውና ፥ "ያኵስም ፡ ሥልጣኔ" ፡ ቢሉ ፥ በጠቅላላውና ፡ በሰፊው ፡ "የኵሽ ፡ ሥልጣኔ" ፣ ወይ ፡ "የኢትዮጵያ ፡ ሥልጣኔ" ፡ ወይም ፡ "ያበሻ ፡ ሥልጣኔ" ፡ ማለት ፡ እንጂ ፥ አንዳንድ ፡ የውጭ ፡ "ቦትላኪ ፡ ታሪክ" ፡ ጸሓፊዎች ፡ አጣመው ፡ የጻፈፉትን ፥ በጠባብነት ፡ ተከትለው ፡ እንደሚያስተጋቡለት ፥ በዛሬዋ ፡ አኵስም ፡ ከተማ ፡ አካባቢ ፡ የተወሰነ ፡ የመንደር ፡ ሥልጣኔ ፡ ማለት ፡ አይደለም ።

ኢትዮጵያ ፡ ግን ፡ የመጣተኞችም ፡ ሀገር ፡ ናት ፤ ዐያሌ ፡ ሕዝቦች ፡ ካራቱም ፡ የዓለም ፡ አግጣጫዎች ፡ እንደ ፡ ማዕበል ፡ እየሠገሩ ፡ መጥተው ፡ በመላ ፡ ብሔሯ ፡ (በመላ ፡ ምድሯ) ፡ ሰፍረውባታል ። አንዳንዴም ፡ መምጣታቸው ፡ ነውጦችን ፡ እየቀሰቀሰ ፥ ደግሞ ፡ ደግሞ ፡ የሚያገረሽ ፡ ጠብና ፡ ግጭትን ፡ በታሪክ ፡ አስከትሏል ። ኾኖም ፥ በቀዳማዊ ፡ ምኒልክ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ (10 ኛ ፡ ምእትያ ፡ ቅ.ል.ክ.) ፡ ኢትዮጵያ ፡ በርትዕ ፡ ኹነትነት ፡ ዳግመኛ ፡ ስትከወንና ፡ ኗሪዎቿ ፡ ኹሉ ፡ የዘር ፡ ወይም ፡ የሃይማኖት ፡ አመሳሶ ፡ ሳይደረግባቸው ፡ በሀገራዊነት ፡ እኩል ፡ ኾነው ፡ የሚኖሩባት ፡ ሀገር ፡ ስትኾን ፥ እነዚህ ፡ ጠቦችና ፡ ግጭቶች ፡ አንዴ ፡ ለመቼውም ፡ መፍትሔያቸውን ፡ አግኝተዋል ። ይህም ፡ ድርስ ፡ የዐማራነትንና ፡ ያማርኛ ፡ ቋንቋን ፡ መወለድ ፡ አብሥሯል ።

ከጢት ፡ ከመሠረት ፥ እንዲህ ፡ በሀገራዊነት ፡ የተሠራውን ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ ሕዝብነት ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ ጐትቶ ፡ ዛሬ ፡ በዘር ፡ መምተሪያ ፡ መታትሮ ፡ ሀገር ፡ አልባ ፡ ለማድረግ ፡ የባዕዳን ፡ ደባ ፡ ቢፈጸምበትም ፡ ቅሉ ፥ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፥ ዛሬም ፡ እንደ ፡ ጥንቱ ፥ በሀገራዊ ፡ ባሕርዩ ፡ መከላከያ ፡ መድኅኒቱን ፡ ስለተጐናጸፈ ፥ ለዘለቄታው ፡ ከቶዉኑ ፡ የሚያሠጋው ፡ አይኾንም ። የመከፋፈል ፣ የማነስ ፣ የመጕደል ፡ አደጋ ፡ ዛሬም ፡ ቢኾን ፡ ለተወሰነ ፡ ዘመን ፡ ይመጣበት ፡ ይኾናል ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ተመልሶ ፡ የሚድንበትንና ፡ የሚሞላበትን ፥ ማንም ፡ የማይነጥቀውን ፡ ማብረሻውንም ፡ ይዟል ፤ ርሱም ፡ ሀገራዊነት ፡ ይባላል ። የማታ ፡ ማታ ፡ ባሸናፊነት ፡ ይዘልቃል ። የቀረውም ፡ ዓለም ፡ ቢኾን ፥ ከንግዲህ ፡ "ሀገራዊነት" ፡ ብለን ፡ ልንሰምየው ፡ በሚገባ ፡ ታሪካዊ ፡ የርትዕ ፡ ግሥጋሤ ፡ ዐብሮት ፡ ይገሠግሣል ።

23 ከታመነ ፡ ምንጭ ፡ የተገኘ ፡ ጥናታዊ ፡ አኃዝ ፡ እንደሚያመለክተው ፥ **የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ብዛት** ፡ የ 103 ፡ ሚልዮን ፡ ዕርከንን ፡ በ 2007 ፡ ዓ.ም. ፡ ዐልፏል ፥ ይህውም ፡ ላለፉት ፡ 70 ፡ ዓመታት ፡ ከመነሻው ፡ 30 ፡ ሚልዮን ፡ ባ 1.8% ፡ ዓመታዊ ፡ የሕዝብ ፡ ብዛት ፡ እድገት ፡ ተሰልቶ ፡ ነው ። አኃዙ ፡ የባሕር ፡ ምድርን ፡ (የኤርትራን) ፡ ነዋሪ ፡ ብዛት ፡ ጨምሯል ፤ ይህኛው ፡ በባሕር ፡ ምድር ፡ 1.8 ፡ ሚልዮን ፥ በቀረው ፡ ዓለም ፡ 1.4 ፡ ሚልዮን ፡ ይገመታል ።

24 **<u>አህጉራዊ</u>** ፤ የሀገሮች ፥ ወይም ፡ ወለ ፡ አህጉራዊ ፡ (international) ።

"አህጉር" ፥ በግእዝ ፥ የ"ሀገር" ፡ ብዙ ፡ ነው ። ሀገር ፡ (አንድ ፡ ሀገር ፡ ወይም ፡ አገር) ፤ አህጉር ፡ (ኹለት ፡ ሀገሮች) ፤ አህጉራት ፡ (የብዙ ፡ ብዙ ፡ ሀገሮች) ። "አህጉር"ን ፡ ለ"continent" ፡ ማዋሉ ፡ የተለመደ ፡ ስሕተት ፡ ነው ፤ ለ"continent" ፡ ትኽክለኛው ፡ ትርጕም ፡ "የብስ" ፡ (መጣጥ ፣ ደረቅ ፡ መሬት) ፡ መኾኑን ፡ ምሁራን ፡ ዘወትር ፡ ያሳስባሉ ።

የተጻውዖ ፡ ስሞችን ፡ ትተን ፥ የእንግሊዝኛ ፡ ቃላት ፡ ግፋ ፡ ቢል ፡ 150'000 ፡ ቢደርሱ ፡ ነው ፤ እነሱንም ፡ ባንድ ፡ አነስተኛ ፡ መጽሐፍ ፡ ልንመዘግባቸው ፡ እንችላለን ። ዐማርኛ ፡ ግን ፡ ፈጽሞ ፡ በተለየ ፡ ዐይነት ፡ የሚመደብ ፡ ቋንቋ ፡ ነው ፤ ቍጥሩ ፡ በትኽክል ፡ ሊታወቅ ፡ የማይችል ፡ የግስ ፡ ብዛት ፡ አለው ፥ ምናልባት ፡ በትሪልዮን ፡ ቤት ፡ የሚሰፈር ። መዝገበ ፡ ቃለት ፡ ውስጥ ፡ የሰፈሩት ፡ ዋና ፡ ዋና ፡ ዘሮችና ፡ ስሞች ፣ ቅጽሎችና ፡ አገባቦች ፡ ብቻ ፡ ናቸው ። የስምና ፡ ያንቀጽ ፡ ዝርዝሮች ፡ ተሟልተው ፡ በማስሊያ ፡ ይረቡ ፣ ይገሰሱ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ እንጂ ፥ ባንድ ፡ ሰው ፡ አእምሮ ፡ ባንድ ፡ ሺሕ ፡ ዘመን ፡ ዕድሜም ፡ ተዘርዝረው ፡ አያልቁ ። ዐውደ ፡ ቀለም ፡ የጽሑፍ ፡ ማምረቻ ፥ ባቋራጭ ፡ የቃኘልን ፥ ያማርኛ ፡ ቋንቋ ፡ ኀያልነት ፡ ያስከተለውን ፡ ይህን ፡ እጅግ ፡ አስቸጋሪ ፡ ኹኔታ ፡ ነው ። በማስሊያ ፡ ታሪክ ፥ በተለይ ፡ ደግሞ ፥ በኢትዮጵያዊ ፡ ስሌት ፡ ታሪክ ፡ ለመዠመሪያ ፡ ጊዜ ፡ የተሟላ ፡ ያማርኛ ፡ ፊደል ፡ መጠንቀቂያ ፡ መግበር ፡ ተበጅቶ ፡ እንሆ ፡ ዛሬ ፡ በነጻ ፡ ቀርቧል ።

ከዚህ ፡ ጋራ ፥ መጠነኛ ፡ የኾነ ፡ (ማለት ፥ ከርባታ ፡ ውጪ ፥ መዝገበ ፡ ቃላት ፡ ውስጥ ፡ ያሉትን ፡ ቃላት ፡ ብቻ ፡ የሚጠነቅቅ) ፡ የግእዝና ፡ የሶማልኛ ፡ ፊደል ፡ መጠንቀቂያ ፥ ከፈረንሳይኛውና ፡ ከእንግሊዝኛው ፡ ጋራ ፡ ቀርቧል ።

ከዚህ ፡ ወዲያ ፥ ላማርኛ ፡ (60'000 ፡ ቃላት) ፣ ለግእዝ ፡ (27'000 ፡ ቃላት) ፣ ለእንግሊዝኛ ፡ (200'000 ፡ ቃላት) ፡ ያሏቸው ፥ የተሟሉ ፡ መዛግብተ ፡ ቃላት ፡ ታክለዋል ፤ ለፈረንሳይኛ ፡ ደግሞ ፥ ነጻና ፡ ሙሉ ፡ መዘገበ ፡ ቃላት ፡ ለጊዜው ፡ ስለማይገኝ ፥ መለስተኛ ፡ ግስ ፡ (36'000 ፡ ቃላት ፡ ብቻ) ፡ ታክሏል ።

በምዕራፍ ፡ 1 ፡ ጠቅላላ ፡ መግለጫ ፡ ከተሰጠ ፡ በኋላ ፥ በምዕራፍ ፡ 2 ፡ ስለ ፡ ተከላና ፡ ስላገልግሎት ፡ ዝርዝር ፡ መግለጫ ፡ ይከተላል ። ያኹኑ ፡ የመመሪያ ፡ ዝግጅት ፡ ለምዕራፍ ፡ 2 ፡ ዐዲስ ፡ ክፍልን ፡ አክሏል ፤ ክፍሉም ፡ ዘወትር ፡ ለሚቀርቡ ፡ ተደጋጋሚ ፡ ጥያቄዎች ፡ መልሳቸውን ፡ ይሰጣል ። ስለ ፡ ቀሪ ፡ ሥራ ፡ ባጪሩ ፡ ተገልጾ ፥ ምዕራፍ ፡ 2 ፡ ይፈጸማል ።

በምዕራፍ ፡ 3 ፥ ስለግእዝ–ዐማርኛ ፡ ፊደል ፣ አገባብና ፡ ትርጕም ፡ አጠነቃቀቅ ፡ ዝርዝር ፡ መግለጫ ፡ ቀርቦ ፥ መመሪያው ፡ ይደመደማል ።

እስከዚህ ፡ ድረስ ፡ መግቢያ ፡ ነበር ፤ ከንግዲህ ፡ ዝርዝር ፡ ኹኔታውን ፡ በሥዕላዊ ፡ ግጻዌ ፡ እየታገዝን ፡ አንድ ፡ ባንድ ፡ እናያለን ።

Amharic [25] is, above all, the language of the citizens of Ethiopia [26], since the reign of Emperor Mnilk 1st (10th Century B.C.). In the 11th century A.D., as the seat of government moved from Akwsm to Lasta, Amharic, the language of the citizenry, unseated G'z as the official language of Ethiopia, and became both the national (citizen) and official language of Ethiopia.
Amharic, the language of Ethiopian citizenship, spoken by about 100 million people in Ethiopia and two to three million in the rest of the world, is among the top 15 most spoken languages in the World, and the second most spoken Semitic language after Arabic.
Like most other Ethiopian and Semitic languages, Amharic is a highly generative, agglutinative and inflectional language, with a rich, pattern-based morphology;

L'amharique [27] est, avant tout, la langue des citoyens de l'Éthiopie [28], depuis le règne de l'empereur Mnilk 1er (10ème siècle avant J.C.). Au 11ème siècle A.D., lorsque le siège du gouvernement fut déplacé de Akwsm vers le Lasta, l'amharique supplanta le g'z comme langue officielle de l'Éthiopie, et devint à la fois langue nationale (citoyenne) et officielle de l'Éthiopie.
L'amharique, langue de citoyenneté éthiopienne, est, aujourd'hui, parlée par près de 100 millions d'individus en Éthiopie, et par 2 à 3 millions autres dans le reste du monde; elle figure ainsi parmi les 15 langues les plus parlées au monde, et la deuxième langue sémitique la plus parlée, après l'arabe.
Comme la plupart des langues éthiopiennes et sémitiques, l'amharique est une langue hautement générative, agglutinante et

---

25 **Amhara** is the collective name of the citizens of Ethiopia, irrespective of ethnic background. Etymologically, "am" ("people") and "hara" ("free") in unison mean "Free People". Amharic is therefore the language of the citizenry of Ethiopia: the language of Ethiopian citizenship.

26 "**Ethiopia**" is synonymous with "ኵሽ • Kush" (or more precisely "Kwsh"), as testifies the Hebrew Old Testament. The name "Ethiopia" comes from the name of the son of Kush called "ኢትዮጲስ • Ethiopis" or "ጦቢያ • Ṫobiya" ; from the name of his other son "አቢስ • Abis" comes the collective name "Abesha" synonymous with "Ethiopian". The people are alternatively known as "ኵሻውያን • Kushites", "ኢትዮጵያውያን • Ethiopians" or "አበሻ • Abesha or Abyssinians"; and their city "አኵስም • Akwsm" (etymologically, "City of the Kushites") is the capital city of the land of Kush. Hence, "Axumite" civilisation is none other than Ethiopian civilisation. But, Ethiopia is also a land of immigration where waves upon waves of foreign peoples arrived and settled permanently over millennia, sometimes provoking great upheavals. During the reign of Emperor Mnilk 1st (10th century B.C.) such conflicts were once and for all resolved when Ethiopia was reconstituted as a State of Right where all inhabitants had equal rights as citizens and no longer discriminated against as members of ethnic or religious groups. This event marked the birth of the Amhara (citizens) and the Amharic language.

The foreign led attempt at destroying this unity of the Ethiopian people are presently carried out through a, foreign inspired and imposed, retrograde constitution extolling the separation of the people on the basis of ethnicity. However, this does not unduly worry the Ethiopian people. The risks of temporary division, dismemberment, and diminution are there; but the ultimate antibody, the ultimate cure is already with the Ethiopian people, as their inalienable and inherent attribute: it is called ፡ ሀገሬዊነት ፡ or citizenship.

27 **Amhara** est le nom collectif des citoyens éthiopiens, par de là les origines ethniques. Étymologiquement, "am" ("peuple") et "hara" ("libre") signifient ensemble "Peuple Libre". L'amharique est ainsi la langue de l'ensemble des citoyens de l'Éthiopie: langue de citoyenneté.

28 "**Éthiopie**" est synonyme de "ኵሽ • Koush" (ou plus précisément "Kwsh"), comme le certifie l'Ancien Testament hébreux. Le nom "Éthiopie" a pour origine le nom du fils de Koush appelé "ኢትዮጲስ • Ethiopis" ou "ጦቢያ • Ṫobiya"; du nom de l'autre de ses fils "አቢስ • Abis" provient le nom collectif "Abesha, synonyme d'éthiopien. Le peuple est connu sous les noms de "ኵሻዊ • koushite", ou "ኢትዮጵያዊ • éthiopien", ou encore "አበሻ • abesha ou abyssin". Enfin, "አኵስም • Akwsm" (étymologiquement, "Cité des koushites") est la capitale de tout le pays de Koush; et la civilisation "axoumite" n'est autre que la civilisation éthiopienne. Mais l'Éthiopie est aussi une terre d'immigration où des vagues entières de populations étrangères s'y sont succédées et s'y sont installées de manière permanente, provoquant parfois de grands bouleversements. Sous le règne de l'empereur Mnilk 1er (10ème siècle avant J.C.) de tels conflits ont été réglés de manière définitive lorsque l'Éthiopie s'est reconstituée en un état de droit où tous les habitants ont des droits égaux en tant que citoyens, et non plus discriminés en raison de leur appartenance ethnique ou religieuse. Cet événement marque la naissance des Amharas (citoyens) et de la langue amharique.

Les tentatives, menées depuis l'étranger durant des décennies, pour détruire cette unité du peuple éthiopien, sont désormais effectuées principalement par le biais d'une constitution rétrograde, inspirée et imposée depuis l'étranger, et prônant la séparation sur la base de l'identité ethnique. Cependant, elles n'inquiètent pas outre mesure le peuple éthiopien. Les risques de division, de démembrement, de diminution temporaires sont là; de même que l'anticorps ultime, l'ultime remède qui est l'attribut inaliénable du et inhérent au peuple éthiopien: cela s'appelle ፡ ሀገሬዊነት ፡ ou citoyenneté.

making its computerisation quite a challenging exercise. With AwdeQelem, Amharic is now endowed with its own text editor with spell-checking capabilities; a first. But AwdeQelem is a global-oriented application, open to the wide world: English and French forming its principal highways to the rest of the world, with a few more languages to be added in the near future. After a brief presentation of AwdeQelem, in chapter 1, chapter 2 will take us through the different features and aspects of AwdeQelem, from installation to usage. This edition of the users' manual has effected a chapter reassignment: chapter 3 becomes a section in chapter 2, and the new chapter 3 presents brief notes on G'z-Amharic spell-checking, grammar-checking and semantic-checking.	flexionnelle, avec une morphologie riche; ce qui rend l'informatisation de la langue un exercice particulièrement difficile. Avec AwdeQelem, l'amharique dispose d'un traitement de texte à sa mesure, doté d'un correcteur orthographique; une première. AwdeQelem a cependant une orientation globale: le français et l'anglais constituant ses principales avenues vers le reste du monde, avec quelques autres langues qui s'y ajouteront dans un avenir proche. Après une courte présentation générale de AwdeQelem, au chapitre 1, nous verrons au chapitre 2 le détail des différents aspects et fonctionnalités de AwdeQelem, depuis l'installation jusqu'à l'utilisation. Cette édition du manuel effectue un remaniement de chapitre: le chapitre 3 devenant une section du chapitre 2, et le nouveau chapitre 3 présentant de brèves observations sur la correction orthographique, grammaticale et sémantique g'z-amharique.

፩ • 1

ጠቅላላ ፡ መግለጫ • General Presentation • Présentation Générale

ዐውደ ፡ ቀለም ፡ የጽሑፍ ፡ ማምረቻ ፡ የመዠመሪያው ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ ነጻ ፡ ባለፊደል ፡ መጠ̊ንቀቂያና ፡ ባለመዝገበ ፡ ቃላት ፡ የጽሑፍ ፡ ማምረቻ ፡ መግበር ፡ ነው ፤ ግና ፡ በዚህ ፡ ወጣትነቱ ፥ እጅግ ፡ ኀያል ፡ ችሎታን ፡ ያስጨብጣል ።

ኢትዮጵያዊነቱ ፤ በኢትዮጵያዊ ፡ አስሊ ፡ በመ̇ገበሩ ፡ ብቻ ፡ አይደለም ፤ ኢትዮጵያዊ ፡ ቋንቋንና ፡ ጻሕፍን ፡ መሠረት ፡ አድርጎ ፥ በኢትዮጵያዊ ፡ ቅጥንብር ፡ (ቅጥና ፡ ሕብር) ፡ ተከሥቶ ፥ የዓለምን ፡ ቋንቋዎች ፡ (እንግሊዝኛ ፣ ፈረንሳይኛ ፣ ሶማልኛ ፥ በቅርቡ ፡ ደግሞ ፣ ሷሂሊ ፣ ኤስፓኛኛ ፣ ሌላም) ፡ የተቻለውን ፡ ያኽል ፡ በማሳተፍ ፡ የሰው ፡ ልጅን ፡ ኹሉ ፡ በሀገራዊነት ፡ ለመጥቀም ፡ በመነሣቱም ፡ እንጂ ።

ነጻነቱ ፤ ከ**ዐውደ ፡ ቀለም** ፡ መርበቢያ ፡ ከ awde-qelem.net ፥ ወይም ፡ ከ**ዋዜማ ፡ ሥርዐት** ፡ መርበቢያ ፥ ከ gzamargna.net ፡ በነጻ ፡ ከመና̇ኘ̇ቱ ፡ ጋራ ፥ ኢትዮጵያዊው ፡ ጻሕፍና ፡ ቋንቋ ፡ በለገሱት ፡ ብሔራዊ ፡ ሀብትና ፡ ብቃት ፥ ከኹሉም ፡ ጋራ ፡ ተስተካክሎና ፡ ኹሉንም ፡ አስተካክሎ ፡ ዐብሮ ፡ ለመሥራት ፡ በማስቻሉም ፡ እንጂ ።

የጽሑፍ ፡ ማምረቻነቱ ፤ ጽሑፍን ፥ ባውድማ ፡ ላይ ፡ እንደሚበራይ ፡ እንዳዝመራ ፡ ብትን ፡ ነዶ ፥ ምርቱን ፡ ከገለባው ፡ ለመለየት ፡ በማስቻሉ ፡ እንጂ ።

ዐውደ ፡ ቀለም ፥ እንደ ፡ Notepad++ ፡ የጽሑፍ ፡ ማምረቻ ፡ እንጂ ፥ እንደ ፡ Word ፡ ወይ ፡ OpenOffice ፡ ወይም ፡ LibreOffice ፥ የቃል ፡ ማሳኪያ ፡ ወይም ፡ የጽሑፍ ፡ ማሰናጃ ፡ አይደለም ። ግብሩ ፥ የጽሑፍን ፡ ፊደላት ፡ ለመጠ̊ንቀቅ ፥ የቃላቱን ፡ ትርጕም ፡ ትኽክለኛነት ፡ ለማግኘት ፡ በሚያስችሉ ፡ በፊደል ፡ መጠ̊ንቀቂያና ፡ በመዝገበ ፡ ቃላት ፡ መግበሮች ፡ አማካይነት ፥ የመፈለጊያና ፡ የማማረጫ ፣ የማጣሪያና ፡ የመተኪያ ፡ አገልግሎቶችን ፡ መስጠት ፡ እንጂ ፥ የጽሑፍን ፡ ቅርጸት ፣ የገጽን ፡ አሰታተር ፣ የሰነድን ፡ አቀጻጽ ፡ ማስተካከል ፣ ማሳመር ፣ ማሰናዳት ፥ ባንድ ፡ ቃል ፥ ማሳካት ፡ አይደለም ። ይህን ፡ ለሚሹ ፥ እላይ ፡ የተጠቀሱት ፡ የጽሑፍ ፡ ማሳኪያ ፡ መግበሮች ፡ አሉላቸው ። ለነዚህኞቹ ፡ ደግሞ ፥ **ዐውደ ፡ ቀለም** ፡ ጥሩ ፡ ረዳት ፡ ኾኖ ፥ የጐደላቸውን ፡ ያሟላላቸዋል ።

ይህ ፡ መግበር ፡ የ**ዐውደ ፡ ቀለም** ፡ የመዠመሪያው ፡ ክለሳ ፡ እንደ ፡ መኾኑ ፡ መጠን ፥ ገና ፡ የሚገጥሙት ፡ ያልታዩ ፡ ብዙ ፡ ችግሮችና ፡ ጕድለቶች ፡ ይኖራሉ ። እነዚህን ፡ በኺደት ፡ እያረምናቸውና ፡ እያሟላናቸው ፥ **ዐውደ ፡ ቀለምን** ፡ ብቁ ፡ መግበር ፡ እናደርገዋለን ፤ ለዚህም ፡ የኹላችኹ ፡ ትብብር ፡ ታላቅ ፡ ጥቅም ፡ ይኖረዋል ።

AwdeQelem is the first free Ethiopian text processor with spell-checking and dictionary functionalities; as such it is still young but already offers powerful features. *Ethiopian*: because it is developed by an Ethiopian informatician, but also because it is based on the Ethiopian script and languages, bedecked with Ethiopian attires, while open to the world at large, by bringing together in the same application as much of the world's languages as possible (English, French, Somali, with Swahili, Spanish soon to be added, and more), offering thus its citizen service to all.	AwdeQelem est le premier traitement de texte éthiopien gratuit avec des fonctionnalités de correction orthographique et de dictionnaire; de ce fait, il est encore jeune mais offre déjà de puissantes caractéristiques. *Éthiopien*: parce qu'il est développé par un informaticien éthiopien, mais surtout parce qu'il est fondé sur l'écriture et les langues éthiopiennes; paré des couleurs éthiopiennes, ouvert cependant sur le monde en unissant dans la même application autant de langues du monde que possible (français, anglais, somali, et bientôt, swahili, espagnol et davantage); il rend ainsi un service citoyen à tous.

Free: it is freely available from the AwdeQelem web-site: awde-qelem.net, and from the Wazéma System website: gzamargna.net, but also because it seeks to avail its users of the possibility to interact across languages and scripts with independence and equality, thanks to the complete and universal nature of the Ethiopian script and languages. *Text processor*: because it makes possible the processing of text in a way similar to the threshing of crop to separate seeds from husks. AwdeQelem, like Notepad++ and others like it, is a text processor, not a desktop publishing or an office suite like Word, OpenOffice, LibreOffice or InDesign, etc. Its principal function is to provide, with respect to letters and words, the ***search/ choose/verify/replace*** alternatives of a spell-checker and a dictionary tool. Its function is not to provide font and page layout embellishments, or document formatting. The latter functionalities are best provided by the above mentioned applications, among others. To those working with desktop publishing or office suites, or any work environment for that matter, AwdeQelem provides them with irreplaceable support services. As this is the first version of AwdeQelem, many imperfections and other bugs are yet to be discovered and dealt with: many versions have to pass before AwdeQelem becomes fully mature. In this natural process, the cooperation of users is of crucial importance.	*Gratuit*: parce qu'il est librement disponible auprès des sites de AwdeQelem: awde-qelem.net, et de Système Wazéma: gzamargna.net, mais aussi parce qu'il ambitionne de donner à ses utilisateurs la possibilité d'interagir, par delà les langues et écritures, avec indépendance et égalité; cela grᎯace au caractère complet et universel de l'écriture et des langues éthiopiennes. *Traitement de texte*: parce qu'il rend possible le traitement du texte à la manière du battage de la récolte pour séparer le grain de l'épi. AwdeQelem, comme Notepad++ par exemple, est un traitement de texte, et non un environnement de travail intégré comme Word, OpenOffice, LibreOffice ou InDesign. Sa fonction principale est celle d'offrir par le biais du correcteur orthographique et du dictionnaire électronique, l'alternative ***rechercher/choisir/vérifier/remplacer***, et non l'embellissement de la mise en page ou le formatage de document: tâches qui reviennent aux applications citées plus haut. Pour ceux qui travaillent dans le cadre d'un environnement de travail intégré, AwdeQelem leur pourvoi un service de soutien irremplaçable. Comme nous n'en sommes qu'à la première version de AwdeQelem, maintes imperfections et autres bogues attendent à être découverts et réglés: la maturation de AwdeQelem nécessitera plusieurs versions. Dans ce processus naturel, votre coopération en tant qu'utilisateur est d'une importance cruciale.

የመግበሩ ፡ ዋና ፡ ዋና ፡ ዐቅሞችና ፡ ዘዴዎች ፡ በጥቂት ፡ ገጾች ፡ እንደሚከተለው ፡ ይብራራሉ ።

Here follows a relatively concise description of the principal features and functionalities of AwdeQelem.	Voici, à présent, une brève description des principales caractéristiques et fonctionnalités de AwdeQelem.

፪ • 2

ማሟሻ • getting started • mise en marche

2.1 ፩ ክለሳ ፡ 1.3 ፡ ምን ፡ ዐዲስ ፡ ይዞ ፡ መጣ? • what is new in v.1.3? • quoi de neuf dans v.1.3?

<table>
<tr><td rowspan="2">2.1.1</td><td colspan="2">ዐውደ ፡ ቀለም ፡ ክ.1.2 ፡ ቃላትን ፡ በዐምስት ፡ ቋንቋዎች ፡ (ዐማርኛ ፣ እንግሊዝኛ ፣ ፈረንሳይኛ ፡ ግእዝ ፣ ሶማልኛ) ፡ ርስ ፡ በርስ ፡ የማተራጐም ፡ ችሎታን ፡ አክሎ ፡ ነበር ። ለ 37'000 ፡ ያማርኛ ፡ ቃላት ፣ ለ 200'000 ፡ የእንግሊዝኛ ፡ ቃላት ፣ ለ 100'000 ፡ የፈረንሳይኛ ፡ ቃላት ፣ ለ 2'600 ፡ የግእዝ ፡ ቃላት ፣ ለ 1'000 ፡ የሶማልኛ ፡ ቃላት ፥ አንዱ ፡ ከሌላው ፡ የሚተራጐምበትንም ፡ ዐቅም ፡ አዳብሮ ፡ አቅርቦ ፡ ነበር ። አኹን ፡ ደግሞ ፥ ክለሳ ፡ 1.3 ፡ እነዚህን ፡ አኃዞች ፡ ለዐማርኛ ፡ 42'000 ፣ ለግእዝ ፡ 3'300 ፣ ለሶማልኛ ፡ ደግሞ ፡ 1'250 ፡ አድርሷቸዋል ። በተለይ ፡ ደግሞ ፡ የዓለማችን ፡ 200 ፡ በላይ ፡ ሀገሮች ፡ ይዞታዎች ፡ ስም ፡ እና ፡ የመዲናቸው ፡ ስም ፡ በራሳቸው ፡ አጠራርና ፡ በዐማርኛ ፡ አጠራር ፡ እዐማርኛው ፡ መዝገበ ፡ ቃላት ፡ ውስጥ ፡ በነቂስ ፡ ተመዝግበዋል ። በተጨማሪም ፥ ከ 800 ፡ በላይ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ወረዳዎች ፡ (የኤርትራን ፡ ጨምሮ) ፡ ስም ፡ ታክሏል ። የተመዘገቡት ፡ ያማርኛ ፣ የግእዝና ፡ የሶማልኛ ፡ ቃላት ፡ ብዛት ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ በሚከታተሉት ፡ ክለሳዎች ፡ እየጨመረ ፡ ይኼዳል ።</td></tr>
<tr><td>Version 1.2 of AwdeQelem, came to you with the simultaneous word translation functionality, enhanced by the introduction of two additional languages to the existing three languages (Amharic, English, French, G'z, Somali). Version 1.2 had mutually translatable 37'000 Amharic words, 200'000 English words, and 100'000 French words, 2'600 G'z words, and 1'000 Somali words are. Version 1.3 has now increased the numbers to 42'000 for Amharic , 3'300 for G'z and 1'250 for Somali. In particular, the names of over 200 countries and dependencies, together with the names of their capital cities, have been added to the Amharic dictionary, together with the names of over 800 Ethiopian districts (including those of Eritrea). These numbers will continue to increase with subsequent versions.</td><td>La version 1.2 de AwdeQelem vous est parvienu avec la fonctionnalité de traduction simultanée de vocabulaires enrichie de deux langues supplémentaires (g'z et somali) en plus de l'amharique, le français, et l'anglais). La version 1.2 avait 37'000 mots amhariques, 100'000 mots français, et 200'000 mots anglais, 2'600 mots g'z, 1'000 mots somalis mutuellement traduisibles. La version 1.3 a accru ces chiffres à 42'000 pour l'amharique, 3'300 pour le g'z et 1'250 pour le somali. En particulier, les noms de plus de 200 pays et territoires dépendants, ainsi que leurs capitales, sont ajoutés dans le dictionnaire amharique, avec aussi les noms de plus de 800 districts (wereda) éthiopiens (y compris ceux de l'Érythrée). Ces chiffres continueront à croître avec les versions futures.</td></tr>
<tr><td rowspan="2">2.1.2</td><td colspan="2">የቃላት ፡ መተረሪያ ፡ እና ፡ የጽሑፍን ፡ መሰደሪያ ፡ መግበሮች ፡ ለዐውደ ፡ ቀለም ፡ ታክለዋል ፡ [ዝርዝሩ ፡ እገጽ ፡ 82-87 ፡ ተመልክቷል] ።</td></tr>
<tr><td>A wordList maker and a text sorting</td><td>Un compilateur de liste de mots et un</td></tr>
</table>

<table>
<tr><td></td><td>tool are added to the application AwdeQelem [details are found on pages 82-87].</td><td>outil de tri de texte sont ajoutés à l'application AwdeQelem [pour plus de détails voire les pages 82-87].</td></tr>
<tr><td rowspan="2">2.1.3</td><td colspan="2">የዐማርኛ ፡ ፊደል ፡ መጠ̊ንቀቂያው ፡ መግበር ፡ በጥራትም ፡ በግጸትም ፡ በመጠኑ ፡ ተሻሽሏል ።
የተሳሳቱ ፡ የዐማርኛ ፡ አጻጻፎችን ፡ አጥርቶ ፡ የመለየት ፡ ዐቅሙ ፡ ባማካይ ፡ ካ 5% ፡ እስካ 10% ፡ ዳብሯል ።
አሻሚ ፡ አጻጻፍ ፡ ቀድሞ ፡ በብርቱካን ፡ ቀለም ፡ ይከሠት ፡ የነበረው ፡ (ከቀይ ፡ ቀለም ፡ ጋራ ፡ ተቀራራቢ ፡ በመኾኑ) ፥ ከክለሳ ፡ 1.3 ፡ አንሥቶ ፡ በግራጫ ፡ ቀለም ፡ እንዲከሠት ፡ ተደርጓል ።</td></tr>
<tr><td>The Amharic spell-checker has undergone moderate improvements in performance and appearance. Its ability to precisely identify wrong spellings for Amharic has been improved by an average of 5 to 10%.

From version 1.3 onwards, ambiguous spellings will be signalled by a grey background rather than the orange one (which is easily confused with the red background, signalling erroneous spelling).</td><td>Le correcteur orthographique pour l'amharique a subit de légères améliorations en terme de performance et d'apparence.

Sa capacité à identifier avec précision les fautes d'orthographie amharique a été augmentée, en moyenne, de 5 à 10%.

À partir de la version 1.3, les orthographies ambiguës seront signalées par un fond gris plutôt qu'un fond orange [lequel est susceptible d'être confondu avec le fond rouge, signalant une faute d'orthographie].</td></tr>
<tr><td rowspan="2">2.1.4</td><td colspan="2">የዐማርኛ ፡ መዝገበ ፡ ቃላት ፡ ውስጥ ፥ በለቀማ ፡ ወቅት ፡ የገቡ ፡ የፊደል ፡ ስሕተቶችና ፡ ግድፈቶች ፡ ታርመዋል ።</td></tr>
<tr><td>Remaining misspellings introduced in the Amharic dictionary during its input have been removed.</td><td>Le restant de fautes d'orthographe introduites lors de la saisie du dictionnaire amharique a été éliminé.</td></tr>
<tr><td rowspan="2">2.1.5</td><td colspan="2">ሌሎች ፡ ጥቃቅን ፡ ማሻሻያዎች ፡ ተከናውነዋል ፤ ውጤቱን ፡ ተገልጋዩ ፡ ይፈርደዋል ።
የማሻሻያ ፡ አስተያየቶችንና ፡ ጥቈማዎችን ፡ የሰጡኝን ፡ ኹሉ ፡ ከልብ ፡ አመሰግናለኹ ።</td></tr>
<tr><td>Other small improvements have been made; the user will be ultimate judge.

Once again, thank you to all those who made some of the suggestions.</td><td>D'autres améliorations de moindres importances ont aussi été effectuées; l'utilisateur en sera juge.

Encore une fois, merci à tous ceux qui m'ont fait certaines des suggestions.</td></tr>
</table>

2.2 ፤ ዕቃሜ • system requirements • besoins en ressources

ምግባር • operating system • système d'exploitation	▶	• ዊንዶውዝ ፡ ኤንቲ ፣ 2000 ፣ ኤክስፒ ፣ ቪስታ ፣ ዊንዶውዝ ፡ 7 ፣ 8 ፣ 10 • Windows NT, 2000, XP, Vista, Windows 7, 8, 10

ምዝካር • memory (RAM) • mémoire	▶	• ከተመሳሳይ ፡ መግበሮች ፡ የተለየ ፡ የምዝካር ፡ ዐቅም ፡ አይጠይቅም • not more memory requirements than for similar applications • ne nécessite pas plus de capacités de mémoire que d'autres applications similaires
ቅርጸት • font • police de caractères [AO Addis Abeba Unicode, AO Desta Unicode, AO Tesfa Unicode]	▶	• የዋዜማ ፡ ሥርዐት ፡ ቅርጸቶች ፡ ያሻሉ ፤ እነዚህም ፡ እዐውደ ፡ ቀለም ፡ ማኅደር ፡ ውስጥ ፡ ዐብረው ፡ ይፈለፈላሉ ፤ እነሱን ፡ እ C:\Windows\Fonts ፡ ማኅደር ፡ ውስጥ ፡ መዶል ፡ ይበቃል • Wazéma System fonts are required; and these are found in the AwdeQelem folder; drag and drop them into C:\Windows\Fonts folder • Les polices de caractères de Système Wazéma sont requises; placez les dans le dossier C:\Windows\Fonts à partir du dossier AwdeQelem.
መፍቻ−ገበታ • keyboard system • clavier	▶	• የዋዜማ ፡ ሥርዐት ፡ መፍቻ−ገበታ ፡ በማማረጫነት ፡ ይቀርባል ፤ ርሱም ፡ ከዐውደ ፡ ቀለም ፡ ጋራ ፡ ዐብሮ ፡ ተፈልፍሎ ፥ "Wazema 2003 Pan-Ethiopian Unicode Keyboard v3.exe" ፡ በተባለ ፡ ተከናዋኝ ፡ ሰነድነት ፡ "Wazéma2003_k3_20030827" ፡ እተሠኘ ፡ ማኅደር ፡ ውስጥ ፡ ይገኛል ። እዋዜማ ፡ ሥርዐት ፡ መመሪያ ፡ ውስጥ ፡ ዝርዝር ፡ የተከላ ፡ መረጃ ፡ ከሙሉ ፡ መለማመጃ ፡ ጋራ ፡ ይገኛልና ፥ መመሪያውን ፡ አየት ፡ ማድረጉ ፡ ይጠቅማል ። [<u>ማስጠንቀቂያ</u> ፤ የዋዜማ ፡ ሥርዐት ፡ መፍቻ−ገበታ ፡ እስከ ፡ Windows XP ፡ ድረስ ፡ ለኹሉም ፡ የ Windows ፡ ምግባር ፡ ክለሳዎች ፡ አላንዳች ፡ ችግር ፡ ያገለግላል ። ከ Windows ፡ 7 ፡ ወዲህ ፡ ግን ፥ Microsoft ፡ በተለይ ፡ ባደረጋቸው ፡ ለውጦች ፡ ምክንያት ፥ እንደ ፡ Word ፡ ባሉ ፡ የ Microsoft ፡ መሳሊያዎች ፡ ላይ ፡ የዋዜማ ፡ ሥርዐት ፡ መፍቻ−ገበታ ፡ አይሠራም ፤ ነገር ፡ ግን ፡ እንደ ፡ OpenOffice ፣ Notepad++ ፡ ባሉ ፡ ሌሎች ፡ መሳሊያዎች ፡ ላይ ፡ አለምንም ፡ ችግር ፡ በ Windows ፡ 8 ፣ 10 ም ፡ ጭምር ፡ ይሠራል ።] • the Wazéma System keyboard system is made available as an alternative; it too is extracted with AwdeQelem, in its own folder "Wazéma2003_k3_20030827". The Wazéma System User's manual provides detailed instructions and exercises to master the keyboard system; it is worth having a look. [<u>Warning</u>: the Wazéma System keyboard system works fine on all versions of the Windows operating system. However, starting from Windows 7, Microsoft having made substantial changes to keyboard handling on their own software (MSOffice, Notepad, ...), the Wazéma System keyboard system no longer works on these applications, but works perfectly well on all other non-Microsoft applications such as OpenOffice, Notepad++, etc.]. • le système de clavier de Système Wazéma est mis à votre disposition; celui-ci aussi est extrait avec AwdeQelem, dans le dossier "Wazéma2003_k3_20030827". Le manuel utilisateur de Système Wazéma contient les instructions ainsi qu'une séries d'exercices pour maitriser

		le système de clavier; ça vaut la peine d'y jeter un coup d'œil. [Avertissement: le système de clavier de Système Wazéma fonctionne dans toutes les versions du système d'exploitation Windows; cependant, depuis la version Windows 7, Microsoft a effectué des modifications dans la gestion du système de clavier dans ses propres logiciels [MSOffice, Notepad, ...] de sorte que le système de clavier de Système Wazéma n'y fonctionne plus, mais continue cependant à fonctionner parfaitement dans toutes les applications autres que celles de Microsoft, comme OpenOffice et Notepad++, etc.]
ጥንቃቄ • precautions • précautions	▶	• "ኢንተርኔት"ና ፡ ስለላ ፥ የማይለያዩ ፡ ጣምራ ፡ ናቸውና ፥ ማስሊያዎ ፡ ከኢንተርኔት ፡ ጋራ ፡ በቀጥታ ፡ (በሽቦም ፡ ኾነ ፡ ሽቦ ፡ አልቦ) ፥ ወይ ፡ በተዘዋዋሪ ፡ (በ"ሲዲ"ም ፡ ኾነ ፡ "ሜመሪ-ስቲክ") ፥ አካላዊ ፡ ግንኙነት ፡ ሊኖረው ፡ እስከ ፡ ቻለ ፡ ድረስ ፥ በ"ለካፊ" ፣ "ዦሮ ፡ ጠቢ" ፣ "ሰርጎ ፡ ገቢ"ና ፡ በመሳሰሉት ፡ አማካይነት ፥ የመረጃ ፡ መሰረቅ ፣ ወይ ፡ መበላሸት ፣ ወይም ፡ መደምሰስ ፡ አደጋ ፡ አለበት ። ስለዚህ ፥ በማስሊያ ፡ አማካይነት ፡ ሥራን ፡ የሚሠራ ፡ ኹሉ ፡ ይህን ፡ ዐውቆ ፡ ሊጠነቀቅ ፡ ይገባል • Internet and spying are as inseparable as the two sides of the same coin; a computer physically linkable to Internet, directly through wired or wireless connection, or indirectly through CD or "memory stick", is exposed to "viruses", "spyware", "Trojan horses", and subsequent data theft, corruption or even loss. It is therefore essential to take appropriate steps • Internet et espionnage sont aussi inséparables que la lumière et l'ombre. Un ordinateur physiquement connectable à Internet, directement avec ou sans fil, ou indirectement par le biais de CDs et clés USB, est exposé au "virus", "logiciel espion", et autre "cheval de Troie", qui lui volerons des données s'ils ne lui en détruisent ou corrompent pas. Il est donc essentiel de prendre les mesures appropriées.

2.3 ፫ ተከላ • Installation

የዐውደ ፡ ቀለም ፡ ተከናዋኙ ፡ እሽግ ፡ awdeqelem.exe ፥ ከ ፦

awde-qelem.net

ወይም ፡ ከዋዜማ ፡ ሥርዐት ፡ መርበቢያ ፡ ከ ፦

gzamargna.net

ሲቀዳ ፡ በተፈልፋይና ፡ በተተካይ ፡ ሰነድነት ፡ ነው ። awdeqelem.exeን ፡ በመጠቈሚያ ፡ ጠቍሞ ፥ የግራ ፡ ዝራርን ፡ ኹለት ፡ ጊዜ ፡ ሲቀጨቅጩበት ፥ የታሸገው ፡ ሰነድ ፡ የሚፈለፈልበት ፡ የ WinZip Self-Extractor መሳተፊያ ፡ ይከሠታል ። "UNZIP" ፡ የሚለውን ፡ ዝራር ፡ ሲጫኑት ፡ ሰነዱ ፡ ይፈለፈልና ፥ ፍልፈላው ፡ ተከናውኖ ፡ ሲያበቃ ፥ "CLOSE" ፡ የሚለውን ፡ ዝራር ፡ ተጭኖ ፡ መዝጋትና ፡ ወደተፈለፈለው ፡ የዐውደ ፡ ቀለም ፡ ማኅደር ፡ መኼድ ።



የተከላ ፡ ረድፎችን ፡ በሥዕላዊ ፡ መግለጫ ፡ እንደሚከተለው ፡ እናያለን ።

The self-executing package of AwdeQelem፡ awdeqelem.exe, is downloadable from the Wazéma System website፡ gzamargna.net, as a self-extracting and self-installing file. Double-click awdeqelem.exe with the left button of the mouse to display the WinZip Self-Extractor dialog and trigger the file extraction and self-installation process by pressing "UNZIP"and pressing "CLOSE" at the end of it. Let us follow the steps in the following pictorial presentation፡

L'emballage d'auto-execution AwdeQelem, awdeqelem.exe, est téléchargeable à partir du site de Système Wazéma ፡ gzamargna.net, sous la forme d'un fichier qui s'extrait et s'installe automatiquement. Double-cliquez awdeqelem.exe avec le bouton de gauche pour déclencher le processus d'installation. Suivons les étapes avec la présentation graphique qui suit፡



ግጸዊ ፡ 1 ፤ እተፈለፈለው ፡ AwdeQelem_1-3_20140621 ፡ ማኅደር ፡ ውስጥ ፥ ዐውዴ ፡ ቀለም ፡ መግበር ፡ awdeqelem_1-3_20140621 ፡ በሚል ፡ ስም ፡ ከሌሎች ፡ ረዳት ፡ ቅምሮች ፡ ጋራ ፡ ተደርድሮ ፡ ይገኛል ። መግበሩን ፡ ለማስነሣት ፥ awdeqelem_1-3_20140621ን ፡ ለይቶ ፡ በመጠቈሚያው ፡ ይቀጨቅጫል ። የመግበሩም ፡ የመጀመሪያው ፡ ገጽ ፡ ለጥቆ ፡ በሚታየው ፡ መልክ ፡ ይከሠታል ።

Figure 1፡ Inside the extracted folder፡ AwdeQelem_1-3_20140621, you will find among supporting programmes, the application AwdeQelem as awdeqelem_1-3_20140621. Start it by double-clicking it.

Figure 1፡ À l'intérieur du dossier፡ AwdeQelem_1-3_20140621, vous trouverez l'application AwdeQelem, sous l'intitulé awdeqelem_1-3_20140621, parmi divers autres programmes de soutien. Démarrez la en cliquant deux fois.

2.4 ፤ አገልግሎት • usage • utilisation



ግጻዌ ፡ 2 ፤ ዐውደ ፡ ቀለም ን ፡ ሲያስነሡ ፥ የጽሑፍ ፡ ማምረቻው ፡ ከመከሠቱ ፡ በፊት ፡ ካ 10 ፡ እስከ ፡ 20 ፡ ካልኢታት ፡ ወይም ፡ "ሰከንዶች" ፡ ይፈጃል ፤ ከርሱ ፡ በፊት ፡ የመዛግብተ ፡ ቃላቱ ፡ ሰነዶች ፡ ምግባሩ ፡ ላይ ፡ መጫን ፡ ስላለባቸው ፡ ነው ። ቀድሞ ፡ የሚከሠትልን ፡ እላይ ፡ የተመለከተው ፡ የመቀመሪያው ፡ የ SWI-Prolog ፡ ዋና ፡ መሳተፊያ ፡ ገጽ ፡ ነው ፤ ይህ ፡ መሳተፊያ ፡ አንዳንድ ፡ የክንዋኔ ፡ መልክቶችን ፡ ለማስታወቅና ፥ ቀላል ፡ የኾኑ ፡ የ Prolog ፡ ቅምሮችን ፡ ለማከናወን ፡ ይውላል ፤ ነገር ፡ ግን ፥ አብዛኞቻችን ፡ እንደሌለ ፡ ልንቈጥረውና ፡ ልናልፈው ፡ እንችላለን ። በ Prolog ፡ የመቀመር ፡ ልምድ ፡ ያላቸው ፡ ተገልጋዮች ፡ ግን ፡ ሊሠሩበት ፡ ይችላሉ ፤ በተለይ ፡ "Settings" ፡ የሚለውን ፡ መምረጫ ፡ ተጭነው ፡ ቅርጸቱን ፡ ወደዋዜማ ፡ ቅርጸት ፡ ሊለውጡለት ፡ ይችላሉ ።
ሌሎቻችንን ፡ የማይመለከት ፡ ስለ ፡ ኾነ ፥ በዚሁ ፡ እንተወውና ፡ ወደጽሑፍ ፡ ማምረቻው ፡ እናምራ ።

Figure 2: As we start the application, it takes some 10 to 20 seconds while the dictionary resources are loaded onto the operating system, and before AwdeQelem's main window displays. The first interface to appear in the meantime is the SWI-Prolog interpreter's interface, shown above, which serves as a means of communicating system and application execution details; or, to those who are Prolog literate, to interpret or execute basic Prolog code, and to modify its settings such as typeface, etc..
To most of us this is irrelevant, therefore we can safely disregard it and wait for the display of the actual AwdeQelem window as follows.

Figure 2: Lorsque l'on démarre l'application AwdeQelem,
il se passe 10 ou 20 secondes durant lesquelles le ressources des dictionnaires sont chargées dans le système d'exploitation, et avant que la fenêtre principale de AwdeQelem n'apparaisse. En attendant, la première interface à apparaître est l'interface de l'interpréteur SWI-Prolog, ci-dessus, qui sert principalement de moyen de communiquer des détails d'exécution du système ou de l'application; ou encore, pour ceux qui programment en Prolog, de moyen d'interpréter ou exécuter des codes sources Prolog, ou encore de modifier à partir de "Settings" des détails comme les polices de caractères, etc..
Pour la plupart d'entre nous, cela est sans importance; nous attendons donc l'apparition de la principale fenêtre de AwdeQelem.



ግጸዌ ፡ 3 ፤ እንሆ ፥ የዐውደ ፡ ቀለም ፡ ዋና ፡ ገጽ ። ከተለመደው ፡ የጽሑፍ ፡ ማምረቻ ፡ መግበር ፡ ለየት ፡ ያለ ፡ መልክ ፡ ቢያሳይም ፥ ዐውደ ፡ ቀለም ፡ እጅግ ፡ ይመቻል ። የመስኮቹና ፡ ያዝራሩ ፡ አርእስት ፡ ግብራቸውን ፡ ይገልጻሉ ፤ ብዙ ፡ ትንታኔ ፡ አይሹም ። የብዙዎቹን ፡ ግብርም ፡ በሚከተሉት ፡ ገጾች ፡ በዝርዝር ፡ እናያለን ። ለጊዜው ፥ ከላይ ፡ ወደ ፡ ታች ፡ ስናይ ፥ እራስጌ ፥ የስንዳታ ፡ መሳተፊያው ፡ ይታየናል ፡ (ሰነድ ፡ መክፈቻ ፣ ሰነድ ፡ መመዝገቢያ ፣ ወዘተ.) ፤ እዚህ ፡ ላይ ፥ ክለሳ ፡ 1.1 ፡ ያመጣልን ፡ ዐዲስ ፡ ነገር ፥ የቅርጸቶችን ፡ መጠንና ፡ ዐይነት ፡ መለወጥ ፡ ማስቻል ፡ ነው ። ጽሑፎችን ፡ ከሦስቱ ፡ የዋዜማ ፡ ቅርጸቶች ፡ በመረጥነው ፡ ልንከሥታቸው ፡ እንችላለን ፤ መጠናቸውንም ፡ ትልቅ ፣ መኻከለኛ ፡ ወይም ፡ ትንሽ ፡ ብለን ፡ እንደ ፡ ፍላጎታችን ፡ ልንለዋውጣቸው ፡ እንችላለን ።

እወገቡ ፡ ላይ ፥ የሚከፈተው ፡ ሰነድ ፡ ይዘት ፡ የሚከሠትበት ፡ መስክ ፡ ብጫ ፡ ቀለም ፡ ለብሶ ፡ ይታየናል ። እግርጌ ፥ የቃል ፡ ማኼጃው ፡ ዐውድማ ፡ ይታየናል ፤ በዚህኛው ፡ መሳተፊያ ፡ ላይ ፥ የምንሠራበትን ፡ ጻሕፍና ፡ ቋንቋ ፡ እንወስንበታለን ፥ የምናኺደውን ፡ ቃል ፡ እናመለክትበታለን ፤ ቃሉንም ፡ እናሥሥበታለን ፥ እናጣራበታለን ፥ እናርምበታለን ፥ እንፈታበታለን ፥ እንተነትንበታለን[29] ፥ ወዘተ. ።

የዐውደ ፡ ቀለም ፡ ክለሳ ፡ 1.1 ፡ ቃልን ፡ ባንድ ፡ አፍታ ፡ ወደ ፡ ሦስት ፡ ቋንቋዎች ፡ የመተርጎም ፡ ችሎታን ፡ ሰጥቶናል ፤ በርሱ ፡ ላይ ፥ ክለሳ ፡ 1.2 ፡ ደግሞ ፥ ከቋንቋዎቹ ፡ ተርታ ፡ ግእዝንና ፡ ሶማልኛን ፡ አክሎልናል ፤ ሌሎችም ፡ ይከተላሉ ። ይህውም ፡ "በ" ፡ በሚል ፡ ስም ፡ እተመለከተው ፡ ማማረጫ ፡ መስክ ፡ ላይ ፡ ሊተረጎምልን ፡ የምንሻውን ፡ ቃል ፡ አስፍረን ፥ "ይተርጎም" ፡ የሚለውን ፡ ዝራር ፡ በመጫን ፡ እግርጌ ፡ እሚገኘው ፡ ሰፊ ፡ መስክ ፡ ላይ ፡ ትርጉሙን ፡ በቀጥታ ፡ ባማርኛ ፣ በእንግሊዝኛ ፣ በፈረንሳይኛ ፣ በግእዝና ፡ በሶማልኛ ፡ [30] ፡ እናገኛለን ። ዝርዝሩን ፡ እቦታው ፡ ስንደርስ ፡ እንመለስበታለን ።

ከግራ ፡ ወደ ፡ ቀኝ ፡ ስንመለከት ፡ ደግሞ ፤ በግራ ፥ እስካኹን ፡ የተነገረው ፡ ኾኖ ፥ መኻለኛው ፡ ዐምድ ፡ የተከፈተውን ፡ ሰነድ ፡ ቃላት ፡ ዝርዝር ፡ በነቂስ ፡ ያሳየናል ፤ የቀኙ ፡ ዐምድ ፡ ደግሞ ፥ የምንፈልገውን ፡ ቃል ፡ ኹሉ ፥ ከነዝርዝሮቹ ፣ ከነሞክሼዎቹ ፡ የምንደረድርበት ፡ ይኾናል ። ለጥቀን ፡ በዝርዝር ፡ እናየዋለን ።

Figure 3: Here is the principal page of AwdeQelem. Slightly different from what we are accustomed to with popular text processors; however AwdeQelem is a very

Figure 3: Voici la page principale de AwdeQelem. Quelque peu différente de ce à quoi les traitements de texte en vogue nous ont habitués; néanmoins, AwdeQelem est un

29 በዚህ ፡ ክለሳ ፥ ላማርኛ ፡ ብቻ • in the current version, for Amharic only • pour l'amharique seulement dans la présente version

30 ለጊዜው ፥ የተተራጎሙት ፡ ቃላት ፥ ለግእዙ ፡ 2600 ፥ ለሶማልኛው ፡ ደግሞ ፡ 1000 ፡ ብቻ ፡ ናቸው ። ተከታዮቹ ፡ ክለሳዎች ፡ እነዚህን ፡ አኃዞች ፡ ዕጥፍ ፡ ድርብ ፡ ያበዟቸዋል ።

user-friendly application indeed, with a down to earth Graphical User Interface, where field and button titles speak for themselves.

At the top we see the filing and editing dialogue with a standard menu followed by a series of file handling buttons (opening, saving, and closing).

In the middle is the body page where the content of the opened file is displayed.

At the bottom is the area where script and language are set, and where words are literally processed individually: where they are searched, spell-checked, corrected, analysed [31], looked-up in the dictionary, etc. Here again, version 1.1 has introduced simultaneous word translation in three languages: Amharic, English, French; further, version 1.2 has now included G'z and Somali [32] in the list of translatable languages, with a few more to come. Once a given word is indicated in the "by" field of alternatives, it suffices to press the "translate" button on the right, for the translations to appear in the five languages above, in the lower text field entitled "translations". We will come back to this most fruitful feature later on.

From left to right we see, in addition to the main view of the text field, a middle column where file's word-list is displayed entirely, followed on the right, by a smaller column where the search outputs are listed as derivatives or as homonyms.

outil très convivial, avec une interface conventionnelle et pratique, où les intitulés des champs et boutons parlent d'eux mêmes.

À l'entête figure le dialogue de fichage et d'édition avec un menu standard, suivi par une série de boutons relatifs à la gestion des fichiers (ouverture, sauvegarde, fermeture, etc.).

Au milieu, nous avons le corps de la page où le contenu du ficher ouvert est visualisé.

Enfin, en bas, nous avons le dialogue où l'écriture et la langue sont sélectionnées, où les mots sont littéralement traités un par un: où ils sont recherchés, vérifiés, corrigés, analysés [33], consultés dans le dictionnaire, etc.. A ce stade, l'on doit mentionner une autre nouveauté introduite par la version 1.1: la possibilité de traduction simultanée en trois langues: amharique, français, anglais; la version 1.2 a ajouté le g'z et le somali, et quelques autres suivront prochainement. En effet, il suffit d'indiquer le mot à traduire dans le champ des alternatives "par", et en appuyant le bouton "traduire" situé à droite. Les traductions dans les cinq langues sont alors affichées dans le champ texte situé en bas de la fenêtre. Nous reviendrons plus en détail sur cette fonctionnalité fort intéressante dans quelques instants.

En partant de gauche à droite, nous avons déjà vu le champs principal où le contenu du fichier ouvert est affiché; à sa droite figurent deux colonnes, dont celle du milieu où tous les mots contenus dans le fichier sont listés; et celle de la droite où le résultat des recherches est listé, qu'il s'agisse des dérivés du mot recherché ou de ses homonymes.

31 In the current version, for Amharic only.

32 The translatable words for G'z number only 2600, and those for Somali only 1000; future versions will significantly increase these figures.

33 Pour l'amharique seulement dans la présente version.

2.4.1 የነባር ፡ ሰነድ ፡ ከፈታ • opening of an existing file • ouverture d'un fichier existant

ዐውደ ፡ ቀለም ፡ መግበር ፡ ብቻውን ፡ አልመጣላችኹም ፤ ዐብረውት ፡ የልዩ ፡ ልዩ ፡ ቋንቋዎች ፡ (ዐማርኛ ፣ ግእዝ ፣ እንግሊዝኛ ፣ ፈረንሳይኛ ፣ ሶማልኛ ፣ ወዘተ.) ፡ የታወቁ ፡ ጽሑፎች ፡ በ".txt" ፡ አቀጻጽ ፡ ተሰናድተው ፥ "ቀለም ፡ ቀንድ" ፡ (QelemQend) ፡ እተሠኘ ፡ ልዩ ፡ ማኅደር ፡ ውስጥ ፡ ለናሙና ፡ ያኽል ፡ ተከማችተውላችኋል ። ለማሳያ ፡ ያኽል ፥ እስቲ ፡ አንደኛውን ፡ ... ፡ ለምሳሌ ፥ ያማርኛ ፡ መጽሐፍ ፡ ቅዱስን ፡ እንክፈት ። (ዐማርኛ ፡ ባታነቡ ፥ የእንግሊዝኛም ፣ የፈረንሳይኛም ፣ የሶማልኛም ([34]) ፣ ወዘተ. ፡ መጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ እዚሁ ፡ ማኅደር ፡ ውስጥ ፡ አለላችኹ ፤ የሚመቻችኹን ፡ ምረጡ) ። ግጻዌ ፡ 3 ፡ ከዚህ ፡ በታች ፡ እንደሚያመለክተን ፥ "ነባር ፡ ሰነድ ፡ ይከፈት" ፡ የሚለውን ፡ ዝራር ፡ በመጫን ፡ ሰነዱን ፡ ከዐውደ ፡ ቀለም ፡ ኾነን ፡ መርጠን ፡ ስንከፍተው ፥ ሰነዱ ፡ የያዘው ፡ ጽሑፍ ፡ እዋናው ፡ የጽሑፍ ፡ መስክ ፡ ላይ ፡ ይከሠትልንና ፥ እቀኙ ፡ በሚገኘው ፡ ዐምድ ፡ ላይ ፡ የጽሑፉ ፡ ቃላት ፡ በነቂስ ፡ በ"ሀለሐመ" ፡ ተራ ፡ ይደረደሩልናል ። የቃላቱ ፡ በነቂስ ፡ መደርደር ፡ ዐያሌ ፡ ጥቅሞች ፡ አሉት ፤ ከነዚህ ፡ ውስጥ ፡ ጥቂቶቹን ፡ ለመጥቀስ ፡ ያኽል ፥

- ቃላትን ፡ በቀላሉ ፡ ፈልጎ ፡ ለማግኘት ፤
- የፊደል ፡ ስሕተቶችን ፡ በፍጥነት ፡ ለማየትና ፥ አጣርቶ ፡ ለማረም ፡ ወይም ፡ ለመተካት ፤
- የማናውቀው ፡ ጽሑፍ ፡ ቢኾን ፡ ደግሞ ፥ ይዘቱን ፡ በፍጥነት ፡ ለመገንዘብ ፤
- የማናውቃቸው ፡ ቃላት ፡ ቢኖሩበት ፡ ወዲያው ፡ በመዝገበ ፡ ቃላት ፡ ለማጣራትና ፡ ለመረዳት ፤ አለዚያም ፡ ወደምናውቀው ፡ ቋንቋ ፡ በቅጽበት ፡ ተርጕመን ፡ ለመረዳት ፤
- ወዘተ.

34 ለሶማልኛ ፡ ተናጋሪዎች ፥ ቁርኣን ፡ በሶማልኛ ፡ ቋንቋ ፡ ዐብሮ ፡ ይገኛል ።

AwdeQelem is not coming to you alone; with it are made available samples of some of the most important literature compiled in ".txt" format and archived within the QelemQend ("inkstand") folder. As an example, let us open the Amharic Bible (for those who do not read Amharic, the English, French, Somali ([35]), etc. versions of the Bible are also available in their respective folders). As shown in Figure 4 below, by pressing the "open existing file" button, we select and open the said file which is then displayed in the text page of AwdeQelem. On its right, the middle word-list column lists automatically and in alphabetical order all the words contained in the text. The exhaustive listing of words has the added advantage, among others, of making it easy to:

- seek and find a particular word;
- see quickly spelling mistakes and make the necessary corrections or replacements;
- quickly have a feel for the content if we are new to the text;
- lookup and verify unknown or unclear words with the help of the associated dictionary; or even immediately translate them into the language we are more familiar with;
- etc.

AwdeQelem ne vient pas tout seul; avec lui sont mis à notre disposition un échantillon de littératures parmi les plus importantes, organisé en format ".txt", et archivé dans le dossier QelemQend ["grand encrier"]. Illustrons cela en ouvrant la Bible amharique [pour ceux qui ne lisent pas l'amharique, les versions française, anglaise, somali ([36]), etc., sont aussi disponibles dans leurs dossiers respectifs]. Comme nous le montre la figure 4, en appuyant le bouton "ouvrir fichier existant" et en ouvrant le fichier susmentionné, le contenu du texte apparaît dans la page texte de AwdeQelem. À sa droite, la colonne du milieu liste automatiquement l'intégralité des mots du texte, par ordre alphabétique. Le dressage exhaustif de la liste des mots offre, entre autres, l'avantage:

- de rendre aisée la recherche d'un mot en particulier;
- de déceler plus rapidement les fautes d'orthographie et d'effectuer aisément leurs correction ou remplacement;
- d'examiner d'un coup d'œil le contenu d'un texte qui nous est inconnu;
- de chercher et vérifier la signification d'un mot inconnu ou obscure à l'aide du dictionnaire correspondant; ou encore d'obtenir une traduction immédiate dans la langue qui nous est plus familière;
- etc.

35 For Somali speakers, the Somali version of the Qur'an is also available.

36 Pour les somalo-phones, la version somali du Qur'an est aussi mise à leur disposition.



ግጻዌ ፡ ፬ ፤ እዐውደ ፡ ቀለም ፡ መሳተፊያ ፡ ራስጌ ፥ ሰነድ ፡ ነክ ፡ የኾኑ ፡ መስኮችና ፡ አዝራር ፡ ይታያሉ ፡ (የሰነድ ፡ መሳተፊያ) ። እወገብጌ ፥ የሰነዱ ፡ ይዘት ፡ የተከሠተበት ፡ የጽሑፍ ፡ መስክና ፡ የሰነዱ ፡ ቃላት ፡ በነቂስ ፡ የተተረሩበት ፡ ዐምድ ፡ ይታያል ። እግርጌ ፥ ቃል ፡ ነክ ፡ የኾኑ ፡ መስኮችና ፡ አዝራር ፡ ይታያሉ ፡ (የቃል ፡ መሳተፊያ) ፤ ግብራቸው ፡ ከስማቸው ፡ ይገኛል ።

Figure 4: The graphical user interface of AwdeQelem is made up of three vertical sections: the top most is the file interface where filing related tasks are grouped.
The middle section is the text interface where the content of the opened file is displayed together with the list of words, on the right hand side column.
Finally, the bottom section is the word interface where word related tasks are grouped.

Figure 4: L'interface graphique de AwdeQelem consiste en trois sections verticales: celle du haut est l'interface de fichier, où les tâches relatives au fichage sont regroupées.
La section médiale est l'interface relative au texte, celle où le contenu du fichier ouvert est affiché ainsi que la liste des mots dans la colonne de droite.
Enfin, la section du bas est l'interface où les tâches relatives au mot sont regroupées.

2.4.2 ፤ የቃል ፡ መረጣና ፡ ግኝት • word selection and finding • sélection et recherche de mot

ጽሑፍ ፡ ኹሉ ፡ በቃል ፡ ይከወናል ፤ ቃል ፡ ደግሞ ፡ ተራውን ፡ በፊደል ፡ ወይም ፡ በጠቅላላው ፡ በኀርመት ፡ ይከወናል ። በዚህ ፡ መሠረት ፥ በዐውደ ፡ ቀለም ፡ መግበር ፡ አሠራር ፥ ፊደሎች ፡ በጻሕፍ ፡ (ኢትዮጵያዊ ፥ ወይም ፡ ምዕራባዊ) ፡ ይሰደራሉ ፤ ቃላት ፡ ደግሞ ፡ በቋንቋ ፡ ይሰደራሉ ። የማንኛውም ፡ ቃል ፡ አኺዶ ፡ እንግዲህ ፥ ቃሉ ፡ የተጻፈበትን ፡ ጻሕፍና ፡ የሚነገርበትን ፡ ቋንቋ ፡ አስቀድሞ ፡ ያገናዝባል ። ግጻዌ ፡ 4 ፡ ላይ ፡ ያየነው ፡ የሰነድ ፡ ከፈታ ፥ በመኻል ፡ ዐምድ ፡ ላይ ፡ የሰነዱን ፡ ቃላት ፡ በፊደል ፡ ተራ ፡ በነቂስ ፡ ደርድሮልናል ፤

እግርጌ ፡ ደግሞ ፡ ጽሑፉ ፡ የተጻፈበትን ፡ ጻሕፍና ፡ ቋንቋ ፡ ገዛውን ፡ አመልክቶልናል ።
ግጻዌ ፡ 5 ና ፡ 6 ፡ ደግሞ ፡ ከቃላት ፡ መደርደሪያው ፡ እንዴት ፡ አድርገን ፡ አንድን ፡ ቃል ፡ ለይተን ፡ ከቃላት ፡ ተራው ፡ እንደምንመርጥና ፡ እጽሑፉ ፡ ውስጥ ፡ እንደምናገኘው ፡ ያሳዩናል ።

A text is made up of words, and words in turn are made up of letters, or more generally of characters. AwdeQelem is built based on this general principle, so that letters are first sorted by script (Western or Ethiopian), then words are sorted by language. The processing of any single word takes into account the script in which it is written together with the language it is used in. As we saw already in figure 4, the opening of a given file results in the display of its content and that of its list of words, while at the same time AwdeQelem determines automatically the script and the language used in the opened file.
Figures 5 and 6 will now show us how we select a given word from the list of words, and how we search it in the text body.

Un texte est composé de mots, et les mots sont à leur tour composés de lettres, ou plus généralement de caractères. AwdeQelem est fondée sur ce principe, de telle sorte que les lettres sont d'abord triées par écriture (occidentale ou éthiopienne), puis les mots triés par langue. Le traitement de chaque mot tient compte de l'écriture dans laquelle il est inscrit, ainsi que de la langue dans laquelle il est utilisé. Comme l'avons déjà vu dans la figure 4, l'ouverture de tout fichier donne lieu à l'affichage de son contenu et de sa liste de mots, alors que dans le même temps AwdeQelem détermine automatiquement l'écriture et la langue utilisées dans le fichier ouvert.
Figures 5 et 6 vont maintenant nous montrer comment on sélectionne un mot donné depuis la liste de mots, et comment on le recherche dans le corps du texte.



ግጸዌ ፡ 5 ፤ የቃላት ፡ ተራውን ፡ ዐምድ ፡ በመንሻረሪያው ፡ ከላይ ፡ ወደ ፡ ታች ፥ ከታች ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ ስንንሻረርበት ፥ የሰነዱን ፡ ጠቅላላ ፡ የቃላት ፡ ይዘት ፡ አንድ ፡ ሳይቀር ፡ እናይበታለን ። ማየትም ፡ ብቻ ፡ አይደለም ፤ ቃሉን ፡ በመጠቈሚያው ፡ መርጠን ፥ እጽሑፉ ፡ ውስጥ ፡ የት ፡ የት ፡ እንደሚገኝ ፡ በቅጽበት ፡ እናገኝበታለን ። ቀጣዩ ፡ ግጸዌ ፡ 6 ፡ በዝርዝር ፡ ያሳየናል ።

Figure 5: All words contained in the file are listed in the middle column, which we may inspect by sliding up and down. We may also select it and find out where in the text it is used and how many times, as figure 6 will show us.

Figure 5: Tous les mots contenus dans le dossier sont listés dans la colonne du milieu que l'on peut examiner de haut en bas. On peut aussi sélectionner tout mot de la liste pour savoir où exactement il apparaît dans le texte, et combien de fois, ce que va nous montrer la figure 6.



ግጻዌ ፡ 6 ፤ ለምሳሌ ፥ እመጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ውስጥ ፡ "ኢትዮጵያ" ፡ የሚለው ፡ ቃል ፡ ስንት ፡ ጊዜ ፡ እንደ ፡ ተጠቀሰ ፡ ለማወቅ ፡ ብንሻ ፥ ከቃላት ፡ መደርደሪያው ፡ ዐምድ ፡ ቃሉን ፡ በመጠቈሚያችን ፡ ግራ-ዝራር ፡ ጠቍመነው ፥ በቀኝ-ዝራር ፡ ስናቀባብለው ፥ እግርጌ ፡ ቃል ፡ መስክ ፡ ላይ ፡ "ኢትዮጵያ" ፡ የሚለው ፡ ቃል ፡ ይሰፍርና ፥ እጽሑፉ ፡ ውስጥ ፡ ቃሉ ፡ የሚገኝበት ፡ ቦታ ፡ በቀይ ፡ ፍላጻ ፡ ይመለከትልናል ፤ የቦታውም ፡ መናጠቢያ ፡ በመነሻ ፡ ቍጥርና ፡ በኅርመት ፡ ተራ ፡ ተቀናጅቶ ፡ "ቦታው" ፡ እተሠኘው ፡ መስክ ፡ ላይ ፡ ይመለከትልናል ፡ (እዚህ ፡ ላይ ፡ 152 ኛ ፡ መነሻ ፥ 5213 ኛ ፡ ኅርመት) ። ከዚህ ፡ ወዲያ ፥ እግርጌ ፡ መስኮቹ ፡ ላይ ፡ ቃሉ ፡ እጽሑፉ ፡ ውስጥ ፡ ስንት ፡ ጊዜ ፡ እንደ ፡ ሰፈረ ፡ እናያለን ፡ (47 ፡ ጊዜ) ።
"ኢትዮጵያ" ፡ የሚለው ፡ ቃል ፡ የሰፈረባቸውን ፡ ቦታዎች ፡ ኹሉ ፡ ለመጐብኘት ፡ ብንሻ ፡ ደግሞ ፥ የመሽጋገሪያውን ፡ '+' ፡ ዝራር ፡ እየተጫን ፡ አንድ ፡ ባንድ ፡ መጐብኘት ፡ እንችላለን ።
በጅምላ ፥ "ኢትዮጵያ" ፡ የሚለው ፡ ቃል ፡ እመጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ውስጥ ፡ 47 ፡ ጊዜ ፡ መጠቀሱን ፡ እናያለን ፤ ኾኖም ፥ ይህ ፡ አኃዝ ፡ ዝርዝሮችንም ፡ ይጨምራልና ፥ ከጅምላ ፡ ይልቅ ፡ ዝርዝሩን ፡ ግጻዌ ፡ 7 ፡ ያስረዳናል ።

Figure 6: A left click of the mouse on a given word from the word-list column selects it; then a right click makes the selected word appear in the "word" field in the lower part of the interface, together with the number of times this particular word appears in the text (in the above example, the word "ኢትዮጵያ" appears 47 times in the displayed text); in addition, the coordinates of the position are further specified in the field "position" as "152th paragraph and 5213th character".

Each occurrence of a given word in the

Figure 6: Un clic du bouton de gauche au dessus d'un mot quelconque de la liste le sélectionne; puis un clic du bouton de droite fait apparaître ce mot dans le champ "mot" de l'interface, en même temps que le nombre de fois où ce même mot apparaît dans le corps du texte (dans l'exemple ci-dessus, le mot "ኢትዮጵያ" apparaît 47 fois dans le texte); de plus, les coordonnées de la position sont précisées dans le champ "position" avec les détails: "152ème paragraphe et 5213ème caractère"

Chacune des occurrences d'un mot

text can be visited in succession by pressing the "+" button.
However, the given word can have many other derivations and homonyms; figure 7 will show us how to explore these.

quelconque dans le texte peut être visitée successivement en appuyant le bouton "+".
Néanmoins, ce même mot peut aussi avoirs plusieurs dérivés et homonymes; la figure 7 nous montrera comment explorer ceux là.



ግጸዊ ፡ 7 ፤ በመሳተፊያው ፡ የቀኝ ፡ ዐምድ ፡ ላይ ፡ የፍለጋ ፡ ዘዴዎች ፡ ይገኙልናል ፡ (ያሠሣ ፡ መሳተፊያ) ። "ይታሠሥ" ፡ የሚለውን ፡ ዝራር ፡ ብንጫን ፥ "ኢትዮጵያ" ፡ የሚለው ፡ ቃል ፡ ብቻውን ፡ ወይም ፡ ምእላድ ፡ ታክሎበት ፡ የተጻፈባቸውን ፡ ቃላት ፡ ኹሉ ፡ አግበስብሶ ፡ ያመጣልናል ። የተግበሰበሱትንም ፡ ቃላት ፥ አንድ ፡ ባንድ ፡ መርጠን ፡ በማቀባበል ፡ (የመጠቈሚያውን ፡ አዝራር ፡ ግራ-ቀኝ ፡ አከታትሎ ፡ በእየቃሉ ፡ ላይ ፡ በመጠቈም) ፥ ብዛታቸውን ፡ ማግኘትና ፥ የሰፈሩበትንም ፡ ቦታ ፡ በቀዩ ፡ ዕልባት ፡ ለይተን ፡ አንድ ፡ ባንድ ፡ መጐብኘት ፡ እንችላለን ።

Figure 7: On the rightmost column of the interface are found search alternatives: the "search" button seeks the word in all its inflected forms in the text; whereas the "pick-up" button seeks the word in all its derived forms; finally, the "rake" button seeks all the inflections, derivations and homonyms of the word in the text.
Each of these words can in turn be searched in the text body, pin-pointed by

Figure 6: Sur la colonne de droite de l'interface on trouve des moyens alternatifs de recherche de mots: le bouton "rechercher" nous permet de trouver dans le corps du texte toutes les inflexions du mot indiqué; alors que le bouton "cueillir" étend cette possibilité aux dérivés; enfin, le bouton "ratisser" nous donne la possibilité de rechercher les inflexions, les dérivés et les homonymes du mots indiqué, dans le

the red caret, and visited individually in all its occurrences as we will see shortly.

corps du texte.
Chacun de ces mots peut à son tour faire l'objet d'une recherche dans le texte, localisé avec précision par le biais du signe d'insertion rouge, et visité individuellement dans toutes ses occurrences, comme nous allons le voir tout de suite.



ግጸዊ ፡ 8 ፤ በመሳተፊያው ፡ የቀኝ ፡ ዐምድ ፡ ላይ ፡ "ይቃረም" ፡ የሚለውን ፡ ብንጫነው ፡ ደግሞ ፥ "ኢትዮጵያ" ፡ የሚለውን ፡ ቃል ፡ ዝርዝሮች ፡ ኹሉ ፡ ከጽሑፉ ፡ ውስጥ ፡ ቃርሞ ፡ ያመጣልናል ። የመቃረሙን ፡ ዐቅም ፡ ለመፈተሽ ፡ ከተጸውዖ ፡ ስም ፡ ይልቅ ፡ ሌላ ፡ የሚዘረዘር ፡ ግስ ፡ እናመለክትና ፡ እጽሑፉ ፡ ውስጥ ፡ እንቃርመው ። ግጸዊ ፡ 9 ፡ ዝርዝሩን ፡ ያሳየናል ።

Figure 8: As mentioned earlier in the manual, Amharic and G'z, as well as most Ethiopian languages, are highly generative and inflectional. The "search", "pick-up" and "rake" functionalities show their full potential when applied to root words, as we shall see in figure 9.

Figure 8: Comme mentionné précédemment dans le manuel, l'amharique et le g'z, ainsi que la plupart des langues éthiopiennes, sont hautement génératives et flexionnelles. Les fonctions de "rechercher", "cueillir" et "ratisser" sont mieux illustrées appliquées à des radicaux, comme nous le verrons dans la figure 9.

2.4.3 ፲ የቃል ፡ አጻጻፍ ፡ ጥሩትና ፡ ዕርማት • spell-checking and correction of word • vérification et correction de mot



ግጻዌ ፡ 9 ፤ ለምሳሌ ፥ "ዓላማ" ፡ የሚለውን ፡ ቃል ፡ እመፈለጊያው ፡ መስክ ፡ ላይ ፡ እንጻፍና ፡ "ይገኝ" ፡ የሚለውን ፡ ዝራር ፡ እንጫን ። ግጻዌ ፡ 9 ፡ እንደሚያሳየን ፥ የፍለጋው ፡ ውጤት ፡ 0 ፡ ነው ፤ በዚህ ፡ አጻጻፍ ፡ "ዓላማ" ፡ የሚባል ፡ ቃል ፡ እጽሑፉ ፡ ውስጥ ፡ አልተገኘም ። ምናልባት ፡ ፊደል ፡ አሳስተን ፡ ይኾናልና ፤ ብዙ ፡ ሳንደክም ፥ እመሳተፊያው ፡ እግርጌ ፡ ላይ ፡ "ይጣራ" ፡ የሚለውን ፡ ዝራር ፡ እንጫነው ። ውጤቱን ፡ ግጻዌ ፡ 10 ፡ ያሳየናል ።

Figure 9: The following examples are for Amharic words; those readers who do not speak Amharic may try the illustrated functions on a text written in the language of their choice.
The example shows an unsuccessful search for a misspelt word. In which case, by pressing the "verify" button, it will be possible for us to obtain its correct spelling, as we will see next.
NB: the "word analysis" function effected through the button "verify" and output to the field "analysis" is currently only available in full for Amharic, where prefix, suffix and stem alternatives are listed in detail for each analysed word. Future versions of AwdeQelem will,

Figure 9: L'exemple suivant est donné pour l'amharique; les lecteurs qui ne connaissent pas l'amharique peuvent essayer les fonctions illustrées sur un texte écrit dans la langue de leur choix.
L'exemple illustre l'échec résultant d'une recherche de mot incorrectement orthographié. Il s'agit ensuite d'appuyer le bouton "vérifier" pour obtenir éventuellement l'orthographie correcte, comme on va le voire à présent.
NB: la fonction "analyse de mot" réalisée par l'intermédiaire du bouton "vérifier", et dont le résultat est affiché dans le champ "analyse", est pour le moment entièrement applicable uniquement pour la langue amharique, où pour chaque mot analysé les

hopefully, fill these shortcomings and extend the function to other languages.

préfixes, suffixes et radicaux possibles sont listés en détail. Les versions ultérieures de AwdeQelem, il est espéré, combleront ces lacunes en étendant cette fonction à d'autres langues.



ግጻዌ ፡ 10 ፤ ጽሑፉ ፡ የታረመ ፡ በመኾኑ ፥ "ዓላማ" ፡ በዚህ ፡ አጻጻፉ ፡ እጽሑፉ ፡ ውስጥ ፡ አልተገኘም ፤ የ"ዓላማ" ፡ አጻጻፍ ፡ ስሕተት ፡ ቢኾን ፡ ነው ። "ይጣራ" ፡ የሚለውን ፡ ዝራር ፡ ተጭነን ፥ ላመለከትነው ፡ ቃል ፡ የቀረበውን ፡ ትኽክለኛ ፡ አጻጻፍ ፡ በማማረጫ ፡ ቃል ፡ መስክ ፡ ላይ ፡ "ዐላማ" ፡ ተብሎ ፡ እናገኛለን ([37]) ። ዐይን-ዓ-ራብዕ ፡ በዐይን-ዐ-ግእዝ ፡ ተተክቶ ፡ በማማረጫነት ፡ በቃሉ ፡ ቀኝ ፡ መስክ ፡ ላይ ፡ ተመልክቶልናል ። ይህኑ ፡ ውጤት ፡ "ትንታኔ" ፡ የተባለው ፡ መስክ ፡ ማማረጫ ፡ የኾኑትን ፡ ቃላት ፡ ኹሉ ፡ በመደዳ ፡ ከሥር ፡ እስከ ፡ ጫፍ ፡ ደርድሮ ፡ ያሳየናል ። በማማረጫነት ፡ የቀረበልንን ፡ "ዐላማ" ፡ ፍቺ ፡ ለማረጋገጥ ፡ ብንሻ ፡ ደግሞ ፥ "ይፈታ" ፡ የሚለውን ፡ ዝራር ፡ እንጫነውና ፥ በቀጥታ ፡ ወዳማርኛ ፡ መዝገበ ፡ ቃላቱ ፡ መሳተፊያ ፡ እንኼዳለን ።

ግጻዌ ፡ 11 ፡ ይህኑ ፡ ያሳየናል ።

Figure 10: When, by pressing the "verify" button, a particular word is verified for its spelling, the output containing possibly alternative words is listed in the field "by" ([38]). A correctly spelt word is

Figure 10: Lorsque l'orthographie d'un mot quelconque est vérifié par le biais du bouton "vérifier", le résultat contenant éventuellement des mots alternatifs est listé dans le champ "par". Un mot correctement

37 ይህ ፡ የዐውደ ፡ ቀለም ፡ የመዠመሪያ ፡ ክለሳ ፡ እንደ ፡ መኾኑ ፡ መጠን ፥ ለጊዜው ፡ የተፈለገው ፡ ከፍጥነት ፡ ይልቅ ፡ ሙሉነት ፡ ስለ ፡ ኾነ ፥ እንደ ፡ ማጣራት ፡ ያሉ ፡ ግብሮች ፡ ለፍጥነት ፡ ገና ፡ አልሰሉም ፥ ዘገምተኞች ፡ ናቸው ። የሚቀጥሉት ፡ ክለሳዎች ፡ ሙሉነትን ፡ ከፍጥነት ፡ ጋራ ፡ እንዲያጣምሩ ፡ የተቻለውን ፡ ያኽል ፡ ይሻሻላሉ ።

38 As this is the first version of AwdeQelem, the emphasis is more on exhaustiveness than on processing speed, and such functions as spelling verification are not yet optimised for speed. Future versions will hopefully combine exhaustiveness with speed.

repeated in this list; for a misspelt word alternatives are offered; finally, for words impossible to verify, the empty sign "∅" is given as output.

To lookup the definition of any word in the alternatives list, it suffices to press the "define" button which opens for us the AwdeQelem Dictionary tool as figure 11 shows below.

orthographié réapparait dans la liste; par contre si le mot est mal orthographié, l'alternative nous est offerte dans la liste [39]. Enfin, s'il est impossible de vérifier le mot, le signe vide "∅" apparaît dans le résultat.

Pour chercher un mot dans le dictionnaire, il suffit d'appuyer le bouton "définir" qui nous livre l'outil Dictionnaire AwdeQelem, comme nous le montre la figure 11 ci-dessous.



ግጸዌ ፡ 11 ፤ እንሆ ፡ የመዝገበ ፡ ቃላቱ ፡ መሳተፊያ ። ወረድ ፡ ብለን ፡ ዳግመኛ ፡ በዝርዝር ፡ እንመለስበታለን ፤ ለያዝነው ፡ ማብራሪያ ፡ የሚኾነንን ፡ ባጪሩ ፡ እንግለጽ ። የመዝገበ ፡ ቃላቱ ፡ መሳተፊያ ፡ ከላይ ፡ ወደ ፡ ታች ፡ ለሦስት ፡ ይከፈላል ። እራስጌ ፣ የጻሕፍ ፤ የቋንቋና ፡ የመዝገበ ፡ ቃላት ፡ ዐይነት ፡ መምረጫ ፡ ይገኛል ። ቀጥሎ ፣ እወገቡ ፡ ላይ ፣ ተፈቺው ፡ ቃል ፡ የሚሰፍርበት ፡ መስክ ፣ እንዲሁም ፡ የመፍቻ ፡ አዝራሮችና ፣ የፍቺ ፡ ዐይነቶች ፡ መስኮች ፡ ይገኛሉ ። በመጨረሻም ፣ እግርጌ ፣ የመዝገበ ፡ ቃላቱ ፡ ፍቾች ፡ የሚከሠቱባቸው ፡ መስኮች ፡ ይታያሉ ። መስኮቹ ፡ ኹለት ፡ ናቸው ፤ የላይኛው ፡ የጽሑፍ ፡ መስክ ፡ ነው ፤ ፍቺዎቹ ፡ በ.txt ፡ አቀጻጽ ፡ የሚጻፉ ፡ በመኾኑ ፣ በመጠቌሚያው ፡ አጕልቶ ፡ መቅዳትንና ፣

39 La présente version de AwdeQelem étant la première, l'accent est mis plutôt sur l'exhaustivité que sur la vitesse de traitement; ce qui fait que les opérations comme la vérification orthographique sont encore lentes. Les versions avenir feront en sorte que ces fonctions là seront optimisées pour la vitesse, et combineront exhaustivité et vitesse.

እሌላ ፡ ጽሑፍ ፡ ውስጥ ፡ መለጠፍን ፡ ያስችላል ። የታችኛው ፡ መስክ ፡ ደግሞ ፥ የንምር ፡ መስክ ፡ ነው ፤ ይህም ፡ ማለት ፥ የተነመረን ፡ የመዝገበ ፡ ቃላትን ፡ ገጽ ፡ በሥዕልነት ፡ የሚከሥት ፡ ማለት ፡ ነው ። ላማርኛ ፡ ቋንቋ ፡ የጽሑፍም ፡ የንምርም ፡ መዝገበ ፡ ቃላት ፡ አንድጋ ፡ ይገኛል ፤ ጽሑፍ ፡ መዝገበ ፡ ቃላት ፥ የከሣቴ ፡ ብርሃን ፡ ተሰማ ፡ ሀብተ ፡ ሚካኤል ፡ ግጽው ፡ "ያማርኛ ፡ መዝገበ ፡ ቃላት" ፡ (1948 ፡ ዓ.ም.) ፡ በሚገባ ፡ ተለቅሞ ፡ ከራሱ ፡ ከዐውደ ፡ ቀለም ፡ "ያማርኛ ፡ መዝገበ ፡ ቃላት" ፡ ጋራ ፡ ተጣምሮ ፡ ባንድነት ፡ በጽሑፍ ፡ አቀጻጽ ፡ ቀርቧል ፤ ንምር ፡ መዝገበ ፡ ቃላት ፡ ደግሞ ፡ ያለቃ ፡ ደስታ ፡ ተክለ ፡ ወልድ ፡ "ዐዲስ ፡ ያማርኛ ፡ መዝገበ ፡ ቃላት" ፡ ሞላውን ፡ ተነምሮ ፥ የቃላት ፡ ፊቺዎቹ ፡ ከያንዳንዱ ፡ የዐውደ ፡ ቀለም ፡ ቃላት ፡ ዝርዝር ፡ ጋራ ፡ ተገናዝቦ ፡ ተቀምሯል ። የዐውደ ፡ ቀለም ፡ መዝገበ ፡ ቃላት ፡ መግበር ፡ እንግዲህ ፥ ላማርኛ ፡ ብቻ ፡ የሦስት ፡ መዛግብተ ፡ ቃላትን ፡ ዐቅም ፡ ባንድ ፡ ጊዜ ፡ ያስጨብጣል ። ወደ ፡ ፊት ፡ ደግሞ ፡ ይህኑ ፡ እያዘመነ ፣ እያዳበረና ፡ እያሟላ ፡ ይኼዳል ። በተለይ ፥ ባንድ ፡ ወገን ፥ ዘመናዊ ፡ ጥበብና ፡ ኪነት ፡ ያስገኟቸውን ፡ ዐዳዲስ ፡ የውጭ ፡ ቃላት ፡ በተቻለ ፡ ፍጥነት ፡ እየተረጐመ ፡ ያሟላል ። በሌላ ፡ ወገን ፥ የተረሱትን ፡ የግእዝና ፡ ያማርኛ ፡ ቃላት ፥ እንዲሁም ፡ የሌሎቹን ፡ የኢትዮጵያ ፡ ቋንቋዎች ፡ ቃላትን ፡ እንዳስፈላጊነታቸው ፡ በጥንቃቄ ፡ ላገልግሎት ፡ ያበቃል ። ለዘመናችን ፡ ወይም ፡ በጠቅላላው ፡ የማይገቡ ፥ በተለይ ፡ "ዘር" ፡ ነክ ፡ አባባሎችን ፡ በተገቢ ፡ እያስተካከለ ፡ ያዘጋጃል ።

ከዚህ ፡ ወዲያ ፥ ወረድ ፡ ብለን ፡ እንደምናየው ፥ የግእዝም ፣ የእንግሊዘኛና ፡ የፈረንሳይኛ ፡ መዛግብተ ፡ ቃላትም ፡ አሉት ።

ወደተነሣንበት ፡ እንመለስና ፥ "ዐላማ" ፡ ለሚለው ፡ ቃል ፥ ከሣቴ ፡ ብርሃን ፡ ተሰማ ፡ ሀብተ ፡ ሚካኤል ፡ ዘርዘር ፡ አድርገው ፡ 5 ፡ ፍቺዎችን ፡ ይሰጡናል ፤ አለቃ ፡ ደስታ ፡ ተክለ ፡ ወልድም ፥ በገጽ ፡ 930 ፡ 1ኛና ፡ 2ኛ ፡ ዐምድ ፡ ላይ ፥ በኹለት ፡ አፈታት ፡ ጠቅለል ፡ አድርገው ፡ ይፈቱልናል ። ለ"ዐላማ" ፡ በሞክሼነት ፡ ወይም ፡ በዝርዝርነት ፡ እምዝገበ ፡ ቃላት ፡ ውስጥ ፡ የሚገኙትን ፡ ቃላት ፡ ለመክሠት ፡ ደግሞ ፥ "ይፈታ ፡ (+)" ፡ የሚለውን ፡ ዝራር ፡ መጫን ፡ ይበቃል ። ግጻዌ ፡ 12 ፡ ይህኑ ፡ ያሳየናል ።

Figure 11: The AwdeQelem Dictionary interface is made up of three parts:

• the topmost part is the dialogue containing the fields and buttons to determine the particular script, language and dictionary to be used for the lookup of a word in the dictionary;

• the middle part is the dialogue containing the entry field of the word to be looked up in the dictionary and the output fields of the by-products of the lookup (derivatives/synonyms/homonyms) together with the associated buttons;

• finally, the bottom part is a dual display made up of two fields where the definitions from the dictionary/ies are output in text or graphic format. The top display is a text format field listing definitions in text format, which is the case for English (WordNet-English dictionary together with the English-Amharic AwdeQelem glossary), French (the MyThes French glossary) and Amharic (the Tesemma Habte Mikaél Gtsw Amharic dictionary together with the AwdeQelem

Figure 11: L'interface du dictionnaire AwdeQelem consiste en trois parties:

• la partie supérieure contient le dialogue [c'est-à-dire les champs et boutons] pour déterminer de manière spécifique l'écriture, la langue et le dictionnaire à utiliser pour obtenir la définition d'un mot;

• la partie médiale contient le dialogue pour le champ de saisie du mot à consulter dans le dictionnaire, ainsi que les champs de sortie des sous-produits de la consultation [dérivés/synonymes/homonymes] et les boutons correspondants;

• enfin, la partie inférieure consiste en un écran dual où les définitions des dictionnaires consultés sont affichées en format texte ou graphique, selon le cas. L'écran supérieur est en format texte listant les définitions de format texte, ce qui est le cas pour le français [le glossaire MyThes], l'anglais [le dictionnaire WordNet-anglais, ainsi que le glossaire AwdeQelem anglais-amharique], l'amharique [le dictionnaire amharique de Tesemma Habte Mikaél Gtsw, ainsi que le dictionnaire amharique de

Amharic dictionary); the lower display is an image format field displaying definitions in graphic format from the scanned page of the dictionary; this is the case for Amharic (scanned Amharic dictionary of Desta Tekle Weld) and G'z (scanned G'z dictionary of Kidane Weld Kflé). A dictionary for the Somali language is not yet available; but a small 1000-word glossary (Somali-Amharic-English-French) is now available (with plans for an additional 4000).

AwdeQelem]. L'écran inférieur est en format image, affichant les définitions contenues dans les pages numérisées de dictionnaires existants; c'est le cas pour l'amharique [dictionnaire amharique numérisé de Desta Tekle Weld], et pour le g'z [dictionnaire g'z numérisé de Kidane Weld Kflé]. Le dictionnaire pour la langue somali n'est pas encore disponible, mais un bref glossaire de 1000 mots [somali-amharique-français-anglais] est maintenant disponible [avec 4000 autres en préparation].



ግጻዌ ፡ 12 ፤ እንሆ ፡ "ይፈታ ፡ (+)" ፡ የሚለውን ፡ ዝራር ፡ ተጭነን ፡ "ዝርዝርና ፡ ሞክሼ" ፡ አተሠኘው ፡ ዐምድ ፡ ላይ ፡ ከ"ዐላማ" ፡ ጋራ ፡ ዝርዝሮቹ ፡ "ዐላሚ" ፣ "ዒላማ" ፣ "ዕልም" ፣ ወዘተ. ፤ እንዲሁም ፡ ሞክሼዎቹ ፡ "አላማ" ፣ "አላሚ" ፣ "አለማ" ፣ "አላመ" ፣ ወዘተ. ፥ ተደርድረው ፡ ይገኙልናል ።
ከዚህ ፡ ወዲያ ፥ የንምር ፡ መዝገበ ፡ ቃላቱን ፡ ገጾች ፡ አንድ ፡ ባንድ ፡ ለመክሠትም ፡ ኾነ ፡ አተለየ ፡ ንምር ፡ ገጽ ፡ ለመድረስ ፥ "+" ፡ የተሠኘውን ፡ መደመሪያ ፡ ዝራር ፡ መጫን ፡ ይበቃል ፤ ገጾቹን ፡ ተራ ፡ በተራ ፡ ይከሥትልናል ።
አኹን ፥ ወደ ፡ ጽሑፍ ፡ ማምረቻው ፡ እንመለስና ፥ የቀሩትን ፡ ዘዴዎቹን ፡ እንልመድ ።

Figure 12: For scanned pages, the "+" button is available to navigate through all

Figure 12: Concernant les pages numérisées, nous disposons du bouton "+" pour

the pages of the scanned dictionary by incrementing the page number, or to reach a particular page by incrementing from a starting page number. Let us now return to AwdeQelem text processor to discover its other functions.	naviguer à travers chacune des pages du dictionnaire numérisé en incrémentant le numéro de page, ou pour atteindre une page particulière en partant d'un numéro de page donné. Retournons maintenant vers le traitement de texte AwdeQelem pour découvrir ses autres fonctions.

2.4.4 ፤ የመዘርዘርና ፡ የማሞካሸት ፡ ዐቅም ፡ በዐውዴ ፡ ቀለም • derivational / inflectional and homonymic capabilities of AwdeQelem • aptitudes dérivationnelles / flexionnelles et homonymiques de AwdeQelem



ግጻዌ ፡ 13 ፤ እጽሑፍ ፡ ማምረቻው ፡ ተመልሰናል ። በቀኝ ፡ ዐምዱ ፡ ላይ ፡ "ይጋበስ" ፡ የተሰመየ ፡ ዝራር ፡ አለ ፤ ስንጠቀመው ፥ የ"ዓላማ"ን ፡ ዝርዝሮችና ፡ ሞክሼዎች ፡ ከነምእላዶቻቸው ፡ አግበስብሶ ፡ ያመጣልናል ። ምእላዶች ፡ በሥርና ፡ በጫፍ ፡ እቃሉ ፡ ግንድ ፡ ላይ ፡ የሚታከሉ ፡ እንደ ፡ ዐቢይ ፡ አገባብና ፡ እንደ ፡ ዐመሎች ፡ ያሉ ፡ ተጨማሪዎች ፡ ናቸው ። ለምሳሌ ፡

"ለ" ፡ "በ" ፡ "ከ" ፡ "እስከ" ፡ "እንደ" ፡ "ስለ" ፡ "የ" ፡ "የሚ" ፡ ወዘተ. ▶ በሥር ፡ የሚታከሉ ፡ ምእላዶች ፡ ናቸው ፡ (ም. ፦ ለዐላማ) ፤

"ን" ፡ "ም" ፡ "ና" ፡ "ማ" ፡ "ስ" ፡ "ሳ" ፡ "ኮ" ፡ "ው" ፡ "ቸው" ፡ "ዬ" ፡ ወዘተ. ▶ በጫፍ ፡ የሚታከሉ ፡ ምእላዶች ፡ ናቸው ፡ (ም. ፦ ዐላማዬ) ።

እነዚህ ፡ የሥርና ፡ የጫፍ ፡ ምእላዶች ፡ ባማርኛ ፡ ብዙ ፡ ናቸው ፤ በተለይ ፡ ደግሞ ፡ ርስ ፡ በራሳቸው ፡ ስለሚጠማመሩ ፡

(ም. ፥ በሥር ፦ "ስለ" + "አል" + "ተ" ▶ "ስላልተ" ፥

በጫፍ ፡ ደግሞ ፦ "ለት" + "እና" ▶ "ለትና" ፥

የሥሩና ፡ የጫፉ ፡ ምእላዶች ፡ ከ"ነገረ" ፡ ግንድ ፡ ጋራ ፡ ሲዋሐዱ ፡

"ስላልተነገረለትና" ፡ ያለውን ፡ ዝርዝር ፡ ቃል ፡ ይወልዱልናል ፤ በዚህ ፡ ዐይነት ፡ ዐማርኛ ፥ ካንድ ፡ ዘር ፡ ("ነገረ") ፥ እልፍ ፡ አእላፍ ፡ ቃላትን ፡ የሚወልድ ፡ ኀያል ፡ ቋንቋ ፡ ነው ፡ (እስቲ ፡ ይሀን ፡ አንድ ፡ ቃል ፡ "ስላልተነገረለትና"ን ፡ ወደ ፡ እንግሊዝኛ ፡ ባንድ ፡ ቃል ፡ ይተርጕሙት!) ።

በዚህና ፡ በሌሎቹም ፡ ያማርኛ ፡ የተለዩ ፡ ዐቅሞቹ ፡ ሙሉ ፡ በሙሉ ፡ እንድንጠቀምባቸው ፥ አስቀድመን ፡ የቃላቱን ፡ አጻጻፍና ፡ ትርጕሞቻቸውን ፡ ጠንቅቀን ፡ ማወቀ ፡ ይኖርብናል ። በዚህ ፡ ረገድ ፡ ዐውደ ፡ ቀለም ፡ ትልቁን ፡ ርዳታ ፡ ያበረክትልናል ።

መቼም ፡ ፊደል ፡ መጠንቀቅ ፡ እጅና ፡ እግሩ ፡ ተሰብሮ ፡ ነው ፡ እዘመናችን ፡ ጸሐፍት ፡ ዘንድ ፡ የገባው ፤ እስቲ ፡ አንድ ፡ አፍታ ፥ ከኢንተርኔት ፡ አልባሌ ፡ ጽሑፍ ፡ እንቅዳና ፥ እጽሑፍ ፡ ማምረቻችን ፡ ላይ ፡

ለጥፈነው ፥ የፈደልና ፡ የትርጉም ፡ አጠነቃቀቁን ፡ እንፈትሽበት ፡ (ግጻዌ ፡ 14) ።	
Figure 13: The derivation and inflection capabilities of AwdeQelem, particularly with regards to a highly generative and inflectional language like Amharic, offer a unique advantage. To illustrate this further, we copy and paste some text at random from an Amharic news website (almost all Ethiopian websites are notorious for their bad spelling) and try to edit the sample text to correct its orthography and clarify its wording, with the help of AwdeQelem.	Figure 13: Les capacités de dériuation et de flexion de AwdeQelem offrent, notamment pour des langues aussi hautement génératiues et flexionnelles que l'amharique, un auantage unique. Pour illustrer cela, nous allons copier et coller un texte pris au hasard dans un site Internet d'information en amharique [presque tous les sites éthiopiens sont notoires pour leur mauuaise orthographie], et nous allons essayer d'éditer le texte échantillon en corrigeant son orthographie et en clarifiant son énoncé, à l'aide de AwdeQelem.

2.4.5 ፤ በዐውደ ፡ ቀለም ፡ የታገዘ ፡ የጽሑፍ ፡ ዝግጅት • AwdeQelem assisted text edition • édition de texte assisté par AwdeQelem

ቋንቋ ፡ ኹሉ ፥ በተለይ ፡ ደግሞ ፡ ግእዝና ፡ ዐማርኛ ፥ የቃላት ፡ አጻጻፍ ፡ ሥርዐትና ፡ ደንብ ፡ አላቸው ፤ እነዚህንም ፡ ማክበር ፡ ብዙ ፡ ጥቅም ፡ አለው (40) ።

ለናሙና ፡ ያኽል ፥ ባጋጣሚ ፡ ካንድ ፡ የዜና ፡ መርበቢያ ፡ የተቀነጨበው ፡ የዜና ፡ ጽሑፍ ፥ መጋቢት ፡ 25 ፡ ቀን ፡ 2004 ፡ ዓ.ም. ፡ የወጣ ፡ ነው ። የያዘውን ፡ ጉዳይ ፡ ትችት ፡ ለሌሎች ፡ ትተን ፥ የፈደል ፣ ያገባብና ፡ የትርጉም ፡ አጠነቃቀቁን ፡ በዐውደ ፡ ቀለም ፡ ታግዘን ፡ እንደሚከተለው ፡ እንተንትነው ።

ጥቅሱ ፡ ይህ ፡ ነው ፡—

> *"የአውሮፓ ኅብረትና የምሥራቅ አፍሪካ የልማት በየነ መንግሥታት ድርጅት (ኢጋድ) በክልሉ ፀጥታና ደኅንነት ችግሮች ላይ በጋራ ለመሥራት ትናንት አዲስ አበባ ውስጥ ስምምነት አደረጉ፡ ፡ አውሮፓ ኅብረት በአፍሪካ ቀንድ ያሉት ግጭቶችንና ችግሮችን ለመፍታት በቅርቡ ባፀደቀው ‹‹ስትራቴጂክ ማዕቀፍ›› መሠረት ትናንት ከኢጋድ ጋር ከመከረ በኋላ ሁለቱም በጋራ ለመሥራት ለመጀመርያ ጊዜ የተስማሙ ሲሆን፣ በተለይ ሶማሊያ፣ ኤርትራና ሱዳን የውይይቱ ማዕከል ነበሩ፡ ፡" (በ A0 Desta Unicode ፡ ቅርጸት)*

> *"የአውሮፓ ኅብረትና የምሥራቅ አፍሪካ የልማት በየነ መንግሥታት ድርጅት (ኢጋድ) በክልሉ ፀጥታና ደኅንነት ችግሮች ላይ በጋራ ለመሥራት ትናንት አዲስ አበባ ውስጥ ስምምነት አደረጉ፡፡ አውሮፓ ኅብረት በአፍሪካ ቀንድ ያሉት ግጭቶችንና ችግሮችን ለመፍታት በቅርቡ ባፀደቀው «ስትራቴጂክ ማዕቀፍ» መሠረት ትናንት ከኢጋድ ጋር ከመከረ በኋላ ሁለቱም በጋራ ለመሥራት ለመጀመርያ ጊዜ የተስማሙ ሲሆን፣ በተለይ ሶማሊያ፣ ኤርትራና ሱዳን የውይይቱ ማዕከል ነበሩ፡፡" (በ Nyala፡ ቅርጸት)*

ቀዳሚ ፡ ትችት ፤

ደራሲው ፡—

1) በጽሑፉ ፡ ነቍጥን ፡ (ኹለት ፡ ነጥብን) ፡ " ፡ " ፡ አላሰፈረም ፤ የምርጫ ፡ ጉዳይ ፡ ነው ። (የኢትዮጵያ ፡ ጻሕፍ ፡ upper-case ና ፡ lower-case ፡ ብሎ ፡ ስለማይለይ ፥ የፊደላቱ ፡ መጠጋጋት ፡ የቃላትንም ፡ መጠጋጋት ፡ አስከትሎ ፡ ንባብን ፡ ከማስቸገርም ፡ የባሰ ፥ የትርጉም ፡ መፋለስን ፡ ሊያስከትል ፡ ስለሚችል ፥ «ነቍጥን ፡ ጨምራችኹ ፡ ጻፉ» ፡ ሲሉ ፡ ሊቃውንት ፡ ዘወትር ፡ ያሳስባሉ ። እውነትም ፥ እላይ ፡ በ A0 Desta Unicode ፡ ቅርጸት ፡ ዘርዘር ፡ ብሎ ፡ የሚታየን ፡ ጽሑፍ ፡ በ Nyala ፡ ቅርጸት ፡ ተጽፎ ፡ ስናየው ፥ የሊቃውንቱ ፡ ማስጠንቀቂያ ፡ ርግጥ ፡ ኾኖ ፡ እናገኘዋለን ። ቃላቱን ፡ በቅጽበት ፡

---

40 ወረድ ፡ ብሎ ፥ ምዕራፍ ፡ 3 ፡ የፈደል ፡ መጠንቀቅ ፡ ጉዳይ ፡ በዝርዝር ፡ ይተነትናል ።

ልንለያቸው ፡ ሲገባ ፤ ፊደላቱ ፡ ከመጠጋጋታቸው ፡ የተነሣ ፥ ቃላቱን ፡ መለየቱ ፡ አዳጋች ፡ ኾኗል ።
በ Nyala ፡ ቅርጸት ፡ የተጻፈውን ፡ ጽሑፍ ፡ ኹለት ፡ ነጥብ ፡ ብንጨምርበትማ ፥ ፈጽሞ ፡ አስቀያሚ ፡ ይኾናል ።

"የአውሮፓ፡ኅብረትና፡የምሥራቅ፡አፍሪካ፡የልማት፡በየነ፡መንግሥታት፡ድርጅት፡(ኢጋድ)፡በክልሉ፡ፀጥታና፡ደኅንነት፡ችግሮች፡ላይ፡በጋራ፡ለመሥራት፡ትናንት፡አዲስ፡አበባ፡ውስጥ፡ስምምነት፡አደረጉ፡፡አውሮፓ፡ኅብረት፡በአፍሪካ፡ቀንድ፡ያሉት፡ግጭቶችንና፡ችግሮችን፡ለመፍታት፡በቅርቡ፡ባፀደቀው፡«ስትራቴጂክ፡ማዕቀፍ»፡መሠረት፡ትናንት፡ከኢጋድ፡ጋር፡ከመከረ፡በኋላ፡ሁለቱም፡በጋራ፡ለመሥራት፡ለመጀመርያ፡ጊዜ፡የተስማሙ፡ሲሆን፣ በተለይ፡ሶማሊያ፣ ኤርትራና፡ሱዳን፡የውይይቱ፡ማዕከል፡ነበሩ፡፡" (በ Nyala፡ ቅርጸት)

የ Nyala ፡ ቀራጮች ፡ ለምን ፡ ዐላማ ፡ ይህን ፡ አደረጉ ፧ ራሱን ፡ የቻለ ፡ ጥያቄ ፡ ነው ።

2) አራት ፡ ነጥብን ፡ (።) ፡ ለመጻፍ ፡ ኹለት ፡ ጊዜ ፡ ነቍጥን ፡ (" ፡ ፡ ") ፡ ጽፏል ፤ ምናልባት ፡ በመፍቻ–ገበታው ፡ አራት ፡ ነጥብ ፡ እንዴት ፡ እንደሚመታ ፡ ደራሲው ፡ ስላላወቀ ፡ ይኾናል ። እዋዜማ ፡ ሥርዐት ፡ መመሪያ ፡ ላይ ፡ ዘዴውን ፡ በቀላሉ ፡ ሊያገኘው ፡ ይችላል ።
3) ነጠላ ፡ ሠረዝ ፡ (" ፥ ") ፡ እና ፡ ንኡስ ፡ ሠረዝ ፡ (" ፣ ") ፥ መልካቸው ፡ ኹለት ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ኹሉ ፥ ሚያቸውም ፡ ኹለት ፡ ነው ። ኹለቱም ፡ አረፍተ ፡ ነገርንና ፡ ፈርጀ ፡ ነገርን ፡ በማይጫፈሩ ፡ ዐጫጭር ፡ ቃሎች ፡ ይከፋፍላሉ ፤ ከንኡስ ፡ ሠረዝም ፡ ነጠላ ፡ ሠረዝ ፡ ይከፋፍላል ። ለምሳሌ ፦ *ቃልን ፡ ከቃል ፥ በየንባቡና ፡ በየስልቱ ፣ በየብልቱ ፡ ለይተው ፣ ነጥለው ፣ ዘርዝረው ፣ ደምረው ፥ አንድ ፡ ፈርጅ ፡ አድርገው ፡ የሚያሳዩ ፡ የቃል ፡ ምልክቶች ፡ አራት ፡ ናቸው ።* ([41])
4) "ስትራቴጂክ" ፡ የሚል ፡ የፈረንጅ ፡ ቃል ፡ እናያለን ፤ ዐማርኛው ፡ ምን ፡ ይኾን?
5) "አፍሪካ" ፡ ነው ፡ ወይስ ፡ "አፍሪቃ" ፡ ሊባል ፡ የሚገባው?
6) "በየነ ፡ መንግሥታት" ፡ ምን ፡ ማለት ፡ ይኾን?
7) "ማዕቀፍ" ፡ ሲሉ ፡ ምን ፡ ለማለት ፡ ነው?
8) የፊደሉስ ፡ አጠነቃቀቅ ፡ እንዴት ፡ ነው? "ፀጥታ" ፡ ነው ፡ የሚባል ፥ ወይስ ፡ "ጸጥታ" ፥ ወይስ ፡ ደግሞ ፡ "ሰጥታ"?

አጠገባችን ፡ ባለሚያን ፡ ይዘን ፡ ካልኾነ ፡ በቀር ፡ ብቻችንን ፡ ለነዚህ ፡ ኹሉ ፡ ጥያቄዎች ፡ መልሱን ፡ ማግኘቱ ፡ ለጥቂቶቻችን ፡ ሳይቸግረን ፡ አይቀርም ። "እዚህ ፡ ላይ ፡ ዐውደ ፡ ቀለም ፡ ምን ፡ ያኽል ፡ ይረዳናል?" ፡ ብሎ ፡ ለጠየቀ ፥ መልሱ ፦ እጅጉን! ፡ ነው ።

<u>በዐውደ ፡ ቀለም ፡ የታገዘ ፡ ዝርዝር ፡ ትችትና ፡ ዕርማት ።</u>

እላይ ፡ የጠቀስነውን ፡ ጽሑፍ ፡ እስቲ ፡ በዐውደ ፡ ቀለም ፡ የጽሑፍ ፡ ማምረቻ ፡ እናኺደው ። (ግጻዌ ፡ 14)

41 **ኪዳነ ፡ ወልድ ፡ ክፍሌ** ፡ (አለቃ) ፤ *መጽሐፈ ፡ ሰዋስው ፡ ወግስ ፡ ወመዝገበ ፡ ቃላት ፡ ሐዲስ ።* ዐዲስ ፡ አበባ ፥ አርቲስቲክ ፡ ማተሚያ ፡ ቤት ፥ 1948 ፡ ዓ.ም. ፤ ገጽ ፡ 44 ።



ግጸዌ ፡ 14 ፤ ጽሑፉ ፡ ገና ፡ በሰነድ ፡ ያልተመዘገበ ፡ በመኾኑ ፥ ይዘቱ ፡ በቀኙ ፡ ዐምድ ፡ ላይ ፡ አልተተረረልንም ። ይህኑ ፡ ለማድረግ ፥ "ይተረር" ፡ የሚለውን ፡ ዝራር ፡ እንጠቍመው ።

Figure 14: As the text has not yet been saved in a file, its word-list does not yet automatically appear in the "word-list" column. Even so, pressing the "list" button achieves the same result.

Figure 14: Comme le texte n'a pas encore été sauvegardé, sa liste de mot n'apparait pas automatiquement dans la colonne "liste de mots". Néanmoins, en appuyant le bouton "lister", on obtient le même résultat.



ግጸዌ ፡ 15 ፤ ጽሑፉ ፡ ዐጪር ፡ በመኾኑ ፥ ቃላቱን ፡ አንድ ፡ ባንድ ፡ ልናርማቸው ፡ እንችላለን ፤ ይህን ፡ ለማድረግም ፥ ለተመረጠው ፡ ቃል ፡ "ይጣራ" ፡ የሚለውን ፡ ዝራር ፡ እንጠቀማለን ። ነገር ፡ ግን ፥ በዚህ ፡ ረገድ ፡ የጠቅላላውን ፡ ጽሑፍ ፡ የፊደል ፡ ዕርማት ፡ አንድጋ ፡ በዐውደ ፡ ቀለም ፡ ልናከናውነው ፡ ስለምንችል ፥ ጊዜ ፡ እናተርፋለን ። እቃል ፡ መሳተፊያው ፡ ላይ ፡ "ኹሉም ፡ ይጣራ" ፡ የሚለውን ፡ ዝራር ፡ መጠቈም ፡ ይበቃል ። (ግጸዌ ፡ 16)

Figure 15: The text being short, the spelling correction ([42]) could be done word by word by pressing for each selected word the "verify" button. However, AwdeQelem offers the possibility of automatically checking and highlighting spelling errors or ambiguities for the whole text, saving us even more time. To that effect, we press the "verify all" button, as shown in figure 16.
(NB: once again, in AwdeQelem v.1, the colour coded spelling error or ambiguity highlighting facility is only available for Amharic)

Figure 15: Le texte étant court, on peut se contenter de vérifier l'orthographie ([43]) de chacun de ses mots en appuyant le bouton "vérifier" pour chaque mot sélectionné. Cependant, AwdeQelem nous offre la possibilité de corriger et de souligner automatiquement les erreurs ou ambiguïtés du texte en entier; ce qui nous économise encore plus de temps. Pour ce faire, il nous suffit d'appuyer le bouton "tout vérifier", comme nous le montre la figure 16.
(NB: encore une fois, dans AwdeQelem v.1, la notification par couleur des erreurs ou ambiguïtés orthographiques n'est possible que pour l'amharique)

---

42 cf. Chapter 3, below, covers in detail G'z and Amharic spelling, syntactic and semantic correction (taken from *"Appendix 6: On G'z and Amharic Spelling"* of Wazéma System User's Manual, (p.88)). In its present form, the chapter is in Amharic only.

43 cf. Le chapitre 3, ci-dessous, présente en détail les aspects de la correction orthographique, syntactique et sémantique en g'z et amharique (tiré de l'*"Appendice 6: sur l'orthographie g'z et amharique"* du manuel utilisateur de Wazéma Système, (p.88)). Dans sa forme présente, le chapitre est rédigé uniquement en amharique.

ከግእዝ ፡ ወደ ፡ ዐማርኛ ፡ የፊደል ፡ አወራረስ ፡ ሥርዐት ፡ ዐጪር ፡ መግለጫ

G'z to Amharic letter inheritance system in brief • système de succession de lettres du g'z à l'amharique en bref

(ሀ) ▶ (አ)	(ሐ ፣ ኀ) ▶ (ዐ)	(ደ) ▶ (ጀ) (ዘ) ▶ (ዠ)	(ከ) ▶ (ኸ)	(ጸ ፣ ፀ) ▶ (ጠ ፣ ጨ)
ሀለወ ▶ አለ	ሐሰበ ▶ ዐሰበ	ዐዋድ ▶ ዐዋጅ	ክልኤት ▶ ኹለት	ነጸፈ ▶ ነጠፈ
ሀይመነ ▶ አመነ	ኀየለ ▶ ዐየለ	ዘገነ ▶ ዠገነ	በላእኩ ▶ በላኹ	ጼው ▶ ጨው
ሃይማኖት ▶ እምነት	ሐቃፊ ▶ ዐቃፊ	ዘመረ ▶ ዠመረ	ኩነት ▶ ኹነት	ፀር ▶ ጠር



ግጻዌ ፡ 16 ፤ የቃላቱ ፡ ተራ ፡ ዐምድ ፡ ቃላቱን ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ቀለማት ፡ አመልክቷቸው ፡ እናያለን ። እያንዳንዱ ፡ ቀለም ፡ ትርጕም ፡ አለው ።

- ነጭ ፤ የቃሉን ፡ ባዕድነት ፡ ወይም ፡ ግዑዝነት ፡ ያመለክታል ። ባዕዳን ፡ ቃላት ፡ በባዕድ ፡ ጻሕፍ ፡ የተጻፉት ፡ ናቸው ። ግዑዝ ፡ ቃላት ፡ ብዙውን ፡ ጊዜ ፡ በኹሉም ፡ ጻሕፎች ፡ የሚገኙ ፡ አኃዞች ፡ (0 ፡ 1 ፡ 2 ፡ ...) ፡ እና ፡ አህጉራውያን ፡ ምልክቶች ፡ (−*/+%${&) ፡ ናቸው ።
- አረንጓዴ ፤ እመዝገበ ፡ ቃላት ፡ ውስጥ ፡ ያለ ፡ ቃልን ፡ ያመለክታል ፤ ባረንጓዴ ፡ ቀለም ፡ የተመለከተ ፡ ቃል ፡ ጽሕፈቱ ፡ ጥንቁቅ ፡ ነው ፡ ማለትም ፡ ነው ። እያዝነው ፡ ጽሑፍ ፡ ወሰጥ ፡ "መንግሥታት" ፡ ባረንጓዴ ፡ ቀለም ፡ ስለተመለከተ ፡ በትኽክለኛ ፡ አጻጻፉ ፡ ተጽፏል ፡ ማለት ፡ ነው ።
- ደማቅ ፡ አረንጓዴ ፤ እንደቀደመው ፡ አረንጓዴ ፥ ቃሉ ፡ እመዝገበ ፡ ቃላት ፡ ውስጥ ፡ ያለ ፡ ኾኖ ፥ ሞክሼ ፡ ቃል ፡ አለው ፡ ማለት ፡ ነው ። ለምሳሌ ፥ "ለመሥራት" ፡ የሚለው ፡ ቃል ፡ በደማቅ ፡ አረንጓዴ ፡ ተመልክቷል ፥ ምክንያቱም ፥ "መሥራት" ፡ እና ፡ "መስራት" ፡ ሞክሼ ፡ ናቸው ። "መሥራት" ፡ ከግእዙ ፡ "ሥርዐ" ፡ (ሥራ ፥ አበጀ) ፡ ካለው ፡ ይገሰሳል ፤ "መስራት" ፡ ደግሞ ፡ ከግእዙ ፡ "ሰርሐ" ፡ (ሰራ ፥

ጣረ ፣ ተሸከመ ፣ ደከመ) ፡ ካለው ፡ ይገሰሳል ። ስለዚህ ፣ ጸሓፊ ፣ "መሥራት" ፡ ብሎ ፡ ሲጽፍ ፣ የትኛውን ፡ መ(ሥ/ስ)ራት ፡ እንደ ፡ ፈለገ ፡ ለመለየት ፡ እንዲረዳው ፡ ተብሎ ፡ ነው ።

- ብጫ ፤ ቃሉ ፡ ዝርዝር ፡ መኾኑን ፡ ያመለክታል ። ለምሳሌ ፣ "ለመፍታት" ፡ የሚለው ፡ ቃል ፡ በብጫ ፡ ተመልክቷል ፤ ዝርዝር ፡ የኾነበትም ፡ ምክንያት ፡ "መፍታት" ፡ በስምንት ፡ እመዝገበ ፡ ቃላቱ ፡ ውስጥ ፡ ተመዝግቦ ፡ "ለ" ፡ በምእላድነት ፡ ስለ ፡ ታከለበት ፣ በ"ለ" ፡ ተዘርዝሯልና ፡ ነው ። እንዲሁ ፣ "ሶማሊያ" ፡ የሚለው ፡ ቃል ፡ በብጫ ፡ ተመልክቷል ፣ ይህውም (44) ፡ እመዝገበ ፡ ቃላቱ ፡ ውስጥ ፡ የተመዘገበው ፡ "ሶማልያ" ፡ ስለ ፡ ኾነ ፣ "ሶማሊያ" ፡ በዝርዝርነት ፡ ተመልክቷል ። ዐውደ ፡ ቀለም ፡ ዝርዝርነቱን ፡ ካመለከተለት ፣ የጽሑፉ ፡ አዘጋጅ ፡ "ሶማልያ" ፡ ብሎ ፡ አስተካክሎ ፡ ለመጻፍ ፡ በቂ ፡ መረጃን ፡ አግኝቷል ፡ ማለት ፡ ነው ።
- ግራጫ ፤ አሻሚ ፡ አጻጻፍን ፡ ያመለክታል ። ለምሳሌ ፡ "ሁለቱም" ፡ የሚለው ፡ ቃል ፣ በግራጫ ፡ ቀለም ፡ ተመልክቷል ። አሻሚነቱ ፡ ለ"ኹለት" ፡ እና ፡ ለ"ሃሌታ" ፡ ሞክሼና ፡ ዝርዝር ፡ በመኾኑ ፡ ነው ። ቃሉን ፡ ለይቶ ፡ ለማጣራት ፣ አዘጋጁ ፡ "ይጣራ" ፡ የሚለውን ፡ ዝራር ፡ በመጠቈም ፣ ማማረጫ ፡ ቃላቱን ፡ አግኝቶ ፡ ትኽክሉን ፡ ቃል ፡ መርጦ ፡ ለማረም ፡ ያመቸዋል ። "ሁለቱም" ፡ ለሚለው ፡ ቃል ፡ እንግዲህ ፣ ከ"ሃሌታ" ፡ ይልቅ ፡ "ኹለት" ፡ ተስማሚው ፡ ስለሚኾን ፣ "ኹለቱም" ፡ ተብሎ ፡ ይታረማል ፡ ማለት ፡ ነው ። ሌሎች ፡ ተመሳሳይ ፡ አሻሚ ፡ አጻጻፎች ፡ አሉ ፤ ለምሳሌ ፣ "ቁረጡ" ፡ ለ"ቈረጠ" ፡ እና ፡ ለ"ቀረጠ" ፡ ዝርዝር ፡ ቢኾንም ፣ በርባታው ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ "ቍረጡ" ፡ እንጂ ፡ "ቁረጡ" ፡ ስሕተት ፡ ስለ ፡ ኾነ ፣ ዕርማት ፡ እንደሚያሻው ፡ ለማመልከት ፡ ሲባል ፡ በግራጫ ፡ ቀለም ፡ ይመለከታል ። ባንዳንድ ፡ ለመለየት ፡ በሚያስቸግር ፡ ኹኔታም ፣ ትኽክለኛው ፡ አጻጻፍም ፡ እንኳ ፣ ኾነ ፡ ተብሎ ፣ ባሻሚነት ፡ ተመድቦ ፡ ሊታይ ፡ ይችላል ፤ የመሳሊያው ፡ ውስንነት ፡ ያመጣው ፡ ስለ ፡ ኾነ ፣ በእየክለሳው ፡ እየተሻሻለ ፡ ይኼዳል ። በዚህ ፡ ረገድ ፣ ክለሳ ፡ 1.3 ፡ የቀደመውን ፡ ክለሳ ፡ በመጠኑ ፡ አሻሽሎታል ።
- ቀይ ፤ እመዝገበ ፡ ቃላት ፡ ውስጥ ፡ ያልተገኘና ፣ በዝርዝርነት ፡ ወይ ፡ በሞክሼነት ፡ ያልተመደበ ፡ ቃል ፣ ወይም ፡ ስሕተትነቱ ፡ ጒልሕ ፡ የኾነ ፡ ቃል ፡ ማለት ፡ ነው ። ለምሳሌ ፣ "በአፍሪካ" ፡ የሚለው ፡ ቃል ፡ እመዝገበ ፡ ቃላት ፡ ውስጥ ፡ "አፍሪቃ" ፡ ተብሎ ፡ እንጂ ፡ "አፍሪካ" ፡ ተብሎ ፡ ስለማይገኝ ፣ የሌላም ፡ ቃል ፡ ዝርዝር ፡ ወይም ፡ ሞክሼ ፡ ስላልኾነ ፣ ስሑት ፡ አጻጻፍ ፡ ነው ፡ ለማለት ፡ በቀይ ፡ ተመልክቷል ። አኹንም ፣ አዘጋጁ ፣ "አፍሪካ" ፡ ለሚለው ፡ ቃል ፡ "ይጣራ"ን ፡ ጠቍሞ ፡ ስሕተቱን ፡ ሊያርም ፡ ይችላል ።
- ወዘተ.

Figure 16: The colour codes that highlight the "word-list" column have the following meanings:

- white: indicates the foreign nature or the neutrality of the word vis-à-vis the particular script or language [ex.: numerals, international signs, symbols or markings shared by all or most scripts, etc.];
- green: correctly spelt word [i.e.: word contained in dictionary];
- dark-green: correctly spelt word with homonym [ex.: ሠሁ and ስሁ];
- yellow: word derived from a root word [ex.: ቤት‣ቤቱ];

Figure 16: Les codes couleurs signalisant la colonne "liste de mots" ont les significations suivantes:

- blanche: indiquant le caractère étranger ou la neutralité du mot vis-à-vis de l'écriture ou de la langue [ex.: les chiffres, les signes et autres symboles internationaux partagés par la plupart des écritures ou langues, etc.];
- verte: mot correctement épelé [ex.: mot figurant dans le dictionnaire];
- verte foncée: mot correctement épelé ayant cependant un ou plusieurs homonyme[s] [ex.: ሠሁ et ስሁ];
- jaune: mot dérivé d'un radical [ex.: ቤት ‣

44 "ህ" ፡ የሀሌታው ፡ ሀ ፡ "ኸ" ፡ ድምፅ ፡ ነው ። በተለመደው ፡ ፊደል ፡ ውስጥ ፡ የለም ፤ ነገር ፡ ግን ፣ "ይሀ" ፡ የሚለው ፡ ቃል ፡ ተዘርዝሮ ፡ "ይኸውም" ፡ ሲባል ፣ አለቦታው ፡ "ኸ" ፡ መግባቱን ፡ በመገንዘብ ፤ እንዲሁም ፣ እንደ ፡ ትግርኛ ፡ ላሉ ፡ ቋንቋዎች ፡ ተፈላጊነቱን ፡ በማወቅ ፡ (ም. ፡ ባማርኛ ፡ "በረሄ" ፡ የተባለው ፡ የተጸውዖ ፡ ስም ፡ በትግርኛ ፡ "በረህ" ፡ ነው ፣ እንዲሁም ፡ "አብረህት" ፣ ... ፤ "በረኸ" ፡ ብሎ ፡ መጻፉ ፡ ድምፅን ፡ ይቀይራል ፣ አንቀጽንም ፡ ከ"በርሀ" ፡ (በራ) ፡ ወደ ፡ "በረከ" ፡ (ተንበረከከ) ፡ ይለውጣል) ፣ በዘመናችን ፡ የነበሩ ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ሊቃውንት ፡ ያመለከቱትን ፡ ተጨማሪ ፡ "ህ" ፡ ፊደል ፡ በዋዜማ ፡ ቅርጸቶች ፡ አክዬዋለኹ ። ኾኖም ፡ በሀገራዊ ፡ ሥልጣን ፡ እስከሚጸድቅ ፡ ድረስ ፡ በሐሳብ ፡ ደረጃ ፡ የቀረበ ፡ መኾኑን ፡ በትሕትና ፡ አሳስባለኹ ።

ሙሉ ፡ ሐተታውን ፡ እዋዜማ ፡ ሥርዐት ፡ መመሪያ ፡ ውስጥ ፡ ያገኟል ።

- grey: ambiguity due to homonymy [ex.: ኣዲስ ▸ ዐዲስ / አዲስ]
- red: incorrectly spelt or unknown word [ex.: ተፅዐኖ ▸ ተጽዕኖ].

- gris: ambiguïté due à une homonymie [ex.: ኣዲስ ▸ ዐዲስ / አዲስ];
- rouge: mot incorrectement épelé ou inconnu [ex.: ተፅዐኖ ▸ ተጽዕኖ].

እንግዲህ ፡ ባንድ ፡ አፍታ ፡ ጽሑፉ ፡ በሙሉ ፡ በፊደል ፡ አጠነቃቀቁ ፡ ከተመለከተልን ፡ ዘንዳ ፥ ዕርማቱን ፡ በመዝገበ ፡ ቃላቱ ፡ ፊደል ፡ ከትርጉም ፡ እያጣራን ፡ እናቃናዋለን ። የመዝገበ ፡ ቃላቱ ፡ ጥቅም ፡ እዚህ ፡ ላይ ፡ ነው ። ቃሉ ፡ ባረንጓዴ ፡ መመልከቱ ፡ ያጻጻፍ ፡ ትኽክልነቱን ፡ እንጂ ፡ ለጽሑፉ ፡ የትርጉም ፡ ትኽክልነቱን ፡ አያመለክተንም ። ለምሳሌ ፡ "ማዕቀፍ" ፡ የሚለው ፡ ቃል ፡ ባረንጓዴ ፡ ስለተመለከተ ፥ አጻጻፉ ፡ ትኽክል ፡ መኾኑን ፡ አግኝተናል ፤ ይህ ፡ አጻጻፍ ፡ ግን ፡ ከተፈለገው ፡ ትርጉም ፡ ጋራ ፡ ይኼዳልን? ፡ የጽሑፉ ፡ ደራሲ ፡ "ስትራቴጂክ ፡ ማዕቀፍ" ፡ ሲል ፥ በእንግሊዝኛ ፡ "strategic framework" ፡ ያሉትን ፡ ከሞላ ፡ ጐደል ፡ የተረጐመ ፡ ይመስላል ። ታዲያ ፥ "strategic"ን ፡ "የዐቅድ" ፡ ወይም ፡ "ዐቅዳዊ" ፡ ሊለው ፡ ይችል ፡ ነበር ፤ ለዚህም ፡ ግጻዌ ፡ 17 ፡ እና ፡ ግጻዌ ፡ 18 ፡ እንደሚያሳዩን ፥ ለምዕራባዊ ፡ ጻሕፍና ፡ ለእንግሊዝኛ ፡ ቋንቋ ፡ "ይተርጐም" ፡ የሚለውን ፡ ዝራር ፡ ተጭነን ፡ የቃሉን ፡ ያማርኛና ፡ የፈረንሳይኛ ፡ ትርጉሞች (45) ፥ ከነአምሳያዎቻቸው ፡ እናገኛለን ። አለዚያም ፥ የእንግሊዝኛ ፡ ፍቺውን ፡ በዝርዝር ፡ ለማግኘት ፡ ብንፈልግ ፥ ግጻዌ ፡ 19 ፡ እንደሚያሳየን ፥ "ይፈታ" ፡ የሚለውን ፡ ዝራር ፡ ተጭነን ፡ የእንግሊዝኛውን ፡ መዝገበ ፡ ቃላት ፡ በማየት ፡ ያማርኛ ፡ ትርጉሙንም ፡ እናገኝበታለን ።



ግጻዌ ፡ 17 ፤ "ስትራቴጂክ" ፡ የሚለውን ፡ ቃል ፡ በእንግሊዝኛ ፡ አጻጻፉ ፡ ማማረጫ ፡ መስክ ፡ ላይ ፡ አመልክተን ፥ ጻሕፉንም ፡ ምዕራባዊ ፡ አድርገን ፥ ቋንቋውንም ፡ እንግሊዝኛ ፡ ብለን ፥ "ይተርጐም"ን ፡

45 ክለሳ ፡ 1.2 ፡ ግእዝንና ፡ ሶማልኛን ፡ አክሏል ፤ የሚተራጐሙት ፡ ቃላት ፡ ብዛት ፡ ለጊዜው ፡ አነስተኛ ፡ ነው ።

ጠቅመን ፡ እግርጌ ፥ "ትርጉሞች" ፡ እተሠኘው ፡ መስክ ፡ ላይ ፡ የእንግሊዝኛው ፣ ያማርኛው ፣ የፈረንሳይኛው ፡ ትርጉሞችና ፡ አምሳያዎቻቸው ፡ በመሥመር ፡ ተደራርበውና ፡ በረድፍ ፡ ተነጻጽረው ፡ ይቀርቡልናል ። "strategic" ፡ "ቅጽል" ፡ እንደ ፡ መኾኑ ፡ መጠን ፥ ላማርኛው ፡ በ"ቅ" ፡ ረድፍ ፥ ለእንግሊዝኛውና ፡ ለፈረንሳይኛው ፡ ደግም ፡ ቅጽል ፡ "adjective" ፡ እንደ ፡ መኾኑ ፡ መጠን ፥ በ"a" ፡ ረድፍ ፡ ተረድፎ ፡ ይቀርብልናል ። ("ስ" ፡ ስምን ፡ ያመለክታል ፥ "አ" ፡ አንቀጽን ፥ "ቅ" ፡ ቅጽልን ፡ ያመለክታል ፥ "ገ" ፡ ንኡስ ፡ አገባብን ፡ ወይም ፡ ተውላጠ ፡ ግስን ፡ ያመለክታል ፡ (የእንግሊዝኛ ፡ አገባብ ፡ በ"adverb" ፡ ረድፍ ፡ የረደፋቸው ፡ ቃላት ፡ ኹሉ ፡ ባማርኛ ፡ ብዙውን ፡ ጊዜ ፡ በዚሁ ፡ ረድፍ ፡ አይገኙምና ፥ ለስሙ ፡ በ"ገ" ፡ ረድፍ ፡ ቢረደፉም ፡ ቅሉ ፥ ከ WordNet ፡ ለመስተካከል ፡ ተብሎ ፡ እንጂ ፡ ተገቢ ፡ ኾኖ ፡ አይደለም ። እንደዚሁ ፥ ዐቢይ/ደቂቅ ፡ አገባብን ፡ WordNet ፡ ገና ፡ ስላላከላቸው ፥ ለጊዜው ፡ አይተራጎሙም) ። እያንዳንዱ ፡ መሥመር ፡ እማማረጫው ፡ መስክ ፡ ላይ ፡ ሊተረርልን ፡ ይችላል ፤ የዚህንም ፡ አደራረግ ፡ ግጻዌ ፡ 18 ፡ ያሳየናል ።

[ማስጠንቀቂያ ፤ የፈረንሳይኛው ፡ መተርጐሚያ ፡ መዝገበ ፡ ቃላት ፡ የተዘጋጀው ፡ WOLF ፡ ከተባለው ፡ ነጻ ፡ WordNet-በቀል ፡ ንምራዊ ፡ መዝገበ ፡ ቃላት ፡ ነው ፤ መዝገበ ፡ ቃላቱን ፡ አሰናድቶ ፡ በኢንተርኔት ፡ አማካይነት ፡ ለኹላችንም ፡ በነጻ ፡ ያበረከተልን ፡ በኗ ፡ ሳጎ ፡ (Benoît Sagot) ፡ የሥራውን ፡ ጉድለቶች ፡ ዐብሮ ፡ ገልጾልናል ። WOLF ፡ ያለቀ ፣ የተከናወነ ፡ ሥራ ፡ አይደለም ፤ ገና ፡ ብዙ ፡ የዕርማት ፡ ሥራ ፡ ይቀረዋልና ፥ ዐልፎ ፡ ዐልፎ ፡ ስሕተት ፡ ይኖረዋል ። ጥቂቶቹን ፡ በበኩሌ ፡ ዐርሜያቸዋለኹ ፤ ለምሳሌ ፥ ካ 16100 ፡ አንቀጾች ፡ 3617 ቱ ፡ (20%) ፡ ስሕተት ፡ ኾነው ፡ ተወግደዋል ፤ በስሞችና ፡ በቅጽሎችም ፡ ተመሳሳይ ፡ የስሕተት ፡ መጠን ፡ ሊኖር ፡ ይችላልና ፥ መጠንቀቁ ፡ ይገባል ። ወደ ፡ ፊት ፡ የሚከታተሉት ፡ የዐውደ ፡ ቀለም ፡ ክለሳዎች ፡ ጉድለቶቹን ፡ እያሟሉ ፡ ይኼዳሉ ፤ ይህንም ፡ ሲፈጽሙ ፥ ከዕውቅ ፡ የፈረንሳይኛ ፡ ቋንቋ ፡ ተቋማት ፡ ይፋ ፡ የወጡትን ፡ መመሪያዎች ፡ ያከብራል ።]

Figure 17፡ "ስትራቴጂክ" is the transliteration of the English word "strategic". To translate it into Amharic, we need only enter it into the alternatives field ("by"), set the script to "Western Script", and the language to "English"; then press the "translate" button on the right of the screen. The translations of the word in all its senses, together with their synonyms are then listed in the lowermost "translations" field, in all the languages available. "strategic" being itself an adjective with two senses, the "a" abbreviation precedes both its translations ("n" stands for "noun", "v" stands for "verb", "a" stands for "adjective", "r" stands for "adverb").

These different translations and their synonyms can in turn be listed in the alternatives field, to be used for replacing a given word in the body of the text, or for further look up in the dictionary, as we will see now.

[Warning፡ the WordNet-French alternative dictionary is as provided by Benoît Sagot's WOLF free-ware digital resource. As its

Figure 17፡ "ስትራቴጂክ" est la transcription du mot anglais "strategic". Pour le traduire en amharique, il nous suffit d'inscrire le mot anglais dans le champs des alternatives "par", en sélectionnant "écriture occidentale" pour l'écriture, et "anglais" pour la langue, avant de presser le bouton "traduire" situé à droite. Les traductions du mots dans toutes ses acceptions ainsi que les synonymes correspondants, dans chacune des langues disponibles, sont alors listées dans cet ordre, en bas dans le champ intitulé "traductions", avec chaque catégorie grammaticale indiquée par une abréviation ["n" pour "nom", "v" pour "verbe", "a" pour "adjectif", "r" pour "adverbe"]. "stratégique" étant un adjectif, avec deux acceptions, il sera dans les deux cas précédé de l'indicateur "a".

Ces différentes traductions ainsi que leurs synonymes peuvent, à leur tour, être listés dans le champ des alternatives, où ils pourront servir pour remplacer un autre mot dans le texte principal, ou pour faire l'objet d'une consultation individuelle dans le dictionnaire, comme nous allons le voir

author advised us, WOLF is still a "works in progress"; it is incomplete and sometimes even erroneous. Out of 16100 verbs, I have discarded 3617 (20%) as they were not verbs at all; the same proportion of mistakes could affect nouns and adjectives. It is therefore, the user's responsibility to use the whole thing with caution. Future versions of AwdeQelem will hopefully correct these misgivings. In so doing, it shall follow scrupulously the public guidelines of official institutions of the French language.]

maintenant.

[Avertissement: le dictionnaire alternatif au WordNet-français est la ressource en libre que Benoît Sagot nous a dotée sous la forme du dictionnaire numérique WOLF, tout en soulignant son caractère incomplet. WOLF est incomplet, parfois même erroné: sur 16100 verbes, par exemple, j'ai dû rejeter 3617 qui n'en étaient pas; des proportions similaires d'erreurs pourraient affecter les noms et les adjectives. Il revient donc à l'utilisateur de procéder avec caution. Les versions à venir de AwdeQelem tâcheront de rectifier cette situation. En ce sens, les recommandations publiques des organismes officiels de la langue françaises seront aussi respectées scrupuleusement.]



ግጻዌ ፡ 18 ፤ እግርጌ ፡ መስክ ፡ ላይ ፡ በመሥመር ፡ ከተረደፉልን ፡ ትርጉሞች ፡ መኻከል ፥ "ዐማርኛ" ፡ የሚለውን ፡ መደዳ ፡ በመጠቈሚያው ፡ የግራ ፡ ዝራር ፡ ለይተን ፡ መርጠን ፥ ከዚያ ፥ የተመረጠውን ፡ መሥመር ፡ በመጠቈሚያው ፡ የቀኝ ፡ ዝራር ፡ ዳግም ፡ ስንጠቍም ፥ የመሥመሩ ፡ ጠቅላላ ፡ የትርጕምና ፡ ያምሳያ ፡ ቃላት ፡ ይዘት ፡ እማማረጫው ፡ መስክ ፡ ላይ ፡ ይተረርልናል ። ከዚያ ፡ ወዲያ ፥ እንደ ፡ ፍላጎታችን ፥ እጽሑፉ ፡ ውስጥ ፡ ሌላ ፡ ቃልን ፡ እንተካበታለን ፥ አለዚያም ፡ የቃሉን ፡ ፍቺ ፡ እመዝገበ ፡ ቃላት ፡ ውስጥ ፡ እንመለከታለን ።

አኹን ፡ ለያዝነው ፡ ጕዳያችን ፥ "ስትራቴጂክ" ፡ ተብሎ ፡ የነበረውን ፡ ቃል ፥ "ይተካ"ን ፡ ተጭነን ፡ በ"ዐቅዳዊ" ፡ አለዚያም ፡ በ"ዐቅድ" ፣ ወዘተ. ፡ እንተካዋለን ።
አኹን ፡ ደግሞ ፡ ራሱን ፡ የእንግሊዝኛውን ፡ ቃል ፡ "strategy"ን ፡ በእንግሊዝኛው ፡ መዝገበ ፡ ቃላት ፡ ፈትን ፥ የመዝገበ ፡ ቃላቱን ፡ ጠቅላላ ፡ አገልግሎት ፡ በዝርዝር ፡ እንመልከት ። (ግጻዌ ፡ 19)

Figure 18: Whichever language is chosen ('English', 'ዐማርኛ', 'Français'), the whole set of senses attached to the translated word, as expressed by the set of synonyms, can be listed in the alternatives field "by"; it suffices to select the line corresponding to the chosen language, then right-click on the selected line. The above example illustrates this for the example we saw earlier: we have just obtained the Amharic translations for the word "strategic"; we need only choose the one suitable, and either effect a replacement in the text or look up the word in the dictionary.
Let us now examine the features offered by the dictionary (Figure 19).

Figure 18: Quelque soit la langue choisie ('Français', 'ዐማርኛ', 'English'), l'ensemble des acceptions attachées au mot traduit, tel qu'il est représenté par l'ensemble des synonymes, peut être listé dans le champs des alternatives "par"; il suffit pour cela de sélectionner la ligne correspondant à la langue choisie, pour ensuite appuyer cliquer le bouton de droite de votre souris. L'exemple ci-dessus illustre ce cas pour l'exemple énoncé plutôt: nous venons d'obtenir les traductions amhariques du mot anglais "strategic"; il ne nous reste plus qu'à choisir celle qui nous convient, ou bien voir sa définition dans le dictionnaire.
Examinons maintenant les possibilités offertes par le dictionnaire (figure 19).



ግጻዌ ፡ 19 ፤ የእንግሊዝኛው ፡ መዝገበ ፡ ቃላት ፡ ፕሪንስተን ፡ ምድራስ ፡ ካዘጋጀው ፡ "WordNet" ፡ ከተባለው ፡ ነጻ ፡ የእንግሊዝኛ ፡ ንምራዊ ፡ መዝገበ ፡ ቃላት ፡ የተቀዳ ፡ ነው ። ከ 200000 ፡ ያላነሱ ፡ የእንግሊዝኛ ፡ ቃላትን ፡ በዝርዝር ፡ መፍታት ፡ ብቻ ፡ ሳይኾን ፡ ቃላቱን ፡ ባምሳያ ፡ ባምሳያቸው ፡ ቀምሮና ፡ አደራጅቶ ፡ ይዟል ። ዐውደ ፡

ቀለምም ፡ ይህን ፡ ታላቅ ፡ ዐቅም ፡ ላገልግሎት ፡ አብቅቷል ።
WordNet ፡ ከሰጠው ፡ ፍቺ ፡ ጐን ፥ የዐውደ ፡ ቀለም ፡ ትርጕም ፡ በማእዘን ፡ ቅንፍ ፡ [...] ፡ ውስጥ ፡ ተመልክቶ ፡ {ዐቀ-ክ 1..} ፡ በሚል ፡ ፊርማ ፡ ተለይቶ ፡ ይታያል ። ለጊዜው ፡ 37'000 ፡ ቃላት ፡ ብቻ ፡ ወዳማርኛ ፡ ተተርጕመዋል ፡ (<18.5%) ።
ያተረጓጐሙ ፡ ቅደም ፡ ተከተል ፡ ተፈላጊ ፡ ቃላትን ፡ በማስቀደም ፡ መኾን ፡ ሲገባው ፥ ፈጽሞ ፡ በነሲብ ፡ ተራ ፡ ተከናውኗል ። እንዲሁም ፡ ያገር ፣ የከተማ ፣ የሰው ፡ ስሞች ፣ ወዘተ. ፡ ገና ፡ በሥርዐት ፡ ተለቅመው ፡ አልተመዘገቡም ። ክለሳ ፡ 2 ፡ ላይ ፡ ትርጐማውን ፡ በተሟላና ፡ አግባብነት ፡ ባለው ፡ ቅደም ፡ ተከተል ፡ ለማከናወንና ፡ የተተረጐሙትን ፡ ቃላት ፡ ብዛት ፡ 40000 ፡ ለማድረስ ፡ ታቅዷል ።
ለያዝነው ፡ ጉዳያችን ፥ "strategic"ን ፡ በ"ዐቅዳዊ" ፡ ወይም ፡ በ"የዐቅድ" ፡ ወይም ፡ በ"ዐቅድያ" ፡ ልንተካው ፡ መቻላችንን ፡ አግኝተናል ። "framework"ንሳ? ፡ (ግጸ፳ ፡ 20 ን ፡ ይመለከቷል ።)

Figure 19: The English dictionary is extracted as is from the WordNet dictionary and integrated into the AwdeQelem dictionary tool. The WordNet dictionary is developed at Princeton University, U.S.A., and made freely available to all.

Out of the 200'000 or so words defined in WordNet, only 37'000 (<18.5%) are, for now, translated into Amharic by AwdeQelem and affixed to the WordNet definition, followed by the {ዐቀ-ክ 1..} signature. However, as the translation is done in an haphazard fashion, mainly due to time constraints, more frequently used words remain non-translated while less used ones are translated. For version 2 of AwdeQelem, the translation will follow a more logical and systematic sequence, at the end of which some 40000 words will be translated/transcribed into Amharic.

Coming back to our discussion, loan words like "strategic framework" can thus be translated into Amharic, using the AwdeQelem translations, as is shown in figure 20, below.

Figure 19: Le dictionnaire anglais est extrait tel quel depuis le dictionnaire WordNet, et intégré dans l'outil de dictionnaire AwdeQelem. Le dictionnaire WordNet est développé par l'université de Princeton, E.U.A., et mis gratuitement à la disposition de tous.

Sur les quelques 200'000 mots définis dans WordNet, pour l'instant, environ 37'000 (soit <18.5%) sont traduits en amharique par AwdeQelem, et ajoutés aux définitions WordNet, suivis par la signature {ዐቀ-ክ 1..}. Néanmoins, comme la séquence de traduction s'est faite de manière fortuite, par manque de temps principalement, parfois des mots plus fréquemment usités restent non traduits, alors que d'autres moins usités le sont. Pour la version 2 de AwdeQelem, une séquence plus logique et systématique sera suivie, et le nombre de mots traduits/transcrits en amharique sera porté à 40000 mots.

Revenant à notre discussion, des mots d'emprunts comme "strategic framework" peuvent être traduits en amharique de cette façon, en utilisant les traductions de AwdeQelem, comme nous le démontre la figure 20, ci-dessous.



ግጻዌ ፡ 20 ፤ "framework"ም ፡ እንደዚሁ ፡ ተፈቶልናል ፤ ያማርኛ ፡ ትርጕሙም ፡ በቅንፍ ፡ ተመልክቷል ። WordNet ፡ "framework"ን ፡ አብራርቶ ፡ በእንግሊዝኛ ፡ የፈታልንን ፥ ዐውደ ፡ ቀለም ፡ ተራውን ፡ ወዳማርኛ ፡ "መሠረት ፥ ማቀፊያ ፥ ምሕቃፍ ፡ (ግ.)" ብሎ ፡ ተርጕሞልናል ። "ምሕቃፍ" ፡ እንጂ ፡ "ማዕቀፍ" ፡ አላለም! ፡ "ማዕቀፍ" ፡ በግእዝ ፡ "ዕንቅፋት" ፡ ማለት ፡ ስለ ፡ ኾነ ፥ "ምሕቃፍ" ፡ ደግሞ ፡ በግእዝ ፡ "ማቀፊያ" ፡ ማለት ፡ ስለ ፡ ኾነ ፥ ቀደም ፡ ሲል ፡ እመረመርነው ፡ ጽሑፍ ፡ ውስጥ ፡ "ስትራቴጂክ ፡ ማዕቀፍ" ፡ ተብሎ ፡ በስሕተት ፡ የተገለጸው ፡ ሐሳብ ፥ "የዐቅድ ፡ መሠረት" ፥ ወይም ፡ "የዐቅድ ፡ ምሕቃፍ" ፡ ተብሎ ፡ ሊታረም ፡ ይችላል ። የጽሑፍ ፡ ማምረቻውን ፡ መለስ ፡ ብለን ፡ ስናይ ፥ "በየነ" ፡ የሚለው ፡ ቃል ፡ ባረንጓዴ ፡ ተመልክቷል ። ርግጥ ፡ ነው ፥ "በየነ" ፡ ፈረደ ፡ ማለት ፡ ኾኖ ፥ እመዝገበ ፡ ቃላት ፡ ውስጥ ፡ ሰፍሯል ። ነገር ፡ ግን ፥ በጽሑፉ ፡ ውስጥ ፡ የዋለው ፡ "inter-governmental" ፡ የሚለውን ፡ የእንግሊዝኛ ፡ ቃል ፡ ለመተርጐም ፡ ስለ ፡ ኾነ ፥ ሊውል ፡ የሚገባው ፡ ቃል ፡ ምናልባት ፡ "በይነ" ፡ እንጂ ፡ "በየነ" ፡ አይደለም ። ("በይነ" ፡ የግእዝ ፡ ቃል ፡ ነው ፤ "ስለ" ፡ ወይም ፡ "በእየ" ፡ ለማለት ፡ ውሎ ፡ ይኾናል ። በግእዝ ፡ አነባበቡም ፡ "ይ" ፡ ሳይጠብቅ ፡ "በይ̊ነ" ፡ ተብሎ ፡ ይነበባል) ፤ አኹንም ፥ ቃሉ ፡ "በየነ" ፡ በራሱ ፡ ትኽክል ፡ ዐማርኛ ፡ ቢኾንም ፥ የዋለበት ፡ ፈርጀ ፡ ነገር ፡ ስሕተት ፡ ነው ። "inter-governmental" ፡ የሚለውን ፡ የእንግሊዝኛ ፡ ቃል ፡ "የመንግሥታት" ፡ ወይም ፡ "መንግሥታታዊ" ፡ ልንለው ፡ እንችላለን ።

አኹን ፡ ደግሞ ፡ ያማርኛው ፡ መዝገበ ፡ ቃላት ፡ ለ'ምሕቃፍ' ፡ የሚሰጠንን ፡ ፍቺ ፡ እንመልከት ። ። (ግጻዌ ፡ 21ን ፡ ይመለከቷል ።)

Figure 20: Most words can thus easily be ascertained with the help of the AwdeQelem dictionary. Let us see now one

Figure 20: La plupart des mots peuvent ainsi être vérifiés à l'aide du dictionnaire AwdeQelem. Voyons à présent un tel

such example using the Amharic dictionary (figure 21).

exemple par le biais du dictionnaire amharique (figure 21).



ግጸዌ ፡ 21 ፤ "ምሕቃፍ" ፡ የግእዝ ፡ ቃል ፡ ነው ፤ ግእዝ ፡ "ሐቀፈ" ፡ ካለው ፡ ዘር ፡ በዘመድ ፡ ዘርነት ፡ የተገሰሰ ፡ ነው ። ባማርኛ ፡ "ማቀፊያ" ፡ ማለትም ፡ ይቻላል ።
ኹሉም ፡ የግእዝና ፡ ያማርኛ ፡ ዘሮች ፡ ወይም ፡ አንቀጾች ፡ ዘመድ ፡ ዘር ፡ አላቸው ። ለምሳሌ ፦

ሐቀፈ ፡ (ግ.) ▶ ምሕቃፍ ፡ (ግ.) • ዐቀፈ ፡ (ዐ.) ▶ ማቀፊያ ፡ (ዐ.)
ዐቀፈ ፡ (ግ.) ▶ ማዕቀፍ ፡ (ግ.) • ዐነቀፈ ፡ (ዐ.) ▶ ማንቀፊያ ፡ (ዐ.)

የዐውደ ፡ ቀለም ፡ ክለሳ ፡ 1.2 ፡ ያመጣልን ፡ ዐዲስ ፡ የቃል ፡ ማራደፊያ ፡ ዐቅም ፡ አለ ። የግሶችን ፡ ዐይነት ፡ ለመለየት ፡ ይህ ፡ የማራደፊያ ፡ ዐቅም ፡ ይጠቅመናል ። "ምሕቃፍ" ፡ የሚለው ፡ ቃል ፡ የ"ሳድስ-ሳድስ-ራብዕ-ሳድስ" ፡ አረዳደፍ ፡ አለው ፤ ብዙ ፡ ዘመድ ፡ ዘሮች ፡ በዚሁ ፡ አረዳደፍ ፡ ይገኛሉ ። ለዚህም ፥ "ይረደፍ" ፡ የሚለውን ፡ ዝራር ፡ መጫን ፡ ይበቃናል ። (ግጸዌ ፡ 22 ን ፡ ይመለከቷል ።)

Figure 21: Version 1.2 of AwdeQelem has introduced the novel word "patternization" function for the Ethiopic script, which lists words in the dictionary that have the same pattern as the word looked up in the dictionary by just pressing the "patternize" button, as figure 22 shows.

Figure 21: La version 1.2 de AwdeQelem a introduit une nouvelle fonction de modélisation pour l'écriture éthiopienne qui liste les mots dans le dictionnaire sur le modèle du mot recherché lorsqu'on presse le bouton "modéliser" comme le montre la figure 22.



ግጻዌ ፡ 22 ፤ "ይሁዳፎ" ፡ የሚለውን ፡ ዝራር ፡ ስንጫነው ፥ "ዝርዝርና ፡ ሞክሼ" ፡ አተሠኘው ፡ ዐምድ ፡ ወስጥ ፡ ከ"ምሕቃፍ" ፡ ጋራ ፡ የሚራደፉት ፡ ቃላት ፡ በሙሉ ፡ ከመዝገበ ፡ ቃላት ፡ በነቂስ ፡ ተተርረው ፡ እናገኛቸዋለን ። ይህ ፡ ዐቀም ፡ የዳበረ ፡ የመርባት ፡ ጠባይ ፡ ላላቸው ፡ እንደ ፡ ግእዝና ፡ ዐማርኛ ፡ ላሉ ፡ ቋንቋዎች ፡ እጅግ ፡ ጠቃሚ ፡ ይኾናል ። ወደ ፡ ፊት ፥ በእየክለሳው ፡ ሌሎችም ፡ ዐቅሞች ፡ ይታከላሉ ።

ወደ ፡ ጽሑፍ ፡ ማምረቻው ፡ እንመለስና ፥ ስሕተቶቹን ፡ እንዲህ ፡ በቀላሉ ፡ ማግኘት ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ ነው ፤ እንዲሁ ፡ የተሳሳቱትን ፡ ቃላት ፡ በቀላሉ ፡ በማረሚያ ፡ ቃላቱ ፡ መተካት ፡ ደግሞ ፡ ዐውደ ፡ ቀለም ፡ ያስጨበጠን ፡ ሌላው ፡ ዐቅም ፡ ነው ።

። (ግጻዌ ፡ 23 ን ፡ ይመለከቷል ።)

Figure 22: The output of the "patternizer" function is listed in the "ዝርዝርና ፡ ሞክሼ • derivatives and homonyms" column, right.
Returning to the text processor, most words can thus easily be ascertained with the help of the AwdeQelem dictionary; they can also be replaced just as easily, thanks to the facilities that the AwdeQelem text processor offers, as we

Figure 22: Le résultat de la modélisation est listé dans la colonne "ዝርዝርና ፡ ሞክሼ • derivatives and homonyms", a droite.
Revenant au traitement de texte, la plupart des mots peuvent ainsi être vérifiés à l'aide du dictionnaire AwdeQelem; ils peuvent aussi être remplacés tout aussi aisément, grâce aux fonctions du traitement de texte AwdeQelem, comme nous allons le voir à présent [figure 23].

will see now, in figure 23.



ግጻዌ ፡ 23 ፤ ቀደም ፡ ሲል ፡ እንዳየነው ፥ "በአፍሪካ" ፡ በቀይ ፡ ቀለም ፡ ተመልክቶልን ፥ ዕርማቱ ፡ "በአፍሪቃ" ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ አረጋግጠናል ። ኾኖም ፥ "አፍሪካ" ፡ ለብቻው ፡ (ማለት ፡ "በ" ፡ ሳይቀጠልበት) ፡ በዝርዝርነት ፡ በብጫ ፡ ቀለም ፡ መመልከቱ ፡ የሌላ ፡ ቃል ፡ ዝርዝር ፡ መስሎ ፡ ሲታየን ፡ ይችላል ፤ ይህም ፡ ራሱ ፡ ያጻጻፍ ፡ ስሕተት ፡ መኖሩን ፡ እንድንጠረጥር ፡ ያደርገናል ። ምክንያቱም ፡ በትኽክል ፡ የተጻፈ ፡ ስም ፡ ኹሉ ፡ ባረንጓዴ ፡ መመልከት ፡ ስላለበት ፥ "አፍሪካ" ፡ የሚለውም ፡ ስም ፡ ባረንጓዴ ፡ መመልከት ፡ ነበረበት ። ስሕተት ፡ ከኾነ ፡ ዘንዳ ፡ ለምን ፡ በቀይ ፡ አልተመለከተም ፡ ቢሉ ፥ መልሱ ፡– "አፍሪካ" ፡ የ"ፈረከ" ፡ ዝርዝር ፡ የመኾን ፡ ዕድል ፡ ኖሮት ፡ ነው ፥ የሚል ፡ ይኾናል ። ("አፍሪቃ" ፡ የሚለው ፡ ስም ፡ ግእዝ ፡ "ፈረቀ/ለየ ፣ አዳነ ፣ ቤዠ" ፡ ካለው ፡ ይወጣል) ። ያልተዘረዘረ ፡ ስም ፡ በዝርዝርነት ፡ ቢመለከት ፡ ያጻጻፍ ፡ ስሕተት ፡ ቢኖረው ፡ ነውና ፥ በብጫ ፡ የተመለከተን ፡ ስም ፡ ኹሉ ፡ በተቻለ ፡ መጠን ፡ መርምሮ ፡ ማረም ፡ ይገባል ።

አኹን ፡ ደግሞ ፥ ዕርማቱን ፡ በገቢር ፡ እንፈጽማለን ። "አፍሪካ"ን ፡ በ"አፍሪቃ" ፡ ከመተካታችን ፡ በፊት ፥ በቀኝ ፡ ዐምድ ፡ በኩል ፡ "ይታሠሥ" ፡ የሚለውን ፡ ዝራር ፡ ተጭነን ፡ ቃሉ ፡ የሚገኝባቸውን ፡ ዝርዝሮች ፡ ኹሉ ፡ አግኝተን ፥ በስሕተት ፡ ሌላ ፡ ቃልን ፡ እንዳንተካ ፡ እናረጋግጥና ፥ ርግጠኞች ፡ ስንኾን ፥ "ኹሉም ፡ ይተካ" ፡ የሚለውን ፡ ዝራር ፡ ጠቅመን ፥ "አፍሪካ" ፡ ተብሎ ፡ የተጻፈባቸውን ፡ ቦታዎች ፡ ኹሉ ፡ በቅጽበት ፡ በ"አፍሪቃ" ፡ እንተካቸዋለን ። (ግጻዌ ፡ 24ን ፡ ይመለከቷል ።)

Figure 23: In some instances, words such as simple nouns may be signalled as derivatives (yellow background colour); this in itself is indicative of some spelling mistake. That is why it is sometimes useful to check on the legitimacy of the colour coded indication, as the prefix|stem|suffix

Figure 23: Il arrive que des noms communs simples soient signalés comme des dérivés [arrière-plan jaune]; ceci, en soi, est indicatif d'une erreur d'orthographie. C'est pourquoi il est parfois utile de questionner la légitimité de l'indication par couleur, lorsque l'on sait que la décomposition de

decompositions can deliver some unexpected but valid compound words. Once the manual verification is done and before the correction is effected, it is advisable to press the "search" button for the word awaiting correction and display all its instances in the text as a simple or compound word, thereby avoiding the possibility of replacing by accident a similar or an homonym compound word. Once the resulting list of instances are examined and no possibility of error exists, then we may press the "replace all" button for the alternative spelling, and complete the correction over the whole text, as shown in figure 24.

tout mot en préfixe|radical|suffixe peut nous livrer de manière inattendue des mots composés valides. Une fois que la vérification manuelle est effectuée, il est conseillé d'afficher toutes les occurrences en mot simple ou composé du mot examiné, en appuyant le bouton "rechercher"; ce faisant on évite toute possibilité de remplacement accidentel d'un mot composé similaire ou homonyme. Une fois que cette dernière vérification est effectuée, on peut procéder au remplacement complet de toutes les occurrences du mot erroné par l'alternative en appuyant le bouton "tout remplacer", et appliquer ainsi la correction sur le texte en entier [figure 24].



ግጻዌ ፡ 24 ፤ "አፍሪካ" ፡ ተብሎ ፡ በስሕተት ፡ የተጻፈው ፡ ቃል ፡ እጽሑፉ ፡ ውስጥ ፡ እ 2 ፡ ቦታ ፡ ላይ ፡ ሰፍሯል ፤ 2 ቱም ፡ በ"አፍሪቃ" ፡ ተተክተዋል ።

አንድ ፡ ስሕተት ፡ ታረመ ፤ ሌሎቹም ፡ በዚሁ ፡ ዐይነት ፡ ይታረማሉ ። ዕርማቱ ፡ ሲያልቅ ፥ የቃላቱ ፡ ቀለማት ፡ ባብዛኛው ፡ አረንጓዴ ፡ (ጥንቁቅ) ፤ ብጫ ፡ (ዝርዝር) ፡ እና ፡ ነጭ ፡ (ባዕድ ፡ አለዚያም ፡ ግዑዝ) ፡ ይኾናሉ ፤ አንዳንድ ፡ ሊታረሙ ፡ የማይችሉ ፡ አሻሚ ፡ ቃላት ፡ ወይም ፡ እመዝገበ ፡ ቃላት ፡ ውስጥ ፡ ገና ፡ ያልሰፈሩ ፡ ቃላት ፡ ቢኖሩ ፥ በግራጫ ፡ (አሻሚ) ፡ እና ፡ በቀይ ፡ (ያልታወቀ ፡ ቃል) ፡ ቀለም ፡ ተለይተው ፡ ይታያሉ ። በዝርዝርነት ፡ በብጫ ፡ ቀለም ፡ ከሚቀልሙት ፡ ውስጥ ፡ ያንዳንዶቹን ፡ ስሕተትነት ፡ መለየት ፡ ያዳግታል ፤

ለምሳሌ ፥ እጽሑፉ ፡ ውስጥ ፡ "ዕርዳታ" ፡ ወይ ፡ "እርዳታ" ፡ የሚል ፡ ቃል ፡ ቢኖር ፥ ዐውደ ፡ ቀለም ፡ በብጫ ፡ ያመለክትልናል ። ነገር ፡ ግን ፡ "ዕ/እ" ፡ ካነጋገር ፡ ስሕተት ፡ የመጣ ፡ ትርፍ ፡ ፊደል ፡ ነውና ፥ ሊወገድ ፡ ይገባል ። አንቀጹ ፡ "ረዳ" ፡ ስለ ፡ ኾነ ፥ "ርዳታ" ፡ እንጂ ፡ "እርዳታ" ፡ ተብሎ ፡ አይጻፍም ፤

እንደዚሁ ፡—	እርምጃ ×	እርግጫ ×	እርዳታ ×	እርጉዝ ✓
	ርምጃ ፡ ✓	ርግጫ ✓	ርዳታ ✓	ርጉዝ ×
	(ረመደ)	(ረገጠ)	(ረዳ)	(አረገዘች)

ከፊደልና ፡ ከቃል ፡ ዕርማት ፡ በኋላ ፡ ያማርኛ ፡ አባባል ፡ ዕርማት ፡ ሊካኼድ ፡ ይችላል ። ይህ ፡ ሰፊ ፡ ሥራ ፡ በመኾኑ ፥ እዚህ ፡ ላንጨርስ ፡ አንዠምረውም ። ኾኖም ፥ ለናሙና ፡ ያኽል ፥ አንዱን ፡ ጕልሕ ፡ ስሕተት ፡ ነጥለን ፡ ይዘን ፡ እንደሚከተለው ፡ እናስረዳበት ።

እጥቅሱ ፡ ውስጥ ፡ "ስምምነት ፡ አደረጉ" ፡ የሚል ፡ ቃል ፡ ሰፍሯል ። በዘመናችን ፥ "አደረገ" ፡ የሚለው ፡ አንቀጽ ፡ አላግባብ ፡ ላረፍተ ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡ ማሰሪያ ፡ እየኾነ ፡ የሐሳብን ፡ ጣዕም ፡ ፈጽሞ ፡ ያበላሻል ።

"ዐብራችኹን ፡ ቈዩ" ፡ ማለት ፡ ሲበቃ ፡ "ዐብራችኹን ፡ ቈይታ ፡ አድርጉ" ፥

"ሞክሩ" ፡ ማለት ፡ ሲበቃ ፡ "ሙከራ ፡ አድርጉ" ፥

"ጣሩ" ፡ ማለት ፡ ሲበቃ ፡ "ጥረት ፡ አድርጉ" ፡ የትርፍ ፡ ትርፍ ፡ ነው ፤ አያሻም ።

እላይ ፡ "ስምምነት ፡ አደረጉ" ፡ ያሉበትን ፡ አረፍተ ፡ ነገር ፡ "ተስማሙ" ፡ ብለን ፡ ልናሻሽለው ፡ እንችላለን ። ዕርማቱ ፡ ሲጠናቀቅ ፡ እላይ ፡ ያኼድነው ፡ ዐጪር ፡ ጽሑፍ ፡ በምን ፡ መልክ ፡ እንደሚከሠትልን ፡ ቀጥለን ፡ እናያለን ፡ (ግጸዌ ፡ 25) ።

Figure 24: One misspelling has been corrected; likewise, the rest of the text will be spell-checked. Once the whole text is spell-checked, the range of colour of the word-list will have white (neutral), green (correct spelling) and yellow (derived word) as the dominant colours. A 100% precision cannot be achieved; which explains the presence of grey (ambiguous spelling) and red (unknown word) background colourings.

An example of a fully spell-checked sample text shows the following palette (figure 25).

Figure 24: Une correction orthographique vient d'être effectuée; le restant du texte sera corrigé de la même manière. Une fois la correction orthographique effectuée pour l'ensemble du texte, la palette de couleur dominante ira du blanc (neutre) au vert (orthographie correcte), en passant par le jaune (mot dérivé). Une précision de 100% est quasi-impossible; ce qui explique la présence du gris (orthographie ambigüe) et du rouge (mot inconnu) à l'arrière-plan.

Un exemple de texte entièrement corrigé affiche la palette suivante (figure 25).



ግጸዌ ፡ 25 ፤ እንሆ ፥ ጠቅላላው ፡ ዕርማት ፡ ይህን ፡ የመሰለ ፡ ውጤት ፡ ሰጥቶናል ፤ አብዛኛው ፡ ቃላት ፡ ባረንጓዴ ፡ (ጥንቁቅ) ፡ እና ፡ በብጫ ፡ (ዝርዝር) ፡ ቀለማት ፡ ተመልክተዋል ። ዐልፎ ፡ ዐልፎ ፡ በግራጫ ፡ ቀለም ፡ የተመለከቱ ፡ አሉ ፤ እነሱም ፡ አሻሚ ፡ ኾነው ፥ ለጊዜው ፡ ባለው ፡ መዝገበ ፡ ቃላትና ፡ ቅምር ፡ ካሻሚነት ፡ ለማስወገድ ፡ ስላልተቻለ ፡ ነው ። ወደ ፡ ፊት ፥ በተሻለ ፡ ዐቅም ፡ ይታረማሉ ። ለያዝነው ፡ ሥራ ፥ የቀሩ ፡ የነጠብጣብ ፡ ዕርማትን ፡ አጠናቅን ፥ ጽሑፉን ፡ በሰነድነት ፡ እንመዝግበው ።

(ግጸዌ ፡ 26)

"ኹለት ፡ ነጥብ ፡ ያስፈልጋል|አያስፈልግም" ፡ የሚለው ፡ ጕዳይ ፡ እሊቃውንቱ ፡ ዘንድ ፡ መልሱን ፡ አግኝቷል ፦ ያስፈልጋል ። ለዚህም ፡ ማስረጃ ፥ የኹለት ፡ ነጥብ ፡ መኖር ፡ ለጽሑፍ ፡ ተነባቢነትና ፡ ለቃላት ፡ ሙሉነት ፡ የሚያተርፍልንን ፡ ጥቅም ፡ አብራርተው ፡ ያቀርባሉ ([46]) ።

Figure 25: We have completed the spell-checking of our sample text; if there remains one thing it is the issue of punctuation proper to the Ethiopian script. Traditionally, the Ethiopian script uses the "two points/neqwt" '፡' as separator instead of "space" for the good reason that its letters are the equivalent of upper-case Latin letters (lower-case is non-existent in the Ethiopian script). Without proper separators, the readability of the text and the integrity of the words are compromised (the same word can be read as two separate words and still make

Figure 25: Nous avons complété la correction orthographique du texte exemple; il nous reste maintenant à nous attarder un instant sur une question de ponctuation propre à l'écriture éthiopienne. Traditionnellement, l'écriture éthiopienne utilise comme espace séparateur les "deux points/neqwt" '፡', pour la bonne raison que les lettres éthiopiennes sont équivalentes aux majuscules latines. Sans séparateurs adéquats, la lisibilité du texte et l'intégrité des mots sont compromis (le même mot peut être lu comme deux mots séparés, et avoir un sens dans le

46 ኪዳን ፡ ወልድ ፡ ክፍሌ ፡ (አለቃ) ፤ መጽሐፈ ፡ ሰዋስው ፡ ወግስ ፡ ወመዝገበ ፡ ቃላት ፡ ሐዲስ ። ዐዲስ ፡ አበባ ፥ አርቲስቲክ ፡ ማተሚያ ፡ ቤት ፥ 1948 ፡ ዓ.ም. ፤ ገጽ ፡ 43-44 ።

sense within a text; or two words can be read as one and still make sense). In this regard, the Microsoft Nyala font (typeface) which has a very narrow inter-character space for Ethiopian characters, and an even more narrow two-point separator space, as a side-effect, forces users to abandon the two-point separator altogether, thereby decreasing the readability of text written in Ethiopian characters.

The substitution of the two-point separator gives us an improved result with the Wazéma font (AO Desta Unicode).
as shown in figure 26.

contexte; ou encore, deux mots peuvent être lus comme un seul et avoir aussi un sens). A cet égard, la police de caractère Nyala de Microsoft, qui alloue un espace inter-caractère étroit et un espace séparateur "deux-points" encore plus étroit, a pour effet pervers de forcer les utilisateurs à abandonner une fois pour toutes le séparateur "deux-points"; réduisant par là même la lisibilité et l'intelligibilité du texte d'écriture éthiopienne.

La substitution du séparateur "deux-points" nous donne un résultat meilleur dans la police de caractères Wazéma (AO Desta Unicode), comme nous montre la figure 26.



ግጻዌ ፡ 26 ፤ እስካኹን ፡ የሠራነው ፡ ኹሉ ፡ በሰነድ ፡ ውስጥ ፡ ያልተመዘገበ ፡ ነውና ፣ ልንመዘግበው ፡ ብንሻ ፣ "እንዳዲስ ፡ ይመዝገብ" ፡ የሚለውን ፡ ዝራር ፡ እንጠቀ፝ምና ፣ የሰነድ ፡ ስም ፡ ማመልከቻ ፡ መሳተፊያ ፡ ላይ ፣ ማማረጫ ፡ የሚኾነን ፡ ዐዲስ ፡ የሰነድ ፡ ስም ፡ በጽሑፍ ፡ ማምረቻው ፡ ይቀርብልናል ፤ የሰነዱ ፡ ስም ፡ ቢስማማን ፣ "ይኹን" ፡ ብለን ፡ እናጸድቀዋለን ፤ ባይስማማን ፡ ደግሞ ፣ ዐዲሱን ፡ የሰነድ ፡ ስም ፡ እመሳተፊያው ፡ ላይ ፡ አመልክተንና ፡ "ይኹን"ን ፡ ጠቀ፝መን ፣ የታረመ ፡ ጽሑፋችንን ፡ እንመዘግባለን ።
የጽሑፍ ፡ ማምረቻው ፡ ያቀረበልን ፡ ዐዲስ ፡ የሰነድ ፡ ስም ፡
"c:/users/blablabla/documents/prolog/awdeqelem_mamretcha_2016_2_20_215620.txt" ፡
ለኹለት ፡ ይከፈላል ። የመዠመሪያው ፡ ክፍል ፡ ሰነዱ ፡ የሚመዘገብበትን ፡ ማኅደር ፡ ያመለክታል ፤

"c:/users/blablabla/documents/prolog/"
ኹለተኛው ፡ ክፍል ፡ የሰነዱ ፡ ስም ፡ ይኾናል ፤ ላዲስ ፡ ሰነድ ፡ ኹሉ ፥ ዐዲስና ፡ አንድያ ፡ የሰነድ ፡ ስም ፡ ተበጅቶ ፡ በማማረጫነት ፡ ይቀርባል ፤
"awdeqelem_mamretcha_2016_2_20_215620 .txt"
ለሰነዱ ፡ ልንሰጥ ፡ የምንፈልገው ፡ ስም ፡ ሌላ ፡ ቢኾን ፡ (ለምሳሌ ፡ "moukera.txt") ፥ በማማረጫነት ፡ የቀረበልንን ፡ የሰነድ ፡ ስም ፡ ለይተን ፡ እንደልዝና ፥ በምትኩ ፡
"c:/users/blablabla/documents/prolog/moukera.txt"
ብለን ፡ "ይኹን" ፡ የሚለውን ፡ ዝራር ፡ ጠቍመን ፡ እናጸድቀዋለን ።
ከዚህ ፡ ወዲያ ፡ የምናከታትላቸውን ፡ ማዘመኛዎች ፡ ኹሉ ፡ ለመመዝገብ ፡ "ይመዝገብ" ፡ የሚለውን ፡ ዝራር ፡ መጠቈም ፡ ይበቃል ።

[ማሳሰቢያ ፤
• በዚህኛው ፡ የዐውደ ፡ ቀለም ፡ ክለሳ ፥ የሰነድ ፡ ስሞች ፡ ኹሉ ፡ በምዕራባዊ ፡ ፊደል ፡ መመዝገብ ፡ አለባቸው ። በኢትዮጵያዊ ፡ ወይም ፡ በሌላ ፡ ፊደል ፡ ቢመዘገቡ ፥ የሰነዶቹ ፡ ይዘት ፡ ተነባቢ ፡ ብቻ ፡ ይኾንና ፥ ሊለዋወጡት ፡ ወይም ፡ ሊያዘምኑት ፡ አይቻልም ፤
• በዐውደ ፡ ቀለም ፡ የሚመዘገቡት ፡ ሰነዶች ፡ ኹሉ ፡ በ UTF-8 ፡ የ UNICODE ፡ አቀጻጽ ፡ አቀማመር ፡ ነው ።]

Figure 26፡ None of the modifications we have made so far to the original text have been saved in a file. To save then in a file, we press the "save as" button which displays for us a file naming and saving dialogue. In the dialogue, an automatically generated file name is suggested. If the suggested file name suites us, we press "OK" and the new file is saved. Otherwise, we can overwrite it and enter the file name of our choice.
Further updates to the file will be saved by pressing the "save" button.
[NB፡
• in the current version of AwdeQelem, file names are limited to Latin characters. Use of other characters in the file name makes the file a "read only" file with no possibility of updating it;
• AwdeQelem saves all text files in UTF-8 encoding format.]

Figure 26፡ Aucune des modifications apportées au texte original n'ont été sauvegardées dans un fichier. Pour ce faire, on appuie le bouton "sauvegarder comme" qui nous affiche un dialogue de désignation et de sauvegarde de fichier. Dans le dialogue un nom de fichier généré automatiquement nous est suggéré. Si le nom de ficher suggéré nous convient, on appui le bouton "OK" et le fichier est sauvegardé. Autrement, on écrase le nom suggéré, et l'on inscrit le nom de fichier de notre choix.
Les mises à jour ultérieures seront sauvegardées en appuyant le bouton "sauvegarder" tout court.
[NB፡
• dans la présente version de AwdeQelem, les noms de fichier sont limités aux caractères latins. L'usage d'autres caractères rend le fichier à lecture seule, sans possibilité de le mettre à jour;
• AwdeQelem sauvegarde les fichiers textes en codage de format UTF-8.]



ግጻዌ ፡ 27 ፤ ሰነዱን ፡ ከመዝጋታችን ፡ በፊት ፥ "Inter-Governmental Authority on Development" ፡ የሚለውን ፡ ሙሉ ፡ መጠሪያ ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ ጻሕፍ ፡ እንዴት ፡ እንደምንመልሰው ፡ እንመልከት ። ለዚህ ፡ ለምለሳ ፡ ሥራ ፡ እንዲያገለግል ፡ ተብሎ ፡ የተበጀ ፡ የመመለሻ ፡ መግበር ፡ አለልን ፤ እዐውደ ፡ ቀለም ፡ መምረጫ ፡ ላይ ፥ "መጋብርት" ፡ የሚለውን ፡ መግቢያ ፡ በመጠቈሚያው ፡ ጠቍመን ፡ መመለሻውን ፡ እናስነሣ ።

Figure 27: Let us now transliterate the name of the international organisation: "Inter-Governmental Authority on Development" into the Ethiopian script. We start the AwdeQelem Transcriber tool from the "tools" menu.

Figure 27: Transcrivons maintenant le nom de l'organisme international: "Inter-Governmental Authority on Development" en écriture éthiopienne. Pour cela, on démarre l'outil AwdeQelem transcripteur depuis le menu "outils".



ግጻዌ ፡ 28 ፤ ዐውደ ፡ ቀለም ፡ የጸሐፎ ፡ መመለሻ ፡ በምዕራባዊ ፡ ጻሕፍ ፡ የተጻፉን ፡ የአሜሪካን ፡ እንግሊዝኛና ፡ የሶማልኛ ፡ ጽሑፎችን ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ ጻሕፍ ፡ ይመልሱበታል ። እንደሚታወቀው ፥ እንግሊዝኛ ፡ ብዙ ፡ ዐይነት ፡ "ላሕይ" ፡ አለው ፤ የብሪታንያ ፤ ያሜሪካ ፤ የጃማይካ ፤ ወዘተ. ፡ ... ። ለጊዜው ፥ የእንግሊዝኛው ፡ መመለሻ ፡ ላሜሪካን ፡ እንግሊዝኛ ፡ ብቻ ፡ ይውላል ። ይህውም ፡ የተቻለው ፥ እግዚአብሔር ፡ ይስጣቸውና ፥ የካርነጊይ ፡ ሜለን ፡ ምድራስ ፡ ተመራማሪዎች ፡ ላሜሪካን ፡ እንግሊዝኛ ፡ ያሰናዱት ፡ CMUdict ፡ የተባለው ፡ የቃላት ፡ ላሕይ ፡ ማውጫ ፡ መዝገብ ፡ በመኖሩ ፥ ርሱን ፡ መሠረት ፡ በማድረግና ፡ ጥቂት ፡ ማሻሻያን ፡ በማከል ፥ የዐውደ ፡ ቀለም ፡ የጸሐፎ ፡ መመለሻ ፡ መግበር ፡ 99% ፡ የእንግሊዝኛ ፡ ቃላትን ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ ጻሕፍ ፡ ለመመለስ ፡ ያስችላል ። የተመለሰው ፡ ጽሑፍ ፡ ስሕተት ፡ እንዳይኖረው ፡ ዳግመኛ ፡ በዝርዝር ፡ መጣራት ፡ ይኖርበታል ።

የእንግሊዝኛ ፡ ቃላትን ፡ ላሕይ ፡ በጽሑፍ ፡ አስተካክሎ ፡ ለመክተብ ፡ ፈጽሞ ፡ አይቻልም ፡ ቢባል ፡ ማጋነን ፡ አይኾንም ። አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፥ የተጻፈው ፡ ቃልና ፡ ንባቡ ፡ አይገናኙም ፤ ለምሳሌ ፡ "EBONY" ፡ እና ፡ "EBONICS" ፥ ባጻጻፍ ፡ የተቀራረቡ ፡ ቢመስሉም ፥ በንባብ ፡ የተራራቁ ፡ ናቸው ።

"EBONY" ፡ ሲነበብ ፡ "ኤበኒይ" ፡ ነው ።

"EBONICS" ፡ ደግሞ ፡ "ኢ.ይቦኒክስ" ፡ ነው ፤

በምዕራባዊ ፡ ጻሕፍ ፡ እንደተጻፈው ፡ በቀጥታ ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ ጻሕፍ ፡ እንመልስኽ ፡ ብንለው ፥

"EBONY" ፡ ሲመለስ ፡ "ኧቦንይ" ፡ ይኾናል ፤

"EBONICS" ፡ ደግሞ ፡ "ኧቦኒክስ" ፡ ይኾናል ። የእንግሊዝኛን ፡ አጻጻፍና ፡ ንባብ ፡ ያልለመደ ፡ ሰው ፥ ፊደሉን ፡ ብቻ ፡ በማወቅ ፡ ንባቡን ፡ ሊያስተካክል ፡ ፈጽሞ ፡ አይችልም ። ይህን ፡ ተረድተው ፥ የካርነጊይ ፡ ሜለን ፡ ምድራስ ፡ ተመራማሪዎች ፥ ለያንዳንዱ ፡ የእንግሊዝኛ ፡ ቃል ፡ ተገቢውን ፡ ላሕይ ፡ ሲመዘግቡ ፥ ለነዚህ ፡ ኹለት ፡ ቃላትም ፡—

EBONY	EH1 B AH0 N IY0
EBONICS	IY0 B AO1 N IH0 K S

ብለው ፡ የቀመሩትን ፡ ይዞ ፡—

EBONY	EH1 B AH0 N IY0	ኤበኒይ
EBONICS	IY0 B AO1 N IH0 K S	ኢ.ይቦኒክስ

ብሎ ፡ አስተካክሎ ፡ ማድመጥ ፡ ወይም ፡ ማንበብ ፡ ተችሏል ።

ወደ ፡ ርእሳችን ፡ እንመለስና ፥ በምኅጻረ ፡ ቃል ፡ I.G.A.D. ፡ የተባለው ፡ ስም ፡ በረዥሙ ፡ ሲጻፍ ፥

"Inter-Governmental Authority on Development" ፡ ነው ። በኢትዮጵያ ፡ ጻሕፍስ? ግጻዌ ፡ 29 ፡ ይገልጽልናል ።

Figure 28: Thanks to the availability of Carnegie Mellon University's CMUdict American pronunciation list for nearly 130000 English words (including names), it is now possible to transliterate virtually any English word into the Ethiopian script in the correct pronunciation. Without the availability of CMUdict, this would have been extremely difficult to achieve.

Figure 29, below, shows how this is done with AwdeQelem Transcriber.

Figure 28: Grâce à la disponibilité du CMUdict de l'université Carnégie Mellon, la liste de prononciation de près de 130000 mots anglais prononcés à l'américaine, il est maintenant possible de transcrire quasiment tous les mots anglais en écriture éthiopienne dans la prononciation correcte. Sans la ressource CMUdict, ceci aurait été extrêmement difficile à réaliser.

La figure 29, ci-dessous, va nous montrer comment cela se fait avec l'outil AwdeQelem transcripteur.



ግጻዌ ፡ 29 ፤ ዐውደ ፡ ቀለም ፡ የጸሐፎ ፡ መመከሻ ፡ ለሙሉ ፡ ሰነድም ፥ ላጪር ፡ ቃልም ፡ እኩል ፡ ያገለግላል ። ሙሉ ፡ የእንግሊዝኛ ፡ ሰነድን ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ ጻሕፍ ፡ የምንመልስ ፡ ቢኾን ፥ ሰነዱን ፡ ገና ፡ ስንከፍተው ፥ የጻሕፉ ፡ (ምዕራባዊ) ፡ እና ፡ የቋንቋው ፡ (እንግሊዝኛ) ፡ ዐይነት ፡ በቀጥታ ፡ ተለይቶ ፡ ይቀርብልናል ፤ ከዚያ ፥ "ሰነዱ ፡ ይመለስ" ፡ የሚለውን ፡ ዝራር ፡ መጠቈም ፡ ይበቃናል ፤ ሙሉው ፡ ሰነድ ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ ጻሕፍ ፡ ይመለስልናል ።

ቀደም ፡ ሲል ፥ ከጽሑፉ ፡ የቀዳነውን ፡ "Inter-Governmental Authority on Development" ፡ የሚለውን ፡ ቃል ፡ "የሚመለስ ፡ ቃል" ፡ እተባለው ፡ መስክ ፡ ውስጥ ፡ እናሰፍረውና ፥ እራስጌ ፥ ተመላሹን ፡ ጻሕፍ ፡ "የአሜሪካ ፡ እንግሊዝኛ ፡ በምዕራባዊ ፡ ጻሕፍ" ፡ የሚለውን ፡ ለይተን ፡ መርጠን ፥ "ቃሉ ፡ ይመለስ" ፡ የሚለውን ፡ ዝራር ፡ እንጠቀሜማለን ። ውጤቱን ፡ ግጻዌ ፡ 30 ፡ ያሳየናል ።

Figure 29: The AwdeQelem Transcriber

Figure 29: L'outil AwdeQelem Transcripteur

tool helps transcribe from American-English or Somali in Western script to American-English or Somali in Ethiopian script, be it: • an entire file (by opening the file to be transcribed, and pressing the "transcribe file" button); • or a snippet of text (by pasting it onto the field "to transcribe" and pressing the "transcribe expression" button). Following up on our earlier example, we paste "Inter-Governmental Authority on Development" onto the field "to transcribe", then set the script from which we intend to effect the trancription by selecting "English-USA in Western script" and press the "transcribe expression" button. The result of the transcription is shown in figure 30, below.	aide à transcrire de l'anglais-américain ou du somali en écriture occidentale vers l'anglais-américain ou le somali en écriture éthiopienne, que ce soit: • un fichier entier (en ouvrant le fichier à transcrire, puis en appuyant le bouton "transcrire fichier"); • ou un bout de texte (en le collant dans le champ "à transcrire", puis en appuyant le bouton "transcrire l'expression"). Reprenant notre exemple, on inscrit l'intitulé "Inter-Governmental Authority on Development" dans le champ "à transcrire", puis, après avoir sélectionné l'écriture à transcrire, on appui le bouton "transcrire l'expression". Le résultat de la transcription apparaît dans la figure 30, ci-dessous.

2.4.6 ፤ ኃሜሪካዊ ፡ እንግሊዝኛ ፡ ጽሑፎና ፡ የሶማልኛ ፡ ጽሑፎ ፡ ምለሳ ፡ ከምዕራባዊ ፡ ጸሕፎ ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ ጸሕፎ • Transcription of American English text and Somali text from Western Script to Ethiopian Script • Transcription de textes en anglais américain et en somali, de l'écriture occidentale vers l'écriture éthiopienne



ግጻዌ ፡ 30 ፤ እንሆ ፦ "Inter-Governmental Authority on Development" ፡ "ኢንተርጋቨርንሜንተል ፡ ኧቶሪቲይ ፡ ኦን ፡ ዲቬለፐመንት" ፡ ተብሎ ፥ ባሜሪካን ፡ እንግሊዝኛ ፡ ላሕይ ፡ ተመልሶልናል ።

ለብሪታንያ ፡ እንግሊዝኛ ፡ የሚበጀው ፡ መመለሻ ፡ ስላልደረሰልን ፡ ነው ፡ እንጂ ፥ እሱኛው ፡ ይህኑ ፡ ቃል ፡ ምናልባት ፦

"ኢንተርጋቨርንሜንተል ፡ ኦቶርቲይ ፡ ኦን ፡ ዲቨሎፐመንት" ፡ ይለው ፡ ይኾናል ።

ባሜሪካን ፡ እንግሊዝኛ ፡ ላሕይም ፡ ቢኾን ፥ ቃሉ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ፊደል ፡ አላንዳች ፡ አሻሚነት ፡ ተመልሶልናል ።

ይህ ፡ አህጉራዊ ፡ ቋንቋ ፡ ለኾነው ፡ ለእንግሊዝኛ ፡ ነው ። እንደ ፡ ዐረብኛ ፣ ፈረንሳይኛ ፣ ኤስፓኘኛ ፣ ወዘተ. ፡ ላሉ ፡ ሌሎች ፡ አህጉራውያን ፡ ቋንቋዎች ፡ ጽሑፎችን ፡ እንደዚሁ ፡ ወደኢትዮጵያ ፡ ጻሕፍ ፡ ለመመለስ ፡ የሚያስችሉ ፡ ክለሳዎችን ፡ ለማከታተል ፡ ዕቅድ ፡ አለ ።

የራሳችን ፡ ቋንቋ ፡ ለኾነው ፡ ለሶማልኛ ፥ መመለሻ ፡ ማብጀት ፡ ባላስፈለገ ፡ ነበር ፤ ምክንያቱም ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ጻሕፍ ፡ የተሻለ ፡ የሚያገለግለው ፡ ሌላ ፡ ጻሕፍ ፡ አይገኝለት ። ኾኖም ፥

• አንድም ፥ ሶማልኛ ፡ በጎረቤቶቻችንና ፡ እኅት ፡ አገሮቻችን ፡ ሶማልያና ፡ ጂቡቲ ፡ ስለሚነገርና ፥ መንግሥቶቻቸው ፥ ማማረጫን ፡ በማጣት ፥ የሮማይስጥን ፡ "ቁቤ" ፡ ጻሕፍ ፡ ስለ ፡ ያዙ ፤

• አንድም ፥ በኛው ፡ በኢትዮጵያችን ፥ ያንዳንድ ፡ ምዕራባውያን ፡ ኀይሎች ፡ ጣልቃ ፡ ገብነት ፡ ለልዩ ፡ ልዩ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ቋንቋዎች ፡ (ኦሮምኛን ፣ ሶማልኛ ፣ ዐፈርኛን ፣ ወዘተ.) ፡ ይህኑ ፡ "ቁቤ" ፡ ጻሕፍ ፡ በግድ ፡ ስላስጫነባቸውና ፥ ርስ ፡ በርሳቸውም ፡ እንዳይናበቡ ፡ አድርጎ ፡ ስለከፋፈላቸው ፤ ከኢትዮጵያዊ ፡ ጻሕፍ ፡ ሊለዩ ፡ የማይገባቸውን ፡ ለጊዜው ፡ የተለዩ ፡ ስላስመሰላቸውም ፤

በቀላሉ ፡ ወደኢትዮጵያ ፡ ጻሕፍ ፡ የሚመለሱበትን ፡ መንገድ ፡ መክፈት ፡ ለችግሩ ፡ ግማሽ ፡ መፍትሔን ፡ ያበጃል ።

ርግጥ ፡ ነው ፥ ሶማልኛን ፡ በምዕራባዊ ፡ ጻሕፍ ፡ ለመጻፍ ፡ ሲወስኑ ፥ በዚያው ፡ በፈረንጅኛው ፡ መፍቻ-ገበታና ፡ በፈረንጅኛው ፡ ቅርጸት ፡ በቀጥታ ፡ ለመሥራት ፡ አመችቷልና ፥ ዐዲስ ፡ መፍቻ-ገበታ ፡ መሥራት ፣

ዐዲስ ፡ ቅርጸት ፡ መቅረጽ ፡ አላስፈለጋቸውም ፤ በዚህ ፡ ረገድ ፡ ከ Unicode ፡ በፊት ፡ ጊዜያዊ ፡ ጥቅም ፡ ተገኝቶበት ፡ ይኾናል ። Unicode ፡ ከመጣ ፡ ወዲህ ፡ ግን ፥ ኹኔታው ፡ ፈጽሞ ፡ ስለ ፡ ተለወጠ ፥ ጉዳቱ ፡ ከጥቅሙ ፡ እጅጉን ፡ አመዝኗል ። እንደ ፡ "ቀ" ፣ "ሐ" ፣ "ዐ" ፣ "ጨ" ፣ "ጸ" ፣ "ዾ" ፣ ... ፡ ያሉ ፡ ድምፆች ፡ በምዕራባዊው ፡ ጸሕፍ ፡ ስለማይገኙ ፥ ያሉትን ፡ ፊደሎች ፡ ("Q" ፣ "H" ፣ "X" ፣ "C" ፣ "DH" ፣ ...) ፡ አለድምፃቸው ፡ ድምፅ ፡ በመስጠት ፡ ለዋውጦ ፡ አውሎ ፥ ባሻሚነት ፡ ሊጽፉባቸው ፡ ተገደዋል ።

ለምሳሌ ፡ "ሙሐመድ" ፡ የሚለውን ፡ ስም ፥

ሶማልኛ ፡ ተናጋሪው ፡ "muxaammad" ፡ ብሎ ፡ በቁቤ ፡ የጻፈውን ፥ አሮምኛ ፡ ተናጋሪው ፡ xaa ን ፡ "ሙጣመድ" ፡ ብሎ ፡ ያነበዋል ፤ ዐፈርኛ ፡ ተናጋሪው ፡ ደግሞ ፡ "ሙኻመድ" ፡ ብሎ ፡ ያነበዋል ።

እንደዚሁ ፡ ዐፈርኛ ፡ ተናጋሪው ፡ "mucaammad" ፡ ብሎ ፡ በቁቤ ፡ የጻፈውን ፥ አሮምኛ ፡ ተናጋሪው ፡ caa ን ፡ "ሙጫመድ" ፡ ብሎ ፡ ያነበዋል ፤ ሶማልኛ ፡ ተናጋሪው ፡ ደግሞ ፡ "ሙዓመድ" ፡ ብሎ ፡ ያነበዋል ።

በግልጽ ፡ እንደሚታየው ፥ ምዕራባዊው ፡ ጻሕፍ ፡ ኵሻውያን ፡ ቋንቋዎችንም ፡ ኾነ ፡ ሴማውያን ፡ ቋንቋዎችን ፡ ባንድ ፡ ዐይነት ፣ በትኽክል ፣ አላንዳች ፡ አሻሚነትና ፡ ፊደልን ፡ በመቈጠብ ፡ ሊጽፋቸው ፡ አልቻለም ። ለያንዳንዳቸው ፥ በጥግንግን ፥ በተበጀላቸው ፡ የቁቤ ፡ ጻሕፍ ፡ ርስ ፡ በርሳቸው ፡ እንደማይሰማሙና ፡ እንደማይናበቡ ፡ ኾነው ፡ ተከፋፍለው ፣ ተነጣጥለው ፣ አንሰውና ፡ ደክመው ፥ ምናልባት ፡ የእንግሊዝኛ ፡ ቀለብ ፡ ለመኾን ፡ ተደግሰዋል ።

ኹሉም ፡ ተመልሰው ፡ የኢትዮጵያን ፡ ጻሕፍ ፡ ሊያቅፉና ፡ መሠረታዊ ፡ አንድነታቸውን ፡ ሊያገኙበት ፥ እውኑ ፡ አያደር ፡ ይመራቸዋል ።

ተፈላጊነቱን ፡ ዐውቀው ፡ ሲጠባበቁ ፡ ለኖሩቱ ፦ እንሆ ፥ *ዐውደ ፡ ቀለም ፡ የጻሕፍ ፡ መመለሻ ፡ ለሶማልኛ!* ጥቅሙን ፡ ላላወቁቱ ፡ ደግሞ ፦ *እስቲ ፡ ምክሩት* ፡ እያልን ፡ እየጋበዝን ፥ በቁቤ ፡ የተጻፈ ፡ የሶማልኛ ፡ ሙሉ ፡ ሰነድ ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ ጻሕፍ ፡ እንዴት ፡ በቀላሉ ፡ እንደሚመለስ ፡ በተከታዩ ፡ ግጻዌ ፡ 31 ፡ እናሳያለን ።

Figure 30 : There it is, the accurate transcription of American-English text in Western script into American-English text in Ethiopian script.

An English-Amharic translation tool is not yet available; but armed with the AwdeQelem Dictionary tool, we can easily do the translation ourselves.

Finally, let us give an example transcription of a Somali text in Western script into one in Ethiopian script.

The Somali language is one of over 80 Ethiopian (Kushitic) languages. It is also spoken in the young Republics of Somalia and Djibouti, whose respective régimes adopted the Western script for writing the Somali language. The result of the decision is mixed. On the plus side, computer keyboard and font issues have been avoided; Somali can be written with a very limited set of letters (A-Z), but at a price. On the minus side, sounds not available in Western phonetics required the equivocation of some Western letters to represent those sounds (ዐሊ/'Ali became Caali; ሙሐመድ/Muhammed became

Figure 30 : Voila, la transcription fidèle d'un texte anglais-américain en écriture occidentale vers un texte anglais-américain en écriture éthiopienne.

Un outil de traduction anglais-amharique n'a pas encore vu le jour; mais, armés de l'outil Dictionnaire AwdeQelem, on peut facilement effectuer la traduction nous-même.

Enfin, donnons un exemple de transcription d'un texte somali en écriture occidentale vers celui en écriture éthiopienne.

La langue somali est une des plus de 80 langues éthiopiennes (couchitiques). Elle est aussi parlée dans la jeune République de Somalie, dont le précédent régime lui dota d'un système d'écriture utilisant les lettres occidentales. Le résultat de cette décision reste mitigé. Sur le coté positif, les problèmes de clavier et de police de caractères sont, d'office, évacués en faisant en sorte que le somali puisse s'écrire avec le minimum de lettres possible (A-Z); mais cela à un prix. Les sons absents de la phonétique occidentale nécessitèrent l'ambiguïté forcée de certaines

Muxaammad, etc.]. In addition, long vowels required the duplication of vowels, ultimately giving a less than economical writing system. Moreover, the limited nature of the vowel system further restrains the capacity of the Western inspired Somali script to precisely, unambiguously and briefly represent Ethiopian and foreign names, such as አበባ/Abeba rendered as Ababaa , ቱቢንገን/Tubingen rendered as Tubingan ("u" pronounced as "ou" and "e" as "é" in all cases), etc. As a result, the Somali script finds itself enclosed in a little ghetto of its own, similar to that in which such other languages as Afar and Oromo are required to be compartmentalised and isolated in.

This is where the Ethiopian script becomes interesting as it has very clear advantages in uniformly, unequivocally, precisely and economically catering for all the sound systems of Afro-Asiatic languages, or indeed any language family for that matter.

Here follows a transcription example for an entire Somali file written in the Western script (figure 31).

lettres latines pour représenter ces sons [ዐሊ/'Ali devient Caali, ሙሐመድ/Muhammed devient Muxaammad, etc.]. De plus, les voyelles longues requièrent une duplication de voyelle, ce qui finalement se traduit par un système d'écriture peu économique. De plus, le caractère restreint des voyelles disponibles rend limitée la capacité de cette écriture particulière d'inspiration occidentale de représenter de manière précise, brève et sans ambiguïté, des noms ou noms propres éthiopiens ou étrangers tel አበባ/Abeba rendu par Ababaa, ቱቢንገን/Tubingen rendu par Tubingan ["u" se prononçant comme "ou", et "e" comme "é" dans tous les cas], etc. L'écriture somali se retrouve, de fait, enfermée dans un petit ghetto à elle seule, similaire à celui dans lequel sont tenues à être cloisonnées et tout aussi isolées les langues Afar et Oromo, entre autres.

C'est là que l'écriture éthiopienne devient intéressante, du fait qu'elle a un avantage net quant à sa capacité à pourvoir, uniformément, sans ambiguïté, avec précision et de manière économique, aux besoins de tous les systèmes de sons, afro-asiatiques ou autres.

Voici à présent un exemple de transcription d'un fichier entier de texte somali en écriture occidentale vers l'écriture éthiopienne [figure 31].

የጻሕፎች ፡ ማነጻጸሪያ ፡ ሰንጠረዥ • Scripts' Correspondence Table • Table de correspondance d'écritures

(የኢትዮጵያ ፣ የዐረብ ፣ የምዕራብ ፣ የሶማልኛ-ቁቤ • Ethiopian, Arabic, Western, Western for Somali • éthiopienne, arabe, occidentale, occidentale pour le somali)

አ	በ	ቨ	ገ	ጘ	ደ	ዸ	ሀ	ወ	ዘ	ሐ	ኀ	ጠ	ጨ	የ	ከ	ለ	መ	ነ	ሠ	ዐ	ፈ	ጸ	ፀ	ቀ	ረ	ሰ	ሸ	ተ	ተ̄	ቸ	ጸ	ፐ
ا	ب	ڤ	ج	غ	د	ذ	ه	و	ز	ح	خ	ط	ظ	ي	ك	ل	م	ن	س	ه	ف	ص	ض	ق	ر	ص	ش	ت	ث	چ		پ
A	Be	Ve	Ge	Ghe	De	Dhe	Ha	We	Ze		Khe			Ye	Ke	Le	Me	Ne	Se		Fe	Tse		Qe	Re	Se	She	Te	The	Tche		Pe
A	Ba	Va	Ga	Gha	Da	Dha	Ha	Wa	Za	Xa	Kha			Ya	Ka	La	Ma	Na	Sa	Ca	Fa			Qa	Ra	Sa	Sha	Ta	Tha			Pa

ከ	ኩ	ኪ	ካ	ኬ	ክ	ኮ	ኰ	ኵ	ኲ	ኳ	ኴ	ኩ^	ኪ^	ኬ^	ኮ^					
ك	كُ	كِ	كى		كْ		كْوَ	كْوْ	كْوِ	كْوى										
Ke	Kou	Ki	Ka	Ké	K	Ko	Kwe	Kw	Kwi	Kwa	Kwé									
Ka	Ku	Ki	Kaa	Ke	K	Ko	Kwa	Kw	Kwi	Kwaa	Kwe	Kuu	Kii	Kee	Koo					

በምዕራባዊ ፡ ጻሕፍ ፡ "ቫወል" ፡ የተባሉት ፡ a ፣ e ፣ i ፣ o ፣ u ፣ ... ፡ አናባቢዎች ፡ በመኾናቸው ፥ "ኮንሶነንት" ፡ ቀድሚቸው ፥ ለብቻቸው ፡ እንዲነቡ ፡ የተፈለገ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፥ ጭረት ፡ ' ፡ ሊቀድማቸው ፡ ያሻል ። ታዲያ ፥ ቢያንስ ፡ ሦስት ፡ ዐይነት ፡ ጭረቶች ፡ ስላሉ ፡ (' ፣ ' ፣ ´) ፡ እና ፡ እነዚህ ፡ ጭረቶች ፡ ደግሞ ፡ ለጥቅስ ፡ ምልክትነትም ፡ ስለሚያገለግሉ ፥ አንዱን ፡ ብቻ ፡ (´) ፡ ለተናባቢነት ፡ ሚያ ፡ አውለነዋል ። ለምሳሌ ፦

la'aan በ ለ'ኣን ይመለሳል ፤ ×

la’aan በ ለ’ኣን ይመለሳል ፤ ×

la´aan በ ለኣን ይመለሳል ። ✓

ስለዚህ ፡ እተመላሹ ፡ ጽሑፍ ፡ ውስጥ ፡ ተናባቢው ፡ ጭረት ፡ ´ ፡ እንዲኾን ፡ ያሻል ። ርሱንም ፡ ለመምታት ፡ ALT ን ፡ ተጭኖ ፡ 0180 ን ፡ ከቍጥር ፡ ጠፍጣፉ ፡ መምታት ፡ ይበቃል ፤ ከዚያ ፡ መቀየር ፡ ያለባቸውን ፡ ጭረቶች ፡ ኹሉ ፡ በ"Find and Replace" ፡ መለወጥ ፡ ይቻላል ።

The Western alphabet letters are regrouped in two main categories: consonants and vowels. Any vowel preceded by a consonant will vocalise the consonant, unless a so-called "glottal stop" is interposed between them, as in :

la'an or la’an or la´an

However, these three strokes have different other roles as separators, apostrophes, etc. That is why, it is necessary to commit one of them to fulfil the role of a glottal stop, exclusively; we have chosen ´ which has ASCII code 180, and can be entered by pressing 0180 from the numeric keypad of your keyboard while pressing the ALT key, and all remaining occurrences can be replaced by "Find & Replace".

Therefore, before transcribing the Somali text in Western script into Ethiopian script, verify that the role of glottal stop

Les lettres de l'alphabet occidental sont regroupées dans deux catégories principales: consonnes et voyelles. Toute voyelle précédée d'une consonne vocalise la consonne qui la précède, à moins qu'un soi-disant "coup de glotte" ne s'intercale entre les deux comme cela:

la'an ou la’an ou bien la´an

Cependant, ces trois traits jouent différents roles: ceux d'apostrophes, de séparateurs, etc. C'est pourquoi il est nécessaire de confier exclusivement le rôle de coup de glotte à l'un d'entre eux; nous avons choisi ´ qui a un code ASCII 180, et peut être écrit en appuyant 0180 sur les touches du pavé numérique de votre clavier, tout en appuyant la touche ALT, et en remplaçant le restant des occurrences en utilisant "trouver et remplacer".

Par conséquent, avant de transcrire le texte somali en écriture occidentale vers

is played by ʼ and not by ' or ʾ, since the resulting transcription differs, as the following example shows:

la'aan is transcribed into ለ'አን ×

laʾaan is transcribed into ለʾአን ×

laʼaan is transcribed into ለአን ✓

celui en écriture éthiopienne, vérifiez que le rôle de coup de glotte est bien joué par ʼ et non par ' ou ʾ, puisque le résultat de la transcription en sera affectéé, comme nous le montre l'exemple suivant:

la'aan is transcribed into ለ'አን ×

laʾaan is transcribed into ለʾአን ×

laʼaan is transcribed into ለአን ✓



ግጸዊ ፡ 32 ፤ "ሰነዱ ፡ ይከፈት" ፡ የሚለውን ፡ ዝራር ፡ ጠቍመን ፥ የተባበሩት ፡ መንግሥታትን ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ መብቶች ፡ ብሔራዊ ፡ ድንጋጌን ፡ የሶማልኛ ፡ ትርጕም ፡ የያዘውን ፡ ሰነድ ፡ ከዐውደ ፡ ቀለም ፡ የሶማልኛ ፡ ማኅደር ፡ ለይተን ፡ እንከፍትና ፥ "ሰነዱ ፡ ይመለስ" ፡ የሚለውን ፡ ዝራር ፡ ስንጫን ፥ ጠቅላላው ፡ ጽሑፍ ፡ በቅጽበት ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ ጻሕፍ ፡ ይመለስልናል ፤ የተመለሰውም ፡ ሰነድ ፡ ስም ፡ ነባሩ ፡ የሰነድ ፡ ስም ፡ ኾኖ ፡ "_MLASH" ፡ የሚል ፡ ቅጽል ፡ በጫፍ ፡ ይቀጠልበታል ። ዐይነተኛው ፡ ጽሑፍና ፡ ምላሹ ፡ ጐን ፡ ለጐን ፡ ተነጻጽረው ፡ ይታዩናል ። ንበትን ፡ ለማርዘም ፡ ምዕራባዊው ፡ ጻሕፍ ፡ አናባቢን ፡ ሲደጋግም ፡ (A ▶ AA ፣ O ▶ OO ፣ ወዘተ.) ፥ ኢትዮጵያዊው ፡ ጻሕፍ ፡ ግእዙን ፡ ራብዕ ፡ (አ ▶ ኣ) ፥ ሌሎቹን ፡ ዐጽቆች ፡ ደግሞ ፡ በማርዘሚያ ፡ ምልክት ፡ ያረዝማል ፡ (ኡ ▶ ኡ^ ፣ ኢ ▶ ኢ^ ፣ ወዘተ.) ፤ (ም. ፤ ምዕራባዊው ፡ ጻሕፍ ፦ QOF KASTAA WUXUU XAQ U LEEYAHAY NOLOL, XORRIYO IYO NABAD GELYO ፡ ብሎ ፡ የጻፈውን ፥ ኢትዮጵያዊው ፡ ጻሕፍ ፦ ቆፍ ፡ ከስታ ፡ ዉሑ^ ፡ ሐቅ ፡ ኡ ፡ ሌ^የሀይ ፡ ኖሎል ፥ ሖሪዮ ፡ ኢዮ ፡ ነበድ ፡ ጌልዮ ፡ ብሎ ፡ ይጽፈዋል ።) እሰነድ ፡ መሳተፊያው ፡ ላይ ፡ እንደምናየው ፥ በ 11660 ፡ የቁቤ ፡ ፊደላት ፡ የተጻፈው ፡ የሶማልኛ ፡ ጽሑፍ ፥ በ 5946 ፡ የኢትዮጵያ ፡ ፊደላት ፡ ብቻ ፡ ተመልሷል ፡ (-50%) ። እንዲህ ፡ የተመለሰውን ፡ ሰነድ ፡ በዐውደ ፡ ቀለም ፡ የጽሑፍ ፡ ማምረቻ ፡ ከፍተን ፥ በፊደል ፡ ማረሚያው ፡ ዕርማቱን ፡ ልናከናውን ፡ እንችላለን ።

Figure 32: Let us click the "open file" button and open the Somali version of the "Universal Declarations of Human Rights" found in the Somali folder of AwdeQelem then press the "transcribe file" button. The opened file is fast transcribed into the Ethiopian script, saved with a suffix "_MLASH" added automatically to the file-name, and its transcription displayed next to the original text.

Figure 32: Appuyons le bouton "ouvrir le fichier" pour ouvrir la version somali de la "Déclaration Universelle des Droits de l'Homme" depuis le dossier somali de AwdeQelem; appuyons ensuite le bouton "transcrire le fichier". Le fichier ouvert est rapidement transcrit en écriture éthiopienne, sauvegardé avec un suffixe "_MLASH" ajouté automatiquement au nom de ficher, et son contenu affiché à coté du texte original.

In the Western script, long vowels are represented by the doubling of vowels (ex. E▸EE); whereas in the Ethiopian script a special sign is used for that purpose (ኤ ▶ ኤ^), except for the (A▸AA) sound where the first and fourth orders are used instead, as in the case of the Arabic "fetha/lengthening Alif" (አ ▶ ኣ).

On the filing interface at the top of the screen, the characters ratio Western/Ethiopian of 11660/5946 is indicated, showing a nearly 50% reduction in character use due to the transcription.

The transcribed file may now be re-opened from AwdeQelem Text Processor for further spell-checking if that were required (Figure 33).

L'écriture occidentale représente les voyelles longues en doublant les voyelles [E▸EE], alors que l'écriture éthiopienne utilise un signe spécial [ኬ▸ኬ^], à l'exception des voyelles [A▸AA] qui sont représentées par le 1er et 4ème ordre de ከ [ከ▸ካ], à la manière du "fetha/Alif long" arabe.

Comme il est indiqué sur l'en-tête de l'écran, dans l'interface de fichage, le ratio de caractères occidentaux/éthiopiens de 11660/5946 signifie une réduction de près de 50% du nombre de caractères utilisés par la transcription.

Le fichier transcrit peu maintenant être ouvert à partir du traitement de texte AwdeQelem, s'il s'avérait nécessaire de procéder à la vérification de son orthographie [Figure 33].



ግጸዌ ፡ 33 ፤ ለሶማልኛ ፡ ጽሑፍ ፡ ሙሉ ፡ የፊደል ፡ ማረሚያን ፡ ለማብጀት ፡ ቋንቋውን ፡ አስቀድሞ ፡ ማወቅ ፡ ያሻል ። ቋንቋውን ፡ ስለማላውቀው ፥ ከታረሙ ፡ መጻሕፍትና ፡ መዛግብተ ፡ ቃላት ፡ የዋና ፡ ዋና ፡ ቃላትን ፡ ዝርዝር ፡ በመልቀምና ፡ በመቀመር ፥ አነስተኛ ፡ ዕርማትን ፡ የሚያስችል ፡ የፊደል ፡ መጠ̊ንቀቂያ ፡ ተሰናድቷል ። ሶማልኛ ፥ እንደ ፡ ዐማርኛ ፡ ወይም ፡ ግእዝ ፥ አንቀጽን ፡ በአዕማድ ፡ የማርባት ፡ ጠባይ ፡ ባይኖረውም ፥ ቃላትን ፡ በመዘርዘርና ፡ በማዋሐድ ፡ ግን ፡ ይመስላቸዋል ። ስለዚህ ፥ የፊደል ፡ መጠ̊ንቀቂያ ፡ በቀላሉ ፡ ሊሠራለት ፡ አይቻልም ፤ የቡድን ፡ ሥራ ፡ ነው ። በሥራው ፡ የተጠመዱ ፡ ቢኖሩ ፥ ይህ ፡ የዐውደ ፡ ቀለም ፡

ኻሮምር ፡ የተሻለ ፡ ሥራን ፡ ለመሥራት ፡ ይበልጡን ፡ ይገፋፋቸዋል ፡ ብዬ ፡ ተስፋ ፡ አደርጋለኹ ።

እላይ ፡ የምናየው ፡ በኢትዮጵያ ፡ ፊደል ፡ የተጻፈን ፡ የሶማልኛ ፡ ጽሑፍ ፡ ዕርማት ፡ ነው ። ባረንጓዴ ፡ ቀለም ፡ የተመለከቱት ፡ እመዝገበ ፡ ቃላት ፡ ውስጥ ፡ የሚገኙ ፡ ቃላት ፡ ናቸው ። ሰነዱ ፡ ቃላት ፡ ከተለቀመባቸው ፡ የታረሙ ፡ ሰነዶች ፡ አንዱ ፡ በመኾኑ ፥ ቃላቱ ፡ ኹሉ ፡ ባረንጓዴ ፡ ቀለም ፡ ቀልመው ፡ ይታያሉ ፤ አያስደንቅም ። ኾኖም ፥ እላይ ፡ እንደ ፡ ገለጽኹት ፥ የሶማልኛ ፡ ግስ ፥ እንዳማርኛ ፡ የመዘርዘር ፡ ጠባዩ ፡ እጅግ ፡ የዳበረ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፥ ቃላቱ ፡ ተለቅመው ፡ አያልቁም ። ነገር ፡ ግን ፥ ዝርዝሩን ፡ ትቶ ፥ የቃሉን ፡ ዘር ፡ ወይም ፡ ስም ፡ በመያዝ ፡ ብቻ ፡ አብዛኛውን ፡ የፊደል ፡ ስሕተት ፡ ሊጠንቅቁበት ፡ ይቻላል ። በዚህ ፡ ዐይነት ፥ ቀለም ፡ አልባ ፡ የኾኑትን ፡ ቃላት ፡ ኹሉ ፡ (ማለት ፥ ባረንጓዴ ፡ ቀለም ፡ ያልተመለከቱትን) ፡ አንድ ፡ ባንድ ፡ በማጣራት ፡ ስሕተትነታቸውን ፡ ማግኘትና ፡ ማረም ፡ ይቻላል ። አስቀድሞ ፡ ግን ፥ የተመዘገበው ፡ ግስ ፡ ብዛት ፡ አኹን ፡ ካለበት ፡ (≃50000 ፡ ቃላት) ፡ መጠን ፡ 3 ፡ ወይም ፡ 4 ፡ ዕጥፍ ፡ ማደግ ፡ ይኖርበታል ።

Figure 33: To develop a complete spell-checker for Somali, one needs at least to know the language. As I do not speak the Somali language, the intention here is to provide instead a small set of Somali words extracted from spell-checked Somali text, to serve as a word-base against which basic spell-checking can be done.

To those linguists and informaticians already working on such a Somali project, I hope AwdeQelem will provide further impetus.

AwdeQelem's Somali spell-checker comes in two varieties: Somali in Western script, and Somali in Ethiopian script. Figure 29 shows us the latter.

Once again, green shows that the word is correctly spelt (it is in the dictionary). In fact, as the above file has served as a source document from which Somali words have been extracted to populate the spell-checker word-base, logically all of its words are perfectly spelt! Nevertheless, as the Somali language is a highly inflectional language, its lexicon is extremely large; therefore the spell-checker word-base must be expanded further from its current size of ≃50000 Somali words by a factor of 3 or 4 to become really interesting. Having said that, it is still possible to carry out decent spell-checking with the capacities offered by AwdeQelem.

Figure 33: Développer un correcteur orthographique complet pour la langue somali nécessite a priori la connaissance de la langue. Ne parlant pas le somali, mon intention est d'offrir une base de mots somalis extraits de documents textuels vérifiés, pouvant servir à la vérification orthographique de textes.

J'espère que l'illustration offerte ainsi par AwdeQelem donnera aux linguistes et informaticiens déjà penchés sur un tel projet somali, une impulsion supplémentaire pour venir à bout.

Le correcteur orthographique somali de AwdeQelem a deux versions: somali en écriture occidentale, et somali en écriture éthiopienne. Figure 29 nous illustre celle-ci.

Encore une fois, la couleur verte indique que le mot est correctement orthographié [présent dans le dictionnaire]. En réalité, le fichier concerné a déjà servi de base d'extraction de mots somalis pour le correcteur orthographique; par conséquent, la totalité de ses mots est parfaitement orthographiée! Ceci dit, comme la langue somali est très flexionnelle, son lexique est assez considérable, nécessitant une multiplication par 3 ou 4 de la taille présente du correcteur orthographique qui ne compte que quelques ≃50000 mots, pour qu'il devienne vraiment intéressant. Il est tout de même, encore possible d'effectuer une correction automatique relativement efficace avec les capacités offertes par AwdeQelem.

2.4.7 ፤ የቃላት ፡ መተለሰያና ፡ የጽሑፍ ፡ መሰደሪያ • WordList Maker and Text Sorter • "Établisseur" de liste de mots et trieur de texte



ግጸዌ ፡ 34 ፤ ባንድ ፡ ጽሑፍ ፡ ውስጥ ፡ የሰፈሩ ፡ ቃላትን ፡ በነጠላ ፡ ለቅሞ ፡ ለመሰነድ ፡ የሚያስችል ፡ ዐዲስ ፡ ግብረት ፡ በዐውደ ፡ ቀለም ፡ ክለሳ ፡ 1.3 ፡ ታክሏል ። እላይ ፡ የምናየው ፡ ከ 1922 ፡ ዓ.ም. ፡ እስከ ፡ 2002 ፡ ዓ.ም. ፡ የዓለም ፡ የእግር ፡ ኳስ ፡ ዋንጫ ፡ አሸናፊዎች ፡ ሀገሮችን ፡ ዝርዝር ፡ ነው ። እጽሑፉ ፡ ውስጥ ፡ የሰፈሩት ፡ ቃላት ፡ በሙሉ ፡ በ"ሀ-ለ-ሐ-መ" ፡ የፊደል ፡ ተራ ፡ እ"ቃል ፡ ተራ • WordList" ፡ ዐምድ ፡ ውስጥ ፡ ተዘርዝረዋል ። እነዚህን ፡ የተዘረዘሩ ፡ ቃላት ፡ በተለየ ፡ ሰነድ ፡ ለመመዝገብ ፡ ብንፈልግ ፥ እ"ዝግጅት • Editing • Édition" ፡ መምረጫው ፡ ላይ ፡ "የቃላት ፡ ተራው ፡ ይከሠት ፡ ወይም ፡ ይመዝገብ" ፡ የሚለውን ፡ ንኡስ ፡ መምረጫ ፡ በመጠቈም ፡ ግብረቱን ፡ እናስነሣለን ። ።

Figure 34: Version 1.3 of AwdeQelem has added a new functionality for saving the list of words in a given text document. Shown above is the list of countries that have won the football World Cup between 1930 and 2010 A.D.. In the adjoining "ቃል ፡ ተራ • WordList" column, the list of words is already automatically listed in alphabetical order. To save the list of words into a file, click the "ዝግጅት • Editing • Édition" menu entry, then click again the "display or save wordlist" sub-menu entry.

Figure 34: La version 1.3 de AwdeQelem a ajouté une nouvelle fonction permettant de sauvegarder la liste de mots d'un document donné. Figure ci-dessus la liste des pays vainqueurs de la Coupe du Monde de football entre 1930 et 2010 A.D.. Dans la colonne voisine "ቃል • WordList" figure déjà, par ordre alphabétique, la liste des mots du texte. Pour sauvegarder cette liste de mots dans un fichier, il suffit de cliquer sur le menu "ዝግጅት • Editing • Édition", puis cliquer encore sur le sous-menu "afficher ou sauvegarder la liste des mots".



ግጻዌ ፡ 35 ፤ የቃላት ፡ መተረሪያው ፡ መሳተፊያ ፡ ላይ ፡ እንደምናየው ፥ የቃላቱ ፡ ዝርዝር ፡ ሰፍሮልናል ። በንፈልግ ፡ እንዳለ ፡ እንመዘግበዋለን ፥ አለዚያም ፥ የምንለዋውጠው ፡ ነገር ፡ ቢኖር ፡ ለዋውጠን ፡ ስንጨርስ ፡ እንመዘግበዋለን ።

Figure 35: As shown on the dialogue of the wordList maker, the list of words is displayed. Depending on our choice, we may save it in a file as is, or, we may bring modifications to it before saving it.

Figure 35: Dans l'interface de l'"établisseur" de liste de mots, apparaît la liste des mots. Selon notre souhait, on peut soit sauvegarder la liste telle-quelle, ou bien on peut lui apporter quelques modifications avant de la sauvegarder.



ግጸዊ ፡ 36 ፤ ባንድ ፡ ጽሑፍ ፡ ውስጥ ፡ የሰፈሩ ፡ መሥመሮችን ፡ ለመሰደርና ፡ ለመመዝገብ ፡ የሚያስችል ፡ ዐዲስ ፡ ግብረት ፡ በዐውደ ፡ ቀለም ፡ ክለሳ ፡ 1.3 ፡ ታክሏል ። እላይ ፡ የምናየው ፡ ከ 1922 ፡ ዓ.ም. ፡ እስከ ፡ 2002 ፡ ዓ.ም. ፡ የዓለም ፡ የእግር ፡ ኳስ ፡ ዋንጫ ፡ አሸናፊዎች ፡ ሀገሮችን ፡ ዝርዝር ፡ ነው ። እነዚህን ፡ በመሥመር ፡ የተዘረዘሩ ፡ ልቅሞች ፡ በ"ሀ-ለ-ሐ-መ" ፡ ተራ ፡ ሰድሮ ፥ በተለየ ፡ ሰነድ ፡ መመዝገብን ፡ ብንፈልግ ፥ እ"ዝግጅት • Editing • Édition" ፡ መምረጫው ፡ ላይ ፡ "ጽሑፉ ፡ በመሥመር ፡ ይሰደር" ፡ የሚለውን ፡ ንኡስ ፡ መምረጫ ፡ በመጠቈም ፡ ግብረቱን ፡ እናስነሣለን ።

Figure 36: Version 1.3 of AwdeQelem has added a new functionality for saving a given text document after sorting it by line. To that effect, click the "ዝግጅት • Editing • Édition" menu entry, then click again the "sort text by line" sub-menu entry.

Figure 36: La version 1.3 de AwdeQelem a ajouté une nouvelle fonction permettant de trier par ligne le contenu d'un document avant de le sauvegarder dans un fichier. Pour ce faire, il suffit de cliquer sur le menu "ዝግጅት • Editing • Édition", puis cliquer encore sur le sous-menu "trier le texte par ligne".



ግጸዊ ፡ 37 ፤ ከዚያ ፥ የቀደመው ፡ ጽሑፍ ፡ በዐዲስ ፡ መሳተፊያ ፡ ውስጥ ፡ ይከሠትልንና ፥ ይዘቱን ፡ በመሥመር ፡ ለመሰደር ፡ ያስችለናል ፤ ስንሰድረው ፡ ግን ፥ አንድ ፡ ዐይነት ፡ የኾኑትን ፡ መሥመሮች ፡ ሳንቀንስ ፡ ልንመዘግባቸው ፡ ብንወድ ፥ "ጽሑፉ ፡ በመሥመር ፡ ይሰደር" ፡ የሚለውን ፡ ዝራር ፡ እንጫናለን ፡ (ግጸዊ ፡ 38) ፤ አንድ ፡ ዐይነት ፡ የኾኑትን ፡ መሥመሮች ፡ ልናስወግዳቸው ፡ ብንወድ ፡ ደግሞ ፥ "ጽሑፉ ፡ በነጠላ ፡ መሥመር ፡ ይሰደር" ፡ የሚለውን ፡ ዝራር ፡ እንጫናለን ፡ (ግጸዊ ፡ 39) ። የተሰደረውን ፡ ጽሑፍ ፡ ከመመዝገባችን ፡ በፊት ፥ ሌሎች ፡ ለውጦችን ፡ ለናደርግለትም ፡ እንችላለን ።

Figure 37: Then, the original text appears in a new dialogue where it is possible for us to sort the list either with duplicates by pressing the "sort text by line" button (figure38), or without duplicates by pressing the "sort text by line without duplicates" button (figure 39). We may bring further modifications to the sorted text before saving it.

Figure 37: Apparaît alors le texte original dans un nouveau dialogue où il nous est maintenant possible de trier la liste soit avec répétition[s] en cliquant le bouton "trier le texte par ligne" [figure 38], soit sans répétition[s] en cliquant le bouton "trier le texte par ligne sans répétitions" [figure 39]. On peut apporter d'autres modifications au texte ainsi trié, avant de le sauvegarder.

ግጻዌ ፡ 38 ፤ በመሥመር ፡ የተሰደረው ፡ ጽሑፍ ።

Figure 38: The text as sorted with duplicates.	Figure 38: Le texte tel qu'il est trié avec répétition[s].



ግጻዌ ፡ 39 ፤ በነጠላ ፡ መሥመር ፡ የተሰደረው ፡ ጽሑፍ ።

Figure 39: The text as sorted without duplicates.	Figure 39: Le texte tel qu'il est trié sans répétition[s].

2.5 ፤ ተደጋጋሚ ፡ ጥያቄዎች • Frequently asked questions • Questions fréquemment posées

<table>
<tr><td rowspan="2">1</td><td colspan="2">• የዐውደ ፡ ቀለም ፡ ክ.1 ፡ መስኮት ፥ ባንዳንድ ፡ መታያዎች ፡ ላይ ፥ መጠኑ ፡ እየተትረፈረፈ ፡ ተሟልቶ ፡ አይታይም ። መፍትሔው ፡ ምን ፡ ይኾን ፧

▶ ይህም ፡ ችግር ፡ ከዐውደ ፡ ቀለም ፡ ክ.1 ፡ አፈጣጠርና ፡ ከመታያው ፡ የጥቃቄ ፡ መጠን ፡ ማነስ ፡ ይነሣል ። ፊተኛው ፡ መፍትሔ ፡ ይህኑ ፡ የጥቃቄ ፡ መጠን ፡ ከቊጥጥር ፡ ሰሌዳው ፡ ማሳደግ ፡ ነበር ፤ ከክ.1.1 ፡ ወዲህ ፡ ግን ፥ የዐውደ ፡ ቀለም ፡ ገጽ ፡ ላነስተኛም ፡ የመታያ ፡ ጥቃቄ ፡ መጠን ፡ እንዲስማማ ፡ ኾኖ ፡ ተሻሽሏል ።</td></tr>
<tr><td>• The window of AwdeQelem v.1 does not fit properly on my computer screen, as if it were oversized. What is the solution?

▶ This was mainly due to the way AwdeQelem was made, and the lower resolution of the screens in question. The temporary solution was to increase the screen resolution from the Control Panel. In v.1.1 of</td><td>• La fenêtre de AwdeQelem v.1 paraît quelque peu sur-dimensionnée sur l'écran de mon ordinateur. Quelle est la solution?

▶ Cela provient de la façon dont AwdeQelem est conçu dans sa version 1, ainsi que de la faiblesse de la résolution des écrans en question. La solution provisoire consistait à augmenter la résolution de l'écran à partir du Panneau de Configuration. Dans la v.1.1, cela est</td></tr>
</table>

<table>
<tr><td></td><td>AwdeQelem, this is now corrected, without the need to increase screen resolution.</td><td>maintenant corrigé: AwdeQelem devrait s'accorder à l'écran sans avoir à accroitre la résolution.</td></tr>
<tr><td rowspan="2">2</td><td colspan="2">• በዐውደ ፡ ቀለም ፡ ክ.1 ፡ የጽሑፍ ፡ ማምረቻ ፥ "ኹሉም ፡ ይተካ" ፡ የሚለውን ፡ ዝራር ፡ ስጫን ፥ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ መግበሩ ፡ እማያቋርጥ ፡ አዙሪት ፡ ውስጥ ፡ ይገባና ፥ አይሠራም ፨
▶ እውነት ፡ ነው ፤ ቅምሩ ፡ ውስጥ ፡ አንድ ፡ ያገባብ ፡ ስሕተት ፡ ተደርጎ ፥ ለተወሰኑ ፡ አተካኮች ፡ መግበሩ ፡ እማያቋርጥ ፡ አዙሪት ፡ ውስጥ ፡ ይገባና ፥ ፈፅመን ፡ ልናቋርጠው ፡ እንገደዳለን ። ይህ ፡ ችግር ፡ በክ.1.1 ፡ ፈጽሞ ፡ ተወግዷል ።</td></tr>
<tr><td>• In AwdeQelem v.1's text processor, the "replace all" function goes into an infinite loop for certain combinations of words. Is there a solution?
▶ It is true; a logic error in the code has been causing this problem: it has now been identified, and corrected in v.1.1.</td><td>• Dans la v.1 du traitement de texte AwdeQelem, la fonction "tout remplacer" entre dans une boucle infinie pour certaines combinaisons de mots. Existe-t-il une solution?
▶ Il est vrai; une erreur logique dans le programme est à l'origine de ce problème: elle est maintenant identifiée, et corrigée dans la v.1.1.</td></tr>
<tr><td rowspan="2">3</td><td colspan="2">• ዐውደ ፡ ቀለም ፡ ለአፕል ፡ ማክ ፡ ታቅዷልን ፨
▶ አልታቀደም ።</td></tr>
<tr><td>• Should we expect an Apple Mac version of AwdeQelem in the near future?
▶ No, not envisaged.</td><td>• Une version Apple Mac de AwdeQelem est elle envisagée dans avenir proche?
▶ Non, elle n'est pas envisagée.</td></tr>
</table>

2.6 ፤ ወደ ፡ ፊት • perspectives

ዐውደ ፡ ቀለም ፡ ሊያከናውናቸው ፡ የሚገቡ ፡ ሌሎች ፡ ብዙ ፡ ግብሮች ፡ አሉ ፤ ለጥቀው ፡ ከተመለከቱት ፡ ውስጥ ፥ የመዠመሪያው ፡ ብቻ ፡ እመጠናቀቅ ፡ ደረጃ ፡ የደረሰ ፡ሲኾን ፥ የቀሩት ፡ በውጥንነት ፡ አለዚያም ፡ በሐሳብነት ፡ ወይም ፡ በዕቅድነት ፡ እዚህ ፡ ተዘርዝረዋል ፦

- *የሰነድ ፡ ማቀመሪያ ፡ መግበር* ፡ (በኢትዮጵያዊ-ANSI ፡ አቀማመር ፡ የተጻፈን ፡ ሰነድ ፡ ወደ ፡ ዓለም ፡ ዐቀፉ ፡ UNICODE ፡ አቀማመር ፡ ለመመለስ ፡ የሚያስችል ፡ መግበር ፤ መግበሩ ፡ ለዋዜማ-ANSI ፣ ለአጋቦስ-Mac ፣ ለኢትዮ-ሲስተምዝ-ዋሽራ-ANSI ና ፡ ለሌሎችም ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ አቀማመሮች ፡ ተጠናቆ ፥ ምለሳው ፡ የሚከናወነው ፡ በ HTML ፡ አቀጻጽ ፡ ለተቀጹ ፡ ሰነዶች ፡ በመኾኑና ፥ የ HTML ፡ አቀጻጽም ፡ በእየጊዜው ፡ ባዳዲስ ፡ ደንቦች ፡ (html ፡ 3 ፣ 4 ፣ 5...) ፡ በመለዋወጡ ፡ ምክንያት ፥ ወጥ ፡ የኾነ ፡ መግበርን ፡ ከዐውደ ፡ ቀለም ፡ ጋራ ፡ ለማዋሐድ ፡ ለጊዜው ፡ አልተቻለም ፡ (የማቀመሩን ፡ ሥራ ፡ ለማካኼድ ፡ የሚሹ ፡ ቢኖሩ ፥ በተለይ ፡ ሊያነጋግሩኝ ፡ ይችላሉ) ፤
- *የግእዝ-ዐማርኛ ፡ የርባታ ፡ መግበር* ፤
- *የቀን ፡ መቍጠሪያ ፡ መመለሻና ፡ የበዓላት ፡ ማውጫ ፡ መግበር* ፤
- *የንምር ፡ ጽሑፍ ፡ ማንጠሪያ ፡ መግበር* ፡ ለኢትዮጵያውያንና ፡ ምዕራባውያን ፡ ኅርመቶች ፤

- *መተርጐሚያ ፡ መግበር* ፡ (በተለይ ፡ እንግሊዝኛ-ዐማርኛና ፡ ፈረንሳይኛ-ዐማርኛ) ፤
- *ያማርኛ ፡ አገባብ ፡ መጠ̊ንቀቂያ ፡ መግበር* ፤
- *ወዘተ.*

AwdeQelem could still be further enhanced with additional functionalities. Of those listed below, the first only has reached a state of near completion; the rest are either in progress, or projected, or merely suggested works:

- *File transcoding tool* (from Wazéma-ANSI, Agabos-Mac, EthioSystems-Washera-ANSI, and other Ethiopian encodings, to the global encoding UNICODE), currently accepting HTML formatted files, but its finalisation delayed by successive changes to the HTML standard. Those interested can contact me directly.
- *G'z and Amharic lexical generation tool*.
- *Calendar conversion tool*.
- *Optical character recognition (O.C.R.) tool* for Ethiopian and Western characters.
- *Translation tool* (particularly English-Amharic and French-Amharic).
- *Amharic grammar checker*.
- Etc.

AwdeQelem peut encore s'enrichir de fonctions additionnelles. Parmi celles listées ci-dessous, seule la première a atteint le stade d'achèvement; les autres sont soit des travaux en cours, soit simplement listés à titre de projet ou de suggestion:

- *Outil de trans-codage de fichier* [depuis Wazéma-ANSI, Agabos-Mac, Ethio-Systems-Washera-ANSI, et autres codages éthiopiens, vers le standard mondial UNICODE], acceptant, dans son état actuel, uniquement des fichiers de format HTML, mais sa finalisation retardée par la série de changements dans le standard HTML. Ceux que cela intéresse peuvent me contacter directement.
- *Outil de génération lexical pour le g'z et l'amharique*.
- *Outil de conversion de calendrier*.
- *Outil de reconnaissance optique de caractères [R.O.C.]* pour les caractères éthiopiens et occidentaux.
- *Outil de traduction* [particulièrement français-amharique et anglais-amharique].
- *Correcteur grammatical amharique*.
- Etc.

፲ • ፫

ስለግእዝ-ዐማርኛ ፡ ቃላት ፡ አጻጻፍ ፣ አገባብና ፡ ትርጕም ፡ መጠንቀቅ

Notes on G'z-Amharic spelling, grammar and semantic checking • brèves observations sur la correction orthographique, grammaticale et sémantique g'z-amharique

(ከዋዜማ ፡ ሥርዐት ፡ መመሪያ ፡ ተቀንጭቦና ፡ በመጠኑ ፡ ተዘምኖ ፡ ዳግመኛ ፡ የቀረበ ።)

'ስሕተትም ፡ የሠለጠነበት ፡ ምክንያት ፥ ጥፈትና ፡ ትምርት ፡ ተባብረው ፡ ባንድ ፡ ሰው ፡ እጅ ፡ ስላልተገኙ ፡ ነው ። ጥፈት ፡ የማያውቁ ፡ መምህራን ፥ የተጣፈውን ፡ ከመተርጐም ፡ በቀር ፥ የጸሐፍትን ፡ ስሕተትና ፡ ግድፈት ፡ ማረምና ፡ ማቅናት ፡ እንዳይችሉ ፥ ሰዋስው ፡ የማያውቅ ፡ ጸሓፊም ፡ መልክአ ፡ ፊደሉን ፣ ሐረጉን ፣ ቅጠሉን ፣ አጣጣሉን ፡ ብቻ ፡ ከማሳመር ፡ በቀር ፥ ንባቡንና ፡ አገባቡን ፡ አጥርቶ ፡ ማወቅ ፥ ፊደሉን ፡ መጠንቀቅ ፡ አይችልም ። '

ኪዳነ ፡ ወልድ ፡ ክፍሌ ፥ መጽሐፈ ፡ ሰዋስው ፥ ገ.6

ቃል ፥ ከባለቤቱ ፡ ዘንድ ፡ በድምፅ ፡ ወይ ፡ በጽሑፍ ፡ ወጥቶ ፡ እተቀባዩ ፡ ዘንድ ፡ ሲደርስ ፥ መልእክቱን ፡ አስተላልፎ ፥ የተፈለገውን ፡ ለውጥ ፡ ወይም ፡ ውጤት ፡ እንዲያስገኝ ፥ በትኽክል ፡ ተነግሮ ፥ በትኽክል ፡ መንበብ ፣ መነበብ ፥ ወይም ፡ መድመጥ ፣ መደመጥ ፡ ይኖርበታል ። ትኽክልነት ፡ ሲጓደል ፥ ውጤትም ፡ ይጓደላል ። ይህ ፡ ለንግግርም ፣ ለጽሑፍም ፡ ይረጋል ።

ንግግርና ፡ ጽሑፍ ፡ በእግረኛና ፡ በመኪነኛ ፡ አካኼድ ፡ ይመሰላሉ ።

እግረኛ ፡ መንገዱን ፡ ሲኼድ ፥ እንዳመቸው ፥ በመንገዱ ፡ ግራም ፡ ቀኝም ፡ መኻልም ፡ ሊኾን ፡ ይችላል ፤ ግፋ ፡ ቢል ፥ ያክብሮትና ፡ የመሳሰሉ ፡ ወጎችና ፡ ባህሎች ፡ ይኖሩታል ። በማነኛውም ፡ ኹኔታ ፥ ጕዳቱ ፡ መለስተኛ ፡ ስለሚኾን ፥ እግረኛ ፡ የ"ትራፊክ" ፡ ሕግ ፡ የለበትም ። እንደዚሁ ፥ ንግግር ፥ ብዙውን ፡ ጊዜ ፡ አገባብን ፡ አይጠነቀቅም ፥ አረፍተ ፡ ነገርን ፡ አይሞላም ፤ በዘዬ ፡ እያቈላመጠ ፥ በቃለ ፡ አጋኖ ፡ እየደገፈ ፥ በቃለ ፡ አኅስሮ ፡ እየገደፈ ፥ ድምፅን ፡ እያገነታ ፡ ወይም ፡ እያሾከሾከ ፥ ራስን ፡ እየነቀነቀ ፥ ፊትን ፡ እያፈካ ፣ አለዚያም ፡ እያኰሳተረ ፥ ወዘተ. ፥ በጥቂት ፡ ቃላት ፡ ብዙ ፡ ይናገራል ፥ ይግባባል ።

የመኪና ፡ መንገድ ፡ ግን ፥ አደጋው ፡ ጽኑ ፡ ጕዳትን ፡ ሊያስከትል ፡ ስለሚችል ፥ የማያከብረውን ፡ የሚያስቀጣ ፡ ጥብቅ ፡ ሥርዐት ፡ አለው ። ነጂው ፦ ቀኝኽን ፡ ኺድ ፣ ቅደም ፣ አስቀድም ፣ ቁም ፡ ይባላል ፤ ምልክቶችን ፡ አክብር ፣ ኀላፊነቶችኽን ፡ ዕወቅ ፥ ብታጠፋ ፡ በሕግ ፡ ፊት ፡ ትጠየቃለኽ ፡ ይባላል ። ጽሑፍም ፡ ይህን ፡ የመሰለ ፡ ሥርዐት ፡ አለው ። 'ባፍ ፡ ያለ ፡ ይረሳል ፤ በጽሑፍ ፡ ያለ ፡ ይወረሳል' ፡ እንዲሉ ፥ በጽሑፍ ፡ ያለ ፡ ኹሉ ፡ ጕዳዩን ፡ ይዞ ፡ ይኖራል ። ይዘቱም ፥ ለፍቅር ፡ ኾነ ፡ ለጠብ ፣ ለጥቅም ፡ ኾነ ፡ ለጕዳት ፣ ለዋጋ ፡ ኾነ ፡ ለብላሽ ፣ ለቁም ፡ ነገር ፡ ኾነ ፡ ለከንቱ ፥ ጸሓፊውንና ፡ የተጻፈለትን ፡ ወገን ፥ አንባቢን ፡ በጠቅላላው ፡ ያገናኛል ፥ ያጠያይቃል ። ስለዚህ ፥ ያጻጻፍ ፣ ያገባብና ፡ የትርጕም ፡ ትኽክልነት ፥ ለጽሑፍ ፡ መልእክት ፡ ተሰሚነት ፣ ለሥርጭቱ ፡ ቅልጥፍና ፣ ለውጤቱም ፡ ስምረት ፡ ዐይነተኛው ፡ ዋስትና ፡ ነው ።

የማስሊያ ፡ ዋነኛው ፡ አገልግሎት ፥ የያዛቸውን ፡ ልቅሞች ፡ ወይም ፡ አላዶች ፡ (data) ፡ በፊደል ፡ ተራ ፡ መሰደሩና ፥ የተፈለገውን ፡ አላድ ፡ በቅጽበት ፡ አግኝቶ ፡ መስጠቱ ፡ ነው ። የማስሊያን ፡ ችሎታ ፡ ሙሉ ፡ በሙሉ ፡ እንድንጠቀምበት ፥ አላዶችን ፡ በሥርዐት ፡ ልንመዘግባቸው ፡ ያሻል ። ለምሳሌ ፥ የስልክ ፡ ማውጫን ፡ በማስሊያ ፡ እንመዝግብ ፡ ብንል ፥ 'አበበ' ፡ በሚል ፡ መጠሪያ ፡ ምናልባት ፡ ያ 1000 ፡ ሰው ፡ ስልክ ፡ ቍጥር ፡ ይመዘገብ ፡ ይኾናል ። የ'አበበ' ፡ ትኽክለኛው ፡ አጻጻፍ ፡ ይኸው ፡ 'አበበ' ፡ ብቻ ፡ ነው ፤ 'ኣበበ'ም ፡ 'ዐበበ'ም ፡ 'ዓበበ'ም ፡ ስሕተት ፡ ነው ። የስልክ ፡ መዝገቡ ፡ በሥርዐት ፡ የተመዘገበ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፥ 'አበበ'ዎች ፡ ኹሉ ፡ በአልፍ ፡ አ-ግእዝ ፡ ቤት ፡ ተሰድረው ፡ ይገኛሉ ። አላግባብ ፡ ተመዝግበው ፡ ቢኾን ፡ ግን ፥ የ'አበበ'ዎችን ፡ ስልክ ፡ ቍጥር ፡ ቢያሠሡ ፡ 'አበበ' ፡ ተብለው ፡ በትኽክል ፡ የተመዘገቡትን ፡ እንጂ ፥ 'ኣበበ' ፥ ወይ ፡ 'ዐበበ' ፡ ወይም ፡ 'ዓበበ' ፡ ተብለው ፡ በተሳሳተ ፡ አጻጸፍ ፡ የተመዘገቡተን ፥ በተሰጠው ፡ የማሠሻ ፡ ዝርዝር ፡ ማስሊያው ፡ ሊያገኛቸው ፡ አይችልም ። ስለዚህ ፥ የአላድ ፡ ወይም ፡ የልቅም ፡ ኹሉ ፡ አመዘጋገብ ፡ ትኽክል ፡ በኾነ ፡ መጠን ፥ የማስሊያውን ፡ ዐቅም ፡ የተሻለ ፡ እንሠራበታለን ፤ የመልእክታችንም ፡ ሥርጭት ፡ የበለጠ ፡ ይቀለጥፍልናል ።

ይህ ፥ ማስሊያው ፡ የሚያስገኘን ፡ ተጨማሪ ፡ ጥቅም ፡ ነው ። እላይ ፥ እቀደሙት ፡ መነሻዎች ፡ ላይ ፡ የጠቀስናቸው ፡ ጥቅሞች ፡ (ማለት ፥ አጻጻፍን ፣ አገባብንና ፡ ትርጕምን ፡ ከመጠንቀቅ ፡ የሚገኙት ፡ ጥቅሞች) ፡

ደግሞ ፡ መሠረታውያን ፡ ናቸው ፤ በዝርዝር ፡ እንመልከታቸው (47) ።

3.1 ፤ ፊደልን ፡ መጠ̊ንቀቅ (48) ።

3.1.1 ፤ ያማርኛ ፡ ከግእዝ ፡ መወለድ ፥ የቃላቱን ፡ ትርጕም ፣ ድምፅና ፡ አጻጻፍ ፥ እንዲሁም ፡ የቋንቋውን ፡ አገባብ ፥ በመጠኑም ፡ ቢኾን ፥ ይወስነዋል ። ካማርኛ ፡ ቃላት ፥ በግምት ፡ 90%ው ፡ በቀጥታ ፡ ከግእዝ ፡ ተወርሰዋል ፤ ቀሪው ፡ ደግሞ ፡ ከሌሎች ፡ የኢትዮጵያ ፡ ቋንቋዎች ፡ ወይም ፡ ከውጪ ፡ አገር ፡ ቋንቋዎች ።

3.1.2 ፤ በቀጥታ ፡ ከግእዝ ፡ የተወረሱት ፡ ቃላት ፥ ወይ ፡ በቁሙ ፡ (ማለት ፡ በትርጕምም ፣ በድምፅም ፣ ባጻጻፍም ፡ ሳይለወጡ) ፥ አለዚያም ፡ ከጥቂት ፡ ለውጥ ፡ ጋራ ፡ ተወርሰዋል ። ለምሳሌ ፥ ግእዝ ፡ 'ቀደሰ' ፡ ያለውን ፡ ዘር ፥ ዐማርኛም ፡ ትርጕም ፡ ሳይለውጥ ፥ ፊደልም ፡ ሳይቀንስ ፣ ሳይጨምር ፥ በቁሙ ፡ 'ቀደሰ' ፡ ይለዋል ። ግእዝ ፡ 'ጸሐፈ' ፡ ያለውን ፥ ዐማርኛ ፡ 'ጸ'ንና ፡ 'ሐ'ን ፡ አዋሕዶ ፥ 'ጻፈ' ፡ ይለዋል ። እንዲሁም ፥ ግእዝ ፥ 'ዐ'ንና ፡ 'ወ'ን ፡ አዋሕዶ ፡ 'ዖቀ' ፡ ያለውን ፥ ዐማርኛ ፡ 'ወ'ን ፡ ለይቶ ፡ አድምጦ ፡ 'ዐወቀ' ፡ ይለዋል ።

3.1.3 ፤ ዐማርኛ ፡ ከግእዝ ፡ የወረሳቸውን ፡ ቃላት ፡ በድምፅ ፡ ሲለውጣቸው ፥ ፊደሎቻቸው ፡ ርስ ፡ በርሳቸው ፡ የሚወራረሱበት ፡ ደንብ ፡ አለ̇ ። ለምሳሌ ፥ ግእዝ ፡ 'ሀለወ' ፡ (ኖረ) ፡ ያለውን ፥ ዐማርኛ ፡ 'አለ̇' ፡ ብሎ ፥ 'ሀሌታው-ሀ'ን ፡ በ'አልፍ-አ' ፡ ይተካዋል ። በጠቅላላው ፥ ፊደሎች ፡ ርስ ፡ በርሳቸው ፡ የሚወራረሱበትን ፡ ደንብ ፡ የሚከተለው ፡ ሰንጠረዥ ፡ ከብዙው ፡ በጥቂቱ ፣ ከረዥሙ ፡ ባጪሩ ፡ ይከሥትልናል ፤

ተወራራሽ ፡ ፊደሎች	ግእዝ	ዐማርኛ
'ሀሌታው-ሀ'ን ፡ 'አልፍ-አ' ፡ ይወርሰዋል ፤	ሀገር ሀይመነ	አገር አመነ
'ድልት-ደ'ን ፡ 'ጀ' ፡ ይወርሰዋል ፤	እድ ፈራዲ	እጅ ፈራጅ
'ዛይ-ዘ'ን ፡ 'ዠ' ፡ ይወርሰዋል ፤	ዘገነ ዘመረ ዝእብ	ዠገነ ▶ ዠግና ፡ ኾነ ዠመረ ዥብ
'ሐመሩ-ሐ'ን ፡ 'ዐይኑ-ዐ' ፡ ይወርሰዋል ፤	ሐገገ ሐሰበ	ዐገገ ዐሰበ
'ኀርሙ-ኀ'ን ፡ 'ዐይኑ-ዐ' ፡ ይወርሰዋል ፤	ኀብአ ኀየለ ኀተመ	ዐባ ፡ (ደበቀ) ዐየለ ዐተመ
'ካፍ-ከ'ን ፡ 'ኸ' ፡ ይወርሰዋል ፤	ክልኤት ኵሉ ኮነ	ኹለት ዅሉ/ኹሉ ኾነ
'ነጉሡ-ሠ'ን ፡ 'ሸ' ፡ ይወርሰዋል ፤	ሤጠ ሤመ	ሼጠ ሾመ/ሠየመ
'ጸሎቱ-ጸ'ን ፡ 'ጠይቱ-ጠ'ና ፡ 'ጨ' ፡ ይወርሱታል ፤	ጸብእ ጸፈነ	ጠብ ጨፈነ

47 ስለ ፡ ግእዝና ፡ ስላማርኛ ፡ የፊደል ፣ ያገባብና ፡ የትርጕም ፡ አጠነቃቀቅ ፡ ሥርዐት ፥ ቀደም ፡ ብሎ ፡ ከተጠቀሱት ፥ ካለቃ ፡ ኪዳነ ፡ ወልድ ፡ ክፍሌና ፡ ካለቃ ፡ ደስታ ፡ ተክለ ፡ ወልድ ፡ መጻሕፍት ፡ ሙሉ ፡ መረጃ ፡ ይገኛል ። ለዚህ ፡ ሥራ ፡ የጠቀሙኝ ፡ እነዚህ ፡ መጻሕፍት ፡ ናቸው ፤ በተለይ ፡ ደግሞ ፥ መጻሕፍቱን ፡ ያስተዋወቁኝ ፥ አገልግሎታቸውን ፡ ያስገነዘቡኝ ፥ እንዲሁም ፡ ከራሳቸው ፡ ሰፊ ፡ ተመክሮና ፡ ጥልቅ ፡ ዕውቀት ፡ ያካፈሉኝ ፥ ባንድ ፡ ቃል ፣ ያስተማሩኝ ፡ ክ. ፡ ሊ. ፡ ጄኔራል ፡ ነጋ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ ፡ ናቸው ። በጽሑፌ ፡ የሚገኘው ፡ ስሕተት ፡ ዅሉ ፡ ግን ፥ የኔና ፡ የኔ ፡ ብቻ ፡ መኾኑ ፡ ይታወቅልኝ ።

48 መጠ̊ንቀቅ ፤ 'ጠ' ፡ ይላላል ።

	ሐጸረ ኀጸረ ዐጸረ	ዐጠረ ፡ (ዐጥርን) ዐጠረ ፡ (ዐጨር ፡ ኾነ) ዐጠረ ፡ (ጠመቀ ፣ ዐጣሪ)
'ፀሓዩ–ፀ'ን ፡ 'ጠይቱ–ጠ'ና ፡ 'ጨ' ፡ ይወርሱታል ፤	ፀመደ ፀመረ	ጠመደ ጨመረ

3.1.4 ፤ 'አልፉ–አ' ፣ 'ዐይኑ–ዐ' ፣ 'ሀሌታው–ሀ' ፣ 'ሐመሩ–ሐ' ፣ 'ኀርሙ–ኀ' ፣ 'ዋዌው–ወ' ፣ በግእዙ ፡ ቃል ፡ መኻል ፡ ወይም ፡ በቃሉ ፡ መጨረሻ ፡ የተገኙ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፣ ብዙውን ፡ ጊዜ ፡ ዐማርኛ ፡ ይውጣቸዋል ፣ ወይም ፡ የቀደማቸውን ፡ ፊደል ፡ ራብዕ ፡ አድርጎ ፡ ያዋሕዳቸዋል ፤ ለምሳሌ ፣

ግእዝ	ዐማርኛ
ገብአ	ገባ
ኀብአ	ዐባ ፡ (ደበቀ)
ጠብሐ	ጠባ ፡ (ዐረደ ፣ በለተ)
ጠበወ	ጠባ ፡ (ጡት ፡ ጠባ)
ጸብሐ	ጠባ ፡ (ነጋ ፣ መስከረም ፡ ጠባ)
ጸብአ	ጠባ ፡ (ወጋ ፣ ሆድን)
ጸብዐ	ጣተ ፡ (ጣትን ፡ ቀሰረ)
ጸሐፈ	ጻፈ
ፈርሀ	ፈራ
ትምሀርት	ትምርት
ትዕግሥት	ትግሥት
ወዘተ.	

3.1.5 ፤ በግእዝና ፡ ባማርኛ ፡ ዲቃላ ፡ ፊደል ፡ ያሰባቸው ፡ ቃላት ፡ የተወሰኑ ፡ ናቸው ። ኾኖም ፣ የካዕብ ፡ ድርቦች ፡ (እነ'ጒ ፡ ኊ ፡ ኩ ፡ ቍ ፡ ...') ፣ እንዲሁም ፡ የግእዝ/ሳብዕ ፡ ድርቦች ፡ (እነ'ጐ ፡ ኈ ፡ ኰ ፡ ቈ ፡ ...') ፡ ብዙውን ፡ ጊዜ ፡ ያሳስቱናል ። ለምሳሌ ፣ 'ጐደለ' ፡ ማለት ፡ ሲገባ ፡ 'ጎደለ' ፡ ተጽፎ ፡ ይታያል ፤ አፍራሻውን ፣ 'ቆመ' ፡ ማለት ፡ ሲገባ ፡ 'ቈመ' ፣ ወዘተ. ። ዛሬ ፣ በዐውደ ፡ ቀለም ፡ ልናርማቸው ፡ ችለናል ። ዘሩ ፡ ዲቃላ ፡ ፊደል ፡ ያለው ፡ እንደ ፡ ኾነ ፣ ርባታው ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ በዲቃላ ፡ ፊደል ፡ ይቀጥላል ፤ ለምሳሌ ፡–

ጐደለ ፣ ጐዳይ ፣ ጒዳይ ፣ ጒድለት ፣ ጐደሎ ፣ ጒዳሌ ፣ ወዘተ.

3.1.6 ፤ ባማርኛ ፣ ነጠላና ፡ ብዙ ፡ እቃሉ ፡ መጨረሻ ፡ ላይ ፡ በሚታከል ፡ ምእላድ ፡ ይለያሉ ። ነጠላው ፡ ቃል ፡ በሳድስ ፡ ቢያልቅ ፣ ብዙ ፡ ሲኾን ፡ ሳድሱ ፡ ሳብዕ ፡ ይኾንና ፡ በ'ች' ፡ ያልቃል ። አለዚያ ፣ ቃሉ ፡ እንዳለ ፡ ኾኖ ፣ 'ዎች' ፡ ምእላድ ፡ ይታከልበታል ፤ ለምሳሌ ፡–

ቤት	▶	ቤቶች
ሥራ	▶	ሥራዎች
በር	▶	በሮች
በሬ	▶	በሬዎች

'በሬ'ን ፡ ሲበዛ ፡ 'በሬዎች' ፡ በማለት ፡ ፋንታ ፥ 'ሮ'ን ፡ አላልተው ፡ 'በሮ̊ች' ፡ የሚሉ ፡ አሉ ፥ በተለይ ፡ በንግግር ። በጽሑፍ ፡ ግን ፥ አሻሚ ፡ ስለሚኾን ፥ 'በሬዎች' ፡ ማለቱን ፡ ብዙዎች ፡ ይመርጣሉ ። በሳድስ ፡ የማያልቁ ፡ ቃሎችን ፡ ኹሉ ፡ በ'ዎች' ፡ ማብዛቱ ፡ የትርጕም ፡ አሻሚነትን ፡ ያስወግዳል ።

ጓዳ ▶ ጓዳዎች

ጓድ ▶ ጓዶች

ከግእዝ ፡ የተወረሰ ፡ የማብዛት ፡ ዘይቤ ፡ ባማርኛም ፡ ይገኛል ፤ ለምሳሌ ፡ በግእዝ ፡ ነጠላው ፡ 'ካህን' ፡ ሲበዛ ፡ 'ካህናት' ፡ እንደሚሠኝ ፥ ባማርኛም ፡ ነጠላው ፡ 'ካህን' ፡ ሲበዛ ፡ እንደ ፡ ግእዙ ፡ 'ካህናት' ፡ ሊሠኝ ፡ ይቻላል ፥ አለዚያም ፡ ባማርኛው ፡ የማብዣ ፡ ዘይቤ ፡ 'ካህኖች' ፡ ማለት ፡ ይቻላል ። 'ካህናቶች' ፡ ማለት ፡ ግን ፡ አይገባም ፤ የግእዝንና ፡ ያማርኛን ፡ ብዢዎች ፡ ስለደራረበ ፥ ትርፍ ፡ ነው ፤ ወይ ፡ 'ካህኖች' ፡ ማለት ፥ አለዚያም ፡ 'ካህናት' ፡ ማለት ፡ ይበቃል ።

3.1.7 ፤ ሣልስ ፡ ቅጽሎች ፡ ኹሉ ፥ ባለሦስት ፡ ፊደል ፡ የኾኑቱ ፥ ኹለተኛ ፡ ፊደላቸው ፡ ራብዕ ፡ ይኾናል ፤ ባላራት ፡ ፊደል ፡ የኾኑቱ ፡ ደግሞ ፡ ሦስተኛ ፡ ፊደላቸው ፡ ራብዕ ፡ ይኾናል ፥ ወዘተ. ፤ ለምሳሌ ፡—

ገጠመ ▶ ገጣሚ

ጸሐፈ ▶ ጸሓፊ

መዘገበ ▶ መዝጋቢ

'ሀ'ና ፡ 'ሃ' ፥ 'ሐ'ና ፡ 'ሓ' ፥ 'ኀ'ና ፡ 'ኃ' ፥ ድምፃቸው ፡ አንድ ፡ ቢኾንም ፥ ሚያቸው ፡ መለያየቱን ፡ ያስተውሏል ።

3.1.8 ፤ በ'ረ' ፡ ቤት ፡ በሚዠምሩ ፡ ቃላት ፡ መነሻ ፡ 'እ'ን ፡ የማስገባት ፡ የተለመደ ፡ ስሕተት ፡ አለ፟ ፤ ለምሳሌ ፡ 'ረመደ' ፡ ብሎ ፡ 'ርምጃ' ፡ ማለት ፡ ሲገባ ፡ 'እርምጃ' ፡ ማለት ፡ ስሕተት ፡ ነው ፤ እንደዚሁም ፡ 'ረዳ' ፡ ብሎ ፡ 'ርዳታ' ፡ ማለት ፡ ሲገባ ፡ 'እርዳታ' ፡ ማለት ፡ ስሕተት ፡ ነው ። 'እ' ፡ ምእላድ ፡ ኾኖ ፡ ባገባብነት ፡ ሲገባ ፡ መድረሻን ፡ ያመለክታል ፤ ለምሳሌ ፡ 'አበበ ፡ እቤቱ ፡ ገባ' ፡ ቢል ። እንደዚሁም ፥ የትንቢት ፡ አንቀጽ ፡ ሥር ፡ ሲኾን ፥ 'እበላ' ፡ 'እጠጣ' ፡ ያሠኛል ።

3.1.9 ፤ አንዳንድ ፡ የውጭ ፡ ቋንቋዎችን ፡ ቃላት ፡ በኢትዮጵኛ ፡ ሲጽፏቸው ፥ የ'አ' ፣ የ'ሀ' ፥ ወይም ፡ የ'ሰ' ፡ ድምፅ ፡ ያለ፟ባቸው ፡ እንደ ፡ ኾነና ፡ የቃላቱ ፡ ዘር ፡ በግእዝ-ዐማርኛም ፡ አንድ ፡ ወይም ፡ ተመሳሳይ ፡ ቢኾን ፥ ፊደልን ፡ መጠንቀቅ ፡ ይኖራል ። ለምሳሌ ፥ ዐረብ ፡ 'مكنص-መክነስ' ፡ ቢል ፥ ቃሉ ፡ በግእዝም ፡ 'ከነሰ' ፡ (ሰበሰበ) ፡ ከሚለው ፡ ስለሚወጣ ፡ በ'ሳቱ-ሰ' ፡ እንጂ ፡ በ'ንጉሡ-ሠ' ፡ ሊጽፉት ፡ አይገባም ። እንደዚሁ ፥ ዐረብ ፡ 'سُلْطان - ሡልጣን' ፡ ቢል ፥ ቃሉ ፡ በግእዝም ፡ ከ'ሠለጠ' ፡ ስለሚገሰስ ፥ በንጉሡ-ሠ ፡ ልንጽፈው ፡ ይገ፟ባ፟ል ። በጽርእ ፡ (በግሪክ) ፡ ደግሞ ፡ 'Omega' ፡ ቢል ፥ በመሠረቱ ፡ 'ዖሜጋ' ፡ በፊደልነት ፡ ከ'ዐይኑ-ዐ' ፡ የተገኘ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፥ ከ'አሜጋ' ፡ ይልቅ ፡ 'ዖሜጋ' ፡ ብለው ፡ በ'ዐይኑ-ዐ' ፡ ሊጽፉት ፡ ይገ፟ባ፟ል ። እንግዲህ ፥ የዓለም ፡ ቋንቋዎችን ፡ ቃላት ፡ ዘር ፡ ኹሉም ፡ ሰው ፡ ካላወቀው ፡ ማለት ፡ አይቻልም ። የሚያውቁ ፡ እያረሙ ፡ ቢጽፉ ፥ የማያውቁ ፡ እየጠየቁ ፡ ቢያርሙ ፥ ኹሉ ፡ ይሰምራል ። ዘሩ ፡ የማይታወቅ ፡ ቃል ፡ ቢኾን ፡ ግን ፥ በ'አልፉ-አ' ፣ በ'ሀሌታው-ሀ' ፣ በ'ሳቱ-ሰ' ፡ መወ፟ሰኑ ፡ ይሻላል ። ለምሳሌ ፡ 'Alaska' ፥ ቃሉ ፡ ለግእዝ-ዐማርኛ ፡ ባጋምም ፡ በቀጋ ፡ ስለማይዘመድ ፥ 'ዐላስካ' ፡ ወይ ፡ 'ዓላስካ' ፡ ወይም ፡ ደግሞ ፡ 'ኣላስካ' ፡ ብሎ ፡ ከመጻፍ ፡ ይልቅ ፥ 'አላስካ' ፡ ብሎ ፡ በ'አልፉ-አ-ግእዝ' ፡ መወ፟ሰኑ ፡ ይቀላል ። እንደዚሁ ፥ 'Scotland' ፡ ቢል ፥ 'ሥኮትላንድ' ፡ ብሎ ፡ ከመጻፍ ፡ ይልቅ ፥ 'ስኮትላንድ' ፡ ብሎ ፡ በ'ሳቱ-ሰ' ፡ መወ፟ሰኑ ፡ ይሻላል ። ዐውደ ፡ ቀለም ፡ የውጭ ፡ ቃላትን ፡ ወደ ፡ ግእዝ-ዐማርኛ ፡ ሲመልስ ፥ የተቻለውን ፡ ያኽል ፡ እነዚህን ፡

ጥንቃቄዎች ፡ አሚልቷል ።

3.1.10 ፤ ብዙዎቻችን ፡ ስላላከበርነው ፡ እንጂ ፥ የግእዝና ፡ ያማርኛ ፡ አጻጻፍስ ፡ ጥብቅ ፡ ሥርዐት ፡ አለው ፤ ሥርዐቱም ፡ ቅን ፣ ገር ፣ ተገቢ ፡ እንጂ ፥ አንዳች ፡ ጠማማ ፣ ወልጋዳ ፥ ወይ ፡ ማስረጃ-አልቦ ፣ ልብ ፡ ወለድ ፡ ነገር ፡ የለውም ። በዚህ ፡ ምክንያት ፥ በላዩ ፡ ታላቅ ፡ 'ሕንጻ' ፡ ሊታነጽበት ፡ ይችላል ። የማንኛውም ፡ ያማርኛ ፡ ወይ ፡ የግእዝ ፡ ቃል ፡ ተገቢ ፡ አጻጻፍ ፡ ዅል ፡ ጊዜም ፡ ቢኾን ፡ አንድና ፡ አንድ ፡ ብቻ ፡ ነው ። ለምሳሌ ፥ 'ሥርዐት' ፡ የሚለውን ፡ ሳቢ ፡ ዘር ፥ በስምንት ፡ ዐይነት ፡ መንገድ ፡ መጻፍ ፡ ይቻላል ፦

ሥርዐት ✓ ስርዐት ×

ሥርዓት × ስርዓት ×

ሥርአት × ስርአት ×

ሥርኣት × ስርኣት ×

ተገቢው ፡ ግን ፡ የመዠመሪያው ፡ 'ሥርዐት' ፡ ብቻ ፡ ነው ። ዘሩ ፡ 'ሠርዐ' ፡ ስለ ፡ ኾነ ፥ 'ሳቱ-ሰ'ና ፡ 'አልፉ-አ' ፡ ተገቢነት ፡ የላቸውም ፤ ከዚህ ፡ ወዲያ ፥ 'ዐይኑ-ዐ'ም ፡ ቢኾን ፥ ተገቢው ፡ ግእዙ-ዐ ፡ እንጂ ፡ ራብዑ-ዓ ፡ ስሕተት ፡ ነው ። ለምሳሌ ፦

- ዘሩን ፡ 'ሰመረ' ፡ ብሎ ፥ ሳቢ ፡ ዘሩን ፡ 'ስምረት' ፡ እንጂ ፡ 'ስምራት' ፡ አይሉም ።
- ዘሩን ፡ 'በለጠ' ፡ ብሎ ፥ ሳቢ ፡ ዘሩን ፡ 'ብልጠት' ፡ እንጂ ፡ 'ብልጣት' ፡ አይሉም ።

እንደዚሁ ፥

- ዘሩን ፡ 'ሠርዐ' ፡ ብሎ ፥ ሳቢ ፡ ዘሩን ፡ 'ሥርዐት' ፡ እንጂ ፡ 'ሥርዓት' ፡ አይሉም ።

ወዘተ. ። ራብዑ ፡ የሚውለው ፡ ብዛትን ፡ ለማመልከት ፡ ነው ፦

- (ም. ፤ ብዙኅ ፥ ብዙኃን/ብዙኃት) ፥
- ወይም ፣ እላይ ፡ (1.7) ፡ እንዳየነው ፥ በሣልስ ፡ ቅጽል ፡ (ም. ፤ ጸሐፊ ፥ ጸሓፊ ፤ ገበረ ፥ ገባሪ) ።

3.1.11 ፤ መደምደሚያውን ፥ የግእዝንና ፡ ያማርኛን ፡ አጻጻፍ ፡ ሥርዐት ፡ በመንገዱ ፡ ቢከተሉት ፥ ከቀላልነቱም ፡ የበለጠ ፥ ምስጢርን ፡ መግለጹ ፣ አእምሮን ፡ ማነጹ ፣ ዐሳብን ፡ ማደርጀቱ ፣ አስተሳሰብን ፡ ማስፋቱ ፣ ነገርን ፡ ማገናዘቡ ፣ ጥቅሙ ፡ በጠቅላላው ፡ እጅግ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፥ ዅል ፡ ጊዜም ፡ በደስታ ፡ ይመላለሱበታል ፤ ከዚያም ፡ ወዲያ ፡ የፊደል ፡ ስሕተት ፥ እንደ ፡ ነውር ፡ ዅሉ ፥ ያጸይፋል ፣ ያሠቀጥጣል ። አለመንገዱ ፡ ግን ፥ ዐቀበት ፡ ነው ፤ አይዘለቅም ።

3.2 ፤ አገባብን ፡ መጠንቀቅ ።

3.2.1 ፤ የዐቢይና ፡ የደቂቅ ፡ አገባቦች ፡ አጻጻፍ ፥ ካልተጠነቀቁለት ፥ ትርጕንም ፡ ይለውጣል ፡ ወይም ፡ ያሻማል ።

3.2.2 ፤ ዐቢይና ፡ ደቂቅ ፡ አገባብ ፡ የተባሉ ፡ እነ ፡ 'እ ፥ እንደ ፥ እስከ ፥ በ ፥ ወደ ፥ ስ ፥ ሲ ፥ ...' ፡ ናቸው ።

3.2.3 ፤ ካገባቡና ፡ አገባቡ ፡ ከሚጫነው ፡ ስም ፡ (ወይ ፡ አንቀጽ) ፡ መካከል ፡ 'የ' ፡ ተጐርዶ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፥ አገባቡና ፡ ስሙ ፡ ይዋደዳሉ ፡ (ይጣበቃሉ) ፥ አለዚያ ፡ በእየራሳቸው ፡ ተለይተው ፡ ይጻፋሉ ። ለምሳሌ ፥

'እንደእግዚአብሔር ፡ ባሪያ ፡ ኹኑ ፡ እንጂ ፡ ...' (1ኛ ፡ ጴጥ. ፥ 2 ፥ 16)

ሲል ፡

'እንደ ፡ <u>የእግዚአብሔር ፡ ባሪያ</u> ፡ ኹኑ ፡ እንጂ ፡ ...'

ማለቱ ፡ ነው ፤ 'የ' ፡ ተውጧል ። ስለዚህ ፥ 'እንደእግዚአብሔር' ፡ ብሎ ፡ ኹለቱን ፡ ቃል ፡ ባንድ ፡ ቃል ፡ አዋዶ ፡ ይጽፏል ። እንዲሁም ፤

'ስለ ፡ ክርስቶስ ፡ መነቀፍ ፡ ...' (ዕብ. ፥ 11 ፥ 25)

ተብሎ ፡ በኹለት ፡ ቃል ፡ የተጻፈውን ፥

'ስለክርስቶስ ፡ ...'

ብሎ ፡ ባንድ ፡ ቃል ፡ መጻፍ ፥ የተጐረደ ፡ ወይም ፡ የተዋጠ ፡ 'የ' ፡ አልነበረምና ፥ አከባድ ፡ የትርጕም ፡ ስሕተት ፡ ላይ ፡ ይጥላል ።

3.2.4 ፤ ዐቢይ ፡ አገባቦች ፡ ('እ ፥ እንደ ፥ እስከ ፥ በ ፥ ወደ ፥ ከ ፥ ስ ፥ ሲ ፥ ...ወዘተ.') ፡ አንቀጽን ፡ ሲጫኑ ፡ ወይም ፡ ሲቀድሙ ፥ አንቀጹ ፡ በ'አ' ፣ በ'ኣ' ፣ በ'ዐ' ፣ ወይም ፡ በ'ዓ' ፡ ፊደል ፡ ቢዠምር ፥ ፊደሉ ፡ ተጐርዶ ፡ ዐቢይ ፡ አገባቡና ፡ አንቀጹ ፡ ተዋሕደው ፡ ይጻፋሉ ፤ መዋደጃ ፡ ፊደላቸውም ፡ ራብዕ ፡ ይኾናል ፥ ወይም ፡ በ'ያ' ፡ ይተካል ። ለምሳሌ ፦

እንደ ፡ አማረ	▶	እንዳማረ
ስለ ፡ ዐሰበ	▶	ስላሰበ
ስ ፡ አገኝ	▶	ሳገኝ
ሲ ፡ አገኝ	▶	ሲያገኝ

3.2.5 ፤ ደቂቅ ፡ አገባቦች ፡ ('እ ፥ እንደ ፥ እስከ ፥ በ ፥ ወደ ፥ ከ ፥ ...ወዘተ.') ፡ ስምን ፡ ሲጫኑ ፡ ወይም ፡ ሲቀድሙ ፥ ስሙ ፡ በ'አ' ፣ በ'ኣ' ፣ በ'እ' ፣ በ'ዐ' ፣ በ'ዓ' ፣ ወይም ፡ በ'ዕ' ፡ ፊደል ፡ ቢዠምር ፥ ፊደሉ ፡ ተጐርዶ ፡ ደቂቅ ፡ አገባቡና ፡ ስሙ ፡ ተዋሕደው ፡ ይጻፋሉ ፤ መዋደጃ ፡ ፊደላቸውም ፥ እንደ ፡ ኹኔታው ፥ ራብዕ ፡ ወይም ፡ ሳድስ ፡ ይኾናል ። ለምሳሌ ፦

እንደ ፡ አገሩ	▶	እንዳገሩ
ስለ ፡ ዐሳቡ	▶	ስላሳቡ
እስከ ፡ አገር	▶	እስከግር

ኾኖም ፥ ይህኛው ፡ የደቂቅ ፡ አገባቦች ፡ ዐዋጅ ፡ ዐልፎ ፡ ዐልፎ ፡ የትርጕም ፡ አሻሚነትን ፡ ስለሚያስከትል ፥ አንዳንዶች ፡ አይቀበሉትም ። ለምሳሌ ፥ 'በእግራቸው ፡ ኼዱ' ፡ ያለውን ፥ 'እ'ን ፡ ጐርዶ ፡ 'በግራቸው ፡ ኼዱ' ፡ ቢል ፡ 'በግራ ፡ አቅጣጫ ፡ ኼዱ' ፡ አሠኝቶ ፡ ትርጕም ፡ ይለውጣል ፥ ያሻማል ። ለኅብርና ፡ ለሠምና ፡ ወርቅ ፡ ጨዋታ ፡ ግን ፡ እጅግ ፡ ያመቻል ።

3.2.6 ፤ የ'ነበረ' ፡ የ'ነው'ና ፡ የ'ነበር' ፡ ሚያ ፡ ይለያያል ። 'ነበረ/ነው' ፡ አለ ፣ ኖረ ፡ ማለት ፡ ኾኖ ፥ ባ 10 ሩ ፡ ሰራዊት ፡ ይዘረዘራል ፡ ('ነበረ' ፣ 'ነበርኽ' ፣ 'ነበረች' ፣ 'ነበርሽ' ፣ .../ 'ነው' ፣ 'ነኽ' ፣ 'ነች' ፥ 'ነሽ' ፣ ወዘተ.) ። 'ነበር' ፡ ግን ፡ በትንቢትና ፡ በቦዝ ፡ አንቀጽ ፡ መጨረሻ ፡ እየገባ ፡ አይዘረዘርም ፡ ('ነው'ም ፡ እንደዚሁ ፡ የማይዘረዘርበት ፡ ኹኔታ ፡ አለ) ። ለምሳሌ ፦

- 'ማን ፡ ያርዳ ፨ የቀበረ ፤ ማን ፡ ይመስክር ፨ የነበረ ። '
- 'እግዚአብሔርም ፡ ያደረገውን ፡ ኹሉ ፡ አየ ፥ እንሆም ፡ እጅግ ፡ መልካም ፡ ነበረ ። '
- 'ምድርም ፡ ባዶ ፡ ነበረች ፥ አንዳችም ፡ አልነበረባትም ፤ ጨለማም ፡ በጥልቁ ፡ ላይ ፡ ነበረ ፤ የእግዚአብሔርም ፡ መንፈስ ፡ በውሃ ፡ ላይ ፡ ሰፎ ፡ ነበር ። ' ('ሰፎ' ፡ ቦዝ ፡ አንቀጽ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፥ 'ሰፎ ፡ ነበር' ፡ ይላል ፡ እንጂ ፥ 'ሰፎ ፡ ነበረ' ፡ አይልም ።)
- 'አብርሃምና ፡ ሣራም ፡ በዕድሜያቸው ፡ ሸምግለው ፡ ፈጽመው ፡ አርጅተው ፡ ነበር ። ' ('አርጅተው' ፡ ቦዝ ፡ አንቀጽ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፥ 'አርጅተው ፡ ነበሩ' ፡ ቢል ፡ ስሕተት ፡ ይኾናል ።)

3.3 ፤ ትርጕምን ፡ መጠንቀቅ ።

3.3.1 ፤ ግእዝና ፡ ዐማርኛ ፡ 'አልፉ-አ'ንና ፡ 'ዐይን-ዐ'ን ፡ ባጻጻፍና ፡ በትርጕም ፡ እንጂ ፡ በድምፅ ፡ አይለዩም ፤ እንደዚሁ ፡ ባንድ ፡ ወገን ፥ 'ሀሌታው-ሀ'ን ፡ 'ሐመሩ-ሐ'ን ፡ 'ኀርሙ-ኀ'ን ፤ በሌላው ፡ ወገን ፥ 'ጸሎቱ-

ጸ'ንና ፡ 'ፀሓዩ-ፀ'ን ፡ ባጻጻፍና ፡ በትርጒም ፡ እንጂ ፡ በድምፅ ፡ አይለዩም ። ለምሳሌ ፥ 'ነጸረ'ና ፡ 'ነፀረ' ፡ ድምፃቸው ፡ አንድ ፡ ሳለ ፥ አጻጻፋቸው ፡ ይለያያል ፤ ያጻጻፋቸው ፡ መለየት ፡ የትርጒም ፡ ልዩነታቸውን ፡ ያመለክታል ። 'ነጸረ' ፡ በ'ጸሎቱ-ጸ' ፡ ሲጻፍ ፡ 'አየ' ፡ ማለት ፡ ነው ፤ በ'ፀሓዩ-ፀ' ፡ ሲጻፍ ፡ ደግሞ ፡ 'ለየ' ፡ ማለት ፡ ነው (49) ።

አበየ ፡ (እምቢ ፡ አለ)	ዐበየ ፡ (ከፍ ፡ አለ)
አደመ ፡ (አማረ)	ዐደመ ፡ (ቀጠረ)
አደፈ ፡ (ጐደፈ ፥ ቈሸሸ)	ዐደፈ ፡ (ጠረገ ፥ ወለወለ)
አዘዘ ፡ (ትእዛዝ ፡ ሰጠ)	ዐዘዘ ፡ (አጸና ፥ አበረታ)
አሰረ ፡ (ጠፈረ)	ዐሠረ ፡ (ዐሥር ፡ አደረገ)
ውሑድ ፡ (የተዋሐደ)	ውኁድ ፡ (የጐደለ)
ሕብር ፡ (ቀለም)	ኅብር ፡ (ኅብረት)
ሐለየ ፡ (አመሰገነ) ▶ ማሕሌት	ኀለየ ፡ (ዐሰበ) ▶ ኀሊና
ሠለጠ ፡ (ሠለጠነ)	ሰለጠ ፡ (ጨረሰ)
ሠየመ ፡ (ሾመ)	ሰየመ ፡ (ሰመየ ፥ ስም ፡ አወጣ)
ሠርዌ/ሠራዊት ፡ (ዐምድ/ዐምዶች)	ሰርዌ/ሰራዊት ፡ (ጦረኛ/ጦረኞች)
ፈጸመ ፡ (ጨረሰ)	ፈፀመ ፡ (ዘጋ)
ቀረጸ ፡ (ቀረጠ)	ቀረፀ ፡ (ሸለተ)

እንግዲህ ፥ 'ያማርኛ ፡ ፊደል ፡ ይቀነስ ፤ አንድ ፡ 'አ' ፥ አንድ ፡ 'ሀ' ፥ 'አንድ ፡ 'ጸ' ፥ አንድ ፡ 'ሰ' ፡ ይበቃል' ፡ የሚለው ፡ ሐሳብ ፥ ከጥቅሙ ፡ ጒዳቱ ፡ ያመዝናል ፡ ብለን ፥ አንዴ ፡ ለመቼውም ፡ እንደመድማለን ።

3.3.2 ፤ የፊደላቱ ፡ አወራረስ ፡ ደንብ ፡ እላይ ፡ እንደተዘረዘረው ፡ ቢኾንም ፥ ባግባቡ ፡ በሥራ ፡ መዋል ፡ አለበት ። ለምሳሌ ፥ 'ጠባይ' ፡ ማለት ፡ ሲገባ ፡ 'ጸባይ' ፡ ማለት ፡ ስሕተት ፡ ነው ፤ 'ጠባይ' ፡ በግእዝም ፡ 'ጠባይዕ' ፡ ነውና ፤ 'ጸ'ን ፡ 'ጠ' ፡ ቢወርሰው ፡ እንጂ ፡ 'ጠ'ን ፡ 'ጸ' ፡ አይወርሰውም ። እንደዚሁ ፥ 'ጠበል' ፡ (የፈለቀ ፡ ውሃ ፥ ወይም ፡ የዝክር ፡ ጠላ) ፡ ማለት ፡ ሲገባ ፥ 'ጸበል' ፡ ቢሉ ፡ ትርጒሙ ፡ ይለያል ፤ 'ጠበል' ፡ በግእዝም ፡ ያው ፡ 'ጠበል' ፡ ነው ፤ 'ጸበል' ፡ ያሉ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ደግሞ ፥ 'ዐቧራ' ፡ ማለት ፡ ነው ።

3.3.3 ፤ ግእዝና ፡ ዐማርኛ ፡ ባጻጻፍና ፡ በትርጒም ፡ እንጂ ፡ በድምፅ ፡ የማይለይዋቸውን ፡ ፊደሎች ፥ ሌሎች ፡ ሴማውያን ፡ የኢትዮጵያ ፡ ቋንቋዎች ፥ (ትግርኛና ፡ ትግረ) ፥ እንደ ፡ ዐረብ ፥ ዕብራይስጥና ፡ ሱርስት ፥ በድምፅም ፡ ይለይዋቸዋል ። 'መሀረ' ፡ (ትምህርት ፡ አስተማረ)ና ፡ 'መሐረ' ፡ (ምሕረት ፡ አደረገ) ፡ በፊደልና ፡ በትርጒም ፡ የተለዩትን ፡ ያኽል ፡ በድምፅም ፡ ይለያሉ ፤ የ'ሐመሩ-ሐ' ፡ ድምፅ ፡ 'ከሀሌታው-ሀ' ፡ ይጠነክራል ፥ ጒረሮን ፡ ያስከፍታል ። እንደዚሁ ፥ ግእዝና ፡ ዐማርኛ ፡ 'እኅት' ፡ ያሉትን ፦

ዐረብኛ ፡ أُخْت • ኡኅት ፡ ብሎ ፥ 'ኅ'ን ፡ አሻክሮ ፡ ያነበዋል ፤

ዕብራይስጥም ፡ אָחוֹת • አኆት ፡ ብሎ ፥ 'ኆ'ን ፡ አሻክሮ ፡ ያነበዋል ።

3.3.4 ፤ በዘመናችን ፥ በተለይ ፡ በማወራኛዎች (50) ፡ የሚዛመቱ ፡ የተለመዱ ፡ ስሕተቶች ፡ አሉ ። ገቢርና ፡ ተገብሮን ፡ ካለመለየት ፡ የሚመጡ ፡ ስሕተቶች ፤ ለምሳሌ ፦ 'ተወከለ' ፡ በሚባልበት ፡ 'ወከለ' ፡ ማለት ፡

49 ደስታ ፡ ተክለ ፡ ወልድ ፤ ርብሐ ፡ ስም ፡ ወአንቀጽ ። ገጽ ፡ 65-66 ን ፡ መመልከት ።
50 ማወራኛ ፤ 'የብዙኃን ፡ ማገናኛ' • media ።

የተለመደ ፡ ስሕተት ፡ ነው ፤ ወካይ ፡ ባለቤት ፡ ነው ፥ ተወካይ ፡ ደግሞ ፡ ባለቤቱ ፡ የወከለው ፥ የውክልናው ፡ ተቀባይ ፡ ነው ። 'አበበች ፡ ሕዝብን ፡ ወክላ ፡ መጣች' ፡ ቢል ፥ ባለቤቱን ፡ ዘርፍ ፥ ዘርፉን ፡ ባለቤት ፡ አድርጓልና ፥ ተሳስቷል ። ማለት ፡ የሚገባው ፥ 'አበበች ፡ በሕዝብ ፡ ተወክላ ፡ መጣች' ፥ ወይም ፡ 'አበበች ፥ ሕዝብ ፡ ወክሏት ፡ መጣች' ፥ ወይም ፡ ደግሞ ፡ 'ሕዝብ ፡ አበበችን ፡ ወክሎ ፡ ላካት' ።

3.3.5 ፤ ፊደልን ፡ ወይ ፡ ትርጕምን ፡ ካለመለየት ፡ የሚሳሳቱትም ፡ አሉ ። ለምሳሌ ፦

- ቀጣና ፡ (መተላለፊያ ፥ መሰምሪያ) ፡ ለማለት ፥ ቀጠና ፡ (ረኃብ) ፡ ማለት ፤

- ቅርታ ፡ (ቅር ፡ መሠኘት) ፡ ለማለት ፥ ቅሬታ ፡ (ትርፍ ፥ ትራፊ ፤ አለዚያም ፡ የ'ቅሬ' ፡ ንግግር) ፡ ማለት ፤

- አዘብጣጭ ፡ (ጐታች ፥ እኂላ ፡ የሚያስቀር) ፡ ለማለት ፥ አድኃሪ ፡ (መራቂ ፥ የኂላ ፡ ሰው ፡ አድራጊ) ፡ ማለት ፤

- ማማረጫ ፡ (የሚያማርጡት ፡ ዕቃ ፡ ወይ ፡ ነገር) ፡ ለማለት ፥ አማራጭ ፡ (ዐብሮ ፡ የሚያማርጥ ፡ ሰው) ፡ ማለት ፤

- ሚያን ፡ መዋል ፡ ለማለት ፡ ሚና ([51]) ፡ መጫወት ፡ (ቃል ፡ በቃል ፡ 'ወገን ፡ መጫወት?!') ፡ ማለት ፤

ወዘተ. ፥ ይህ ፡ ኹሉ ፡ ሊያርሙት ፡ የሚገባ ፡ የተለመደ ፡ ስሕተት ፡ ነው ።

3.3.6 ፤ አባባሎችን ፡ ከውጭ ፡ ቋንቋ ፡ ቃል ፡ በቃል ፡ መመለስ ፡ አግባብ ፡ እየመሰላቸው ፥ አንዳንድ ፡ ሰዎች ፡ ይሳሳታሉ ። ለምሳሌ ፡ እንግሊዝ ፡ 'to take decision' ፡ ቢል ፥ ለ'idiomatic'ዉ ፡ እንግሊዝኛ ፡ አግባብ ፡ ይኾናል ፤ ላማርኛ ፡ ግን ፡ ፈጽሞ ፡ አይኾንም ። 'መወሰን' ፡ ብሎ ፡ ቀናውን ፡ ባማርኛ ፡ ማለት ፡ ሲገባ ፥ ቃል ፡ በቃል ፡ 'ውሳኔ ፡ መውሰድ' ፡ ብሎ ፡ ወዳማርኛ ፡ ቢመልሱት ፡ ትርጕምን ፡ ያጣል ፥ አስተሳሰብን ፡ ያደክማል ፣ ያደበዝዛል ፥ ተናጋሪውንም ፡ ክፉኛ ፡ ያስገምታል ። 'ድርጅታችኹ ፡ ምን ፡ ርምጃ ፡ ለመውሰድ ፡ ያስባል ፧ ' ብሎ ፡ አንዱ ፡ ቢጠይቅ ፥ ኀላፊው ፡ ሲመልሱ ፦ ርምጃ ፡ ይወስዳል ፡ እንጂ ፡ መች ፡ ይወሰዳል ፧ አሉ ፡ ይባላል ፡ (በጥሩ ፡ ዐማርኛ ፥ 'ድርጅታችኹ ፡ ምን ፡ ወስኗል ፧ ' ብሎ ፡ ቢጠይቅ ፡ ያባት) ። እንደዚሁ ፥ እንግሊዝ ፡ 'take a seat' ፡ ቢል ፥ 'መቀመጫ ፡ ውሰድ' ፡ ብሎ ፡ ሰውን ፡ ከማደናገር ፡ ይልቅ ፡ 'ይቀመጡ' ፡ ቢሉ ፡ ይቀናል ።

3.3.7 ፤ የግእዝና ፡ ያማርኛ ፡ ፊደል ፡ መጠንቀቂያን ፡ ዐውደ ፡ ቀለም ፡ እንሆ ፡ ሰጥቶናል ፤ በምዕራፍ ፡ 1 ፡ እና ፡ 2 ፡ እንዳየነው ፥ በዚህ ፡ ረገድ ፡ የነበረብን ፡ ችግር ፡ ተቃሏል ። አኹን ፡ የሚቀረን ፡ ያገባብ ፡ መጠንቀቂያ ፡ መግበር ፡ ['ግራመር−ቼከር'] ፡ ነው ፤ ርሱ ፡ እስኪበጅ ፡ ድረስ ፥ የግእዝና ፡ ያማርኛ ፡ ጽሑፎችን ፡ አገባብ ፡ ለመጠንቀቅ ፥ ለግእዙ ፡ ያለቃ ፡ ኪዳነ ፡ ወልድ ፡ ክፍሌን ፡ *መጽሐፈ ፡ ሰዋስው ፡ ወግስ ፡ ወመዝገበ ፡ ቃላት ፡ ሐዲስ* ፡

http://www.gzamargna.net/html/gzMezgebeQalat.html ፡ መመልከት ፤

ላማርኛው ፡ ደግሞ ፥ ያለቃ ፡ ደስታ ፡ ተክለ ፡ ወልድን ፡ *ዐዲስ ፡ ያማርኛ ፡ መዝገበ ፡ ቃላት* ፡ http://www.gzamargna.net/html/amargnaMezgebeQalat.html ፡ መመልከት ፡ ይረዳል ።

3.3.8 ፤ እነዚህ ፡ ኹለት ፡ መዛግብተ ፡ ቃላት ፡ በጥንታዊው ፡ 'አ ፡ በ ፡ ገ ፡ ደ' ፡ ተራ ፡ የተሠሩ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፥ ቃላቱ ፡ ኹሉ ፡ የግእዙ ፡ ባንቀጽ ፡ ባንቀጻቸው ፥ ያማርኛው ፡ ደግሞ ፡ በዘር ፡ በዘራቸው ፡ በእየአዕማዱ ፥ በዚሁ ፡ ተራ ፡ ተሰድረዋል ፤ ስለዚህ ፡ የ'አ ፡ በ ፡ ገ ፡ ደ'ን ፡ ተራ ፡ ማወቁ ፡ ሥራን ፡ በጣም ፡ ያቀለጥፋልና ፥ አንድ ፡ አፍታ ፦

አ በ ቨ ገ ደ ጀ ሀ ወ ዘ ዠ ሐ ኀ
ጠ ጨ የ ከ ኸ ለ መ ነ ኘ ሠ ዐ ፈ

51 '**ሚና**' ፡ የገና ፡ ጨዋታም ፡ ኾነ ፡ የማንኛውም ፣ ቡድን ፡ ወይም ፡ ወገን ፡ ማለት ፡ እንጂ ፡ 'ሚያ' ፡ (ወይም ፡ በፈረንጅኛ ፡ 'role') ፡ ማለት ፡ አይደለም ። 'የእግሌ ፡ ሚና ፡ ይጫወታል' ፡ ቢሉ ፡ እንኳ ፡ ያስኬዳል ፥ 'እገሌ ፡ ሚና ፡ ይጫወታል' ፡ ማለት ፡ ግን ፡ ትርጕም ፡ የለውም ።

ጸ ፀ ቀ ረ ሰ ሸ ተ ቸ ጰ ፐ

ብሎ ፡ በቃል ፡ መያዙ ፡ ይበጃል ። ካምስት ፡ ደቂቃ ፡ በላይ ፡ አይፈጅብዎም ፤ ይሞክሩት!

3.3.9 ፤ ነገር ፡ ባይን ፡ ይገባል ፡ እንዲሉ ፥ የሚከተለው ፡ ሥዕል ፡ ደኅና ፡ አድርጎ ፡ ያስረዳናል ። በሥዕሉ ፡ ላይ ፡ የምታዩት ፡ ካማርኛው ፡ መዝገበ ፡ ቃላት ፡ ገጽ ፡ 951 ፡ ላይ ፡ 'ዐቀደ' ፡ የሚለው ፡ ዘርና ፡ ግሶቹ ፥ ኹሉም ፡ ከነትርጕማቸው ፡ የተዘረዘሩበትን ፡ ኹኔታ ፡ ነው ። የቃላቱ ፡ አወጣጥ ፡ ስልት ፡ እንደሚከተለው ፡ ነው ፤ ለምሳሌ ፥ 'ማቀጃ' ፡ የሚለውን ፡ ቃል ፡ (ባዕድ ፡ ዘር) ፡ ትርጕም ፡ ለማግኘት ፥ አስቀድሞ ፡ ዘሩን ፡ ማወቅ ፡ አለ ። ዘሩ ፡ 'ዐቀደ' ፡ ነው ፤ ስለዚህ ፡ የ'ዐይኑ–ዐ'ን ፡ ቤት ፡ ለማግኘት ፥ እገጹ ፡ ዐናት ፡ ላይ ፡ ከተደረደሩት ፡ ፊደላት ፡ 'ዐ'ን ፡ ለይቶ ፡ በመጠቈሚያው ፡ መጠቈምና ፥ በዚያው ፡ በ'አ ፡ በ ፡ ገ ፡ ደ' ፡ ተራ ፡ መሠረት ፥ 'ዐቀደ' ፡ የሚገኝበትን ፡ ገጽ ፡ ፈልጎ ፡ ማግኘት ፡ (ገጹ ፡ በቀይ ፡ ቀለም ፡ ተመልክቷል) ፡ 'ዐቀደ' ፡ ከተገኘ ፡ ወዲያ ፥ በባዕድ ፡ ዘር ፡ ተራ ፡ 'ማቀጃ' ፡ ከነትርጕሙ ፡ ተመዝግቦ ፡ ይገኛል ። እንደዚሁ ፥ 'መንገድ' ፡ የሚለውን ፡ ቃል ፡ ለማግኘት ፥ ዘሩ ፡ 'ነገደ' ፡ ስለ ፡ ኾነ ፥ 'ነ' ፡ ቤት ፡ ኼዶ ፥ 'ነገደ' ፡ የሚገኝበትን ፡ ገጽ ፡ መሻት ፤ 'ነገደ' ፡ ከተገኘ ፡ ወዲያ ፥ በ'ነገደ' ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፥ በባዕድ ፡ ዘር ፡ ተራ ፥ 'መንገድ' ፡ ከነትርጕሙ ፡ ተመዝግቦ ፡ ይገኛል ።



3.3.10 ፤ የግእዙ ፡ መዝገበ ፡ ቃላት ፡ አወጣጥም ፡ ይህንኑ ፡ ስልት ፡ የሚከተል ፡ ኾኖ ፥ ቃላቱ ፡ ከዘር ፡ ይልቅ ፡ ባንቀጽ ፡ ይሰደራሉ ። የሚከተለው ፡ ሥዕል ፡ ተጨማሪ ፡ ማብራሪያን ፡ ይሰጠናል ።



ተመሳሳይ ፡ ድምፅ ፡ ያላቸው ፡ ፊደሎች ፥ እንደ ፡ አልፍ–አ / ዐይን–ዐ ፥ ንጉሥ–ሠ / ሳት–ሰ ፥ ወዘተ. ፡ ቃላትን ፡ ለይቶ ፡ ለማግኘት ፡ ትንሽ ፡ ያስቸግራሉ ። ለምሳሌ ፥ በዐይን–ዐ ፡ የሚጻፈውን ፡ ቃል ፡ በአልፍ–አ ፡ ቤት ፡ ቢፈልጉት ፡ አይገኝም ። እንደዚሁም ፥ የምንፈልገው ፡ ቃል ፡ ባስደራጊ ፡ አንቀጽ ፡ ኾኖ ፡ መግቢያውን ፡ አድራጊውን ፡ አንቀጽ ፡ ባናውቀው ፡ (ለምሳሌ ፡ 'አከናወነ' ፡ የሚለውን ፡ ቃል ፡ ለማውጣት ፥ ዘሩ ፡ 'ከነወነ' ፡ መኾኑን ፡ ባናውቅ) ፡ እንቸገራለን ። መዝገበ ፡ ቃላቱን ፡ ያበጁት ፡ ሊቃውንት ፥ ችግራችንን ፡ አስቀድመው ፡ ተገንዝበውልን ፥ በተሳሳተውም ፡ መንገድ ፡ ለሚመጣ ፡ ኹሉ ፡ መግቢያ ፡ በርን ፡ ሳይነሡ ፡ 'የምትሻውን ፡ ቃል ፡ እንዲህ ፡ ብለኽ ፡ ፈደሉን ፡ አስተካክለኽ ፡ ፈልግ' ፡ በሚል ፡ ዐይነት ፥ ዘሩን ፡ በቅንፍ ፡ አመልክተው ፥ ወደ ፡ ትኽክለኛው ፡ መግቢያ ፡ ይመሩናል ። ለጥቆ ፡ የሚታየው ፡ ሥዕል ፡ ኹኔታውን ፡ የተሻለ ፡ ያስረዳናል ።



3.3.11 ፤ በሀገርና ፡ በትውልድ ፡ ፊት ፡ ታላቅ ፡ ኀላፊነትና ፡ ተጠያቂነት ፡ ያለባቸው ፡ መምህራን ፣ ደራስያን ፣ ዜነኞች ፣ የአርትዖትና ፡ የማተሚያ ፡ ድርጅቶች ፡ ወዘተ. ፥ ከዚህ ፡ ቀና ፡ የፊደል ፣ የትርጕምና ፡ ያገባብ ፡ መጠንቀቅ ፡ ተልእኮ ፡ በተስተካከለ ፡ ቀናነት ፡ ይተባበራሉ ። ጥቂቶች ፡ ባይተባበሩ ፡ ደግሞ ፥ የያዘውን ፡ የማይለቅ ፡ ወረቀት ፡ ነገ ፡ ጧት ፡ ምስክር ፡ ይኾንባቸዋል ፤ ለዘመናት ፡ ሲያስፈርድባቸውና ፡ ሲያስነቅፋቸው ፡ ይኖራል ፤ ገበያተኛውም ፡ እያደር ፡ ገሸሽ ፡ ያደርጋቸዋል ። ኢትዮጵያውያን ፡ ወገኖች ፥ ጥቅማቸውም ፣ ክብራቸውም ፣ አለኝታቸውም ፡ ነውና ፥ ተልእኮውን ፡ ተልእኳቸው ፡ አድርገውት ፡ በዚህ ፡ በቀና ፡ መንገድ ፡ እንደሚረማመዱ ፡ ጥርጥር ፡ የለም ፤ ከነሱም ፡ ዐልፎ ፥ በንጹሕ ፡ የንግድ ፡ መንፈስ ፡ የሚሳተፉት ፡ ባዕዳንም ፡ ቢኾኑ ፥ ይከተሏቸዋል ። ግእዝና ፡ ዐማርኛን ፡ አቈርቍዘና ፡ አጣጭቶ ፡ መጨረሻውን ፡ ለመግደል ፥ በምትካቸውም ፡ የራሳቸውን ፡ ባዕድ ፡ ቋንቋ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ላይ ፡ በግፍ ፡ ሊጭኑባት ፡ የሚጠበቡ ፡ አገባሪ ፡ ኀይሎች ፡ ግን ፥ ይህን ፡ አካኼድ ፡ ፈጽመው ፡ ይፃረሩታል ፤ እንዲሰናከልና ፡ እንዲከሽፍም ፡ ሌት ፡ ተቀን ፡ ይጥራሉ ። በቅርቡ ፥ አንድ ፡ ደራሲ ፡ የብዙ ፡ መቶ ፡ ገጽ ፡ ድርሰቱን ፡ ለማሳተምና ፡ ለገበያ ፡ ለማብቃት ፥ ኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ለሚሠራ ፡ ባዕድ ፡ የማተሚያ ፡ ድርጅት ፡ ዐደራ ፡ ሰጥቶት ፡ ነበር ። የድርሰቱን ፡ ረቂቅ ፡ ሲያስረክብ ፥ በፊደልም ፡ ባገባብም ፡ የተቻለውን ፡ ያኽል ፡ አስቀድሞ ፡ ዐርሞና ፡ አሳርሞ ፡ ቢኾንም ፥ ታትሞ ፡ ሲመጣለት ፥ ዕርማቱ ፡ በሙሉ ፡ አንድ ፡ ባንድ ፡ ፈርሰው ፥ በሥርዐት ፡ ተለቅመውና ፡ ተስተካክለው ፡ የነበሩት ፡ አሻሚ ፡ ፊደሎችም ፡ [እነ'አ/ዐ' ፣ እነ'ሀ/ሐ/ኀ' ፣ እነ'ሠ/ሰ' ፣ እነ'ጸ/ፀ'] ፡ ተበውዘውና ፡ ተዘባርቀው ፡ አገኛቸው ። መጽሐፉም ፡ በዚህ ፡ ያማርኛን ፡ ጥራት ፡ በሚያጠፋ ፡ በዝልጉስ ፡ ኹኔታው ፡ ታትሞ ፡ በገበያ ፡ ለሕዝብ ፡ ተናኘ ። ይህ ፥ በሌላው ፡ ዓለም ፡ ከወንጀል ፡ የሚቈጠርና ፡ የሚያስቀጣ ፡ ድርጊት ፥ በኢትዮጵያ ፡ ምድር ፡ ላይ ፡ በገሀድ ፡ ይፈጸማል ። ባዕድ ፡ ድርጅት ፡ በመኾኑ ፥ በጠላትነትም ፡ ይኹን ፡ በዕቡይነት ፥ እንዲህ ፡ ያለውን ፡ እኩይ ፡ ድርጊት ፡ ቢፈጽም ፡ አይደንቅም ፤ ከዚህ ፡ የባሰ ፥ በሕዝብ ፡ ገንዘብ ፣ ለሕዝብና ፡ ለሀገር ፡ ጥቅም ፡ ሊሠራ ፡ የሚገባው ፡ የኢትዮጵያ ፡ አካል ፡ የኾነው ፡ ዐዲስ ፡ አበባ ፡ ምድራስ ፡ (ዩኒቨርሲቲ) ፡ ዐማርኛን ፡ በማጣጨት ፡ ተልእኮ ፡ ግንባር ፡ ቀደም ፡ መኾኑን ፡ ብዙ ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ምሁራን ፡ አጋልጠዋል ። ተቋሙ ፡ ግን ፥ እስካኹን ፥ ምንም ፡ ዐይነት ፡ የመታረም ፡ አዝማሚያ ፡

አላሳየም ፡ ሲሉ ፡ ታዛቢዎች ፡ ይተቹታል ። ሕዝቡ ፥ በሚገብረው ፡ ግብሩና ፡ በገዛ ፡ የገበያ ፡ ዐቅሙ ፡ ሊጠቀም ፡ ሲገባው ፥ በእጅ ፡ አዘር ፣ መጥፊያውን ፡ እንዲያፋፋበት ፡ የተደረገ ፡ ይመስላል ። በዚሁ ፡ ዐይነት ፥ የመንግሥትም ፡ ኾነ ፡ የግል ፡ ማወራኛዎች ፥ ከሞላ ፡ ጐደል ፥ የፌደልም ፡ ኾነ ፡ ያገባብ ፡ መጠንቀቅን ፡ ረምርመው ፡ ወደጥፋት ፡ አግጣጫ ፡ አምርተዋል ። የ"ጥፋት ፡ አግጣጫ" ፡ ያልኩበት ፡ ምክንያት ፥ በዓለማችን ፡ አንድም ፡ ሀገር ፡ ፊደልን ፡ ሳይጠነቅቅ ፡ ወደልማትና ፡ ወደብልጽግና ፡ አግጣጫ ፡ ስላላመራና ፥ ከበለጸጉት ፡ ሀገሮችም ፡ ስላልተቈጠረ ፡ ነው ። የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ራሱን ፡ ገና ፡ አለመግዛቱን ፥ የባዕዳንም ፡ ፈቃድ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ላይ ፡ መፈ፟ጸሙንና ፡ መጽናቱን ፡ እንዲህ ፡ ያሰ፟ው ፡ ድርጊት ፡ እንሆ ፡ ማስረጃ ፡ ኾኖ ፡ ደግሞ ፡ ደጋግሞ ፡ ያረጋግጥብናል ። … ፡ እስከ ፡ ማእዜኑ ∴

መደምደሚያውን ፥ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብን ፡ ቀሪ ፡ ሥራ ፡ በሦስት ፡ ረድፎች ፡ መክፈል ፡ ይቻላል ፦

- አንደኛ ፥ እግዚእናውን ፡ ማስከበር ፤
- ኹለተኛ ፥ በእግዚእናው ፡ ዐዲሱን ፡ ሕገ ፡ መንግሥቱን ፡ መሥራት ፤
- ሦስተኛ ፥ ባዲሱ ፡ ሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ መሠረት ፡ ላይ ፡ ሥልጡንሕዝባዊ ፡ የርትዕ ፡ ኹነቱን ፡ (መንግሥቱን) ፡ ማቆምና ፥ የሀገራዊ ፡ ቋንቋውን ፡ ስያስ ፡ ቀርጾ ፡ በሥራ ፡ ማዋል ።

መደምደሚያ • conclusion

የዐውደ ፡ ቀለም ፡ መግበርን ፡ መመሪያ ፡ እንሆ ፡ ፈጸምን ፤ አንባብያን ፡ የተሟላ ፡ መረጃን ፡ እንዳገኙበት ፡ ተስፋ ፡ አደርጋለኹ ፤ ለዐውደ ፡ ቀለም ፡ መግበርም ፡ ክብር ፡ ሰጥተው ፡ አገልግሎቱን ፡ ለመረመሩ ፡ ኹሉ ፡ ልባዊ ፡ ምስጋናዬን ፡ በትሕትና ፡ አቀርባለኹ ።

የሚያሳስቡት ፡ ማሻሻያ ፣ የሚያመለክቱት ፡ እንከን ፣ ወይም ፡ የሚያካፍሉት ፡ አስተያየት ፡ ይኖራቸዋል ፡ በማለትም ፥ የሚከተለውን ፡ የእ-ጦማር ፡ አድራሻ ፡ አመለክታለኹ ፦

awdeqelem@ttomar.net

ካክብሮት ፡ ሰላምታዬ ፡ ጋራ ፥

ወሌ ፡ ነጋ ።

We have reached the end of the User's Manual of AwdeQelem; I hope all readers have found in it helpful information, and take this opportunity to express to all of them my heartfelt gratitude for their interest.
To those who wish to suggest improvements, to report bugs, or to share ideas, may I suggest the following e-mail address:

awdeqelem@ttomar.net

With my best regards.

Nous avons atteint la fin du manuel utilisateur de AwdeQelem; j'espère que tous les lecteurs y ont trouvé une information utile, et saisi cette occasion pour leur exprimer mes sincères remerciements pour l'intérêt qu'ils ont témoigné.
À ceux qui souhaitent suggérer des améliorations, signaler des bogues, ou partager des idées par courriel, puis-je leur proposer l'adresse suivante:

awdeqelem@ttomar.net

Avec mes salutations distinguées.

Welé Negga

መጠቆሚያ ፡ (ዐማ-እንግ-ፈረ) • Index (Amh-Eng-Fr • amh-ang-fr)

A
Acknowledgement........5, 8
alphabet occidental........78
alphabetical order........38
américain........1, 5, 7, 10, 73, 74, 75, 76
American........1, 5, 7, 10, 73, 74, 75, 76
Amharic...1, 10, 21, 22, 23, 28, 37, 38, 45, 46, 49, 50, 53, 56, 57, 60, 62, 63, 76, 84, 85, 86
amharique.1, 10, 21, 22, 23, 28, 37, 38, 45, 46, 47, 49, 50, 53, 56, 57, 60, 62, 63, 76, 85, 86
anglais. .1, 5, 7, 10, 22, 25, 28, 37, 38, 49, 50, 60, 62, 63, 73, 74, 75, 76, 85
Anjo Anjewierden........8, 9
ANSI........84
associations........9
Avertissements........5, 6
AwdeQelem.1, 3, 5, 6, 7, 9, 10, 22, 25, 26, 27, 28, 29, 30, 31, 33, 34, 35, 36, 37, 38, 40, 41, 47, 48, 49, 50, 51, 52, 53, 56, 61, 63, 64, 69, 70, 71, 73, 74, 76, 80, 81, 82, 83, 84, 98, 109
awde-qelem.net........25
B
Benoît Sagot........8, 10, 60, 61
besoins en ressources........5, 30
bonne volonté........9
C
capabilities........5, 10, 22, 52, 53
Carnegie Mellon University........7, 8, 10, 73
civilisation........9
clavier........30, 31, 76, 78
CMUdict........6, 7, 8, 10, 72, 73
computer........22, 28, 31, 76, 83
conclusion........5, 98
connaissance........9, 82, 85
Contents........5
correcteur orthographique........1, 22, 26, 29, 82
correction........5, 23, 25, 39, 46, 56, 66, 67, 68, 82
courriel........98
culture occidentale........9
D
derivational........5, 52
dérivationnelles........5, 52
dictionary. .1, 7, 10, 25, 26, 28, 35, 37, 39, 48, 49, 50, 51, 59, 60, 61, 62, 63, 64, 76, 82
dictionnaire.1, 7, 10, 25, 26, 35, 37, 39, 48, 49, 50, 51, 59, 61, 62, 63, 64, 76, 82
digital implementation........9
dissemination........9
dissémination........9
E
e-mail........98
edition........1, 5, 22, 53, 109
English...1, 5, 6, 7, 10, 22, 25, 28, 37, 38, 49, 50, 60, 62, 63, 73, 74, 75, 76, 85
enlightenment........9
Ethiopian 1, 5, 9, 22, 25, 26, 30, 41, 45, 53, 68, 69, 71, 73, 74, 75, 76, 77, 78, 80, 81, 82, 84
Ethiopian literature........9
Ethiopian Orthodox Tewahdo Church........9
Ethiopian scholars........9
Ethiopian script.5, 25, 26, 68, 71, 73, 74, 75, 76, 77, 78, 80, 81, 82
F
fichier. .5, 33, 37, 38, 40, 41, 70, 74, 77, 80, 81, 82, 84
file 5, 33, 37, 38, 40, 41, 42, 55, 70, 74, 77, 80, 81, 82, 84
flexionnelles........5, 45, 52, 53
Foreword........5, 6
français6, 7, 10, 22, 25, 28, 37, 38, 49, 50, 60, 61, 62, 85
française........1, 38, 61
Frederic Labbé........8, 10
free........1, 6, 7, 9, 10, 25, 26, 61, 63
French 1, 7, 9, 10, 22, 25, 28, 37, 38, 49, 50, 60, 61, 85
Frequently asked questions........5, 22, 83
G
g'z........1, 22, 23, 37, 45, 50, 57, 84, 86
getting started........5, 28
goodwill........9
gratitude........9, 98
gratuit........1, 6, 7, 9, 10, 25, 26, 63
guide........1, 61
gzamargna.net........25
H
homonymic........5, 52
homonymiques........5, 52
I
implémentation numérique........9
impression........1, 109
individuals........9
inflectional........5, 22, 45, 52, 53, 82
informatics........9, 13
information........53, 98
informatique........9, 13
installation........5, 22, 33
institutions........9, 61
Introduction........5, 20
J
Jan Wielemaker........8, 9
Jean Garicoïx........12
K
Kevin Hendricks........8, 10
keyboard........30, 31, 76, 78
knowledge........5, 8, 9
L
language 6, 9, 10, 21, 22, 25, 26, 28, 37, 39, 41, 45, 46, 47, 49, 50, 53, 58, 60, 62, 76, 77, 82
langue. 6, 9, 10, 21, 22, 25, 26, 28, 37, 39, 41, 45, 46,

47, 49, 50, 53, 58, 60, 61, 62, 76, 77, 82
Laurent Godard..8, 10
literature...9, 38
littérature..9, 38
littérature éthiopienne.......................................9
lumière..9, 32
M
manuel utilisateur...................................6, 31, 98
Microsoft...31, 69
mise en marche...5, 28
mot..5
mutual respect...9
N
Negga Haile Sellassie..9
Negga Hayle Sllasé...9
Notepad++...25, 26, 31
O
opening...................................5, 37, 38, 41, 74
openness...9
OpenOffice...25, 26, 31
operating system...........................1, 3, 30, 31, 35
ordinateur..32, 83
ordre alphabétique..38
orthographie..............6, 39, 46, 53, 56, 65, 67, 81, 86
ouverture...................................5, 9, 37, 38, 41
P
perspectives...5, 84
Preface..5, 11
Préface..5, 11
presentation..5, 22, 25, 33
présentation..5, 22, 25, 33
Princeton University Cognitive Science Lab.............8, 10
print..1, 109
Q
Questions fréquemment posées......................5, 22, 83
R
remerciements...5, 8, 98
respect mutuel...9
S
savants éthiopiens...9
selection...5, 40
sélection.............5, 37, 40, 41, 42, 43, 56, 60, 62, 74
simultaneous translation.......................................1
solidarité...9
solidarity...9
somali..1, 5, 25, 29, 37, 38, 50, 74, 75, 76, 77, 78, 80, 82
somali...1, 5, 25, 29, 38, 50, 74, 75, 76, 77, 78, 80, 82
soutien...9, 26, 34
spell-checker.....................................1, 26, 29, 82
spell-checking................5, 22, 23, 25, 46, 68, 81, 82
spelling..........6, 39, 46, 47, 48, 53, 56, 65, 66, 67, 86
States...9
support..9, 10, 26, 34
SWI-Prolog..................................6, 8, 9, 10, 35
system requirements..5, 30
système d'exploitation.....................1, 3, 30, 31, 35
Système Wazéma.......................................26, 30, 31, 33
T
Table des matières...5
technologie..9, 13
technology...9, 13
text...................................70, 74, 76, 78, 81, 82
text processing..1
text processor..............1, 3, 25, 26, 36, 51, 64, 81, 83
tool........................1, 26, 48, 63, 71, 74, 76, 84, 85
traduction.................1, 28, 37, 39, 60, 62, 63, 76, 85
traduction simultanée..................................1, 28, 37
traitement de texte.........1, 3, 22, 25, 26, 51, 64, 81, 83
Transcriber.......................................1, 71, 73, 74
Transcripteur.....................................1, 71, 73, 74
transcription..........5, 10, 60, 74, 75, 76, 77, 79, 80, 81
Translation......................1, 28, 37, 60, 62, 63, 76, 85
U
UNICODE..................................30, 53, 69, 75, 76, 84
université...................................7, 10, 12, 63
université Carnégie Mellon............................7, 10, 73
université d'Amsterdam.....................................7, 10
université de Princeton....................................7, 63
University..............................6, 7, 8, 9, 10, 63, 73
usage...5, 22, 35, 70
User's Manual..6, 31, 98
UTF-8...70
utilisation..5, 22, 35
V
vérification..............................5, 29, 46, 66, 81, 82
version. 5, 7, 26, 28, 31, 36, 37, 38, 47, 48, 61, 63, 70, 80, 82, 83, 84, 85
W
Wazéma System.......................................26, 30, 31, 33
Western alphabet..78
Western culture..9
Western script............5, 60, 74, 75, 76, 77, 78, 81, 82
Windows...1, 3, 30, 31
WOLF...6, 7, 8, 10
WordNet................6, 7, 8, 10, 28, 49, 60, 61, 63, 64
WordNet Libre Français..10
WordNet-français.....................................7, 10, 61
X
XPCE..8, 9

....1
፤
፤ 36
፧
፧ 18
é
écriture éthiopienne5, 68, 69, 71, 73, 74, 75, 76, 77, 79, 80, 81, 82
écriture occidentale...5, 9, 60, 74, 75, 76, 77, 78, 81, 82
édition..................................1, 5, 22, 37, 53, 109
église orthodoxe tewahdo éthiopienne..........................9
É
États..9
é
éthiopien 1, 5, 9, 22, 25, 26, 41, 45, 53, 68, 69, 71, 73,

74, 75, 76, 77, 78, 79, 80, 81, 82, 84, 85
ሀ
ሀገራዊ.........11, 12, 15, 16, 17, 18, 19, 20, 21, 22, 25, 58
ሀገራዊ ፡ ልሳናችን...19
ሀገራዊ ፡ ልሳን...18
ሀገራዊ ፡ ሥልጣን...58
ሀገራዊ ፡ ቀለም...12
ሀገራዊ ፡ ቋንቋ...17
ሀገራዊ ፡ እግዚእና...17, 18
ሀገራዊ ፡ ዐላማ...15, 19
ሀገራዊነት...20, 25
ሀገር..................................11, 17, 18, 19, 20, 87, 96
ሃ
ሃይማኖት..12, 20, 57
ህ
ህልውና...11, 13, 17, 18
ሆ
ሆሎታ...12
ለ
ለማ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ...12
ለንደን...16, 19
ላ
ላሕይ...6, 8, 72, 75
ላስታ...20
ል
ልምድ...35
ልሳን...18, 20
ልቅ̇ም...86
ልቅ̇ሞች..86
ሐ
ሐውልት...15
ሐዲስ..11, 93
ሕ
ሕብር..25, 92
ሕዝብ..................11, 14, 15, 16, 17, 18, 19, 92, 96, 97
ሕይወት...17
ሕገ ፡ መንግሥት...17, 19
ሕጋዊ...13, 19
ሕግ...7, 11, 58, 86
መ
መለማመጃ...30
መልእክት...86
መመለሻ..............................1, 71, 72, 73, 75, 76, 84
መመሪያ.............1, 6, 7, 17, 21, 30, 54, 58, 60, 86, 98
መሠረት......6, 12, 13, 14, 18, 20, 25, 40, 53, 58, 64, 94
መሣሪያ...8, 13, 15
መሣሪያ ፥ 13
መረጃ..................................19, 30, 31, 58, 87, 98
መረጣ...5, 40
መርበቢያ..13, 17, 19, 25, 33, 53
መሳ̇ሊያ..6, 7, 17, 58
መቀመሪያ..6, 8, 35
መቅድም...5, 11
መቍጠሪያ...84
መብት...7, 18, 19
መተርጐሚያ..60, 84
መተርጐሚያ ፡ መግበር...84
መታሰቢያ...2, 11
መታያ..28, 83
መንኰራኵር...19
መንገድ...........8, 13, 15, 16, 19, 75, 86, 90, 94, 95, 96
መንግሥት............................11, 12, 15, 16, 17, 19, 20
መንፈሳዊ...11, 12
መንፈስ...17, 19, 91, 96
መክፈቻ...36
መዋቅር...17, 18
መዘርዘር...5, 52, 81, 82
መዛግብተ ፡ ቃላት.........................11, 13, 21, 49, 81, 93
መዝገበ ፡ ቃላት.1, 6, 8, 11, 21, 25, 28, 38, 48, 49, 54, 57, 58, 59, 60, 62, 63, 64, 67, 68, 82, 88, 93, 94
መደምደሚያ..5, 90, 98
መደዳ..47, 61
መድረሻ..8, 89
መገኛ..13, 29
መግለጫ.....................................5, 21, 25, 33, 57
መግበር..1, 8, 13, 19, 20, 21, 25, 33, 36, 38, 40, 49, 71, 72, 84, 93, 98
መግቢያ...................................5, 12, 20, 21, 71, 95
መጠቈሚያ....................33, 42, 43, 44, 49, 61, 71, 94
መጠንቀቂያ...93
መጠ̊ንቀቂያ...........................1, 20, 21, 25, 29, 81, 84
መጻፊያ...13
መጽሐፈ ፡ ሰዋስው ፡ ወግስ ፡ ወመዝገበ ፡ ቃላት ፡ ሐዲስ11, 54, 68, 93
መጽሐፍ...20, 38, 43
መጽሐፍ ፡ ቅዱስ...................................20, 38, 43
መፍትሔ............................15, 16, 18, 20, 28, 75, 83
መፍቻ...48
መፍቻ-ገበታ....................................30, 31, 54, 75
ማ
ማመልከቻ...69
ማማረጫ....15, 25, 30, 36, 47, 58, 60, 61, 69, 70, 75, 93
ማምረቻ1, 2, 6, 8, 11, 13, 20, 21, 25, 35, 36, 51, 52, 54, 64, 69, 80, 83
ማሞካሸት...5, 52
ማሟሻ...5, 17, 28
ማረሚያ...64, 80, 81
ማሰሪያ...67
ማሳሰቢያ..6, 70
ማሳኪያ...25
ማስሊያ.................................13, 20, 21, 31, 86
ማስታወሻ...6
ማሻሻያ..30, 72, 98
ማቀመሪያ...84
ማብራሪያ...48, 94
ማተራጐሚያ..1, 28
ማኅደር...30, 33, 38
ማዋሐድ..8, 81, 84
ማውጫ...5, 72, 84, 86
ማዕርግ..12
ማዘመኛ...70
ማጣራት...................................38, 47, 58, 82
ም
ምለሳ...5, 71, 75, 84
ምልክዮሽ..18
ምሕቃፍ..64

ምርምር........18
ምርት........16
ምስጋና........5, 8, 9, 29, 98
ምኒልክ........20
ምእላድ........6, 44, 58, 88, 89
ምዕራባዊ..1, 5, 8, 14, 40, 59, 60, 70, 72, 73, 75, 76, 78, 80
ምዕራፍ........11, 21, 53
ምዝካር........30
ምድራስ........6, 8, 63, 72, 97
ምግባር........1, 3, 30, 31
ሞ
ሞክሼ........36, 49, 50, 52, 58
ሚ
ሚያ........12, 16, 54, 78, 89, 91, 93
ሠ
ሠም........91
ሠምና ፡ ወርቅ........91
ሥ
ሥልጡንሕዝባዊ........19
ሥልጡንሕዝብነት........18
ሥልጡንሕዝብና........18, 19
ሥልጣኔ........8, 18, 20
ሥልጣን........11, 14, 15, 17, 18, 19, 58
ሥርዐት. 11, 13, 14, 15, 16, 17, 18, 53, 57, 58, 63, 86, 87, 89, 90, 96
ሥርጭት........86
ሥነ ፡ ጽሑፍ........8, 11, 12
ሥዕል........49, 93, 94, 95
ረ
ረድኤት........8
ረድፍ........13, 60
ር
ርባታ........21, 58, 84, 88
ርትዕ........12, 17, 18, 19, 20
ሰ
ሰሎሞናዊ ፡ ዘርዐ ፡ ነገሥት........14
ሰነድ. .5, 25, 30, 33, 36, 38, 40, 41, 55, 68, 69, 70, 73, 76, 80, 84
ሰንጠረዥ........78, 87
ሰዋስው........11, 54, 68, 86, 93
ሱ
ሱርስት........92
ሱዳን........53, 54
ሴ
ሴማውያን........20, 76, 92
ሴባስቶፖል........14, 15, 16
ስ
ስሌት........8, 13, 21
ስሌትኛ........8, 13
ስሕተት.6, 11, 17, 20, 47, 58, 60, 64, 65, 66, 67, 72, 82, 83, 86, 87, 89, 90, 91, 92, 93
ስም 11, 12, 20, 33, 45, 58, 65, 69, 70, 76, 80, 82, 90, 92
ሶ
ሶማሊያ........53, 58
ሶማልኛ..1, 5, 21, 25, 29, 36, 38, 72, 75, 76, 78, 80, 81, 82
ሷ
ሷሂሊ........25
ቀ
ቀለማት........57, 66, 68
ቀኝ–ዝራር........43
ቀዳማዊ ፡ ምኒልክ........20
ቀጣና........93
ቃ
ቃላት........6, 8, 20, 21, 36
ቃል...29, 36, 40, 41, 43, 44, 46, 48, 49, 52, 54, 56, 57
ቅ
ቅመራ........8
ቅርጸት........25, 30, 35, 53, 54, 75
ቅኝ ፡ ግዛት........12, 14, 18
ቅጽል........11, 60, 80, 90
ቋ
ቋንቋ........25
በ
በዚሁ........60
ባ
ባለሚያ........54
ቤ
ቤተ ፡ ክርስቲያን........8, 14
ብ
ብሔራዊ........12, 18, 25, 80
ብሔራዊ ፡ ሀብት........25
ብሪታንያ........8, 11, 12, 13, 16, 72, 75
ተ
ተሐድሶ ፡ ቅኝ ፡ ግዛት........12, 18
ተሰማ ፡ ሀብተ ፡ ሚካኤል........11, 49
ተከላ........5, 21, 30, 33
ቴ
ቴዎድሮስ........14, 15
ት
ትርጉም........8, 11, 16, 20, 87, 93, 94, 96
ትግርኛ........58, 92
ትጥቅ........12
ኀ
ኀርመት........29, 40, 43
ኀርመቶች........84
ኀብር........91, 92
ኀትመት........12, 13
ነ
ነኰርኳር........19
ነጋ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ........2, 8, 11, 12, 13, 87
ን
ንጉሡ........14, 89
ንጉሥ........95
አ
አሀጉራዊ........20, 75
አላድ........86
አምሳያ........20, 59, 60
አሰፋ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ........12
አንቀጽ........11, 58, 60, 67, 81, 89, 90, 91, 92, 95
አኵስም........20, 21
አውሮፓ........11, 53, 54
አዝራር........40, 44
አድማሱ ፡ ጀንበሬ........11
አድራሻ........98

አገልግሎት....................5, 6, 8, 14, 16, 20, 35, 62, 86
አገባብ..........................21, 52, 60, 84, 86, 87, 90, 93
አጋቦስ...14, 84
አጋቦስ-Mac...84
አጋቦስ ፡ ወሰሎሞናዊ ፡ ዘርዐ ፡ ነገሥት.............................14
አጻጻፍ 5, 46, 47, 52, 53, 58, 59, 72, 86, 87, 89, 90, 93, 96
አፍሪቃ..............................14, 16, 20, 54, 58, 65, 66
አፕል...83
አፕል ፡ ማክ...83
ኢ
ኢ.ሀ.ሥ.አ...19
ኢትዮጵያ...8, 12, 16
ኢትዮጵያዊ. 1, 5, 8, 11, 12, 13, 15, 17, 18, 19, 21, 25, 40, 70, 71, 72, 73, 75, 76, 80, 84
ኢትዮጵያዊ ፡ ጻሕፍ............1, 5, 8, 71, 72, 73, 75, 76, 80
ኢትዮጵያዊነት...15, 19
ኤ
ኤስፓኞኛ..25
እ
እ-ጦማር...98
እንግሊዝኛ. 1, 5, 6, 8, 16, 18, 20, 21, 25, 28, 36, 38, 52, 59, 60, 62, 63, 64, 72, 73, 75, 76, 84, 93
እግዚእና.......................................11, 16, 17, 18, 19
ኦ
ኦሮምኛ...75, 76
ከ
ከፈይ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ...13
ኪ
ኪነት...8, 13, 18, 49
ኪዳነ ፡ ወልድ ፡ ክፍሌ.....................11, 54, 68, 86, 87, 93
ክ
ክለሳ 1, 3, 5, 6, 17, 25, 28, 31, 36, 47, 58, 60, 63, 70, 75
ክርስቶስ...90, 91
ኰ
ኰሻዊ...21
ኰሽ...20, 21
ወ
ወደ ፡ ፊት...........................5, 20, 49, 60, 68, 84, 93
ዊ
ዊንዶውዝ...1, 3, 30
ዋ
ዋዜማ...13
ዋዜማ-ANSI...84
ዋዜማ ፡ ሥርዐት................13, 25, 30, 31, 33, 54, 58, 86
ዐ
ዐላማ.............12, 13, 15, 16, 18, 19, 47, 49, 50, 52, 54
ዐማርኛ. .1, 6, 12, 13, 18, 19, 20, 21, 28, 38, 52, 53, 54, 57, 61, 62, 64, 81, 84, 86, 87, 88, 89, 91, 92, 93, 96, 97
ዐረብ..20, 78, 89, 92
ዐረብኛ...75, 92
ዐቅም 5, 6, 8, 12, 16, 17, 20, 28, 30, 45, 49, 52, 63, 64, 68, 86
ዐውደ ፡ ቀለም. .1, 3, 5, 6, 7, 8, 11, 12, 13, 17, 19, 20, 21, 25, 28, 29, 30, 33, 35, 36, 38, 40, 49, 52, 53, 54, 56, 58, 60, 63, 64, 67, 70, 71, 72, 73, 76, 80, 82, 83, 84, 98
ዐዲስ 5, 8, 11, 13, 15, 16, 19, 21, 28, 36, 49, 54, 59, 68, 69, 70, 75, 93, 97
ዐፈርኛ...75, 76
ዕ
ዕርማት................5, 46, 54, 56, 58, 60, 67, 68, 81, 82
ዕቃሜ...5, 30
ዕብራይስጥ...92
ዕትም..1, 109
ዕውቀት..8, 12, 17, 18, 87
ዝ
ዝራር.33, 36, 38, 40, 43, 44, 46, 47, 49, 50, 52, 55, 56, 58, 59, 61, 65, 69, 70, 73, 80, 83
ዝግጅት...................................1, 5, 17, 21, 53, 109
የ
የቀን ፡ መቍጠሪያ ፡ መመለሻና ፡ የበዓላት ፡ ማውጫ.............84
የቃል ፡ ማሳኪያ...25
የብሪታንያው...16
የንምር ፡ ጽሑፍ ፡ ማንጠሪያ ፡ መግበር..........................84
የኢትዮጵያውያን ፡ ሀገራዊ ፡ ሥልጡንሕዝባዊ ፡ አንድነት...........19
የግእዝ-ዐማርኛ ፡ የርባታ ፡ መግበር..............................84
ያ
ያማርኛ ፡ አገባብ ፡ መጠንቀቂያ ፡ መግበር.........................84
ደ
ደስታ ፡ ተክለ ፡ ወልድ......................11, 12, 49, 87, 92, 93
ጉ
ጉባኤ...13, 17
ግ
ግራ-ዝራር...43
ግኘታ...5, 40
ግእዝ 1, 11, 12, 13, 18, 19, 20, 21, 36, 38, 47, 49, 53, 57, 64, 65, 81, 84, 86, 87, 88, 89, 92, 93, 96
ግእዝ-ዐማርኛ.......................13, 18, 19, 21, 84, 86, 89
ግድፈት...11, 86
ግጻዌ 21, 33, 35, 36, 38, 40, 41, 42, 43, 44, 45, 46, 47, 48, 49, 50, 52, 53, 54, 55, 56, 57, 59, 60, 61, 62, 63, 64, 65, 66, 67, 68, 69, 71, 72, 73, 75, 76, 80, 81
ጥ
ጥራት...5, 29, 46, 96
ጥርየት..17
ጥርየትኛ..8
ጥቃኄ...28, 83
ጥያቄዎች.....................................5, 17, 21, 54, 83
ጻ
ጻሕፍ 1, 5, 8, 25, 36, 40, 41, 48, 53, 57, 59, 71, 72, 73, 75, 76, 78, 80
ጽ
ጽሑፍ. .5, 8, 11, 25, 29, 38, 40, 49, 51, 52, 53, 54, 56, 64, 67, 68, 72, 78, 80, 81, 82, 84
ጽሑፍ ፡ ማምረቻ 1, 3, 6, 8, 11, 13, 20, 21, 25, 35, 36, 51, 52, 54, 64, 69, 80, 83
ፈ
ፈረንሳይኛ 1, 6, 8, 12, 20, 21, 25, 28, 36, 38, 49, 59, 60, 75, 84
ፈረንጅኛ..11, 75, 93
ፊ
ፊደል. .1, 16, 20, 21, 25, 29, 38, 40, 41, 46, 52, 53, 56, 57, 58, 59, 67, 70, 75, 76, 80, 81, 82, 86, 87, 88, 89, 90, 91, 92, 93, 96

ፊደል ፡ መጠ̊ንቀቂያ........................1, 20, 21, 25, 29, 81
ኡ፡
ኡ፡ኒቬርሲቴ...12
ኢ..ሀ.ሥ.አ...19

www.awde-qelem.net

www.gzamargna.net

3ኛ ፡ ዝግጅት ፥ 1ኛ ፡ ዕትም • 3rd edition, 1st print • 3ème édition ÷ 1ère impression

ዐውደ ፡ ቀለም • AwdeQelem ©ወሌ ፡ ነጋ ÷ መስከረም ፡ 2008 ፡ – ፡ የካቲት ፡ 2014 ፡ ዓ.ም. • Welé Negga, Sept. 2015 – Feb. 2022 A.D.